# የመልዕክተ- ዐቂዳ ማብራሪያ፣ የሀጅና የዑምራ የአፈጻጸም ገጽታ

ዝግጅት፡- ሸይኽ ዐብዱልዐዚዝ ኢብኑ ባዝ

ትርጉም፡- ሙሀመድ ሰዒድ ዐሊ

# የመልዕክተ- ዐቂዳ ማብራሪያ፣ የሀጅና የዑምራ የአፈጻጸም ገጽታ


ዝግጅት፡- ሸይኽ ዐብዱልዐዚዝ ኢብኑ ባዝ

ትርጉም፡- ሙሀመድ ሰዒድ ዐሊ

(አቡ ዐብዱልከሪም)

بسم الله الرحمن الرحيم

# ማውጫ


መግቢያ ገጽ

የላኢላሃ ኢልለሏህ መስፈርቶች ......................................9

ባዕድ አምልኮ መፈጸምና ማብራሪያው ..........................................19

በክንድና በእጅ ላይ ክር ማንጠልጠል...........................................24

ድግምት፣ ደጋሚና የድግምት ህክምና ..............................27

የካዕባን ግድግዳና ልብስ በእጅ ማበስ ..................................35

የውዱእ አደራረግ ስነ-ስርዓት ........................................................39

በአዛንና ከአዛን በሁዋላ የሚባሉ ዚክሮችና ዱዓዎች .......................46

ከመስጂድ የመግባትና የመውጣትና ስነ-ስርዓት.............................48

የአላህ መልእክተኛ የሶላት አሰጋገድ ስነ-ስርዓት ............................49

የጀናዛ ሶላት የአሰጋገድ ስነ-ስርዓት...................................................67

የሀጅ፣ የዑምራና የጉብኝት የአፈጻጸም ገጽታ ................................73

የሀጅና የዑምራ ግዴታነት..............................................................75

ከወንጀል መመለስና ከበደሎች የመውጣት ግዴታነት ..................79

ሀጅ አድራጊው «ሚቃት» ላይ ሲደርስ የሚሰራው ስራ................86

የኢህራም መፈጸሚያ ቦታቸው (ሚቃት) እና ወሰናቸው..................92

ከሀጅ ወራት ውጪ ኢህራም ማድረጊያ ቦታዎች ላይ መድረስ ..........................................................................98

የህጻን ልጅ ሀጅ ..........................................................................102

በኢህራም ወቅት የሚፈቀዱና የሚከለከሉ ነገሮች.............................................................................................105

መካና መስጂደል ሀራም ሲገባ የሚፈጸሙ ተግባሮች....................111

በዙል ሂጃ ወር ስምንተኛው ቀን ኢህራም ማድረግና ወደ ሚና መሄድ .............................................................122

የተለያዩ ምርጥ ዱዓዎች ..........................................................126
ሀጅ አድራጊው እንስሳት በሚታረድበት ዕለት
የሚሰራቸው በላጭ ተግባራት ..................................................148
እንስሳት መስዋዕት ማድረግ ግዴታ የሚሆንበት
‹‹ሙተመቲዕ›› እና ‹‹ቃሪን›› ....................................................155
ሀጃጆችና ሌሎች ሰዎችን በመልካም የማዘዝና ከመጥፎ
የመከልከል ግዴታ .................................................................158
አላህን በመገዛት ስንቅ መሰነቅ ..............................................167
ጉብኝት፣ ህጉና ስርዓቱ .........................................................169
ማሳሰቢያ ...............................................................................185
የቁባእ መስጂድንና በቂዕን መጎብኘት .......................................189
ሰላምታ፣ ማስነጠስና በሽተኛን መጠየቅ...................................193
አዝካሮችና ዱዓዎች.................................................................196
የጧትና የማታ አዝካሮችና ውዳሴዎች.......................................202

# መግቢያ

ምስጋና ለዓለማት ጌታ ይሁን፡፡ እዝነትና ሰላም በሙሀመድ፣ በቤተሰቦቻቸውና በባልደረቦቻቸው እንዲሁም እስከ እለተ ትንሳኤ ድረስ መንገዳቸውን በተከተለ ላይ ሁሉ ይሁን፡፡

ከዚህ ቀጥሎም በሸይኽ ዐብዱል ዐዚዝ ኢብኑ ባዝ በጎ አድራጎት ተቁዋም ስር የሚገኘው የትምህርት ኮሚቴ የተከበሩት አባታችን ሸይኽ ዐብደልዐዚዝ ኢብኑ ባዝ በተለያዩ አጋጣሚዎች ያቀረቡዋቸውን ኢስላማዊ መልዕክቶች በተከታታይ የሚያቀርበው ሂደት አካል ስብስብ የሆነውን ይህን ስራ ለተከበሩ አንባቢዎች ሲያቀርብ ከፍተኛ ደስታ ይሰማዋል፡፡

ይህ የተለያዩ ኢስላማዊ መልእክቶችን የያዘው ስብስብ ለንባብ እንዲበቃ አስተዋጽኦ ላደረጉ አካል ሁሉ፣ አላህ መልካም ምንዳውን እንዲሰጣቸው እንጠይቃለን፡፡ ይህ ጠቃሚ ኢስላማዊ መልእክቶችን አጠናቅሮ የያዘው ስራም ሸይኽ ዐብደልዐዚዝ ኢብኑ ባዝን ቀብራቸው ላይ ጠቃሚ እንዲያደርግላቸውም አላህን እንጠይቀዋለን፡፡

አላህ ሁላችንንም ከፍ ካለው የጀነት ክፍል (ፊርደውስ) እንዲሰበስበን እንጠይቀዋለን፡፡ አላህ በዚህ ነገር ላይ የበላይና ቻይ ነው፡፡

እዝነትና ሰላም በነቢያችን ሙሀመድ፣ በቤተሰቦቻቸውና በባልደረቦቻቸው ላይ ይሁን፡፡

በሸይኽ ዐብዱል ዐዚዝ ኢብኑ ባዝ በጎ አድራጎት ተቋም
የትምህርት ኮሚቴ

## የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ብለዋል፡-

بُنِيَ الإِسلَامُ عَلَى خَمسٍ شَهَادَةِ: أَنْ لَا إِلَهَ إِلَّا اللّٰه وَأَنَّ مُحَمَّدًا رَسُولُ اللّٰه، وَإِقَامِ الصَّلَاةِ، وَإِيتَاءِ الزَّكَاةِ، وَصَوْمِ رَمضَان، وَحَجِّ الْبَيْتِ

‹‹ኢስላም በአምስት ነገሮች ተገንብቷል፡፡ (እነሱም) ከአላህ ውጪ ሌላ አምላክ የለም ብሎ መመስከርና ሙሀመድ የአላህ መልዕክተኛ ነው ብሎ መመስከር ነው፡፡ ሶላትን መስገድ፣ ዘካ ማውጣት፣ ሀጅ ማድረግና የረመዷን ወር መጾም ናቸው፡፡›› (ቡኻሪ ዘግቦታል)፡፡

# የላኢላሃ ኢልለሏህ መስፈርቶችና እሱን ያለማወቅ ያለው አደጋ

ጥያቄ፡- ብዙ ሙስሊም የሆኑ ሰዎች የላኢላሃ ኢለላህን ትርጉም (መልዕክት) እንደማያውቁ ይታያል፡፡ በዚህም ምክንያት መልዕክቱን በሚጻረሩና በሚቃረኑ ነገሮች ላይ መውደቃቸው ወይም የመልዕክቱን ሙሉዕነት የሚያጓድሉ ንግግሮችን መናገራቸውና ተግባሮችን መፈጸማቸው አይቀሬ ነው፡፡ ለመሆኑ የላኢላሃ ኢለላህ ትርጉም ምንድን ነው?

መልስ፡- ላኢላሃ ኢለላህ የሚለው ቃል ሙሀመድ የአላህ መልዕክተኛው ነው ከሚለው ጽንሰ ሃሳብ ጋር በጥምረት ከኢስላም መሰረቶች መካከል አንደኛው ማዕዘን እንደሆነ ጥርጥር የለውም፡፡ አብደላህ ዑመር በዘገበው ሀዲስም የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ብለዋል፡-

«بُنِيَ الإِسلَامُ عَلىَ خَمسٍ: شَهَادَةِ أَنْ لَا إِلَهَ إِلَّا اللّٰه وَأَنَّ مُحَمَّدًا رَسُولُ اللّٰه، وَإِقَامِ الصَّلَاةِ، وَإِيتَاءِ الزَّكَاةِ، وَصَوْمِ رَمضَان، وَحَج الْبَيْت»

‹‹ኢስላም በአምስት ነገሮች ተገንብቷል፡፡ (እነሱም) ከአላህ ውጪ ሌላ አምላክ የለም ብሎ መመስከርና ሙሀመድ የአላህ መልዕክተኛ ነው ብሎ መመስከር ነው፡፡ ሶላትን መስገድ፣ ዘካ ማውጣት፣ ሀጅ ማድረግና የረመዷን ወር መጾም ናቸው፡፡›› (ቡኻሪ ዘግቦታል)፡፡

በሌላ ትክክለኛ የሀዲስ ዘገባ ኢብኑ ዐባስ (ረ. ዐ) እንዳስተላለፉት፣፣ የአላህ መልዕክተኛ ሙዐዝን ወደ የመን በላኩበት ወቅት እንዲህ ብለውታል፡-

«إنَّكَ تأتِي قَومًا من أَهْلِ الْكِتَاب، فَادعهُم إلَى أَن يَشْهَدُو أَنْ لَا إلَهَ إلَّا اللّه وَأنّي رَسُولُ اللّه، فَإن أَطَاعوك لِذَلكَ فَأَعلمهم أَن اللّه افترض عَلَيْهم خَمسَ صَلَوات فِي الْيَوم وَاللّيْلَة، فَإن أطَاعوك لذَلك فَأَعْلمهم أَن اللّه افترض عَلَيهم صَدَقةً، تؤخذ من أَغنيائِهم فتُرَدَّ فِي فُقرَائهِم»

«አንተ የመጽሀፍ ባለቤት ወደ ሆኑ ሰዎች ዘንድ ትሄዳለህ፡፡ ስለሆነም መጀመሪያ ከአላህ ውጪ ሌላ አምላክ እንደሌለና እኔ የአላህ መልዕክተኛ እንደሆንኩ ጥሪ አድርግላቸው፡፡ በዚህ እነሱ ከታዘዙህ (ከተቀበሉህ)፣ አላህ በእነሱ ላይ በቀንና በሌሊት ግዴታ ያደረገባቸው ሶላቶች እንዳሉ አሳውቃቸው፡፡ እነሱ በዚህ ከተቀበሉህ (ከታዘዙህ) ከሀብታሞቻቸው ተወስዶ ለደሃዎቻቸው የሚሰጥ ዘካ አላህ በእነሱ ላይ ግዴታ እንዳደረገባቸው አሳውቃቸው፡፡» በዚህ ነጥብ ላይ የሚያወሱ ብዙ ሀዲሳዊ መረጃዎች አሉ፡፡

ላኢላሃ ኢለላህ ማለት፣ ከአላህ ሌላ የሚመለክ አምላክ የለም ማለት ነው፡፡ ቃሉ ከአላህ ውጪ የሚደረግን አምልኮ ሁሉ ይጻረራል፡፡ ስለሆነም አምልኮ ለአላህ ብቻ እንደሆነ ያረጋግጣል፡፡ አላህ በሐጅ ምዕራፍ ቁጥር 62 ላይ እንዲህ ይላል፡-

﴿ذَٰلِكَ بِأَنَّ ٱللَّهَ هُوَ ٱلۡحَقُّ وَأَنَّ مَا يَدۡعُونَ مِن دُونِهِۦ هُوَ ٱلۡبَٰطِلُ﴾

«ይህ አላህ እርሱ እውነት በመሆኑ፣ ከእርሱም ሌላ የሚግገዙት ነገር እርሱ ፍጹም ውሸት በመሆኑ፣ አላህም እርሱ የሁሉ በላይ ታላቅ

በመሆኑ ነው፡፡»

በምዕራፍ ሙእሚን ቁጥር 117 ላይ ደግሞ፡-

﴿ وَمَن يَدْعُ مَعَ ٱللَّهِ إِلَـٰهًا ءَاخَرَ لَا بُرْهَـٰنَ لَهُۥ بِهِۦ فَإِنَّمَا حِسَابُهُۥ عِندَ رَبِّهِۦٓ ۚ إِنَّهُۥ لَا يُفْلِحُ ٱلْكَـٰفِرُونَ ﴾

«ከአላህም ጋር ሌላን አምላክ ለእርሱ በእርሱ ማስረጃ የሌለውን የሚገዛ ሰው፣ ምርመራውም እጌታው ዘንድ ነው፤ እነሆ! ከሀዲዎች አይድኑም፡፡» በበቀራ ምዕራፍ ቁጥር 163 ላይ ደግሞ፡-

﴿ وَإِلَـٰهُكُمْ إِلَـٰهٌ وَٰحِدٌ ۖ لَّآ إِلَـٰهَ إِلَّا هُوَ ٱلرَّحْمَـٰنُ ٱلرَّحِيمُ ﴾

«አምላካችሁም አንድ አምላክ ብቻ ነው፤ ከእርሱ በቀር ሌላ አምላክ የለም፤ (እርሱ) እጅግ በጣም ርህሩህ አዛኝ ነው፡፡» በአል-በይና ምዕራፍ ቁጥር 5 ላይ ደግሞ፡-

﴿ وَمَآ أُمِرُوٓا۟ إِلَّا لِيَعْبُدُوا۟ ٱللَّهَ مُخْلِصِينَ لَهُ ٱلدِّينَ حُنَفَآءَ ﴾

«አላህን ሃይማኖትን ለእርሱ ብቻ አጥሪዎች፣ ቀጥተኞች ሆነው ሊገግዙት፣ ሶላትንም አስተካክለው ሊሰግዱ፣ ዘካንም ሊሰጡ እንጂ፣ ያልታዘዙ ሲሆኑ (ተለያዩ)፤ ይህም ቀጥተኛይቱ (ሃይማኖት) ድንጋጌ ነው፡፡» እነዚህ ነጥቦች ላይ የሚያትቱ የቁርኣን አንቀጾች ብዙ ናቸው፡፡

ይህን ቃል በንግግር ብቻ ለሚገልጸው ሰው፣ ቃሉ ለእሱ የረባ ነገር የሚጠቅመው ነገር የለም፤ ከሺርክ አዘቅጥ (አዙሪት) ውስጥ አይወጣም፡፡ ነገር ግን የቃሉን ትርጉሙም ያወቀ፣ በእሱም እውነት ያለ እንዲሁም በእሱ ትክክለኛ ትርጓሜ መሰረት የሰራ ሰው፣ በቃሉ ተጠቃሚ ይሆናል፡፡

በዘመነ-ረሱል (ሶ. ዐ. ወ) አስመሳዬች (ሙናፊቆች) እነሱ

ከእሳት የታችኛው ክፍል (አዘቅጥ) ውስጥ የሚገቡ ሆነው፣ ላኢላሃ ኢለላህ የሚለውን ቃል ይሉት ነበር፡፡ ይህን ቅጣት የሚቀምሱበት ምክንያት እነሱ በቃሉ ያላመኑ፣ ስራን ለአላህ ብቻ የማይሰሩና በቃሉ ትክክለኛ ትርጓሜም መሰረት የማይመሩ ስለሆነ ነው፡፡

ከሁሉም እጅግ በጣም የከፋ ክህደት አንጸባራቂዎቹ የሁዲዎችም ከሃዲ ሆነው ቃሉን ይሉታል፡፡ ይሁን እንጂ ለእነሱም ቃሉ አይጠቅማቸውም፡፡ ምክንያት የሁዲዎች በመልዕክቱ ትክክለኛ ትርጓሜ መሰረት የማይሰሩ ስለሆነ ነው፡፡ በዚህ ኡማ ውስጥ ቀብር አምላኪዎችና ‹‹አውሊያዎች››ን አምላኪዎች ለቀብርና ‹‹አውሊያዎች›› ለሚሏቸው ወገኖች ለአላህ የሚገባውን አምልኮ ለእነሱ ስለሚያደርጉ ክህደትን አንጸባርቀዋል፡፡ እነዚህ ወገኖች ይህን ቃል በንግግር ቢገለጹትም፣ ነገር ግን መልሰው በንግግራቸው፣ በእምነታቸውና በስራቸው ይጻረሩታል፡፡

የተወሰኑ ሙስሊሞች አዋቂዎች ላኢላሃ ኢለላህ ስምንት መስፈርቶች እንዳሉት አውስተዋል፡፡ እነዚህ መስፈርቶቹም የሚከተሉት ናቸው፡፡

1ኛ. **ዕውቀት (ዒልም)፡-** እውቀት የማይምነት ተጻራሪ ነው፡፡ ቀደም ብሎ እንደተገለጸው ላኢላሃ ኢለላህ ማለት ከአላህ ሌላ የሚመለክ አምላክ የለም ማለት ነው፡፡ ስለሆነም የሰው ልጅ ከአላህ ውጪ የሚያደርጋቸው አምልኮታዊ ተግባሮች ሁሉ ውድቅ ናቸው፡፡

2ኛ. **እርግጠኝነት (የቂን)፡-** እርግጠኝነት የጥርጣሬ ተቃራኒ ነው፡፡ ይህን ቃል የሚናገረው ሰው፣ አላህ በእውነት መመለክ የሚገባው መሆኑን እርግጠኛ መሆን አለበት፡፡

3ኛ. **ስራን ፍጹም ለአላህ ማድረግ (ኢኽላስ)፡-** የሰው ልጅ የሚሰራውን ስራ ሁሉ ለአላህ ብሎ መስራት አለበት፡፡ ከአምልኮት የተወሰነውን ለነቢይ፣ ለወሊይ፣ ለንጉስ፣ ለጣኦት፣ ለጂኒይ ወይም

ለሌላ ማድረግ (መስጠት) በአላህ ላይ ባዕድ አምልኮ መፈጸም ነው፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ ይህ መስፈርት (ኢኽላስ) ተግባራዊ አልሆነም ማለት ነው፡፡

4ኛ. እውነተኛነት (አስሲድቅ)፡- ይህን ቃል የሚናገረው ሰው፣ በሚለው ቃል ላይ እውነተኛነት ሊሰማው ይገባል፡፡ ይህም ማለት ደግሞ ልቡ ከምላሱ ጋር እንዲሁም ምላሱ ከቀልቡ ጋር ስሙሙ መሆን ሲችሉ ነው፡፡ አንድ ሰው ቃሉን በምላሱ ብቻ ገልጾ፣ በቃለ-መልዕክቱ ግን ልቡ የሸፈተና ብሎም ያላመነ ከሆነ፣ ቃሉን በምላሱ መናገሩ ምንም አይጠቅመውም፡፡ በዚህም ሁኔታው የማስመሰል ስራ እየሰራ ስለሆነ እምነቱና አካሄዱ እንደሙናፊቆቹ ሆነ ማለት ነው፡፡

5ኛ. ውዴታ (አል-መሀባ)፡- ይህ ማለት አንድ ሰው ልዕልናና ልቅና የተገባውን አላህ መውደድ ነው፡፡ ይህን ቃል በንግግር የሚገልጽ ሰው አላህን የማይወድ ከሆነ ካሃዲ ሆነ ማለት ነው፡፡ በዚህም አቋሙ እንደሙናፊቆቹ እንዲሁም ገና ወደ ኢስላም ከቶ ያልገባ ሰው ይሆናል፡፡ ይህን ሃሳብ ከሚመለከቱ ቁርኣናዊ ማስረጃዎች መካከል የሚከተሉት ናቸው፡-

﴿ قُلْ إِن كُنتُمْ تُحِبُّونَ ٱللَّهَ فَٱتَّبِعُونِى يُحْبِبْكُمُ ٱللَّهُ ﴾

‹‹በላቸው፡- አላህን የምትወዱት እንደሆናችሁ ተከተሉኝ፤ አላህ ይወዳችኋልና›› (ኣሊ-ዒምራን፣ 31)፡፡

﴿ وَمِنَ ٱلنَّاسِ مَن يَتَّخِذُ مِن دُونِ ٱللَّهِ أَندَادًا يُحِبُّونَهُمْ كَحُبِّ ٱللَّهِ ۖ وَٱلَّذِينَ ءَامَنُوٓا۟ أَشَدُّ حُبًّا لِّلَّهِ ﴾

‹‹ከሰዎችም ከአላህ ሌላ ባላንጣዎችን (ጣዖታትን) አላህን እንደሚወዱ፣ የሚወዱዋቸው ሆነው የሚይዙ አልሉ፤ እነዚያ ያመኑትም አላህን በመውደድ (ከእነርሱ) ይበልጥ የበረቱ ናቸው፡፡›› (አል-በቀራ፣ 165)፡፡ በዚህ ነጥብ ላይ

የሚያትቱ ቁርኣናዊ አንቀጾች ብዙ ናቸው፡፡

6ኛ. ለትርጓሜው ማደር (አል-ኢንቂያድ)፡- ይህ ማለት አንድ ሰው አላህን ብቻ ሊያመልክና ለሸሪዓውም የሚያድር (የሚታዘዝ) መሆን አለበት ማለት ነው፡፡ በላኢላሃ ኢለላህና በእሱ ሀቅ መሆን ያምናል፡፡ ነገር ግን ቃሉ በሚለውና በአላህ አንድነት ያላመነ ከሆነና እንዲሁም ለሸሪዓው ታዛዥ ካልሆነ፣ እንዲያውም ይባስ ብሎ ይህን ከመፈጸም ከተኩራራ፣ ይህ ሰው ሙስሊም ሳይሆን የኢብሊስንና የመሰሎቹን መንገድ ተከታይ ነው፡፡

7ኛ. መልዕክቱን መቀበል (አል-ቀቡል)፡- ይህ ማለት ቃሉ አላህን በብቸኝነት መመለኩንና ዒባዳ ለሱ ብቻ መሆንን እንዲሁም ከእሱ ውጪ ያሉ ነገሮችም መካድ እንዳለበት የሚያመለክት ሲሆን፣ ይህን አስተሳሰብንም ወዶና ፈቅዶ ከመቀበሉ በላይ በእምነቱ የሙጥኝ ማለት ይኖርበታል፡፡

8ኛ. ከአላህ ውጪ ባለው ነገር መካድ (አል-ኩፍር)፡- ይህ ማለት ከአላህ ውጪ ከሚመለኩ ነገሮች ራሱን ሊያርቅና ያላግባብ የሚመለኩት እነዚህ ነገሮችም በፍጹም ሊመለኩ የማይገባቸው ነገሮች መሆናቸውን ሊያምን ነው፡፡ አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿فَمَن يَكۡفُرۡ بِٱلطَّٰغُوتِ وَيُؤۡمِنۢ بِٱللَّهِ فَقَدِ ٱسۡتَمۡسَكَ بِٱلۡعُرۡوَةِ ٱلۡوُثۡقَىٰ لَا ٱنفِصَامَ لَهَاۗ وَٱللَّهُ سَمِيعٌ عَلِيمٌ﴾

«በጣኦትም የሚክድና በአላህ የሚያምን ሰው ለእርሱዋ መበጠስ የሌላትን ጠንካራ ዘለበት በእርግጥ ጨበጠ፤ አላህም ሰሚ አዋቂ ነው» (አል-በቀራ፣ 256)፡፡ በትክክለኛ ዘገባ እንደተገለጸው፣ ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡-

«مَنْ قَالَ لَا إِلَهَ إِلَّا اللّٰه، وَكَفَرَبِمَا يُعْبَدُ مِنْ دُونِ اللّٰه، حَرُمَ مَالُهُ وَدَمُه، وَحِسَابُهُ عَلَى اللّٰه»

«ላኢላሃ ኢለላህ (ከአላህ በስተቀር የሚመለክ አምላክ የለም) ያለ ሰው፣ እንዲሁም ከአላህ ውጪ በሚመለኩ ነገሮች የካደ ሰው፣ ገንዘቡ፣ ህይወቱ ጥብብቅ ይሆናሉ፡፡ እሱን የሚተሳሰበው አላህ ነው፡፡» (ሙስሊም የዘገቡት)፡፡ በሌላ የሀዲስ ዘገባ የአላህ መልዕክተኛው እንዲህ ይላሉ፡-

«مَنْ وَحَّد اللّٰه، وَكَفَرَ بِمَا يُعْبَدُ مِنْ دُونِ اللّٰه، حَرُمَ مَالُهُ وَدَمُه»

«አላህን አንድ አድርጎ ያመለከ፣ እንዲሁም ከአላህ ውጪ በሚመለኩ ነገሮች የካደ ሰው፣ ገንዘቡና ህይወቱ ጥብብቅ ይሆናሉ፡፡» (ሙስሊም በትክክለኛ ዘገባ አውስቶታል)፡፡

ጉዳዩ እንደዚህ ከሆነ በሁሉም ሙስሊሞች ላይ የቃሉን መስፈርቶች በመጠበቅ የቃሉን ትክክለኛ መልዕክት በሚገባ መንገድ የመፈጸም ግዴታ አለባቸው፡፡ አንድ ሙስሊም የዚህን ቃል ትክክለኛ ትርጓሜ ካንጸባረቀና በእሱ ላይ ቀጥ ካለ የመስፈርቱን ዝርዝር ጉዳዮች ባያውቅም እንኳ ገንዘቡ ጥብብቅ ሙስሊም ይሆናል፡፡ ምክንያቱም የመልዕክቱ ዋና ዓላማ ቃለ-መልዕክቱ እውነት መሆኑን ማወቅና በሱ መስራት ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ አንድ አማኝ መልዕክቱ የሚጠይቀውን ዝርዝር ነጥቦች ሳያውቅ ጥቅል መልዕክቱን ተረድቶ እሱኑ ተግባራዊ ማድረግ ከቻለ የሚጠበቅበትን አድርጓል ማለት ነው፡፡

ሰዎች ከአላህ ውጪ የሚያመለኩት ነገርና ሰዎች ለእሱ የሚደርጉለትን አምልኮ የሚወድ አካል ጣኦት ይሰኛል፡፡ አላህ በቁርኣኑ እንዲህ ይላል፡-

﴿فَمَن يَكْفُرْ بِٱلطَّٰغُوتِ وَيُؤْمِنۢ بِٱللَّهِ فَقَدِ ٱسْتَمْسَكَ بِٱلْعُرْوَةِ ٱلْوُثْقَىٰ لَا ٱنفِصَامَ لَهَا ۗ وَٱللَّهُ سَمِيعٌ عَلِيمٌ﴾

«በጣኦትም የሚክድና በአላህ የሚያምን ሰው ለእርሱዋ መበጠስ የሌላትን ጠንካራ ዘለበት በእርግጥ ጨበጠ፤

አላህም ሰሚ አዋቂ ነው» (አል-በቀራ፣ 256)፡፡ በሌላ የቁርኣን አንቀጽም፡

﴿وَلَقَدۡ بَعَثۡنَا فِي كُلِّ أُمَّةٖ رَّسُولًا أَنِ ٱعۡبُدُواْ ٱللَّهَ وَٱجۡتَنِبُواْ ٱلطَّٰغُوتَ﴾

«በየህዝቡም ሁሉ ውስጥ አላህን ተገዙ፤ ጣዖትንም ራቁ» (አንነህል፣ 36)፡፡

ይሁን እንጂ የሆነ አካል ሰዎች እሱን ቢያመልኩትና ነገር ግን እሱ ማምለካቸውን ካልወደደ ጣኦት አይባልም፡፡ ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የሚሆኑት አንቢያእ፣ ደጋጎች ሰዎች፣ መላኢካ ናቸው፡፡ በአንጻሩ ግን ትክክለኛ ጣኦት የሚባለው፣ ሰዎች እሱን እንዲያመልኩት እንደ ሰይጣን ወደ እሱ ጥሪ ያደረገና ጥሪውም በቀላሉ ተቀባይነት እንዲኖረው ጥሪውና ሳቢ ያደረገ ነው፡፡ እኛንና ሙስሊሞችን አላህ ከሁሉም መጥፎ ነገር እንዲጠብቀን እንለምነዋል፡፡

ላኢላሃ ኢለላህ የሚለው ቃለ-ተውሂድ ሙሉዕነቱን የሚያጓድል ወይም ከፊል ገጽታውን የሚጻረር ማንኛውም ስራ፣ ንግግር ወይም እምነት በአጠቃላይም የትልቁ የሺርክ መገለጫ ከሆነ፣ ቃሉን ሙሉ ለሙሉ የሚጻረረው ነው የሚሆነው፡፡ ለምሳሌ የሞቱ ሰዎችን መማጸን ወይም መለመን፣ ተውሂድን ሙሉ ለሙሉ የሚጻረር ተግባር ነው፡፡ ቃሉንም ከመቃወሙ አልፎ ላኢላሃ ኢለላህን ፉርሽ (ውድቅ) ያደርገዋል፡፡ እንዲሁም በማያሻማ መልኩና ሙስሊም ሊቃውንት ሙሉ ለሙሉ በተስማሙበትን አቋም (ኢጅማዕ) እርም (ሀራም) ያደረጉትን ነገር፣ ማለትም እንደ ዝሙት፣ አስካሪ መጠጥ፣ የወላጆችን ሙብት መጣስ፣ ወለድ መጠቀምና ሌሎች መሰል እርም ነገሮችን የተፈቀዱ ማድረግም ከላኢላሃ ኢለላህ መልዕክት ጋር የሚጣረስ ነው፡፡ እንዲሁም በተመሳሳይ ሁኔታ አላህ ግዴታ ያደረጋቸው በንግግርና በተግባር የሚገለጹ፣ የማያሻሙና ሙስሊም ሊቃውንት አንድ አቋም ይዘው የተስማሙባቸውን

ጉዳዮች ላይ ለምሳሌ በአምስቱ የግዴታ ሶላቶች፣ ዘካ፣ የረመዳን ጾም፣ ለወላጆቹ መልካም መዋል፣ ሸሃደተይኒ (ላኢላሃኢለላህ ሙሀመዱን ረሱሉላህ) በመግለጽና መሰል ነገሮች ላይ ማስተባበል ቃሉን እንደመጻረር ይቀጠራል፡፡

ከንግግሮችና ከስራዎች መካከል ተውሂድንና ኢማንን የሚያሚሸሹ አመለካከቶች እንዲሁም የቃሉን ምሉዕነት የሚጻረሩ ነገሮች ብዙ ናቸው፡፡ ለምሳሌ ትንሹ ሺርክ (የዩልኝ ስራ፣ ከአላህ ውጪ መማል፣ አላህና እገሌ ስለፈለጉ ነው ብሎ ሃሳብ መሰንዘር፣ ይህ ነገር ከአላህና ከእገሌ የመጣነውና መሰል አባባሎችን መናገር) ወንጀሎች ሁሉ ተውሂድንና ኢማንን የሚያዳክሙና የቃሉንን ምሉዕነት የሚጻረሩ ናቸው፡፡ ስለሆነም ከሁሉም አይነት ተውሂድንና ኢማንን ከሚጻረሩ ነገሮችና እንዲሁም ምንዳውን ከሚያጓድሉ ነገሮች መጠንቀቅ ግዴታ ነው፡፡

እንደ አህለ ሱና ወልጀመዓ አቋም መሰረት፣ እምነት በንግግርና በተግባር በጣምራ የሚገለጽ ነው፡፡ መልካም ስራ በተሰራ ቁጥር የእምነት ጥንካሬ የሚጨምርና በተቃራኒው ደግሞ ወንጀል በተሰራ ቁጥር ኢማን እየቀነሰ (እየሚሸሸ ብሎም እየጠፋ) ይሄዳል፡፡

እላይ ለጠቀስነው ጉዳይ መረጃችንም የሚከተለው ቁርአናዊ አንቀጽ ነው፡-

﴿وَإِذَا مَآ أُنزِلَتْ سُورَةٌ فَمِنْهُم مَّن يَقُولُ أَيُّكُمْ زَادَتْهُ هَٰذِهِۦٓ إِيمَٰنًا ۚ فَأَمَّا ٱلَّذِينَ ءَامَنُوا۟ فَزَادَتْهُمْ إِيمَٰنًا وَهُمْ يَسْتَبْشِرُونَ﴾

‹‹ሱራም (ምዕራፍ) በተወረደች ጊዜ ውስጥ፣ ‹ማንኛችሁ ነው ይህቺ (ምዕራፍ) እምነትን የጨመረችለት?› የሚል ሰው አልለ፤ እነዚያ ያመኑትማ የሚደሰቱ ሲሆኑ፣ እምነትን ጨመረችላቸው›› (አት-ተውባ፣ 124)፡፡ እንዲሁም ቁርኣን፣

﴿ إِنَّمَا ٱلْمُؤْمِنُونَ ٱلَّذِينَ إِذَا ذُكِرَ ٱللَّهُ وَجِلَتْ قُلُوبُهُمْ وَإِذَا تُلِيَتْ عَلَيْهِمْ ءَايَٰتُهُۥ زَادَتْهُمْ إِيمَٰنًا وَعَلَىٰ رَبِّهِمْ يَتَوَكَّلُونَ ﴾

‹‹ፍጹም ምእመናን እነዚያ አላህ በተወሳ ጊዜ ልቦቻቸው የሚፈሩት፣ በእነሱም ላይ አንቀጾቻችን በተነበቡ ጊዜ እምነትን የሚጨምሩላቸው፣ በጌታቸውም ላይ ብቻ የሚመኩት ናቸው›› (አል-አንፋል፣ 2)፡፡

﴿ وَيَزِيدُ ٱللَّهُ ٱلَّذِينَ ٱهْتَدَوْا۟ هُدًى ﴾

‹‹እነዚያንም የቀኑትን ሰዎች አላህ ቅንነትን ይጨምርላቸዋል›› (መርየም፣ 76)፡፡

ይህን ነጥብ የሚመለከቱ ብዙ ቁርኣናዊና ሱናዊ ማስረጃዎች አሉ፡፡ ሙስሊም ሊቃውንትም በዐቂዳ፣ በተፍሲር፣ በሀዲስ መጻህፍታቸው ጉዳዩን በሚገባው መልኩ አብራርተውታል፡፡ እነዚህን መረጃዎች ማግኘት የፈለገ ሰውም መረጃዎቹን ማግኘት ይችላል፡፡ ምስጋና ለአላህ ይሁን፡፡

# ባዕድ አምልኮ መፈጸምና ማብራሪያው

ጥያቄ፡- ሺርክ ምንድን ነው?

﴿ يَـٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُوا۟ ٱتَّقُوا۟ ٱللَّهَ وَٱبْتَغُوٓا۟ إِلَيْهِ ٱلْوَسِيلَةَ ﴾

‹‹እናንተ ያመናችሁ ሆይ! አላህን ፍሩ፤ ወደ እርሱም መቃረቢያን (መልካም ስራን) ፈልጉ›› (አል-ማኢዳ፣ 35)፡ ፡ የሚለው ቁርአናዊ አንቀጽ ማብራሪያስ ምንድን ነው?

መልስ፡- ሺርክ የሚለው ቃል ከስሙ መረዳት እንደሚቻለው ‹‹ማጋራት›› ማለት ነው፡፡ ይህም ማለት አምልኮትን ከአላህ ሌላ፣ ለሌላ አካላት ማጋራት ነው፡፡ ይህም ጣኦቶችንና ሌሎችን በመለመን፣ በጭንቅ ጊዜ እንዲደርሱ በመማጸን፣ በእነሱ በመሳል (ነዝር)፣ ለእነሱ በመስገድ (በመንበርከክ-ያልተገባ ክብር በማሳየት)፣ ለእነሱ በመጾም፣ ለእነሱ በመሰዋት (በማረድ- ለምሳሌ ሰዎች ግብጽ ላይ ለአህመድ አል-በደዊ፣ የመን ላይ ደግሞ ለዐይዱሩስ፣ ወዘተ እንደሚያርዱት)፣ ለሰዎች በመስገድ፣ ከአላህ መልዕክተኛ ወይም ከዐብዱል ቃድር ጀይላኒ ወይም ከዐይዱሩስ ወይም ከሌሎች ሙታንና ሩቅ ሰዎች እርዳታን በመጠየቅ (በመሻት) ይገለጻል፡፡ እነዚህ የተዘረዘሩት ሁሉ የሺርክ ተግባር ይሰኛሉ፡፡

እንደዚሁም አንድ ሰው ከዋክብትንና ጂኒን የሆነ ጉዳይ ከጠየቀ ወይም እነሱን በጭንቅ ጊዜ ከተማጸነ ወይም ከእነሱ ልዩ እርዳታ ከፈለገ ወይም ይህን የመሰለ ተመሳሳይ ነገር ከፈጸመ፣ እንደዚሁም እነዚህኑ አምልኮቶች ለግዑዝ ነገሮች ወይም ለሙታን ወይም ሩቅ ለሆኑ ሰዎች ካደረገ አሁንም ድርጊቱ ባዕድ አምልኮ (ሺርክ) ከመሆን አይዘልም፡፡ ልቅና የተገባው አላህ በቁርአኑ እንዲህ ይላል፡-

﴿ وَلَوْ أَشْرَكُوا۟ لَحَبِطَ عَنْهُم مَّا كَانُوا۟ يَعْمَلُونَ ﴾

« ... ባጋሩትም ኖሮ፣ ይሰሩት የነበሩት፣ ከእነሱ በታበሰ ነበር» (አል-አንዓም፣ 88)፡፡ በሌላ አንቀጽም፣

﴿ وَلَقَدْ أُوحِيَ إِلَيْكَ وَإِلَى ٱلَّذِينَ مِن قَبْلِكَ لَئِنْ أَشْرَكْتَ لَيَحْبَطَنَّ عَمَلُكَ وَلَتَكُونَنَّ مِنَ ٱلْخَٰسِرِينَ ﴾

«ብታጋራ ስራህ በእርግጥ ይታበሳል፤ በእርግጥም ከከሀዲዎቹ ትሆናለህ ማለት ወደ አንተም ወደ እነዚያ ከአንተ በፊት ወደ ነበሩበት በእርግጥ ተወርዷል» (አዝ-ዙመር፣ 65) ይላል፡፡

ከአላህ ውጪ ያለን አካል ሙሉ ለሙሉ ማምለክም ሺርክ ሲሰኝ፣ ስራው ደግሞ ሺርክ ወይም ኩፍር (ክህደት) ይባላል፡፡ ይህም ከአላህ ሙሉ ለሙሉ ፊቱን ያዞረና አምልኮቱን ከአላህ ውጪ ላሉ ነገሮች ማለትም ለዛፎች፣ ለድንጋዮች፣ ለጣኦቶች፣ ለጂኒዎች፣ ሰዎች «አውሊያእ» ብለው ለሚጠሩዋቸውና ለሚያመልኩዋቸው ወይም ለሚሰግዱላቸው ወይም ለሚጾምላቸው ለሆኑ ለተወሰኑ ሙታን ያደረገ ነው፡፡ ያለምንም ተቀናቃኝ አምልኮ የሚገባው አላህ ሙሉ ለሙሉ ተዘንግቶ፣ አምልኮ ለፍጡራን ከተፈጸመ ይህ እጅግ በጣም ትልቁ ክህደት (ኩፍር) ወይም እጅግ በጣም ብርቱው ሺርክ ነው፡፡ ደህንነትን ከአላህ ዘንድ እንጠይቃለን፡፡

ልክ እንደዚሁ የአላህን ግኝነት (ኗሪነት) የሚነቅፉና «ጌታ የለም፤ ይልቅ ህይወት ቁስ ነች» ብለው የሶሻሊስት አስተሳሰብ አራማጆችን አቋም የሚያራግቡ፣ የአላህን ኗሪነት የሚጻረሩና የሚነቅፉ ሰዎች እጅግ በጣም ከሃዲዎችና ጠማማዎች ናቸው፡፡ በዚህም አቋማቸው እጅግ በጣም ከፍተኛ ከሆነ ጥመት ውስጥ የተዘፈቁ ሲሆን፣ እትልቁ ሺርክም ውስጥ ገብተዋል፡፡ በአጠቃላይ እነዚህ እምነቶችና መሰሎቻቸው ሺርክ ይባላሉ፤ አስተሳሰቡም በአላህ መካድ ይሰኛል፡፡ አላህ ከዚህ አይነቱ የእምነት አደጋ እንዲጠብቀን ደህንነትን እንጠይቀዋለን፡፡

ሰዎች ከማሃይምነታቸው በመነጨ ሁኔታ ሙታንን መለመንና እነሱን በጭንቅ ጊዜ መማጸን ወደ አላህ እንደ መቃረብ (ተወሱል) አድርገው ስለሚያስቡት ስህተት ላይ ይወድቃሉ፡፡ የሚተገብሩት ተግባርም በኢስላም የተፈቀድ አድርገው ያስቡታል፡፡ ይህ ድርጊታቸው ግን ትልቅ ስህተት ነው፡፡ ምክንያቱም ተግባሩ ትልቅ ሺርክ ነውና፡፡ የተወሰኑ ኣላዋቂዎችና ባዕድ አምልኮ ውስጥ የተዘፈቁ ሰዎች ተግባሩን ‹‹ወሲላ›› (ወደ አላህ መቃረቢያ) ብለው ይጠሩታል፡፡ ነገር ግን ተግባሩ የባዕድ አምላኪዎች መንገድና እንዲህ አይነቱን ተግባርም አላህ በቁርኣኑ ያንቋሸሸውና ያነወረው ነው፡፡ ስለሆነም አላህ ተግባሩን ለማውገዝና ለማስጠንቀቅ መልዕክተኞችን ልኳል፤ መጻህፍትን አውርዷል፡፡

ለነገሩ በቁርኣን የተወሳው ‹‹ወሲላ››፡-

﴿ يَـٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ ٱتَّقُواْ ٱللَّهَ وَٱبۡتَغُوٓاْ إِلَيۡهِ ٱلۡوَسِيلَةَ ﴾

‹‹እናንተ ያመናችሁ ሆይ! አላህን ፍሩ፤ ወደ እርሱም መቃረቢያን (መልካም ስራን) ፈልጉ›› (አል-ማኢዳ፣ 35) ተብሎ ነው የተገለጸው፡፡ በዚህ አንቀጽ ‹‹ወደ እሱ (አላህ) መቃረብ›› የሚለው ጽንሰ ሃሳብ መልእክት፣ የእሱን ትዕዛዝ በመፈጸም ወደ እሱ መቃረብን ነው የሚያመለክተው፡፡ በሁሉም አዋቂዎች ዘንድ ለአንቀጹ እንደተሰጠው ፍችም፣ ሶላት፣ በሐጂና በሌላ አጋጣሚ የሚፈጸመው እርድ፣ ጾም፣ ሶደቃ፣ ዚክርና ቁርኣን ማንበብ ወደ አላህ መቃረብ (ወሲላ) ናቸው፡፡ ይህም በማኢዳ ምዕራፍ ቁጥር 35 ላይ የተወሳው ፍች ነው፡-

﴿ يَـٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ ٱتَّقُواْ ٱللَّهَ وَٱبۡتَغُوٓاْ إِلَيۡهِ ٱلۡوَسِيلَةَ ›› ﴾

‹‹እናንተ ያመናችሁ ሆይ! አላህን ፍሩ፤ ወደ እርሱም መቃረቢያን

(መልካም ስራን) ፈልጉ፡፡» ይህ ማለት ደግሞ የአንቀጹ ትርጉም «የአላህን ትዕዛዝ በመፈጸም ወደ እሱ ቅርበትን ፈልጉ» የሚል መልዕክት ያለው ለመሆኑ ኢብኑ ከሲር፣ ኢብኑ ጀሪር፣ አል-በገዊ፣ ሌሎች የተፍሲር ሊቃውንት ይህንኑ ሃሳብ በጥራዛቸው አውስተውታል፡፡ ወደ አላህ መቃረብ የሚገለጸው እሱን በመታዘዝና ወደ እሱ ቅርበትን በመፈለግ ነው፡፡ ይህ ማለት ደግሞ የትም ቦታ ሆናችሁ፣ አላህ በደነገገው መንገድ ማለትም ሶላት በመስገድ፣ ጾም በመጾም፣ ሶደቃና ሌሎችን መልካም ነገሮች በመስራት ወደ አላህ መቃረብ ይገኛል ማለት ነው፡፡ ስለሆነም ነው አላህ በሌላ ቁርኣናዊ አንቀጽ፣

﴿ أُوْلَٰٓئِكَ ٱلَّذِينَ يَدۡعُونَ يَبۡتَغُونَ إِلَىٰ رَبِّهِمُ ٱلۡوَسِيلَةَ أَيُّهُمۡ أَقۡرَبُ وَيَرۡجُونَ رَحۡمَتَهُۥ وَيَخَافُونَ عَذَابَهُۥٓۚ

«እነዚያ እነርሱ የሚግገዙዋቸው፣ ማንኛውም (ወደ አላህ) በጣም ቀራቢያቸው ወደ ጌታቸው መቃረቢያን (ስራ) ይፈልጋሉ» (አል-ኢስራእ፣ 57) ያለው፡፡

በዚህ መልክ ነው እንግዲህ የአላህ መልዕክተኞችና ተከታዮቻቸው አላህ በደነገገው በመታገል፣ በመጾም፣ አላህን በማውሳት፣ ቁርኣንን በማንበብና ሌሎች መልካም ነገሮችን በመፈጸም ወደ አላህ የሚቃረቡት፡፡

ነገር ግን አንዳንድ ሰዎች «ወሲላ» ማለት ለሙት አካል ጉዳዩን ያሳካልኛል ብሎ ማለምና በጭንቅ ወይም በችግር ጊዜ «አውሊያእን» መማጸን እንደሆነ አድርገው ያስባሉ፡፡ ይህ አስተሳሰብ ግን መሰረተ-ቢስ አስተሳሰብ ነው፡፡ አስተሳሰቡ ጣኦት አምልኳዊ አስተሳሰብ ሲሆን፣ ቁርኣንም ጉዳዩን አስመልክቶ እንዲህ ይላል፡-

﴿ وَيَعۡبُدُونَ مِن دُونِ ٱللَّهِ مَا لَا يَضُرُّهُمۡ وَلَا يَنفَعُهُمۡ

﴿وَيَقُولُونَ هَٰٓؤُلَآءِ شُفَعَٰٓؤُنَا عِندَ ٱللَّهِۚ﴾

‹‹ከአላህም ሌላ የማይጎዳቸውን፣ የማይጠቅማቸውን ይግገዛሉ፤ እነዚህም አላህ ዘንድ አማላጆቻችን ናቸው ይላሉ›› (ዩኑስ፣ 18)፡፡ ታዲያ አላህ ለዚህ እኩይ ለሆነ እምነታቸው እንዲህ ሲል በቁርኣኑ ምላሽ ይሳጣል፡-

﴿قُلۡ أَتُنَبِّـُٔونَ ٱللَّهَ بِمَا لَا يَعۡلَمُ فِي ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَلَا فِي ٱلۡأَرۡضِۚ سُبۡحَٰنَهُۥ وَتَعَٰلَىٰ عَمَّا يُشۡرِكُونَ﴾

‹‹አላህን በሰማያትን በምድር ውስጥ የማያውቀው ነገር ኖሮ፣ ትነግሩታላችሁን? በላቸው፤ ከሚያጋሩት ሁሉ ጠራ፤ ላቀም›› (ዩኑስ፣ 18)፡፡

# በክንድና በእጅ ላይ ክር ማንጠልጠል

ጥያቄ፡- የደረሰን አደጋን ለማስወገድና ለመከላከል ተብሎ ክርን ማንጠልጠል በኢስላም እንዴት ይታያል?

መልስ፡- ይህን ስራ የሚሰራ ሰው ሊነቀፍ ይገባል፡፡ ክርን የሚያንጠለጥል ሰው ስራው ትንሽ ሺርክ ነው፡፡ በዚህም ጉዳይ ላይ የአላህ መልዕክተኛው (ሶ. ዐ. ወ) እንዲህ ብለዋል፡-

«مَنْ تَعلَّق تَميمة فَلَا أَتمَّ اللّه لَهُ ، وَمَنْ تَعلَّق وَدعة فَلَا وَدع اللّه لَه.»

«ተማኢም (ሂርዝ) ያንጠለጠለ ሰው አላህ (ጉዳዩን) አይሙላለት፡፡ ወዳዕ ያንጠለጠለ ሰው ደግሞ አላህ ስክነትን አይለግሰው፡፡» (ኢማሙ አህመድ የዘገበው)፡፡

በሌላ የሀዲስ ዘገባ የአላህ መልዕክተኛ፡-

«مَنْ تَعلَّق تَميمة فَقد أشرك.»

«ተማኢምን (ሂርዝን) ያንጠለጠለ ሰው፣ በእርግጥም ሺርክ ሰራ» ብለዋል፡፡ (ኢማሙ አህመድ የዘገቡት)፡፡

ኹዘይፋ የሆነ ሰው እሱ ወዳለበት ቦታ በገባበት ወቅት፣ ሰውዬው ያለበትን የትኩሳት ህመም ለመፈወስ ብሎ ከእጁ ያንጠለጠለውን ክር ቆረጠበት፤ ተግባሩንም ነቀፈው፡፡ የሚከተለውንም የቁርኣን አንቀጽ አነበበ፡-

﴿ وَمَا يُؤْمِنُ أَكْثَرُهُم بِٱللَّهِ إِلَّا وَهُم مُّشْرِكُونَ ﴾

‹‹አብዛኛዎቻቸው እነርሱ አጋሪዎች ሆነው እንጂ፣ በአላህ አያምኑም›› (ዩሱፍ፣ 106)፡፡ ሑዘይፋ ሰውዬው የፈጸመው ተግባር ሺርክ እንደሆነ አብራራለት፡፡

ክሮችንና ሂርዞችን ማለትም አጥንትን ወይም የቀበሮ ጸጉርን ወይም ጥርስን ማንጠልጠል ወዳዕ (ለአይነ ጥላ መከላከያ) ሲሆን፣ ተግባሩ የጃሂሊያ እንቶ ፈንቶ አስተሳሰብ መገለጫ ነው፡፡ በኢስላም ዘንድም ንቅፍ ተግባር ነው፡፡

ሰዎች ቁርኣን የተጻፈበትን ነገር ‹‹ሂርዝ›› ወይም ‹‹አል-ጃሚዓት›› ብለው የሚጠሩትን ነገር ማንጠልጠል በኢስላም የሚፈቀድ ተግባር አይደለም፡፡ ምክንያቱም የአላህ መልዕክተኛ ተግባሩን የከለከሉት ጥቅል በሆነ መንገድ እንጂ፣ ቁርኣንን ወይም ሌላ ነገር ያለበት ብለው በተለዩ ሁኔታ ያስቀመጡት ነገር የለም፡፡ በዚህ መንገድም ቁርኣንን ከበሽታ መከላከያ አድርጎ መጠቀም፣ ክልክል ነገር እንዲተገበር መንገድ ጠራጊ ነው፤ የሺርክንም በር ይከፍታል፡፡ ስለሆነም መልዕክተኛው እንዲህ ብለዋል፡-

«إِنَّ الرقى وَالتَمَائِمِ وَالتِولَةَ شِرك»

‹‹ሩቅያ፣ ተማኢምና ቲወላ ሺርክ ናቸው፡፡›› (ኢማሙ አህመድ የዘገበው)፡፡

**ሩቃ፡-** በኢስላም ዕውቅና የሌለው ‹‹ሩቃ›› የሚባለው፣ ሸሪዓው በፈቀደው መንገድ ያልተጸመው ነው፡፡ ‹‹ተማኢም››ም ልጆችንና ሴቶችን ከሰው ዓይን ለመጠበቅ፣ እንደዚሁም የጂኒ በሽታ ከያዘው ሰው አካል (አንገት፣ እጅ፣ ክንድ፣ ወዘተ) ላይ የሚንጠለጠል ነው፡፡ ይህ ሁሉ ተግባር የሚነቀፍና የጃሂሊያ ተግባር ነው፡፡

**ቲወላ (መስተፋቅር)፡-** አንድ ሰው ሌላው ሰው ላይ ፍቅር እንዲኖረው ወይም የሆነን አካል እንዲጠላ ለማድረግ ተብሎ

የሚደረግ ነገር ነው፡፡ ስለሆነም ድርጊቱ ድግምት ነው፡፡ የአላህ መልዕክተኛም ተግባሩን ከባዕድ አምልኮ መድበውታል፡፡ ምክንያቱም ተግባሩን ለመፈጸም የጂኒንና የሰይጣንን እገዛ ስለሚጠይቅ ነው፡፡ በምላሹም ድግምት አድራጊው ወይም አድራጊዋ ይህን ተግባር የሚፈጽሙት እንዲሁ ሳይሆን ለጂኒና ለሰይጣን አምልኮት ከመፈጸም በላይ እነሱ የሚወዱትን ስራ በመስራት ወደ እነሱ በመቃረብ ነው፡፡

ክሮች፡- ክሮች (ኹዩጥ) የተማኢም አካል ናቸው፡፡ አንድ ሰው ባጋጠው ህመም ምክንያት ክርን ከእጁ ወይም ከትከሻው ላይ የሚያደርገው፣ ካጋጠመው ህመም እፈወሳለሁ ብሎ ስለሚያስብ ነው፡፡ ለነገሩ ይህ ተግባር ከኢስላም አኳያ ከሚነቀፉ ተግባራት መካከል አንዱ ነው፡፡ በዚህ አጋጣሚም ተግባሩን ከማረም አኳያም፣ የግዴታ ሊፈጸም የሚገባው ነገርም የተንጠለጠለውን ነገር መቁረጥ ነው፡፡

# ድግምት፣ ደጋሚና የድግምት ህክምና በኢስላም መነጽር

ጥያቄ፡- በአሁኑ ጊዜ ድግምትን መጠቀምና ወደ ጠንቋዮች መሄድ በብዛት ይታያል፡፡ ይህ ሁኔታ በኢስላም እንዴት ይታያል? የተደገመበትን ሰውስ እንዴት ማከም ይቻላል?

መልስ፡- ድግምት ከትላልቆቹ ወንጀሎች መካከል አንዱ ነው፡፡ እንዲያውም ኢስላምን አፍራሽ ከሆኑ ወንጀሎች መካከል አንዱ ነው፡፡ አላህ በተከበረው መጽሀፍ እንዲህ ይላል፡-

﴿وَٱتَّبَعُوا۟ مَا تَتْلُوا۟ ٱلشَّيَٰطِينُ عَلَىٰ مُلْكِ سُلَيْمَٰنَ ۖ وَمَا كَفَرَ سُلَيْمَٰنُ
وَلَٰكِنَّ ٱلشَّيَٰطِينَ كَفَرُوا۟ يُعَلِّمُونَ ٱلنَّاسَ ٱلسِّحْرَ وَمَآ أُنزِلَ عَلَى
ٱلْمَلَكَيْنِ بِبَابِلَ هَٰرُوتَ وَمَٰرُوتَ ۚ وَمَا يُعَلِّمَانِ مِنْ أَحَدٍ حَتَّىٰ يَقُولَآ
إِنَّمَا نَحْنُ فِتْنَةٌ فَلَا تَكْفُرْ ۖ فَيَتَعَلَّمُونَ مِنْهُمَا مَا يُفَرِّقُونَ بِهِۦ
بَيْنَ ٱلْمَرْءِ وَزَوْجِهِۦ ۚ وَمَا هُم بِضَآرِّينَ بِهِۦ مِنْ أَحَدٍ إِلَّا بِإِذْنِ ٱللَّهِ ۚ
وَيَتَعَلَّمُونَ مَا يَضُرُّهُمْ وَلَا يَنفَعُهُمْ ۚ وَلَقَدْ عَلِمُوا۟ لَمَنِ ٱشْتَرَىٰهُ
مَا لَهُۥ فِى ٱلْءَاخِرَةِ مِنْ خَلَٰقٍ ۚ وَلَبِئْسَ مَا شَرَوْا۟ بِهِۦٓ أَنفُسَهُمْ ۚ
لَوْ كَانُوا۟ يَعْلَمُونَ ﴿١٠٢﴾ وَلَوْ أَنَّهُمْ ءَامَنُوا۟ وَٱتَّقَوْا۟ لَمَثُوبَةٌ مِّنْ
عِندِ ٱللَّهِ خَيْرٌ ۖ لَّوْ كَانُوا۟ يَعْلَمُونَ﴾

‹‹ሰይጣናትም በሱለይማን (ሰለሞን) ዘመነ መንግስት የሚያነቡትን (ድግምት) ተከተሉ፡፡ ሱለይማን አልካደም፤ (ድግምተኛ አልነበረም)፤ ግን ሰይጣናት ሰዎችን ድግምትን የሚያስተምሩ

ሲሆኑ ካዱ፤ ያንንም በባቢል፣ በሁለቱ መላእክት በሃሩትና በማሩት ላይ የተወረደውን ነገር (ያስተምሩዋቸዋል)፡፡ ‹‹እኛ መፈተኛ ነንና አትካድ›› እስከሚሉም ድረስ አንድንም አያስተምሩም፤ ከእነሱም በሰውዬውና በሚስቱ መካከል በእርሱ የሚለዩበትን ነገር ይማራሉ፡፡ እነርሱም በአላህ ፈቃድ ካልሆነ በእርሱ አንድንም ጎጂዎች አይደሉም፤ የሚጎዳቸውንና የማይጠቅማቸውንም ይማራሉ፡፡ የገዛውም ሰው ለእርሱ በመጨረሻይቱ አገር ምንም ዕድል የሌለው መሆኑን በእርግጥ አወቁ፡፡ ነፍሶቻቸውንም በእርሱ የሸጡበት ዋጋ ከፋ! የሚያውቁ በሆነ ኖሮ (ባልሰሩት ነበር)፡፡ እነርሱም (አይሁዶች) ባመኑና በተጠንቀቁ ኖሮ፣ (በተመነዱ ነበር) የሚያውቁ ቢሆኑ፣ ከአላህ ዘንድ የሆነው ምንዳ (ነፍሶቻቸውን ከሚሸጡበት) በላጭ ነው›› (አል-በቀራ፣ 103-102)፡፡

አላህ በእነዚህ ሁለት አንቀጾች ሰይጣኖች ለሰዎች ድግምት እንደሚደግሙ ይናገራል፡፡ እነሱ በሚሰሩት ነገር ካሃዲ ሲሆኑ፣ ሁለቱ መላኢካ ደግሞ ለሚያስተምሩት ሰው ድግምትን መጠቀም ክህደትና መከራ (ፊትና) እንደሆነ ያስተምራሉ፡፡

አላህም ጨምሮ እንደተናገረው ጥንቆላን የሚማሩ ሰዎች የሚጠቅማቸውን ሳይሆን የሚጎዳቸውን ነገር ነው የሚማሩት፡፡ እንደዚሁም በመጪው ዓለም ምንም አይነት ዕድል የላቸውም፡፡ ይህም ማለት እነዚህ ሰዎች በመጪው ዓለም ምንም አይነት መልካም ነገር የማግኘት ተስፋ የላቸውም፡፡

እንዲሁም ጠንቋዋዮች በድግምታቸው አማካኝነት በባልና ሚስት መካከል ልዩነት እንዲፈጠር ምክንያት ይሆናሉ፡፡ ለነገሩ በአላህ ፈቃድ እንጂ፣ ጥንቆላ አንድንም ሰው አይጎዳም፡፡ ይህ ማለት ምናልባት አንድ ሰው በድግምት ምክንያት አደጋ ቢደርስበት፣ ችግሩ የደረሰበት ከቀደር አኩዋያ እንጂ፣ ድግምት አደጋ በማድረሱ ሸሪዓዊ ዕውቅና የሚሰጠው አያደርገውም፡፡ ምክንያቱም ሁሉም ዩኒቨርሱ ላይ የሚከሰተው ነገር በአላህ የቀደር ውሳኔ ፈቃድ

ነውና፡፡ በዩኒቨርሱ ውስጥ ያለሱ ፈቃድና ውሳኔ የሚከሰት አንዳች ነገር የለም፡፡ በተጨማሪም አንቀጹ ድግምት የኢማንና የተቅዋ ተጻራሪ እንደሆነ አብራርቱዋል፡፡

ምንም እንኳ ተግባሩን የሚፈጽመው ሰው ራሱን ኢስላም ላይ እንደሆነ አድርጎ ቢሞግትም፣ ከዚህ ማስረጃ አንጻር ግን ድግምት ክህደት፣ ጥመትና ከኢስላምም እንደመቀልበስ የሚቆጠር ተግባር ነው፡፡ በትክክለኛ ዘገባ አቡሁረይራ እንደዘገቡት፣ መልዕክተኛው እንዲህ ይላሉ፡- «ሰባት አይነት አጥፊ ነገሮችን ራቁ» አሉ፡፡ እኛም፣ «እነዚህ እነማን ናቸው?» አለን፡፡ እሳቸውም፣ «ከአላህ ጋር ሌላን ፍጡር በአምልኮ ማጋራት (ሺርክ)፣ ድግምት፣ ያለ አግባብ አላህ እርም ያደረገውን የሰው ልጅ ህይወት ማጥፋት፣ ወለድ መጠቀም፣ የየቲም ገንዘብ መብላት፣ ከጦርነት ግንባር ማፈግፈግ፣ ከዝሙት ጥብቅ የሆኑ ሴቶችን ክብር ማጉደፍ ነው» አሉ፡፡ በዚህ ትክክለኛ የሀዲስ ዘገባ መልእክተኛው፣ ሺርክና ድግምት ከሰባቱ አጥፊ ነገሮች መካከል መሆናቸውን አውስተዋል፡፡ ከእነሱም መካከል ሺርክ እጅግ በጣም አደገኛው ነው፡፡ የአላህ መልእክተኛውም አጥፊ የሆነውን በጣም ትልቁን ወንጀል ከድግምት ጋር አጣምረው መግለጻቸው «ድግምት» (ከሺርክ የማይተናነስ) እጅግ በጣም ትልቅ ወንጀል መሆኑን ነው የሚያሳየው፡፡ ምክንያቱም አንድ ሰው ድግምት ለመስራት ሲፈልግ ሰይጣኖችን ማምለክ፣ ከእነሱ ጋር የሚወዱትን መስራትና ለምሳሌ፡- እነሱን መማጸን፣ ለእነሱ ማረድና ስለት ማቅረብ፣ ለእነሱ መታዘዝና ሌሎችን ነገሮችን መስራትና ወደ እነሱ መቃረብ ይጠበቅበታል፡፡

ነሳኢ አላህ ይዘንለትና አቢ ሁረይራን ጠቅሶ እንደዘገበው፣ የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ይላሉ፡-

«مَنْ عقد عُقْدة ثُمَّ نفث فِيهَا فَقد سحر وَمَنْ سحر فَقَد أشرك
وَمن تَعلق شَيْئًا وَكُلِّ إِلَيه»

‹‹ክር ቋጥሮ እዚያ ላይ የነፋ (እፍ ያለ) ሰው፣ ድግምት ሰርቷል፡፡ ድግምት የደገመ ሰው ደግሞ በእርግጥም ሺርክ ሰርቱዋል፡፡ በሆነ ነገር የተመካ ሰው፣ ነገሩ ሁሉ ወደ ተመካበት የሚተው ይሆናል፡፡››

ይህ ነቢያዊ መልዕክት በቁርኣን በአል-ፈለቅ ምዕራፍ ተገልጾ ይገኛል፡- አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ وَمِن شَرِّ ٱلنَّفَّٰثَٰتِ فِى ٱلْعُقَدِ ﴾

‹‹በተቋጠሩ (ክሮች) ላይ ተፊዎች ከሆኑት (ደጋሚ) ሴቶችም ክፋት ... ›› (አል-ፈለቅ፣ 4) ፡፡

በዚህ ነጥብ ላይ የተፍሲር ሊቃውንት የሚከተለውን ሃሳብ ሰንዝረዋል፡- ‹‹እነዚህ ድግምት ሰሪዎች እስር አስረው ሺርካዊ ቃላትን እየተናገሩ በእሱ ላይ ይነፉበታል (እትፍ ይሉበታል)፡፡ ሰዎችን ለመተናኮልና በደል ለመፈጸም ባላቸው እኩይ ፍላጎትም ወደ ሰይጣኖች ይቃረባሉ፡፡

ሙስሊም ሊቃውንት ድግምት በሚደግም ሰው ላይ የተለያዩ አቋዋሞችን አንጸባርቀዋል፡፡ ከፊሎቹ ድግምት መፈጸሙ ከተረጋገጠበት ‹‹ተውበት›› (ወደ አላህ መመለስ) እንዲያደርግ ይጠየቃል፡፡ በዚህም ተውበት ካደረገ፣ እርምጃ አይወሰድበትም ሲሉ፣ ከፊሎቹ ደግሞ ድግምት ማድረጉ ከተረጋገጠበት ‹‹እንዲቶብት›› ሳይጠየቅ ወዲያውኑ ይገደላል ይላሉ፡፡

‹‹ድግምት ማድረጉ ከተረጋገጠበት እንዲቶብት ሳይጠየቅ ይገደላል›› የሚለው ሁለተኛው አቋዋም ትክክለኛ አቋዋም ነው፡፡ ምክንያቱም ድግምት የሰራው ሰው በማህበረሰቡ መካከል መቆየቱ ኢስላማዊ ማህበረሰቡን በመጥፎ ስራው ይበክለዋል፡፡ ምናልባት ቶበት ቢያደርግም እንኳ፣ ብዙ ጊዜ ቶበት በማድረጉ እውነተኛ አይደለም (ቶበቱ ዘላቂ አይደለም)፡፡ ስለሆነም እንዲህ አይነት ተግባር

የሚፈጽም ሰው በህብተረተሰቡ መካከል መኖሩ፣ ለሙስሊሙ ትልቅ አደጋ ነው፡፡

ይህን አቋዋም የደገፉ አዋቂዎች ማስረጃ የሚያድረጉት፣ ቅኑን መንገድ ከተከተሉትና የአላህ መልዕክተኛም ሱናቸውን (መንገዱን) እንድንከተል ካዘዙን ኸሊፋዎች መካከል አንዱ የሆኑት ሁለተኛው ኸሊፋ ዑመር ኢብኑል ኸጧብ ድግምተኞች እንዲቶብቱ ዕድል ሳይሰጣቸው እንዲገደሉ አዘዋል፡፡ እንዲሁም ቲርሚዚ ከጁንዱብ ኢብኑ ዐብዱላህ አል-በጀሊይ ወይም ከጁንዱብ አል-ኸይሪ አል-አዝዲይ መርፉዑ (የዘገባ ሰንሰለቱ ከነቢዩ የሚደርስ) እና መውቁፍ (የዘገባ ሰንሰለቱ ሶሃባ ላይ የሚቆም) በሆነ ሀዲስ እንደዘገበው፡- የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ብለዋል፡-

«حَدُّ السَاحِرِ ضَرْبَةٌ بِالسَيفِ»

‹‹የጠንቋዋይ ቅጣቱ እሱን በሰይፍ አንገቱን መቅላት ነው›› ብለዋል፡፡

በሌላ ተመሳሳይ ዘገባም፣ ‹‹የጠንቋዋይ ቅጣቱ አንገቱን በሰይፍ መቅላት ነው፡፡›› አዋቂዎች ይህ ሀዲስ ሶሂህ ነው ቢሉም፣ ሀዲሱ ግን ጁንዱብ ላይ ‹‹መውቁፍ›› ነው፡፡

በሌላ ዘገባ ከአላህ መልዕክተኛ ባለቤትና የአማኞች እናት ከሆነችው ሀፍሷ በትክክለኛ ዘገባ እንደተረጋገጠው፣ ሀፍሷ ድግምት ያደረገችባትን አገልጋይ ልጃገረድ እንድትቶብት ሳትጠየቅ እንድትገደል አዛለች፡፡ ኢማሙ አህመድ ደግሞ፡- ‹‹ደጋሚ ምንም አይነት የቶበት ጥያቄ ሳይቀርብለት ወዲያውኑ እንደሚገደል ከሶስት የነቢዩ ባልደረቦች ማለትም ከዑመር፣ ከጁንዱብና ከሀፍሱዋ ተረጋግጡዋል›› ይላሉ፡ ፡ ስለሆነም ዋናው ጉዳይ ማንኛውም ድግምትን የሚደግም ሰው ድግምት ማድርጉን እሱ በራሱ ካመነ ወይም ሸሪዓዊ በሆነ ማስረጃ ከተረጋገጠበት፣ እንዲቶብት ሳይጠየቅ ወዲያዉኑ የሞት ፍርድ ይጠብቀዋል ማለት ነው፡፡

ወደ ጠንቋዋዬች ዘንድ መሄድ፣ ስለሆነ ጉዳይ እነሱን መጠየቅና የሚናገሩትንም እውነት ማለት የማይፈቀድ እንደሆነ ቀደም ብለን ካወሳነው ማስረጃ አንጻር መገንዘብ ይቻላል፡፡ ስለሆነም ወደ ጠንቋዋዬችና ወደ ድግምተኞች ዘንድም መሄድ ክልክል ነው፡፡

በድግምት ምክንያት በሽተኛ የሆነ ሰው፣ ሸሪዓዊ የሆነው ‹‹ሩቅያ›› ጠቃሚ ህክምና ሲሆን፣ ይህም የፋቲሃን ምዕራፍ በማንበብና ምራቅን በመትፋት የሚደረገው ህክምና ነው፡፡ አየተለተ ኩርሲይንም ማንበብም እንደዚሁ አስፈላጊ ነው፡፡ ስለድግምት የሚያትቱ የቁርኣን ምዕራፎች አል-አዕራፍ፣ ዩኑስ፣ ጧሃ ናቸው፡፡ አንድ ሰው ለድግምት ሲጋለጥ የአል-ካፊሩንን፣ የአል-ኢኽላስን፣ የአል-ፈለቅንና የአንናስን ምዕራፎች ማንበብ አስፈላጊ ነው፡፡ በትክክለኛና በሚታወቅ የህዲስ ዘገባ የተረጋገጠ ዱዓን ከማለት ጋር የቁርኣን ምዕራፎቹን ሶስት ሶስት ጊዜ እየደጋገሙ ማንበብም ይወደዳል፡፡ ዓኢሻ እንደዘገበችው፣ የአላህ መልዕክተኛ በድግምት በሽታ ለተለከፈ ሰው የሚሉት ዱዓ የሚከተለውን ነው፡-

«اللَّهُمَّ رَبَّ النَّاسِ أَذْهِبِ الْبَاسَ وَاشْفِ أَنْتَ الشَّافِي لَا شِفَاءَ إِلَّا شِفَاؤُكَ شِفَاءً لَا يُغَادِرُ سَقَمًا»

‹‹አልላሁምመ ረብበ ንናሲ፤ አዝሂቢል በእስ፤ ወኢሽፊ አንተ ሽሻፊ፡፡ ላሺፋአ ኢልላ ሺፋኡክ፤ ሺፋአን ላዩጋዲሩ ሰቀመን፡፡››

‹‹አንተ ጌታዬ ሆይ! የሰዎች ጌታ፣ መከራን አስወግድ፤ አንተ ኣዳኝ ነህና አድን፤ ከአንተ ሌላ የሚያድን የለም፡፡ የአንተ ፈውስ ደግሞ የህመምን ጠባሳ ትቶ የማይሄድ ፈውስ ነው፡፡›› (ቡኻሪና ሙስሊም የዘገቡት)፡፡ ይህ ችግር የገጠመው ሰው ይህን ዱዓ ሶስት ጊዜ ደጋግሞ ይለዋል፡፡

እንዲሁም የአላህ መልዕክተኛ በድግምት ምክንያት ታመው

በነበረበት ጊዜ፣ ጂብሪል ለእሳቸው ያደረገላቸውን የሚከተለውን ዱዓ ማድረግ ተገቢ ነው፡፡ ዱዓውም የሚከተለውን ይመስላል፡-

«بِسْمِ اللّٰهِ أَرْقِيكَ مِنْ كُلِّ شَيْءٍ يُؤْذِيكَ ، وَمِنْ شَرِّ كُلِّ نَفْسٍ أَوْ عَيْنِ حَاسِدٍ ، اللّٰهُ يَشْفِيكَ بِسْمِ اللّٰهِ أَرْقِيكَ »

«ቢስሚላሂ አርቂይከ፤ ሚን ኩልሊ ሸይኢን ዩእዚይከ፤ ሚን ሸርሪ ኩሊ ነፍሲን አው ዓይኒን ሃሲዲን፡፡ አልላሁ የሽፊከ፤ ቢስሚላሂ አርቂይከ»

«አንተን ከሚተናኮልህ ከሁሉም ነፍስ ወይም ምቀኛ ዓይን እሱ እንዲፈውስህ በአላህ ስም ሩቅያ አደርግልሃለሁ፡፡ አላህ እንዲያድንህም በአላህ ስም ሩቅያ አደርግልሃለሁ፡፡» (ሙስሊም የዘገበው)፡፡ ይህ ችግር የገጠመው ሰው ይህንንም ዱዓ ሶስት ሶስት ጊዜ ደጋግሞ ይለዋል፡፡ ይህ ሩቅያ ከአላህ ፈቃድ ጋር እጅግ በጣም ጠቃሚው ሩቅያ ነው፡፡ (ሩቅያ የተለያዩ ቀርኣናዊ አንቀጾችን፣ አዝካሮችንና ዱዓዎችን በማለት በሽተኛውን መፈወስ ነው፡፡)

ሌላው የህክምና መንገድ ደግሞ፣ ድግምት ተደርጎበታል ተብሎ የሚጠረጠርንና ለድግመት ምክንያት የሆነን ነገር ማለትም ሱፍ፣ ወይም የታሰረ ክር ወይም ሌላን ነገር  ማስወገድ ተገቢ ነው፡፡ በሽተኛውንም ሸሪዓዊ በሆነ መንገድ ከድግምትና ከጥንቆላ መጠበቂያና መፈወሻ የሆኑ ዱዓዎችንና ዚክሮችን በማለት ትኩረት መስጠት ይገባል፡፡ ከእነዚህ ዱዓዎችና ዚክሮች መካከል የሚከተሉት ተጠቃሽ ናቸው፡-

«أَعُوذُ بِكَلِمَاتِ اللّٰهِ التَّامَّاتِ مِنْ شَرِّ مَا خَلَقَ».

«አዑዙ ቢከሊማቲላሂትታምማት፤ ሚን ሸርሪ ማኸለቅ፡፡»

«ሙሉ በሆኑት የአላህ ንግግሮች፣ ከፈጠረው ነገር ሁሉ ተንኮል እጠበቃለሁ፡፡» ይህ ዱዓ ሶስት ጊዜ ጡዋትና ማታ ይባላል፡፡ ቀደም ብለን የጠቀስናቸውን ሶስቱን የቁርኣን ምዕራፎች ከሱብሂና

ከመግሪብ በኋላ ማለት ያስፈልጋል፡፡ እንዲሁም አየተል ኩርሲይን ከሶላት በኋላና ከመኝታ በፊት ማንበብም (ማለት) ያስፈልጋል፡፡

የሚከተለው አዝካር (ዉዳሴ) ከነቢዩ የተረጋገጠ ስለሆነ አንድ ሰው ይህንኑ አዝካር ጡዋትና ማታ ሶስት ጊዜ ማለት ይወደድለታል፡-

«بِسْمِ اللّٰهِ الَّذِيْ لَا يَضُرُّ مَعَ اسْمِهِ شَيْءٌ فِي الْأَرْضِ وَلَا فِي السَّمَآءِ وَهُوَ السَّمِيْعُ الْعَلِيْمُ».

‹‹ቢስሚላሂልለዚ ላ የዱርሩ መዐ ኢስሚህ ሸይኡን ፊልአርዲ ወላ ፊስሰማኢ ወሁወ ስሰሚዑል ዐሊም፡፡››

‹‹በአላህ ስም (እጠበቃለሁ)፤ ከእርሱ ስም ጋር በምድርም ሆነ በሰማይ ያለ ነገር ሊጎዳ አይችልም፤ እርሱ ሰሚው ዐዋቂው ነው፡፡›› (የ‹‹ሀሰን›› ደረጃ ያለው ትክክለኛ የሀዲስ ዘገባ)፡፡

በዚህ ሁኔታ ከአላህ መልካም ነገር ይገጥመናል ብሎ ጥሩ መመኘት፣ ይህ ነገር ከሰበቦች መካከል አንዱ መሆኑና ከአላህ ፈቃድ ጋር በትክክል የሚፈውሰው እሱ ነው ብሎ ማመን ያስፈልጋል፡፡ ማንኛውም ሰው እነዚህን ዱዓዎችንና ዚክሮችን ሲጠቀም፣ ከመጥፎ ነገር መጠበቂያዎችና መድሃኒቶች ከበሽታው ለመፈወስ ሰበቦች እንጂ ትክክለኛው አዳኝ አላህ መሆኑን መዘንጋት የለበትም፡፡ ከበሽታ ለመዳን ሙሉ ለሙሉ ተስፋ የሚደረገው ከአላህ ዘንድ እንጂ ከሌላ አካል አይደለም፡፡ ነገር ግን በአላህ ፈቃድ ለመዳን ሰበብ የሚሆኑት መድሃኒቶች ጠቃሚነት ይኖራቸዋል፡፡ ድግምቱ የሚያሳድረው አሉታዊ ተጽዕኖም፣ አላህ በሁሉም ነገር ባለው የላቀ ጥበብ አወንታዊ ጥቅም ይኖረዋል፡፡ አላህ በሁሉም ነገር ቻይ፣ አዋቂ ነው፡፡ እሱ ለሰጠው ነገር ማንም ከልካይ የለም፤ እሱ ለከለከለው ነገር ደግሞ ማንም አይሰጥም፤ ለወሰነው ነገርም ማንም ውሳኔውን ቀልባሽ የለም፡፡ ንግስና፣ ምስጋና ለሱ ነው፡፡ እሱ በሁሉም ነገር ቻይ ነው፡፡ እሱ ከጉድለት የጠራና መልካምን ነገር የማጎናጸፍ ባለቤት ነው፡፡

# የካዕባን ግድግዳና ልብስ በእጅ ማበስ ኢስላማዊ እይታ

ጥያቄ፡- በካዕባ ግድግዳና ልብስ እንዲሁም መቃሚ ኢብራሂምንና ሀጀረል አስወድን በእጅ ማበስ ኢስላማዊ እይታ ምንድን ነው?

መልስ፡- ይዚህ ተግባር ከኢስላማዊ እይታ አንጻር አዲስ መጤ (ቢድዓ) ነው፡፡ ስለሆነም ስራውም የሚፈቀድ አይደለም፡፡ ምክንያቱም የአላህ መልዕክተኛ ይህን ተግባር አልሰሩትምና ነው፡፡ የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ይላሉ፡- «የእኛ ትዕዛዝ የሌለበትን ስራ የሰራ ሰው፣ ስራው ተመላሽ (ተቀባይነት የለውም) ነው፡፡» (ቡኻሪ ዘግቦታል)፡፡ በሌላ ሀዲሳዊ ዘገባ የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ይላሉ፡- «በዚህ ጉዳያችን (በኢስላም) የሌለን አዲስ ነገር ይዞ የመጣ ሰው፣ እሱ (ተግባሩ) ተመላሽ ነው፡፡» (ቡኻሪና ሙስሊም የዘገቡት)፡፡ በሌላ ሀዲሳዊ ዘገባም፣ የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ይላሉ፡- «አዳዲስ ዲናዊ ፈጠራዎችን አደራችሁን! ሁሉም አዳዲስ ዲናዊ ፈጠራዎች መጤ ናቸው፡፡ ሁሉም መጤ ነገር ደግሞ ጥመት ነው፡፡» (አቡዳውድ ዘግቦታል)፡፡

አንድ ሰው በካዕባ ግድግዳ ወይም ልብስ ላይ በእጁ የሚያብሰው፣ ከልብሱ ወይም ከግድግዳው የሆነ በረካ ይገኝበታል ብሎ አምኖ ከሆነ፣ ይህ ድርጊቱ ትልቅ ሺርክ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ይህን ተግባር የሚፈጽመው ሰው ይህ ተግባሩ የተባረከ፣ አላህም የደነገገው አድርጎ የሚያስብ ከሆነ፣ እንዲሁም የካዕባ ግድግዳና ልብስ መሳሙም በኢስላም ድንግግ ነው ብሎ የሚያስብ ከሆነ አቋሙ አዲስ መጤ (ቢድዓ) ነው፡፡ እላይ እንደተጠቀሰው ግን የካዕባን ልብስና ግድግዳ የሚስመው ከልብሱና ከግድግዳው የሆነ አንዳች በረካ ፈልጎ ከሆነ፣ ይህ አጉል ተግባሩ ከትልቁ ሺርክ ውስጥ

የሚካተት ነው፡፡ አላህን ደህንነትን እንጠይቀዋለን፡፡

በኢስላም የተደነገገው ነገር ጥቁሩን ድንጋይ (ሐጀረል አስወድ) መሳም ነው፡፡ ይህም አንድ ሰው ሐጀረል አስወድን በቀጥታ ሊስም ወይም በእጁ ነክቶ እጁን መሳም ነው፡፡ ይህን ተግባር የአላህ መልዕክተኛ እራሳቸው የሰሩት ተግባር ነው፡፡ «ሩክነል የማኒይ»ንም በእጁ መንካት የተፈቀደ ተግባር ነው፡፡ እሱም ላይ ሲደርስ፣ «ቢስሚላሂ ወላሁ አክበር» ይበል እንጂ፣ እሱን ሊስመው አይገባውም፡፡ ዑመር ኢብኑል ኸጧብ ሀጀረል አስወድን ሲስም የሚከተለውን ንግግር ተናግሩዋል፡- «እኔ አንተ የማትጎዳና የማትጠቅም ድንጋይ እንደሆንክ አውቃለሁ፡፡ የአላህ መልዕክተኛ አንተን ሲስሙህ ባልተመለከትኩ ኖሮ፣ አንተን አልስምህም ነበር» (ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል)፡፡

እኛ ጥቁሩን ድንጋይ (ሀጀረል አስወደን) የምንስመው፣ የነቢዩን መንገድ ተከትለን እንጂ፣ ከሀጀረል አስወድ «በረካ» (ረድኤት) ፈልገን አይደለም፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ የአላህን መልዕክተኛ ምሳሌ ማድረግ፣ ሱናውንም መከተል እንዲሁም እሱን (መንገዳቸውን) ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ እሳቸውም እንዲህ ብለዋል፡- «የሀጅን የአፈጻጸም ስነ ስርዓት ከእኔ ተከተሉ፡፡» (ቡኻሪ ዘግቦታል)፡፡ በሌላ ሀዲሳዊ መልዕክታቸው የአላህን መልዕክተኛ እንዲህ ብለዋል፡- «እኔ ሶላት ስሰግድ እንዳያችሁት አድርጋችሁ ስገዱ» (ቡኻሪ ዘግቦታል)፡፡

እኛ ሙስሊሞች የአላህ መልዕክተኛ እዝነትና ሰላም በእሳቸው ላይ ይስፈንና፣ እሳቸው እንደሰገዱት አድርገን እንሰግዳለን፤ ሀጅ ባደረጉበት መንገድ ሀጅ እናደርጋለን፡፡ በመቃም ኢብራሂም ሆነ በካዕባ ግድግዳዎች ወይም በመስኮተቶቹ ወይም በልብሶቹ በረካ ፈልገን ግን በእጃችን አናብስም፡፡ በመቃም ኢብራሂም፣ በካዕባ ግድግዳዎች፣ መስኮቶች እንዲሁም በካዕባ ልብሶች ላይ ማበስ አዲስ ዒባዳዊ ፈጠራ (ቢድዓ) ነው፡፡

ማንኛውም ሰው ግን የአምልኮት አካል (ዒባዳ) ስለሆነ በካዕባና በጥቁሩ ድንጋይ መካከል ላይ መቆሙ የተፈቀደ ተግባር ነው፡፡ ይሁን እንጂ ይህ ስራ ዒባዳ በመሆኑ በበሮቹ ዘንድ ራስን ለአላህ ዝቅ ማድረግ እንጂ፣ ከካዕባ የሆነ ነገር መጠየቅና በረካን ከእሱ መፈለግ አይገባም፡፡ ልክ እንደዚሁ አንድ ሰው ካዕባ ውስጥ ከሆነ በዙሪያው ሊዞር፣ በዙሪያው አካባቢ ሆኖ ተክቢራ ሊል ወይም በካዕባና በጥቁሩ ድንጋይ መካከል ላይ በመቆም ደረቱን ወደዚያው አቅጣጫ አድርጎ ዱዓ ማድረጉ የአላህ መልዕክተኛ የሰሩት ስራ በመሆኑ ተግባሩ ችግር የለውም፡፡ ይህ ሁሉ ተግባር ልቅናና ልዕልናና ይገባውና አላህን ለማምለክና ወደሱ ለመቃረብ ተብሎ የሚደረግ ዒባዳ ነው፡፡

የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ብለዋል፡

«لَا تُقْبَلُ صَلَاةٌ بِغَيرِ طَهُورٍ»

‹‹ጡሃራ (ለሶላት የሚያበቃ ንጽህና - ውዱእ ሳይኖር) ሶላት ተቀባይነት የላትም፡፡›› (ሙስሊም የዘገበው)፡፡

•

ውዱእ ለሶላት ትክክለኛነት ቅድመ-ሁኔታ ነው፡፡ ስለሆነም ለሶላት አይቀሬ ጉዳይና ግዴታም ነው፡፡ ልቅናና ልዕልናና የተገባው አላህ በቁርኣኑ እንዲህ ብለዋል፡-

﴿يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُوٓاْ إِذَا قُمۡتُمۡ إِلَى ٱلصَّلَوٰةِ فَٱغۡسِلُواْ وُجُوهَكُمۡ وَأَيۡدِيَكُمۡ إِلَى ٱلۡمَرَافِقِ وَٱمۡسَحُواْ بِرُءُوسِكُمۡ وَأَرۡجُلَكُمۡ إِلَى ٱلۡكَعۡبَيۡنِۚ﴾

‹‹እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ወደ ሶላት በቆማችሁ (ለመቆም ባሰባችሁ) ጊዜ ፊቶቻችሁን፣ እጆቻችሁንም እስከ ክርኖች እጠቡ፡፡ ራሶቻችሁንም (በውሃ) እበሱ፤ እግሮቻችሁንም እስከ ቁርጭምጭሚቶች (እጠቡ)›› (አል-ማኢዳ፣ 6)፡፡ በዚህ መንገድ ነው አላህ አማኞችን ያዘዛቸው፡፡ የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ብለዋል፡-

«لَا تُقْبَلُ صَلَاةٌ بَغَيرِ طَهُورٍ»

‹‹ጡሃራ (ለሶላት የሚያበቃ ንጽህና - ውዱእ- ሳይኖር) ሶላት ተቀባይነት የላትም፡፡›› (ሙስሊም የዘገበው)፡፡ የአላህ መልዕክተኛ በሌላ ነቢያዊ መልእክታቸው እንዲህ ብለዋል፡-

«لَا تُقْبَلُ صَلَاةُ أَحَدِكُمْ إِذَا أَحْدَثَ حَتَّى يَتَوضَّأَ»

‹‹አንድኛችሁ ውዱኡን ፈቶ እንደገና ወዱእ እስካላደረገ ድረስ፣ ሶላቱ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡›› ውዱእ ለሶላት አይቀሬ ጉዳይ ስለሆነ ውዱእ ለማድረግ አንድ ሰው ተጽ ዳድቶ ከሆነ መጀመሪያ ኢስቲንጃእ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ኢስቲንጃእ ውሃ ወይም ንጹህ የሆነ ድንጊያ ወይም ሶፍት (ወረቀት) በመጠቀም የመጸዳጃን ቦታ ሶስት ጊዜ ወይም

ከዚያም በላይ በሆነ መጠን ንጹህ እስኪሆን ድረስ ማጽዳት ስለሆነ ሁለቱ የመጸዳጃ ቦታዎች በደንብ ንጹህ እስኪሆኑ ድረስ ኢስቲንጃእ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

በኢስቲንጃእ አደራረግ፣ የተሻለው የኢስቲንጃ አደራረግ መንገድ፣ በደረቅ ነገር የመጸዳጃ ቦታን መጀመሪያ ንጹህ ካደረጉ በሁዋላ አስከትሎም ቦታውን በውሃ ማጽዳት ነው፡፡ ይህ የኢስቲንጃእ አደራረግ እጅግ በጣም ምሉዕ የኢስቲንጃእ አደራረግ ዘዴ ነው፡፡

ከዚያም በሚከተለው መንገድ ውዱእ ያደርጋል፡፡

1. ውዱእን በአላህ ስም መጀመር ነው፡፡ ይህም «ቢስሚላሂ» ማለት ነው፡፡ በሸሪዐውም የተደነገገውም ነገር ይኼው ነው፡፡ የተወሰኑ ሙስሊም ሊቃውንት በውዱእ ጊዜ፣ «ቢስሚላሂ» ብሎ መጀመር ግዴታ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡



2. ከዚያም መዳፎቹን ሶስት ጊዜ ማጠብ ነው፡፡ ይህ እጅግ በጣም የተሻለው የመዳፍ አስተጣጠብ ነው፡፡

3. ከዚያም ሶስት ጊዜ ውሃን በእፍኝ በመዝገን ወደ አፍና አፍንጫ ውሃ አስገብቶ ወዲያውም የገባውን ውሃ ከአፍንጫ ማስወጣት ነው፡፡



4. ከዚያም ሶስት ጊዜ ፊትን ማጠብ ነው፡፡ ይህም ከላይ ጸጉር መብቀል ከሚጀምርበት የግንባር ክፍል ጀምሮ ወደ ታች እስከ ግንጭል ድረስ ሲሆን፣ ወደ ጎንም ከቀኙ የጆሮ ጫፍ እስከ ግራ ጆሮው ጫፍ ድረስ ያለውን የፊት አካል ማጠብ ነው፡፡



5. ከዚያም እጁን ከጣቶቹ ጫፍ ጀምሮ እስከ ክርኑ ድረስ ማጠብ ነው፡፡ ክርን የውዱእ አካል ስለሆነ አብሮ ይታጠባል፡፡ እጅ ሲታጠብ መጀመሪያ ቀኝ፣ ከዚያም ግራ እጅ ይታጠባል፡፡ ጾታ ሳይለይ የወንድና የሴትም እጅ በዚሁ መልኩ ነው የሚታጠበው፡፡





6. ከዚያም በሁዋላ እጁን ውሃ አስነክቶ ጸጉሩንና ጆሮዎቹን ውሃ ማስነካት (ማበስ) ነው፡፡ በዚህ ሁኔታም ወንድና ሴት ያለ ልዩነት ጸጉራቸውን ውሃ ያስነካሉ፡፡





7. ቀጥሎም እስከ ቁርጭምጭሚቱ ድረስ ቀኝ እግሩን ሶስት ጊዜ ማጠብ፣

ከዚያም የግራ እግሩን ሶስት ጊዜ ማጠብ ነው፡፡ እግርን እስከ ባት አጋማሽ ድረስ ማጠብም የተፈቀደ ነው፡፡



በውዱእ አደራረግ ስነ ስርዓት ውሃን ወደ አፍ ማስገባት (መጉመጥመጥ)፣ ወደ አፍንጫ ውሃ ማስገባት፣ እንዲሁም ፊቶቹን፣ እጆቹንና እግሮቹን ሶስት ሶስት ጊዜ ማጠብ ሱና ነው፡፡ ራስን ከጆሮ ጋር አንድ ጊዜ ማበስም ሱና ነው፡፡ አንድ ሰው ፊቱንና እጁን አዳርሶ እስካደረገ ድረስ፣ አንድ አንድ ጊዜ ውዱእ ቢያደርግ ይፈቀድለታል፡፡ እንዲሁም ሁለት እግሮቹን አዳርሶ እስካደረገ ድረስ፣ አንድ አንድ ጊዜ ወይም ሁለት ሁለት ጊዜ ማጠብም ይፈቀድለታል፡፡ ይሁን እንጂ ሁሉንም የውዱእ አካል ሶስት ሶስት ጊዜ ማድረጉ እጅግ በጣም የተሻለ የዉዱእ አደራረግ ስርዓት ነው፡፡ ከአላህ መልዕክተኛ እንደተረጋገጠው፣ የአላህ መልዕክተኛ (በተለያዩ ጊዚያት) ውዱእ ሲያደርጉ አንድ አንድ ጊዜ፣ ሁሉት ሁለት ጊዜና ሶስት ሶስት ጊዜ ማድረጋቸው ተረጋግጧል፡፡ በሌላ መረጃ እንደተረጋገጠው ደግሞ፣ በአንድ ጊዜ ውዱእ ባደረጉበት አጋጣሚ የተወሰነውን የዉዱእ አካል ሶስት ሶስት ጊዜ ሲያደርጉ፣ ቀሪውን ደግሞ ሁለት ሁለት ጊዜ አድርገዋል፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ ያለው ሁኔታ ሰፊ ነው፡፡ ምስጋና ለአላህ ይሁን፡፡

በውዱእ አደራረግ ስነ-ስርዓት ግዴታው ሁሉንም የውዱእ አካላት በውሃ አዳርሶ አንድ ጊዜ ዉዱእ ማድረጉ ነው፡፡ ይህ ማለት አፉን ከመጉመጥመጥ ጋር ፊቱን፣ ቀኙና ግራ እጁን እስከ ክርኑ ድረስ፣ ራሱን (ጸጉሩን) እና ጆሮዉን አዳርሶ እንዲሁም ቀኙና ግራ እግሮቹን እስከ ቁርጭምጭሚት አዳርሶ ማጠብ ነው፡፡ ይህ ነው የግዴታው የውዱእ አደራረግ፡፡ ቀደም ብለን እንዳወሳነው ውዱእ የሚያደርግ ሰው ሲፈልግ ሁለት ሁለት ጊዜ ማድረግ ቢችልም፣

ሶስት ሶስት ጊዜ ማድረግ ግን በጣም የተሻለ ነው፡፡ በዚህ ሁኔታ የውዱእ አደራረግ ጉዳይ ይቋዋጫል፡፡

ዉዱኡን የጨረሰ ሰው ደግሞ፡-

«أَشْهَدُ أَنْ لَا إِلَهَ إِلَّا اللّٰهُ وَحْدَهُ لَاشَرِيْكَ لَهُ وَأَشْهَدُ أَنَّ مُحَمَّدًا عَبْدُهُ وَرَسُوْلُهُ. اللَّهُمَّ اجْعَلْنِي مِن التَّوَّابِينَ وَاجعَلْنِي من الْمُتَطَهِّرِينَ»

«አሽሀዱ አንልላ ኢላሀ ኢልለላህ ወህደሁ ላሽሪከ ለሁ፤ ወአ ሽሀዱ አንነሙሀመደን ዐብዱሁ ወረሱሉህ፡፡ አልላሁምመ ጅዐልኒ ሚነትተዋቢን፤ ወጅዐልኒ ሚነል ሙተጠህሂሪን» ይላል ፡፡

«ከአላህ በስተቀር አምልኮት የሚገባው ሌላ አምላክ እንደሌለ እመሰክራለሁ፡፡ እሱ አንድና አጋር የሌለው ነው፡፡ ሙሀመድ የአላህ ባሪያና መልእክተኛው እንደሆኑ እመሰክራለሁ፡፡ አላህ ሆይ! ንስሀ (ተውበት) ከሚያበዙት ሰዎች አድርገኝ፤ ከንጹኃንም አድርገኝ፡፡»

ከአላህ መልዕክተኛ እንደተረጋገጠው፣ የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ብለዋል፡- «ከእናንተ አንድኛችሁ ዉዱእ ያደርጋል፤ ውዱኡንም አዳርሶ ያደርጋል፡፡ ከዚያም እንዲህ ይላል፡- አሽሀዱ አንላኢላሃ ኢለላህ፤ ወአነሙሀመደን ዐብዱሁ ወረሱሉህ፡፡ (እንዲህ በማለቱ) ስምንቶቹ የጀነት በሮች ይከፈቱለታል፡፡ ከዚያም በፈለገው የጀነት በር ይገባል፡፡» (ሙስሊም ዘግቦታል)፡፡ ቲርሚዚ ደግሞ ከዚህ በሁዋላ፡-

«اللَّهُمَّ اجْعَلْنِي مِنَ التَّوَّابِينَ وَاجعَلِنِي مِنَ الْمُتَطَهِّرِينَ».

«አላሁምመጅዐልኒ ሚነተውዋቢነ ወጅዐልኒ ሚነልሙተጦህሂሪን፡፡»

«አላህ ሆይ! ንስሀ (ተውበት) ከሚያበዙት ሰዎች አድርገኝ፤

ከንጹኃንም አድርገኝ›› የሚል ዘገባ ጨምሩዋል፡፡ ይህ ዱዓ የሚባለው ውዱእ ከተደረገ በሁዋላ ሲሆን፣ ወንድም ሆነ ሴት ዱዓውን ከመጸዳጃ ቤት ውጪ ይሉታል፡፡ በዚህ መንገድ ነው እንግዲህ ኢስላማዊው የውዱእ አደራረግ ስነ ስርዓት የሚታወቀው፡፡

ውዱእ የሶላት ቁልፍ ነው፡፡ የአላህ መልዕክተኛም እንዲህ ብለዋል፡-

«مِفْتَاحُ الصَّلَاةِ الطهُورُ وَتَحْرِيمهَا التَكْبِيرُ وَتَحْلِيْلُهَا التَسْلِيم»

‹‹የሶላት ቁልፉ ጧሃራ (ዉዱእ) ነው፡፡ (ከሌላ ነገር) እርም የሚያደርጋት ተክቢራ ሲሆን፣ የተፈቀደ የሚያደርጋት ደግሞ ሶላትን ማሳረግ (ተስሊም) ነው፡፡›› (ቲርሚዝ የዘገበው)፡፡

የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ
ይላሉ፡-

«صَلُّوا كَمَا رَأَيْتُمُونِي
أُصَلِّي»

‹‹እኔ ሶላት ስሰግድ እንዳያችሁት
አድርጋችሁ
ስገዱ፡፡›› (ቡኻሪ ዘግቦታል)፡፡

# በአዛንና ከአዛን በሁዋላ የሚባሉ ዚክሮችና ዱዓዎች

1. አቢ ሰዒድ አል-ኹድሪይ (ረ.ዐ) እንዳስተላለፉት፣ የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ብለዋል፡- «የአዛን ጥሪ ስሰሙ፣ አዛን አድራጊው (ሙአዚኑ) የሚለውን በሉ፡፡» (ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል)

2. ጃቢር ኢብኑ ዐብደላህ (ረ.ዐ) እንዳስተላለፉት፣ «የአዛን ጥሪ ሲሰማ፡- አልላሁምመ ረብበ ሃዚሂድደዕወቲ ትታምማ፤ ወሶላቲል ቃኢማ፤ ኣቲ ሙሀመደን አል ወሲለተ፣ ወልፈዲለተ፣ ውብዐስሁ መቃመን መህሙደን፤ አለዚ ወዐድተሁ (ወዐተሁ)፡፡ ያለ ሰው፣ በዕለተ-ትንሳኤ ምልጃዬን (ሸፋዓ) ያገኛል፡፡»

   «አላህ ሆይ! የዚች ሙሉ ጥሪ የዚች ለመስገድ የተቃረበች ሶላት ጌታ የሆንከ፣ ሙሀመድን ወሲላ እና ፈዲላ የተባሉትን (የክብር ደረጃዎች) ለግሳቸው፡፡ ቃል የገባህላቸውን የተመሰገነ ደረጃ አጎናጽፈህ (ከሞት) ቀስቅሳቸው፡፡» (ቡኻሪ የዘገበው)፡፡ በሌላ ዘገባ በይሀቂ በዚህ ሁዲስ ላይ ከተወሳው በተጨማሪ የአላህ መልዕክተኛ የሚከተለውን ጨምረው ማለታቸውን ዘግበዋል፡- «ኢንነከ ላቱኽሊፉል ሚዓድ» «አንተ የገባኸውን ቃል አታጥፍም፡፡»

3. ሰዕድ ኢብኑ ወቃስ (ረ.ዐ) እንዳስተላለፉት፣ የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ብለዋል፡- «አዛን አድራጊው የአዛን ጥሪ ሲያደርግ የሰማው ሰው፣ (ሲጨርስ)፣ ላኢላሃ አለላህ፤ ወህደሁ ላሸሪከ ለሁ፣ ወአንነ ሙሀመደን ዐብዱሁ ወረሱሉህ፤ ረዲይቱ ቢላሂ ረብበን፤ ወቢሙሀመዲን ረሱለን፤ ወቢልኢስላሚ ዲነን ፣ ያለ ሰው ወንጀሉ ይማርለታል፡፡»

   «ከአላህ በስተቀር አምልኮት የሚገባው ሌላ አምላክ እንደሌለ እመሰክራለሁ፡፡ እሱ አንድና አጋር የሌለው ነው፡፡ ሙሀመድ

የአላህ ባሪያና መልእክተኛው እንደሆኑ እመሰክራለሁ፡፡ የአላህ ጌትነትን፣ የኢስላም ሃይማኖትነትንና የነቢዩ ሙሀመድ ነቢይነትን ወድጄ ተቀብያለሁ፡፡» (ሙስሊም የዘገበው)፡፡

4. ዑመር ኢብኑል ኸጧብ (ረ.ዐ) እንዳስተላለፉት፣ የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ብለዋል፡- «አዛን አድራጊው አላሁ አክበር፤ አላሁ አክበር ሲል፣ አንድኛችሁ አላሁ አክበር፤ አላሁ አክበር ካለ፣ ከዚያም አሽሀዱ አንልላኢላሀ ኢልለላህ ሲል፣ አሽሀዱ አንልላ ኢላሀ ኢልለላህ ካለ፣ አሽሀዱ አንነሙሀመደን ረሱሉላህ ሲል ደግሞ፣ አሽሀዱ አንነሙሀመደን ረሱሉላህ ካለ፣ ከዚያም ሀይይየ ዐለ ሶላ ሲል፣ ላሃውለ ወላ ቁወተ ኢልላ ቢላሂ ካለ፣ ከዚያም አላሁ አክበር፤ አላሁ አክበር ሲል፣ እሱም አላሁ አክበር፤ አላሁ አክበር ካለ፣ ከዚያም ላኢላሀ ኢልለልላህ ሲል፣ ላኢላሀ ኢልለልላህ ከልቡ ካለ፣ ጀነት ገባ» ብለዋል፡፡ (ሙስሊም ዘግቦታል)፡፡

5. ዐብደላህ ኢብኑ ዐምር ኢብኑልዓስ (ረ.ዐ) እንዳስተላለፉት፣ የአላህን መልዕክተኛ እንዲህ ሲሉ ሰምቷቸዋል፡- «አዛን አድራጊው አዛን (ጥሪ) ሲያደርግ፣ እሱ የሚለውን (ደግማችሁ) በሉ፡፡ በእኔ ላይም ሰለዋት አውርዱ፡፡ በእኔ ላይ አንድ ሰለዋት ያወረደ ሰው፣ አላህ በእሱ ላይ አስር ሰለዋት ያወርድበታል፡፡ አላህ ለእኔ አል-ወሲላን እንዲሰጠኝ ጸልዩልኝ፡፡ አል-ወሲላ፣ ጀነት ያለች ቤት (ደረጃ) ስትሆን፣ እሱዋ ለማንም የምትገባ ሳትሆን፣ ከአላህ ባሪዎች መካከል ለአንዱ ባሪያ የምትገባ ናት፡፡ እኔ እንድሆን እመኛለሁ፡፡ ይቺን አል-ወሲላ ለእኔ (እንድትሰጠኝ) አላህን የለመነልኝ ሰው፣ (በዕለተ ትንሳኤ) የእኔን ምልጃ (ሸፋዓ) የሚያገኝ ይሆናል፡፡» (ሙስሊም የዘገበው)፡፡

# ከመስጂድ የመግባትና የመውጣት ስነ-ስርዓት

1. አቢ ሁመይዳ ወይም አቢ ኡሰይድ (ረ.ዐ) እንዳስተላለፉት፣ የአላህ መልእክተኛ እንዲህ ብለዋል፡- «አንደኛችሁ ወደ መስጂድ ከገባ፣ አላሁምመፍተህ ሊ አብዋበ ረህመቲከ (አላህ ሆይ! የእዝነትህን በር ክፈትልኝ ይበል)፡፡ ሲወጣ ደግሞ፣ አላሀምመ ኢንኒ አስአሉከ ሚን ፈድሊከ (አላህ ሆይ! ከትሩፋትህ እጠይቅሃለሁ) ይበል፡፡ (ሙስሊምና አቡ ዳውድ ዘግበውታል)፡፡

2. ዐብደላሂ ኢብኑ ዓስ (ረ.ዐ) እንዳስተላለፉት፣ የአላህ መልዕክተኛ ወደ መስጂድ ሲገቡ እንዲህ ይሉ ነበር፡ - «አላሁምመፍተህ ሊ አብዋበ ረህመቲከ (አላህ ሆይ! የእዝነትህን በር ክፈትልኝ)፡፡ ከመስጂድ ሲወጡ ደግሞ፡- «አልላሁምመ ኢንኒ አስአሉከ ሚን ፈድሊከ» (አላህ ሆይ! ከትሩፋትህ እጠይቅሃለሁ፡፡) ይላሉ፡፡ (ሙስሊምና አቡ ዳውድ ዘግበውታል፡፡ ይህ ዘገባ ግን የአቡ ዳውድ ነው)፡፡

3. አቢ ሁረይራ (ረ.ዐ) እንዳስተላለፉት፣ የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ብለዋል፡- «አንድኛችሁ ወደ መስጂድ ከገባ፣ በነቢዩ ላይ ሰላምታ ያቀርብ፡፡ አላሁምመፍተህ ሊ አብዋበ ረህመቲከ (አላህ ሆይ! የእዝነትህን በር ክፈትልኝ) ይበል፡፡ ሲወጣ ደግሞ፡- በነቢዩ ላይ ሰላምታ ያቅርብ፡፡ እንዲህም ይበል፡- አላሁምመ ዕሲምኒ ሚነሽይጧኒርረጂም፡፡» (ከተረገመውም ሰይጣን (ተንኮል) ጠብቀኝ፡፡) (ኢብኑ ማጂህ በትክክለኛ የዘገባ ሰንሰለት ዘግቦታል)፡፡

# የአላህ መልዕክተኛ የሶላት አሰጋገድ ስነ-ስርዓት

ምስጋና ብቸኛ ለሆነው አላህ ይሁን፡፡ በባሪያውና በመልዕክተኛው፣ የእኛ ነቢይ በሆኑት ሙሀመድ እንዲሁም በቤተሰቦቻቸውና በባልደረቦቻቸውም ላይ የእሱ እዝነትና ሰላም ይስፈን፡፡

ይቺ አጭር መልዕክት ሶላት እንዴት እንደሚሰገድ ታትታለች፡፡ ሁሉም ሙስሊም የነቢዩ ሙሀመድን መንገድ በመከተል ጥረት እንዲያደርግ በመሻት፣ ይህን መልዕክት አቅርቤዋለሁ፡፡ የአላህም መልዕክተኛ እንዲህ ይላሉ፡- ‹‹እኔ ሶላት ስሰግድ እንዳያችሁት አድርጋችሁ ሶላት ስገዱ፡፡›› (ቡኻሪ ዘግበታል)፡፡ የሶላትን የአፈጻጸም ስነ-ስርዓት በሚከተለው መንገድ ለአንባቢ አብራራለሁ፡፡

1. መጀመሪያ አዳርሶ ውዱእ ማድረግ፡- ይህ ማለት አላህ በቁርኣኑ ባዘዘው መንገድ ይከናወናል ማለት ነው፡፡ አላህ በቁርኣኑ እንዲህ ይላል፡-

﴿ يَـٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُوٓاْ إِذَا قُمْتُمْ إِلَى ٱلصَّلَوٰةِ فَٱغْسِلُواْ وُجُوهَكُمْ وَأَيْدِيَكُمْ إِلَى ٱلْمَرَافِقِ وَٱمْسَحُواْ بِرُءُوسِكُمْ وَأَرْجُلَكُمْ إِلَى ٱلْكَعْبَيْنِ ﴾

‹‹እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ወደ ሶላት በቆማችሁ (ለመቆም ባሰባችሁ) ጊዜ ፊቶቻችሁን፣ እጆቻችሁንም እስከ ክርኖች እጠቡ፡፡ ራሶቻችሁንም (በውሃ) እበሱ፤ እግሮቻችሁንም እስከ ቁርጭምጭሚቶች (እጠቡ)›› (አል-ማኢዳ፣ 6)፡፡

የአላህ መልዕክተኛ በሀዲሳቸው እንዲህ ብለዋል፡-

«لَا تُقْبَلُ صَلَاةٌ بِغَيْرِ طُهُوْرٍ»

«ሶላት ያለ ውዱእ ተቀባይነት የለውም፡፡»
(ሙስሊም የዘገበው) ፡፡

የአላህ መልዕክተኛ በአንድ አጋጣሚ ሶላቱን በተገቢው መንገድ መስገድ ላልቻለው ግለሰብ እንዲህ ብለውታል፡- «ሶላት ልትሰግድ ስትዘጋጅ፣ ዉዱእን አዳርስህ አድርግ ... » (ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል)፡፡

2. ከዚያም ሰጋጁ ፊቱን ወደ ቂብላ አቅጣጫ (ወደ ካዕባ) በማድረግ መቆም ነው፡፡ ግለሰቡ የትም ቦታ ቢሆን ሁሉም አካሉ ለሶላት ዝግጁና ቀልቡ ደግሞ አላህን ከጃይ መሆን አለበት፡፡ ከዚያም ሶላቱ ሱናም ይሁን ግዴታ የፈለገውን ያህል መስገድ ነው፡፡



በ«ኒያ» (ሶላቱን እንደሚሰግድ ማሰብ) ጉዳይ ላይ ለሰጋጁ የተሻለ የሚሆነው፣ ሰጋጁ «ኒያውን» በንግግር አለመግለጹ ነው፡ ፡ ምክንያቱም «ኒያ»ን በንግግር መግለጽ ከአላህ መልዕክተኛ አልተገኘምና ነው፡፡ ስለሆነም «ኒያውን» በንግግር መግለጹ ተገቢ አይደለም፡፡ የአላህ መልእክተኛ «ኒያ»ን በንግግር እንዳልገለጹ ሁሉ፣ ባልደረቦቻቸውም የእሳቸውን ተከትለው «ኒያ»ን በንግግር የገለጹበት አጋጣሚ አልተንጸባረቀም፡፡

አንድ ሰው ሰዎችን መርቶ እየሰገደም ይሁን፣ ብቻውን እየሰገደ፣ ፊት ለፊቱ ላይ ከለላ (ሱትራ) ማስቀመጥ ወይም ማድረግ ይገባዋል፡፡ በሶላት ጊዜ ፊትን ወደ ቂብላ (ካዕብ) አቅጣጫ ማዞር ከሶላት ቅድመ ሁኔታዎች አንዱ ግዴታ ነው፡፡ ይሁን እንጂ በሶላት ጊዜ ወደ ቂብላ አቅጣጫ

የማይዞርበት ልዩ አጋጣሚ መኖሩ ይታወቃል። ይህንንም ጉዳይ ሊቃውንት በመጻህፍታቸው አብራርተውታል።

3. ከዚያም አላሁ አክበር በማለት ተክቢረተል ኢህራምን በንግግር ይገልጻል። በዚህ ጊዜ ዓይኑ እሱ ሱጁድ የሚያደረግበትን ቦታ የሚመለከት ይሆናል።

4. አላህ አክበር በሚልበት ጊዜ፣ እጁን በትከሻው ትይዩ ወይም በጆሮዎቹ ትይዩ ማድረግ ነው።



5. ከዚያም እጅን ደረት ላይ ማድረግ ነው። ይህም ከአላህ መልዕክተኛ በተረጋገጠው መሰረት የቀኝ እጁን ከግራው እጁ ላይ ማድረግ ማለት ነው።



6. (ከተክቢረተል ኢህራም በሁዋላ) ቀጥሎ ያለውን የመክፈቻ ዱዓ ማለት ሱና ነው።

«اللَّهُمَّ بَاعِدْ بَيْنِي وَبَيْنَ خَطَايَايَ كَمَا بَاعَدتَّ بَيْنَ الْمَشْرِقِ وَالْمَغْرِب، اللَّهُمَّ نَقِّنِي مِنْ خَطَايَايَ كَمَا يُنَقَّى الثَّوْبُ الأَبْيَضُ مِنَ الدَّنَسِ، اللَّهُمَّ اغْسِلْنِي مِن خَطَايَايَ بِالْمَاءِ والثَّلْجِ وَالْبَرَد»

«አላሁምመ ባዒድ በይኒ ወበይነ ኸጣያዬ፣ ከማ ባዐድትተ (ሲነበብ - ባዐተ) በይነል መሽሪቂ ወልመግሪቢ፤ አላሁምመ ነቅቂኒ ሚነል'ኸጣያየ፣ ከማ ዩነቅቀሥሠውቡል አብየዱ ሚነድደነስ፤ አላሁምመግሲልኒ ሚን ኸጣያዬ ቢልማኢ ወሠልጂ ወልበረዲ።»

‹‹አላህ ሆይ! በምስራቅና በምዕራብ አቅጣጫ መካከል ያለውን ርቀት እንዳራራቅከው ሁሉ፣ በእኔና በወንጀሌ መካከል አራርቅ፡፡ ጌታዬ ሆይ! ነጭ ልብስ ከእድፍ እንደሚጸዳው ሁሉ፣ እኔን ከወንጀሌ አጽዳኝ፡፡ ጌታዬ ሆይ! በውሃ፣ በቀቅ (ውሃ)፣ በውሃና በበረዶ ወንጀሌን እጠብልኝ፡፡›› (ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል)፡፡ ወይም የሚከተለውን የመክፈቻ ዱዓ ማለት ይፈቀዳል፡-

«سُبْحَانَكَ اللَّهُمَّ وَبِحَمْدِكَ وَتَبَارَكَ اسْمُكَ وَتَعَالَى جَدُّكَ وَلَا إِلَهَ غَيْرُكَ»

‹‹ሱብሃነከልላሁምመ ወቢሀምዲከ፤ ወተባረከ ኢስሙከ፤ ወተዓላ ጀዱከ፤ ወላኢላ ገይሩከ፡፡››

‹‹አላህ ሆይ! በምስጉንነትህ ከጉድለት የጠራህ ነህ፤ ስምህ የተባረከ ነው፤ ልዕልናህ ከፍ ያለ ነው፤ ከአንተ ሌላ አምላክ የለም፡፡››

(አቡ ዳውድ ‹‹መርፉዕ››፣ ሙስሊም ደግሞ ‹‹መውቁፍ›› አድርገው ዘግበውታል)፡፡

ከእነዚህ ሁለት የመክፈቻ ዱዓዎች ሌላ፣ ከአላህ መልዕክተኛ ትክክለኛነታቸው እስከተረጋገጠ ድረስ፣ በመክፈቻ ጊዜ የተለያዩ ዱዓዎችን ማለት ችግር የለውም፡፡ በላጩ ግን እላይ ያወሳናቸውን ዱዓዎች አንዱን አንድ ጊዜ፣ ሌላውን ደግሞ ሌላ ጊዜ እየለዋወጡ መጠቀሙ ነው፡፡ ይህን ማድረጉ የአላህን መልዕክተኛ መንገድ (ሱና) ከመከተል አኩዋያ ምሉዕ ነው፡፡ ከዚህ የመክፈቻ ዱዓ በሁዋላ፡-

«أَعُوذُ بِاللَّهِ مِنَ الشَّيْطَانِ الرَّجِيمِ»

‹‹አዑዙ ቢላሂ ሚነሽሸይጧኒርረጂም›› ይላል፡፡ ‹‹ከተረገመው ሰይጣን በአንተ እጠበቃለሁ፡፡››

ከዚያም፡-

«بِسْمِ اللَّهِ الرَّحمَنِ الرَّحِيم»

«ቢስሚላሂ ረህማኒረሂም» «እጅግ በጣም ርህሩህና አዛኝ በሆነው ጌታ እጀምራለሁ፡፡»

ቀጥሎም የፋቲሃን (አል-ፋቲሃ) ምዕራፍ ያነባል፡፡ የአላህ መልዕክተኛ ስለ ፋቲሃ ምዕራፍ እንዲህ ብለዋል፡- «የአል-ፋቲሃን ምዕራፍ ሶላት ላይ ያልቀራ (ያላነበበ) ሰው፣ ሶላት የለውም (ሶላት እንዳልሰገደ ነው)፡፡» (ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል)፡፡ ሰጋጁ የሚሰግደው ሶላት ድምጽ ከፍ ተደርጎ የሚሰገድበት ሶላት ከሆነ፣ ድምጽን ከፍ አድርጎ «አሚን» ይላል፡፡ ከዚያም ከቁርአን መካከል የተገራለትን መርጦ ይቀራል (ያነባል)፡፡

7. ቀጥሎም እጁን በትከሻው ወይም በጆሮው ትይዩ አድርጎ በማንሳት ተክቢራ በማለት ወደ ታች ይጎነበሳል (ሩኩዕ ያደርጋል)፡፡ በሩኩዕ ጊዜ ጭንቅላቱ ከወገቡ ጋ እኩል መሆን አለበት፡፡ እንዲሁም የእጁን ጣቶች ዘር ዘር በማድረግ ጉልበቱ ላይ ያሳርፋል፡፡ ሩኩዕ ላይ ረጋ ማለት ይጠበቅበታል፡፡ በቆይታውም (በዚህ ጊዜም)፡



«سُبْحَانَ رَبِّيَ الْعَظِيمِ»

«ሱብሃነረቢየል ዐዚም» «ታላቅ ለሆንከው ጌታ! (ከጉድለት) የጠራህ ነህ!» ይላል፡፡ በሩኩዕ ጊዜ በጣም የተሻለው ዚክር፣ «ሱብሃነረቢየል ዐዚም»ን ሶስት ጊዜ ወይም ከዚያ በላይ መደጋገም ነው፡፡ በተጨማሪም

«سُبْحَانَكَ اللَّهُمَّ رَبَّنَا وَبِحَمْدِكَ، اللَّهُمَّ اغفِرْ لِي»

‹‹ሱብሀነከልላሁምመ ረብበና ወቢሀምዲከ፤ አላሁምመግፊር ሊ፡፡››

‹‹አላህ ሆይ! በምስጉንነትህ ከጉድለት የጠራህ ነህ፡፡ አላህ ሆይ! (ለወንጀሌ) ምህረት አድርግልኝ፡፡›› የሚለውን ዱዓ ማለት ይወደዳል፡፡

8. ከዚያም እጁን በትከሻው ወይም በጆሮው ትይዩ በማድረግ ማንሳት ነው፡፡ በዚህም ጊዜ የሚሰግደው ሰው፣ ሰዎችን እየመራም ይሁን ብቻውን እየሰገደ

«سَمِعَ اللّٰهُ لِمَنْ حَمِدَهُ»



‹‹ሰሚዓልላሁ ሊመን ሀሚዳ›› ‹‹አላህ ያመሰገነውን ሁሉ አዳመጠ፡፡›› ይላል፡፡ ከአጎነበሰበት ቀጥ እንዳለ ጨምሮም የሚከተለውን ይላል፡-

«رَبَّنَا وَلَكَ الْحَمْدُ حَمْدًا كَثِيرًا طَيِّبًا مُبَارَكاً فِيْهِ، مِلْءَ السَّمٰوَاتِ وَمِلْءَ الأَرْضِ، وَمِلْءَ مَا بَيْنَهُمَا وَمِلْءَ مَا شِئْتَ مِنْ شَيْءٍ بَعْدُ.»

‹‹ረብበና ወለከል ሀምድ፤ ሀምደን ከሲረን፣ ጦይይበን፣ ሙባረከን ፊሂ፤ ሚልአስሰማዋቲ፣ ወሚልአርዲ፣ ወሚልአ ማበይነሁማ፤ ወሚልአ ማሺእት፤ ሚንሸይኢን በዕዱ፡፡››

‹‹ጌታችን ሆይ! ምስጋና የሚገባው ላንተ ነው፡፡ በርካታ፣ ጥሩና የተባረከ ምስጋና (ለአንተ ነው የሚገባው፡፡) በሰማያት ሙሉ፣ በመሬት ሙሉ፣ በሁለቱም መካከል ባለ ነገር ሙሉ፣ እንዲሁም አንተ በፈለከው ነገር ሁሉ የሞላ (ምስጋና ይድረስህ)፡፡ የውዳሴና የክብር ባለቤት ነህ፡፡ ባሪያህ ከገለጸህ በላይ የሚገባህ (ጌታ) ነህ፡፡ ሁላችንም ለአንተ ባሪያዎች ነን፡፡››

ሰጋጁ ሶላቱን ተከትሎ የሚሰግድ (መእሙም) ከሆነ፣

«رَبَّنَا وَلَكَ الْحَمْدُ»

‹‹ረብበና ወለከል ሀምድ››ን እስከ መጨረሻው (ሶላቱ እስኪገባደድ ድረስ) ይላል፡፡

የሶላት መሪ (ኢማም) ሆነም ተከትሎ የሚሰግድ (መእሙም)፣ ከሩኩዕ መልስ እጃቸውን ደረታቸው ላይ ማስቀመጥ ይኖርባቸዋል፡፡ ይህን ጉዳይ ሙስሊም በዘገቡትና ዋኢል ኢብኑ ሂጅርና ሰህል ኢብኑ ሰዕድ ባስተላለፉት ሀዲስ የአላህ መልዕክተኛ ይተገብሩት የነበረ መሆኑ ተረጋግጡዋል፡፡

9. ከዚያም አላሁ አክበር በማለት ሱጁድ ማድረግ (ወደ ምድር መውረድ-ግንባር ወደሚያርፍበት ቦታ) ነው፡፡ በዚህ ጊዜ ሰጋጁ የሚችል ከሆነ ጉልበቱን ከእጁ በፊት በማስቀደም ሱጁድ ማድረግ ነው (ሱጁድ ሲያደርግ እጁን መሬት ላይ ከማሳረፉ በፊት ጉልበቱን ያሳርፍ ማለት ነው)፡፡ ይህ ሱጁድ አደራረግ ያቃተው ሰው፣ ከጉልበቱ በፊት እጁን አስቀድሞ ወደ ምድር በመላክ ሱጁድ ማድረግ ይችላል፡፡ የእግሮቹ ጣቶችና የእጆቹ ጣቶች እርስ በርሳቸው የተጠጋጉና እንዲሁም ወደ ቂብላ አቅጣጫ የዞሩ ሆነው፣ በሰባቱ የአካል ክፍሎች ማለትም በግንባሩ፣ በአፍንጫዉ፣ በመዳፎቹ፣ በጉልበቶቹና በእግሮቹ ጣቶች የውስጥ ክፍል ሱጁድ ያደርጋል፡፡ በዚህ ቦታም፡-



«سُبْحَانَ رَبِّيَ الأَعْلَىٰ»

‹‹ሱብሃነረቢየል አዕላ››

‹‹ከፍ ያለው አላህ ጥራት ይገባህ!›› ይላል፡፡

ይህን ዚክር ሶስት ጊዜ ወይም ከዚያም በላይ በዚህ ቦታ እየደጋገመ ይላል፡፡ ከዚህ ዚክር ጋር፣

«سُبْحَانَكَ اللَّهُمَّ رَبَّنَا وَبِحَمْدِكَ، اللَّهُمَّ اغْفِرْ لِي»

‹‹ሱብሀነከላሁምመ ወቢሀምዲከ፤ አላሁምመግፊር ሊ››

‹‹አላህ ሆይ! በምስጉንነትህ ከጉድለት የጠራህ ነህ፡፡ አላህ ሆይ! (ለወንጀሌ) ምህረት አድርግልኝ፡፡›› የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ይላሉ፡- ‹‹በሩኩዕ ላይ ልዕልናና ልቅና የተገባውን ጌታችሁን አልቁበት (ሱብሃነረቢየል አዕላ በሉበት)፡፡ በሱጁድ ላይ ደግሞ ዱዓ በማድረግ ታገሉ (ጥረት አድርጉ)፡፡ የምታደርጉት ዱዓ ተቀባይነት ሊያገኝ ተገቢ ነውና፡፡›› (ሙስሊም የዘገበው)፡፡

ሱጁድ በሚያደርግበት ጊዜም እጆቹንና ክንዶቹን ከጎኑ፣ ሆዱን ከጭኑ፣ ጭኑን ደግሞ ከባቱ ማራራቅ አለበት፡፡ እንዲሁም ክንዱን ከምድር ከፍ ማድረግም አለበት፡፡ የአላህ መለዕክተኛ ጉዳዩን አስመልክቶ እንዲህ ይላሉ፡- ‹‹በሱጁድ ላይ ተስተካከሉ፤ አንድኛችሁ (በሱጁድ ላይ) ውሻ እግሮቹን እንደሚዘረጋው አድርጎ፣ ክንዶቹን አይዘርጋ፡፡›› (ቡኻሪና ሙስሊም የዘገቡት)፡፡ አንድ ሰው የሚሰግደው ሶላት ግዴታም ይሁን ሱና፣ በሱጁድ ቦታ ላይ ከዱንያና ከአኺራ መልካም ጉዳዮች ጌታውን ይጠይቃል፡፡

10. ከዚያም አላሁ አክበር በማለት ጭንቅላቱን ቀጥ ያደርጋል፤ የግራ እግሩን ያነጥፍና ይቀመጥበታል፡፡ ከዚያም ቀኝ እግሩን ደግሞ ይቸክልና እጁን ከጭኑና ከጉልበት በላይ ያስቀምጣል፡፡ በዚህም ጊዜ፡-

«رَبِّ اغْفِرْ لِي، وَارْحَمْنِي وَاهْدِنِي وَارْزُقْنِي وَعَافِنِي وَاجْبُرْنِي»

«ረብቢግፊርሊ፤ ወርሀምኒ፤ ወህዲኒ፤ ወርዙቅኒ፤ ወዓፊኒ፤ ወጅቡርኒ፡፡»



«ጌታዬ ምህረት አድርግልኝ፤ እዘንልኝ፤ ቅኑን መንገድ ምራኝ፤ ሲሳይ፣ ደህንነትን ስጠኝ፤ ጠግነኝ፡፡» ይላል፡፡ በዚህ ጊዜ ሲቀመጥ እርጋታ ሊኖረው ይገባል፡፡

11. ከዚያም አላሁ አክበር በማለት ሁለተኛውን ሱጁድ ያደርጋል፡፡ በዚህና በሌሎቹ የሱጁድ ቦታዎችም ከዚህ በፊት ያደረገውን ነገር ሁሉ ዳግም በዚህ ቦታ ይፈጽመዋል፡፡

12. ከዚያም አላሁ አክበር በማለት ከሱጁድ ጭንቅላቱን ቀጥ ያደርጋል፡፡ በሁለቱ ሱጁዶች መካከልም ለትንሽ ጊዜ ያህል ይቀመጣል፡፡ ይህ መቀመጥ «ጀልሰተ አል ኢስቲራሃ» (የዕረፍት ጊዜ መቀመጥ) ይሰኛል፡፡ ይህን መቀመጥ ተግባራዊ ማድረግ የሚወደድ (ሙስተሀብ) ሲሆን፣ በዚህ ጊዜ ግን የሚደረግ ምንም አይነት ዱዓ ወይም ዚክር የለም፡፡ አንድ ሰው ይህን መቀመጥ ተግባራዊ ባያደርግ በሶላቱ ላይ ችግር የለውም፡፡ ከዚህ በሁዋላ ለሁለተኛው ረከዓ ከተቀመጠበት ይቆማል፡፡ በዚህ ጊዜ ከቻለ ጉልበቱን ይዞ ይቆማል፤ ካልቻል ደግሞ እጁን መሬት ላይ አስደግፎ ይቆማል፡፡ ከዚያም የፋቲሃን ምዕራፍና የተገራለትን ሌላ የቁርኣን ምዕራፍ ይቀራል (ያነባል)፡፡ ከዚያም በአንደኛው ረከዓ የሰራውን ነገር ሁሉ በሌሎችም ረከዓዎች ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

13. የሚሰግደው ሶላት ባለ ሁለት ረከዓ ከሆነ ማለትም እንደ ፈጅር፣ ሱብሂና ዒድ ባሉ ሶላቶች ላይ ከሁለተኛው ሱጁድ ቀጥ ካለ በሁዋላ ቀኝ እግሩን ቸክሎ (ቀጥ አድርጎ) ግራ እግሩን ያነጥፋል፡፡ ቀኝ እጁን ከቀኝ ጭኑ ላይ ያደርጋል፡ ፡ ጠቋሚ ጣቱ ሲቀር ሁሉንም ጣቶቹን አጣምሮ ጭኑ ላይ

ያደርጋል፡፡ በዚህ ጊዜ ላኢላሃ ኢለላህ ሲል፣ ጠቋሚ ጣቱን በአመልካችነት ይጠቀማል፡፡



በተጨማሪም ከእጅ ጣቶቹ መካከል በጣም ትንሹዋንና ከእሱዋ ቀጥሎ ያሉትን ጣቶቹን ቢጨብጣቸውና መካከለኛ ጣቱንና አውራ ጣቱን በማያያዝ ክብ ቢሰራና ላኢላሃ ኢለላህ በሚልበት ጊዜ አመልካች ጣቱን በአመልካችነት ቢጠቀም መልካም ነው፡፡

እላይ ያወሳናቸው ሁለቱም የእጅ አቀማመጦች በነቢያዊ ሀዲስ (በሱና) ተረጋግጠዋል፡፡ ለነገሩ እጅግ በጣም በላጩ አንደኛውን አንድ ጊዜ፣ ሌላኛውን ሌላ ጊዜ መጠቀሙ ነው፡፡ ግራ እጁን ከግራ ጭኑ ላይ አድርጎ፣ በተቀመጠበት ሁኔታ «ተሸሁድ» ይላል፡፡ «ተሸሁድ» የሚከተለው ነው፡-

«التَّحيَّاتُ للّه، وَالصَّلَوَاتُ والطَّيِّبَاتُ، السَّلَامُ عَلَيْكَ أَيُّهَاالنَّبيُّ وَرَحْمَةُ اللّه وَبَرَكَاتُهُ، السَّلَامُ عَلَيْنَا وَعَلَى عبَادَ اللّه الصَّالحينَ، أَشْهَدُ أَن لاَ إلَهَ إلَّا اللّه، وَأَشْهَدُ أَنَّ مُحَمَّدًا عَبْدُهُ وَرَسُولُهُ، اللَّهُمَّ صَلِّ عَلَى مُحَمَّد وَ عَلَى آل مُحَمَّد، كَمَا صَلَّيْتَ عَلَى إبْرَاهيمَ وَعَلَى آل إبْرَاهيمَ، إنَّكَ حَميدٌ مَجيدٌ، اللَّهُمَّ بَارِكْ عَلَى مُحَمَّد وَعَلَى آل مُحَمَّد، كَمَا بَارَكْتَ عَلَى إِبْرَاهِيمَ وَعَلَى آلِ إِبْرَاهِيمَ إنَّكَ حَميدٌ مَّجِيدٌ»

«አትተሀያቱ ሊላሂ ወስሰለዋቱ፣ ወጥጦይይባቱ፣ አሰላሙ አለይከ አይዩሃነቢዩ ወረህመቱላሂ ወበረካቱህ አስሰላሙ አለይና ወዐላ ዒባዲላሂ አስሷሊሂን፡፡ አሽሀዱ አንልላኢላሃ ኢልለላህ፤ ወአሽሃዱ አንነሙሀመደን ዐብዱህ ወረሱልህ፡፡ አላሁምመ ሶልሊ ዐላ ሙሀመድ ወዐላ ኣሊ ሙሀመድ፤

ከማ ሶልለይተ ዓላ ኢብራሂመ ወዐላ ኣሊ ኢብራሂመ፤ ኢንነከ ሀሚዱን መጂድ፡፡ አላሁምመ ባሪክ ዐላ ሙሀመድ ወዐላ ኣሊ ሙሀመድ፤ ከማ ባረክተ ዐላ ኢብራሂመ ወዐላ ኣሊ ኢብራሂመ ኢንነከ ሀሚዱን መጂድ፡፡››

‹‹(ማንኛውም አይነት) ሰላምታ ለአላህ ነው፡፡ (አምስት ወቅት) ሶላትና መልካም ነገሮች ሁሉ ለአላህ ናቸው፡፡ አንተ ነቢይ ሆይ! ሰላም በአንተ ላይ ይሁን፡፡ የአላህ እዝነትና በረከቶችም ይስፈን፡፡ በእኛና በአላህ ቅን ባሪያዎችም ላይ ሰላም ይስፈን፡፡ ከአላህ በስተቀር አምልኮት የሚገባው ሌላ አምላክ እንደሌለ እምሰክራለሁ፡፡ ሙሀመድም ባሪያውና መልእክተኛው መሆናቸውን እመሰክራለሁ፡፡ አላህ ሆይ! በኢብራሂምና በኢብራሂም ቤተሰቦች ላይ እዝነትህን እንዳሰፈንክ ሁሉ፣ በሙሀመድ ላይና በሙሀመድ ቤተሰቦች ላይ እዝነትህን አስፍን፡፡ አንተ ምስጉንና የላቅክ ነህና፡፡ አላህ ሆይ! በኢብራሂምና በኢብራሂም ቤተሰቦች ላይ ረድኤትህን እንዳደረክ ሁሉ፣ በሙሀመድና በቤተሰቦቹ ላይ ረድኤትህን አድርግ፡፡ አንተ ምስጉንና የላቀክ ነህና፡፡›› (ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል)፡፡

ከዚህም በተጨማሪ በዚህ ጊዜ አላህ ከአራት ነገሮች እንዲጠብቀው እሱን መጠየቅ አለበት፡፡ እንዲህም ይላል፡-

«اللَّهُمَّ إِنِّي أَعُوذُ بِكَ مِنْ عَذَابِ جَهَنَّمَ، وَمِنْ عَذَابِ الْقَبْرِ، وَمِنْ فِتْنَةِ الْمَحْيَا وَالْمَمَاتِ، وَمِنْ فِتْنَةِ الْمَسِيحِ الدَّجَّالِ»

‹‹አላሁምመ ኢንኒ አዑዙቢከ ሚን ዐዛቢ ጀሀንነም፤ ወሚን ዐዛቢል ቀብሪ ወሚን ፊትነቲል መህያ፣ ወልመማት፣ ወሚን ፊትነቲል መሲሂል ደጃል፡፡››

‹‹አላህ ሆይ! ከቀብር ቅጣትና ከገሀነም ቅጣት፣ ከህይወትና ከሞት ፈተና እንዲሁም ከሀሳዊው መሲህ ፈተና በአንተ እጠበቃለሁ፡፡›› ከዚያም በሚፈልገው የዱንያና የአኺራ ጉዳዮች ዱዓ ያደርጋል፡፡ ለምሳሌ ለወላጆቹ ወይም ለሙስሊሞች በግዴታ ወይም በሱና ሶላቶች ላይ

ዱዓ ቢያደርግ ችግር የለውም፡፡ ምክንያቱም ኢብኑ መስዑድ (ረ.ዐ) ባስተላለፉት ሀዲስ የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ብለዋል፡- «. . . ከዚያም ከዱዓ እሱን የገረመውን (የሻውን) ዱዓ በመምረጥ በሱ ዱዓ ሊያደርግ ነው፡፡» (አቡ ዳውድ ዘግቦታል)፡፡ በሌላ ዘገባ ደግሞ፡- «. . . በፈለገው ጉዳይ ላይ የፈለገውን ዱዓ ሊመርጥ ነው» ብለዋል፡፡ (ሙስሊም ዘግቦታል)፡፡ ይህ ሲባል የአላህን ባሪያ በሚጠቅመው ዱንያዊና አኺራዊ ጉዳይ ላይ ዱዓ ያደርጋል ማለት ነው፡፡ ከዚያም ወደ ቀኝ ትከሻውና ወደ ግራ ትከሻው በመዞር የሶላቱን ማብቃት እንዲህ በማለት ይቋዋጫል፡-

«السَّلَامُ عَلَيْكُمْ وَرَحْمَةُ اللّٰهِ»

‹‹ አስሰላሙ ዐለይኩም ወረህመቱላህ፤ አስሰላሙ ዐለይኩም ወረህመቱላህ፡፡››

14. የሚሰገደው ሶላት እንደ መግሪብ ባለ ሶስት ረከዓ ወይም እንደ ዙህር፣ ዐስርና ዒሻ ባሉ ባለ አራት ረከዓ ሶላቶች ደግሞ እላይ ያወሳነውን ተሸሁድ (አትተህያቱ ...) ከማለቱ በተጨማሪ በአላህ መልዕክተኛ ላይ ሶላዋት ማድረስ ይጠበቅበታል፡፡ ከዚያም ጉልበቱን በመያዝ (በመመርኮዝ) ከተቀመጠበት ይቆማል፡፡ በዚህም ጊዜ እጁን በትከሻው ትይዩ አድርጎ በማንሳት አላሁ አክበር ይላል፡፡ ቀደም ብሎ እንደተጠቀሰው ሲጋጁ እጆቹን ከደረቱ ላይ ያደርጋል፡፡ ከዚያም ፋቲሃን ብቻ ይቀራል፡፡ ሙስሊም በዘገበውና አቢ ሰዒድ (ረ.ዐ) ባስተላለፉት ሀዲስ ከአላህ መልዕክተኛ የሀዲሱ መረጃ በመረጋገጡ አንዳንድ ጊዜ በሶስተኛውና በአራተኛው ረከዓ ከፋቲሃ በተጨማሪ ሌላ የቀርአን ምዕራፍ ቢቀራ (ቢያነብ) ችግር የለውም፡፡



ከመጀመሪያውም ‹‹ተሸሁድ›› በሁዋላ በአላህ መልዕክተኛ ላይ

ሶለዋት ባያደርስ ችግር የለውም፡፡ ምክንያቱም በመጀመሪያው ተሸሁድ ሰለዋት ማለት የሚወደድ ተግባር እንጂ፣ ግዴታ አይደለም፡፡ ከዚያም በባለ ሁለት ረከዓዎች ላይ እንዳደረገው፣ ከሶስተኛው የመግሪብና ከአራተኛው የዙህር፣ የዐስርና የዒሻ ረከዓዎች በሁዋላ ቀደም ብሎ እንደተወሳው ተሸሁድ ይላል፡፡ በቀኙ በኩል ከዚያም በግራ በኩል ያሰላምታል፡፡ ቀጥሎም ሶስት ጊዜ «አስተግፊሩላህ» «አላህን ምህረት እጠይቃለሁ» ይላል፡፡ ከዚያም እንዲህም ይላል፡-

«اللَّهُمَّ أَنْتَ السَّلَامُ وَمِنكَ السَّلَامُ، تَبَارَكْتَ يَا ذَا الجَلَالِ وَالإِكرَامِ»

‹‹አላሁምመ አንተ ስሰላም፤ ወሚንከስሰላሙ፤ ተባረክተ ያዘልጀላሊ ወልኢክራም፡፡››

‹‹አላህ ሆይ! አንተ ሰላም ነህ፤ ሰላምም የሚገኘው ከአንተ ነው፤ የታላቅነትና የልግስና ባለቤት የሆንከው ጌታ ሆይ! ረድኤተ-ብዙ ነህ፡፡›› (ሙስሊም ዘግቦታል)፡፡

«لَا إِلَهَ إِلَّا اللّٰه وَحْدَهُ لَا شَرِيكَ لَهُ، لَهُ المُلْكُ وَلَهُ الْحَمْدُ، وَهُوَ عَلَى كُلِّ شَيْءٍ قَدِيرٌ، اللَّهُمَّ لَا مَانِعَ لِمَا أَعْطَيْتَ، وَلَا مُعْطِيَ لِمَا مَنَعْتَ وَلَا يَنْفَعُ ذَا الْجَدِّ مِنْكَ الْجَدُّ، لَا حَولَ وَلَا قُوَّةَ إِلَّا بِاللّٰه، لَا إِلَهَ إِلَّا اللّٰه، وَلَا نَعْبُدُ إِلَّا إِيَّاهُ، لَهُ النِّعْمَةُ وَلَهُ الفَضْلُ، ولَهُ الثَّنَاءُ الحَسَنُ، لَا إِلَهَ إِلَّا اللّٰه مُخْلِصِينَ لَهُ الدِّينَ، وَلَو كَرِه الكَافِرُون»

‹‹ላኢላሃ አለላህ፤ ወህደሁ ላሸሪከ ለሁ፤ ለሁልሙልኩ ወለሁል ሀምዱ ወሁወ ዐላ ኩልሊ ሸይኢን ቀዲር፡፡ አላህምመ ላማኒዓ ሊማአዕጦይተ፤ ወላ ሙዕጢየ ሊማ መነዕተ፤ ወላ የንፈዑ ዘልጀድዲ ሚንከልጀዲ፡፡ ወላ ሃውለወላ ቁውወተ ኢልላ ቢልላሂ፤ ላኢላሃኢለላህ፤ ወላነዕቡዱሁ ኢልላ ኢይያሁ፤ ለሁንኒዕሙቱ ወለሁል ፈድሉ፤ ወለሁ ሥሠናኡል

ሀሰኑ፤ ላኢላሃኢለላሁ፤ ሙኽሊሲነ ለሁ ድዲነ ወለው ከሪሃል ካፊሩን፡፡››

‹‹ከአላህ በስተቀር አምልኮ የሚገባው ሌላ አምላክ የለም፤ አንድ ነው አጋርም የለውም፡፡ ንግስና የእርሱ ብቻ ነው፡፡ ምስጋናም የሚገባው ለእርሱ ነው፡፡ እርሱ በሁሉም ነገር ቻይ ነው፡፡ አላህ ሆይ! አንተ የሰጠኸውን ነገር የሚከለክል፣ የከለከልከውንም የሚሰጥ ማንም የለም፡፡ የክብር ባለቤት ከአንተ ዘንድ ክብሩ ቅንጣት አይጠቅመውም፡፡ ሀይልና ብልሃት በአላህ እገዛ ቢሆን እንጂ፣ አይገኝም፡፡ ከአላህ በስተቀር አምልኮ የሚገባው ሌላ አምላክ የለም፡፡ እርሱን እንጂ ሌላ አካልን አንገዛም፡፡ ጸጋ የእርሱ ነው፤ ትሩፋትም ለእርሱ ነው፤ መልካም ውዳሴ የሚግገባው ለእርሱ ነው፡፡ ከአላህ በቀር ሌላ አምላክ የለም፤ ከሀዲዎች ቢጠሉም፣ እምነታችንን ለእሱ አጥርተናል፡፡›› (ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል)

ከዚያም ‹‹ሱብሃነላህ››ን ሰላሳ ሶስት ጊዜ፣ ‹‹አልሀምዱሊላሂ››ን ሰላሳ ሶስት ጊዜ፣ እንዲሁም ‹‹አላሁ አክበር›› ሰላሳ ሶስት ጊዜ መቶ መሙሊያውን ደግሞ ‹‹ላኢላሃ ኢልለላህ ወህደሁ ላሸሪከ ለሁ፣ ለሁልሙልኩ ወለሁል ሀምዱ፤ ወሁወ ዐላ ኩልሊ ሸይኢን ቀዲር ይላል፡፡›› (ሙስሊም የዘገበው)፡፡ ከዚያም ‹‹አየተል ኩርሲይ››ን፣ ‹‹ቁል ሁወልላሁ አሀድ››ን ‹‹ቁል አዑዙ ቢረብቢል ፈለቅ››ን እና ‹‹ቁል አዑዙ ቢረብቢ ንናሲ››ን ከሶላት በሁዋላ ይቀራል (ያነባል)፡፡ እነዚህን የቁርኣን ምዕራፎች ከፈጅርና ከመግሪብ ሶላቶች በሁዋላ ሶስት ጊዜ መደጋገም ይወደዳል፡፡ እነዚህ ተግባሮች ከአላህ መልእክተኛ ዘንድ በትክክለኛ ዘገባ ተረጋግጠዋል፡፡ እንዲሁም ቀደም ብሎ ከተጠቀሰው በተጨማሪ ከሶላተል ፈጅርና ከመግሪብ ሶላት በሁዋላ፣

«لَا إِلَهَ إِلَّا اللّٰهُ وَحْدَهُ لَا شَرِيكَ لَهُ، لَهُ الْمُلْكُ وَلَهُ الْحَمْدُ، يُحْيِي وَيُمِيتُ وَهُوَ عَلَى كُلِّ شَيْءٍ قَدِيرٌ»

«ላኢላሃ ኢለልላህ ወህደሁ ላሸሪከ ለሁ፤ ለሁልሙልኩ ወለሁል ሀምዱ፤ ዩህዪ ወዩሚቱ ወሁወ ዐላ ኩሊሸይኢን ቀዲር፡፡» ይላል፡፡

«ከአላህ በስተቀር አምልኮ የሚገባው ሌላ አምላክ የለም፤ አንድ ነው፤ አጋርም የለውም፡፡ ንግስና የእርሱ ብቻ ነው፡፡ ምስጋናም የሚገባው ለእርሱ ነው፡፡ ህያው የሚያደርገውና የሚገድለው እርሱ ነው፤ እርሱ በሁሉም ነገር ቻይ ነው፡» የሚለውን ዱዓ አስር ጊዜ ደጋግሞ ማለት ይወደዳል፡፡ ይህም ዚክር ከአላህ መልእክተኛ ዘንድ የተላለፈ መሆኑ ተረጋግጡዋል፡፡

ሶላት ሲጋጁ ኢማም (የሶላት መሪ) ከሆነ፣ ሶላቱን ከጨረሰ በሁዋላ ሶስት ጊዜ «አስተግፊሩላህ» እና «አላሁምመ አንተ ስሰላሙ ወሚንከስሰላም ተባረክተ ያዘል ጀላሊ ወልኢክራም» የሚሉትን ዚክሮች ካለ በሁዋላ ወደ ሰዎቹ ይዞራል፡፡ በትክክለኛ የሀዲስ ዘገባ እንደተረጋገጠው፣ ቀደም ብሎ የተወሱትን ዚክሮች ቀጥሎም ይላል፡፡ (ኢማሙ ሙስሊም በትክክለኛ የሀዲስ ዘገባ ዓኢሻን ጠቅሶ እንደዘገበው)፡፡ እላይ ያወሳናቸው አዝካሮች ሱና እንጂ፣ ግዴታ አይደሉም፡፡

ጾታ ሳይለይ ሁሉም ሙስሊም ከዙህር ሶላት በፊት አራት ረከዓ፣ በሁዋላ ላይ ደግሞ ሁለት ረከዓ መስገድ በኢስላም ተደንግጉዋል፡፡ ከመግሪብና ከዒሻ ሶላቶች በሁዋላ ሁለት ረከዓ እንዲሁም ከፈጅር ሶላት በፊት ሁለት ረከዓ መስገድም ሱና ነው፡፡ በአጠቃላይ ከሶላት በፊትና በሁዋላ የሚሰገዱት ሱና ሶላቶች አስራ ሁለት ረከዓዎች ናቸው፡፡ እነዚህ የሱና ሶላቶች «ሱነተርረዋቲብ» ይባላሉ፡፡ እንዲህ

ብለው የተሰየሙበት ምክንያቱም የአላህ መልእክተኛ አገር ቤት ላይ ሲሆኑ ይሰግዱዋቸው የነበረና መንገደኛ ሲሆኑ ግን ከፈጅር ሶላት በፊት ያለውን የፈጅር ሱናና የዊትር ሶላቶችን እንጂ ሌሎቹን አይሰግዱዋቸውም ነበርና ነው፡፡

እነዚህ ሱና ሶላቶች እቤት ላይ መሰገዳቸው እጅግ በጣም በላጭ ነው፡፡ ዘይድ ኢብኑ ሣቢት (ረ.ዐ) እንዳስተላለፉት፣ የአላህ መልእክተኛ፡- «የግዴታ ሶላት ሲቀር እንጂ፣ ለአንድ ሰው እጅግ በጣም በላጩ ከቤቱ የሚሰግደው ሶላቱ ነው» ብለዋል፡፡ (ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል)፡፡ ይሁን እንጂ እነዚህ ሶላቶች መስጂድ ላይ ቢሰገዱ ምንም ችግር የለውም፡፡

እነዚህን ሶላቶች ችላ ሳይሉ ጠብቆ መስገድ ለጀነት መግባት ሰበብ ናቸው፡፡ የአላህ መልእክተኛ እንዲህ ብለዋል፡- «አንድ ሰው በቀንና በሌሊት አስራ ሁለት ረከዓ የሱና ሶላቶችን የሰገደ ሰው፣ አላህ ለሱ በጀነት ውስጥ ቤት ይገነባለታል፡፡» (ሙስሊም በትክክለኛ ዘገባ የዘገበው)፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ ከአስራ ሁለቱ ረከዓ ሱና ሶላቶች በተጨማሪ፣ ከዐስር ሶላት በፊት አራት ረከዓ፣ ከመግሪብ ሶላት በፊት ሁለት ረከዓና ከዒሻ ሶላት በፊት ሁለት ረከዓ መስገድ መልካም ነው፡፡ ምክንያቱም እነዚህን ሶላቶች መሰገድ እንዳለባቸው በትክክለኛ የሀዲስ ዘገባ ተረጋግጡዋልና፡፡ እንዲሁም ከዙህር ሶላት በፊትና በሁዋላ አራት አራት ረከዓዎችን መስገድም እንዲሁ መልካም ተግባር ነው፡፡ ኡሙ ሀቢባ እንዳስተላለፈችው፣ የአላህ መልእክተኛ እንዲህ ይላሉ፡- «ከዙህር ሶላት በፊት አራትና በሁዋላ ደግሞ አራት ረከዓዎችን ጠብቆ የሰገደ ሰው፣ በእሱ ላይ እሳት እርም ይሆንለታል፡፡» (ኢማሙ አህመድ የዘገበው)፡፡ ይህ ማለት ቀደም ብለን ከጠቀስነው ከዙህር ሶላት በሁዋላ ከሚሰገደው ሁለት ረከዓ

ላይ ሌላ ሁለት ረከዓ መጨመር ነው፡፡ ምክንያቱም ዋናዎቹ ሱና ሶላቶች (ሰነኑርረዋቲብ) ከዙህር በፊት አራትና ሁለቱ ደግሞ በሁዋላ የሚሰገዱ ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ ሁለት ረከዓ በሁዋላ ላይ ከጨመረ ኡሙ ሀቢባ ባወሳቸው ሀዲስ የተወሳውን ምንዳ የሚያገኝ ይሆናል፡፡ መልካም ነገርን የማጎናጸፍ ባለቤት አላህ ነው፡፡

እዝነትና ሰላም በነቢዩ ሙሀመድ ኢብኑ ዐብደላህ፣ በቤተሰቦቻቸው፣ በባልደረቦቻቸውና እስከ እለተ ትንሳኤ ድረስ በቅኑ መንገድ በተከተሉትም ላይ ይስፈን፡፡

የአላህ መልእክተኛ እንዲህ ብለዋል፡-

مَنْ صَلَّى عَلَى جَنَازَةٍ فَلَه قِيْرَاطٌ وَمَنْ تَبِعَهَا حَتَّى تُدفَنَ فَلَهُ قِيْرَاطَان

‹‹አንድ ሰው በአንድ ጀናዛ ላይ ከሰገደ (ወደ መቃብር ቦታ ለመሸኘት ካልሄደ) ቂራጥ ይኖረዋል፡፡ ነገር ግን ጀናዛው ላይ (ሰግዶ) ከሸኘና እስኪቀበር ድረስ ከቆየ፣ የሁለት ቂራጥ (ምንዳ) ይኖረዋል፡፡›› (ሙስሊም የዘገበው)፡፡

# የጀናዛ ሶላት የአሰጋገድ ስነ-ስርዓት

ጥያቄ፡- አንድ ሰው በአንድ ጊዜ በአምስት ሬሳዎች (ጀናዛዎች) ላይ ሰገደ፡፡ በእያንዳንዱ ሰው ላይ በሰገደበት የ‹‹ቂራጥ›› ምንዳ ያገኛል? ወይስ የሶላቱ ምንዳ የሚገኘው በተሰገደው ሶላት ልክ ነው?

መልስ፡- ይህ ሰው በሰገደበት ጀናዛ ልክ ‹‹ቂራጥ›› ያገኛል ብለን ተስፋ እናደርጋለን፡፡ አቢ ሁረይራ (ረ.ዐ) እንዳስተላለፉት፣ የአላህ መልእክተኛ እንዲህ ብለዋል፡- ‹‹አንድ ሰው በአንድ ጀናዛ ላይ ከሰገደና ወደ መቃብር ቦታ ለመሸኘት ካልሄደ ቂራጥ ይኖረዋል፡፡ ነገር ግን ጀናዛ ከሸኘና እስኪቀበር ድረስ ከቆየ፣ የሁለት ቂራጥ (ምንዳ) ይኖረዋል፡፡›› (ሙስሊም የዘገበው)፡፡ ከነቢያዊ ሀዲሶች መረዳት እንደሚቻለው፣ በጀናዛ የሚገኘው ምንዳ (ቂራጥ) በጀናዛ ላይ በተሰገደው ሶላት ቁጥር ነው፡፡ ይህም ማለት አንድ ሰው በአንድ ጀናዛ ላይ ከሰገደ፣ አንድ ቂራጥ የሚኖረው ሲሆን፣ ጀናዛውን የሚሸኝ ከሆነ ደግሞ፣ ሌላ ቂራጥ ይኖረዋል፡፡ በጀናዛው ላይ ከሰገደ፣ ከሸኘና መጨረሻም ላይ ጀናዛው ተቀብሮ እስኪያልቅ ድረስ ከቆየ፣ ሁለት ቂራጥ ይኖረዋል፡፡ አላህ ጥራት ይገባውና ይህ የአላህ ትሩፋት ነው፡፡ ለጋስነቱ - በባሮቹ ላይ ያለው የአላህ ትሩፋት ነው፡፡ ለአላህ ምስጋና ይገባው፤ ከሱም ውጪ ሌላ አምላክ የለም፡፡ ከሱም ሌላ ጌታ የለም፡፡ አላህ መልካም ነገርን የማጎናጸፍ ባለቤት ነው፡፡

ጥያቄ፡- በሙዋች ላይ የሚሰገደው ሶላት የአሰጋገዱ ስነ-ስርዓት እንዴት ይፈጸማል? ለሶላቱስ ውዱእ ማድረግ እንደቅድመ ሁኔታ ይቆጠራልን?

መልስ፡- በሙዋች ላይ የሚሰገድ ሶላት የግዴታ ዉዱእ ያስፈልገዋል፡

፡ ምክንያቱም የአላህ መልእክተኛ ዒባዳውን «ሶላት» ብለው ጠርተውታልና ነው፡፡ ይህ ሶላት መክፈቻው «ተክቢራ» ሲሆን፣ መዝጊያው ደግሞ «ሰላምታ» ነው፡፡ ስለሆነም ይህን ሶላት ለመስገድ ውዱእ ማድረግ ያስፈልገዋል፡፡ የፋቲሃን ምእራፍ መቅራትም ግዴታ ነው፡፡ ለሙዋችም ዱዓ ማድረግ፣ በአላህ መልእክተኛም ላይ ሶላዋት ማድረስም እንዲሁ በጣም ያስፈልጋል፡፡

ይህ ሶላት እንደሌላው ሶላት ነው፡፡ ሌላው ሶላት ካለ ዉዱእ ከተሰገደ ተቀባይነት እንደሌለው ሁሉ፣ ሶላተል ጀናዛም ካለ ዉዱእ ከተሰገደ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

## የጀናዛ ሶላት አሰጋገድ የሚከተለውን ይመስላል



1. መጀመሪያ «ተክቢረተል አህራም» (አላሁ አክበር) ማለትና ከዚያም የፋቲሃን ምእራፍና የተገራለትን ሌላ የቁርኣን ምእራፍ ጨምሮ መቅራት (ማንበብ) ነው፡፡



2. ለሁለተኛ ጊዜ «ተክቢራ» ይልና በአላህ መልእክተኛ ላይ ሶለዋት ያደርሳል፤ «ሶላተል ኢብራሂሚያ» ተብሎ የሚታወቀውንም ጨምሮ ይላል፡፡ እሱም የሚከተለው ነው፡-

«اللَّهُمَّ صَلِّ عَلَى مُحَمَّدٍ وَعَلَى آلِ مُحَمَّدٍ ، كَمَا صَلَّيْتَ عَلَى إِبْرَاهِيمَ وَعَلَى آلِ إِبْرَاهِيمَ، إِنَّكَ حَمِيدٌ مَجِيدٌ ، اللَّهُمَّ بَارِكْ

عَلَى مُحَمَّدٍ وَعَلَى آلِ مُحَمَّدٍ ، كَمَا بَارَكْتَ عَلَى إِبْرَاهِيمَ وَعَلَى آلِ إِبْرَاهِيمَ إِنَّكَ حَمِيدٌ مَجِيدٌ.»

«አላሁምመ ሶልሊ ዐላ ሙሀመድ ወዐላ ኣሊ ሙሀመድ፤ ከማሶልለይተ ዐላ ኢብራሂመ ወዐላ ኣሊ ኢብራሂመ ኢንነከ ሀሚዱን መጂድ፤ አላሁምመ ባሪክ ዓላ ሙሀመድ ወዐላ ኣሊ ሙሀመድ፤ ከማ ባረክተ ዐላ ኢብራሂመ ወዐላ ኣሊ ኢብራሂመ

ፊልዓለሚነ ኢንነከ ሀሚዱን መጂድ፡፡»

«አላህ ሆይ! በኢብራሂምና በኢብራሂም ቤተሰቦች ላይ እዝነትህን እንዳሰፈንክ ሁሉ፣ በሙሀመድ ላይና በሙሀመድ ቤተሰቦች ላይ እዝነትህን አስፍን፡፡ አንተ ምስጉንና የላቅክ ነህና፡፡ አላህ ሆይ! በኢብራሂምና በኢብራሂም ቤተሰቦች ላይ ረድኤትህን እንዳደረክ ሁሉ፣ በሙሀመድና በቤተሰቦቹ ላይ ረድኤትህን አድርግ፡፡ አንተ ምስጉንና የላቅክ ነህና፡፡»



3. ለሶስተኛ ጊዜ ተክቢራ ይላል፡፡ ከዚያም ዱዓ ያደርጋል፡፡ ዱዓውም የሚከተለውን ይመስላል፡-

اللَّهُمَّ اغْفِرْ لِحَيِّنَا وَمَيِّتِنَا ، وَشَاهِدِنَا وَغَائِبِنَا ، وَصَغِيرِنَا وَكَبِيرِنَا ، وَذَكَرِنَا وَأُنْثَانَا ، اللَّهُمَّ مَنْ أَحْيَيْتَهُ مِنَّا فَأَحْيِهِ عَلَى الإِسْلاَمِ، وَمَنْ تَوَفَّيْتَهُ مِنَّا فَتَوَفَّهُ عَلَى الإِيمَانِ، اللَّهُمَّ لاَ تَحْرِمْنَا أَجْرَهُ وَلاَ تُضِلَّنَا بَعْدَهُ»



«አላሁምመግፊር ሊሀይዩና፣ ወመይዩቲና፣ ወሶጊ
ወዘከሪና፣ ወኡንሣና፣ ወሻሂዲና፣ ወጋኢቢና፡፡ አ
አህየይተሁ ሚንና ፈአህዩሂ ዐለል ኢማን፤ ወመን
ሚንና ፈተወፍፈትሁ ዐለል ኢስላም፤ አላሁም
አጅረሁ፤ ወላ ቱዲልለና በዕደሁ»

«አላህ ሆይ! በህይወት ላሉትም፣ ለሞቱትም፣ በቅርብ ለሚገኙትም፣ በሩቅ ላሉትም፣ ለህጻናቱም፣ ለአዛውንቱም፣ ለወንዶቹም፣ ለሴቶቹም ወገኖቻችን ምህረትን አድርግላቸው -አውርድላቸው፡፡» (ኢማሙ አህመድ የዘገበው)፡፡

« اللَّهُمَّ اغْفِرْ لَهُ، وَارْحَمْهُ، وَعَافِهِ، وَاعْفُ عَنْهُ، وَأَكْرِمْ نُزُلَهُ، وَوَسِّعْ مُدْخَلَهُ، «وَاغْسِلْهُ بِالْمَاءِ وَالثَّلْجِ وَالْبَرَدِ ، وَنَقِّهِ مِنَ الْخَطَايَا كَمَا يُنَقِّي الثَّوْبَ الأَبْيَضَ مِنَ الدَّنَسِ، اللَّهُمَّ وَأَبْدِلْهُ دَارًا خَيْرًا مِنْ

دَارِه، وَأَهْلًا خَيْرًا مِّنْ أَهْلِهِ، وَأَدْخِلْهُ الْجَنَّةَ وَأَعِذْهُ مِنْ عَذَابِ الْقَبْرِ وَمِنْ عَذَابِ النَّارِ»

‹‹አላሁምመግፊር ለሁ፤ ወርሀምሁ፤ ወዓፊሂ፤ ወዕፉ ዐንሁ፤ ወአክሪም ኑዙለሁ፤ ወወስሲዕ ሙድኸለሁ፤ ወግሲልሁ ቢልማኢ፣ ወሥሠልጂ፣ ወልበረዲ፤ ወነቅቂሂ ሚነልኸጧያ፤ ከማ ዩነቅቂ ሥሠውበል አብየደ ሚነድደነሲ፤ አላሁምመ ወአብዲልሁ ዳረን ሚን ዳሪሂ፤ ወአህለን ሚን አህለሂ፤ ወዘውጀን ኸይረን ሚን ዘውጂሂ፤ ወአድኺልሁል ጀንነተ፤ ወአዒዝሁ ሚን ዐዛቢልቀብሪ፤ ወሚን ዐዛቢ ንናሪ"

‹‹አላህ ሆይ! ማረው፤ እዘንለት፤ ይቅር በለው፤ ምህረትን ለግሰው፤ መስተንግዶውን አሳምርለት፤ መግቢያውን አስፋለት፤ በውሃ፣ በበረዶና በቀቅ (ውሃ) እጠበው፤ ነጭ ልብስ ከእድፍ እንደሚጸዳ ሁሉ፣ እሱን ከወንጀሉ አጥራው፡፡ አላህ ሆይ! ከቤቱም የተሻለ ቤት፣ ከሚስቱም የተሻለ ሚስት ስጠው፡፡ ጀነትን አስገባው፤ ከቀብርና ከእሳት ቅጣት ጠብቀው፡፡›› (ሙስሊም የዘገበው)፡፡

«وَافْسَحْ لَهُ فِي قَبْرِهِ، وَنَوِّرْ لَهُ فِيهِ»

«ወፍሰህ ለሁ ፊቀብሪሂ፤ ወነውዊር ለሁ ፊሂ፡፡» «ቀብሩን አስፋለት፤ ብርሃንም አድርግለት፡፡» (ሙስሊም የዘገበው)፡፡

4. ለአራተኛ ጊዜ «ተክቢራ» (አላሁ አክበር) ይላል፡፡ ከተክቢራው በኋላ ትንሽ ቆዬትም ይላል፡፡ ከዚያም አንድ ጊዜ ወደ ቀኙ በኩል ያሰላምታል፡፡ ሙዋችዋ ሴት ከሆነች፣ ለእያንዳንዱ «ተክቢራ» እጁን ወደ ላይ ማንሳት ይወደዳል፡ ፡ ዱዓውንም፡- «አላሁምመግፊር ላሃ ...» ሙዋቾቹ ሁለት ከሆኑ፡- «አላሁምመግፊር ለሁማ ... «ይላል፡፡ ሙዋቾቹ ከሁለት በላይ ከሆኑ፡- «አላሁምመግፊር ለሁም ...» በማለት ዱዓውን ያደርጋል፡፡

ሙዋቹ ህጻን ከሆነ፣ ዱዓውን በዚህ መንገድ ያደርጋል፡-

«اللَّهُمَّ اجْعَلْهُ فَرَطًا وَذُخْرًا لِوَالِدَيْه، وَشَفِيعًا مُجَابًا، اللَّهُمَّ ثَقِّلْ بِهِ مَوَازِينَهُمَا، وَأَعْظِمْ بِهِ أُجُورَهُمَا، وَأَلْحِقْهُ بِصَالِحِ سَلَفِ الْمُؤْمِنِينَ، وَاجْعَلْهُ فِي كَفَالَةِ إِبْرَاهِيمَ عَلَيْهِ الصَّلَاةُ السَّلَامُ، وَقِهِ بِرَحْمَتِكَ عَذَابَ الْجَحِيمِ»

"አላሁምመጅዐልሁ ፈረጠን፤ ወዙኽረን፤ ሊዋሊደይሂ፤ ወሸፊዐን ሙጃበን፤ አላሁምመ ሠቅቂል ቢሂ መዋዚነሁማ፤ ወአዕዚም ቢሂ ኡጁረሁማ፤ ወአልሂቅሁ ቢሷሊሂ ሰለፊል ሙእሚኒን፤ ወጅዐልሁ ፊ ከፋለቲ ኢብራሂመ ዐለይሂስሶላቱ ወስሰላም፤ ወቂሂ ቢረህሙቲከ ዐዛበል ጀሂም፡፡»

«አላህ ሆይ! (ይህን ልጅ) ቀዳሚ ሽልማት አድርገው፤ ለወላጆቹም ተቀማጭ ሃብት አድርገው፤ ተቀባይነት ያለው አማላጅም አድርገው፡፡ አላህ ሆይ! በርሱ ሳቢያ ሚዛናቸውን ከፍ አድርግላቸው፡፡ ምንዳቸውንም አብዛላቸው፡፡ ከቀዳሚ ቅን ምእመናን ጋር ፈርጀው፤ በኢብራሂም ሞግዚትነት ስርም አድርገው፤ በእዝነትህም ከገሀነም ቅጣት ጠብቀው፡፡) (አብዱረዛቅና ኢብኑ አቢ ሸይባ የዘገቡት)፡፡

ቡኻሪና ሙስሊም እንዲሁም አቡ ዳውድ አነስንና ሰሙራ ኢብኑ ጁንዱብን ጠቅሰው በዘገቡት ሀዲስና ሀዲሱም ከአላህ መልእክተኛ እንደተረጋገጠው፣ ሙዋቹ ወንድ ከሆነ ሶላቱን የሚመራው ሰው (ኢማሙ) ከሙዋቹ ጭንቅላት (ራስ) አካባቢ ሲቆም፣ ሙዋቹዋ ሴት ከሆነች ደግሞ፣ በወገቡዋ ትይዩ ይቆማል፡፡

ነገር ግን የተወሰኑ ሙስሊም ሊቃውንት ሙዋቹ ወንድ ከሆነ፣ ኢማሙ ከሙዋቹ ደረት አካባቢ መቆሙ ሱና ነው ማለታቸው፣ ደካማ አቋም ነው፡፡ እኛ እስከምናውቀው ድረስ ይህ አቋም ጠንካራ ማስረጃ የለውም፡፡

የአላህ መለእክተኛ ስለ ካዕባ ሲናገሩ፡- «(ካዕባ) ህያውና ሙት በሆናችሁበት ሁኔታ ቂብላችሁ ነው» (አቡ ዳውድ የዘገበው) ብለው ያስተላለፉት መልዕክት በመኖሩ፣ በሙዋች ላይ ሶላት ሲሰገድ ሙዋች ወደ ቂብላ መዞር ይኖርበታል፡፡

የተለያየ የጀናዛዎች ስብስብ ከኖረ፣ ወንዱ ከኢማሙ አጠገብ ሲሆን፣ ሴቱዋ ደግሞ ከቂብላው ከጥላ ትሆናለች፡፡ ብዙ ህጻናት ከሆኑ ደግሞ፣ ወንዱ ህጻን ከአዋቂዋ ሴት ይቀድማል፡፡ ከዚያም አዋቂዋ ሴት ትሆናለች፡፡ ህጻኑዋ ሴት ደግሞ ከአዋቂዋ ሴት ቀጥላ ትሆናለች፡፡

የሬሳዎቹ ተግባራዊ አቀማመጥ ደግሞ የሚከተለውን ይመስላል፡-

የወንዱ ህጻን ጭንቅላት ከአዋቂው ወንድ ጭንቅላት ትይዩ ይሆናል፡፡ የአዋቂዋ ሴት የወገብ ክፍል ደግሞ በአዋቂው ወንድ ጭንቅላት ትይዩ አቅጣጫ ይሆናል፡፡ እንደዚሁም የሴትዋ ህጻን ጭንቅላት ከአዋቂዋ ሴት ጭንቅላት ትይዩ አቅጣጫ ይሆናል፡፡ የአዋቂዋ ሴት የወገብ ክፍል ደግሞ፣ በአዋቂው ወንድ ጭንቅላት ትይዩ አቅጣጫ ይሆናል፡፡ ሁሉም ሶላት ሰጋጆች ደግሞ ከኢማሙ ሁዋላ ይሆናሉ፡፡ ከኢማሙ ሁዋላ ለመሆን (ለመቆም) ቦታ ያላገኛ ሰው፣ ከኢማሙ የሁላ ክፍል ከመቆም ውጪ ሌላ አማራጭ የሌለው ከሆነ፣ ከኢማሙ በስተቀኝ በኩል መቆም ይችላል፡፡

# የሀጅ፣ የዑምራና የጉብኝት የአፈጻጸም ገጽታ

ምስጋና ለዓለማት ጌታ ይሁን፡፡ መጨረሻውም አላህን ለሚፈሩ ሰዎች ነው፡፡ የአላህ እዝነትና ሰላም በባሪያውና በመልዕክተኛው ሙሀመድ፣ በቤተሰቦቻቸውና በባልደረቦቻቸው ላይ ይሁን፡፡

ከዚህ ቀጥሎም፣ ይቺ የሀጅን አፈጻጸሙንና ስርዓቱን እንዲሁም በኢስላም ያለውን ደረጃ የምታብራራ አጭር መልዕክት ስትሆን፣ ዑምራንና እንዲሁም ጉብኝትን (ዚያራን) ለማድረግ ያሰበ ሰው ምን ማድረግ እንዳለበት የሚመለከቱ ብዙ ነጥቦችንም አጭርና ግልጽ በሆነ መንገድ ታብራራለች፡፡

ይቺን አጭር መልዕክት በሚገባ ለማቅረብም ቁርኣንና ሱና ሀጅን፣ ዑምራን እንዲሁም ጉብኝትን (ዚያራን) በሚመለከቱ ጉዳዮቹ ላይ ያስቀመጡትን መልዕክት በሚገባ ፈትሻለሁ፡፡

የእነዚህን መልዕክቶች መረጃዎች የሰበብኩበትና መልዕክቱም እንዲደርስ ያደረኩበት ጥረት ዋና ዓላማው በጉዳዮቹ ላይ ኢስላማዊ ዕውቀትን መሰረት ያደረገ መልዕክት ለሙስሊሞች ለማስተላለፍ ስለፈለኩ ነው፡፡ ቁርኣን በምዕራፍ አዝ-ዛሪያት፣ ቁጥር 55 ላይ

- ﴿ وَذَكِّرْ فَإِنَّ ٱلذِّكْرَىٰ تَنفَعُ ٱلْمُؤْمِنِينَ ٥٥ ﴾

‹‹ገስጽም፤ ግሳጼ ምዕመናንን ትጠቅማለች›› የሚለውንም ቁርኣናዊ መልዕክት ተግባራዊ ለማድረግም ነው፡፡

በተጨማሪም አላህ በቁርኣን እንዲህ ይላል፡-

- ﴿ وَإِذْ أَخَذَ ٱللَّهُ مِيثَٰقَ ٱلَّذِينَ أُوتُوا۟ ٱلْكِتَٰبَ لَتُبَيِّنُنَّهُۥ لِلنَّاسِ ١٨٧ ﴾

‹‹አላህ የእነዚያን መጽሀፉን የተሰጡትን ቃል ኪዳን ለሰዎች በእርግጥ ታብራሩታላችሁ፤ አትደብቁትም… ፡፡›› (ኣሊ-ዒምራን፣ 187)፡፡

- ﴿وَتَعَاوَنُوا۟ عَلَى ٱلْبِرِّ وَٱلتَّقْوَىٰ ۝٢﴾

‹‹ … በበጎ ነገርና አላህን በመፍራት ተረዳዱ፤ … ›› (አል-ማኢዳ፣ 2)፡፡

በትክክለኛ የሀዲስ ዘገባ የአላህ መልዕክተኛ ሶስት ጊዜ እንዲህ ብለዋል፡-

- ‹‹ዲን ማለት ምክክር ነው፡፡›› የአላህ መልዕክተኛ ይህ ምክክር ለማን ነው አልናቸው፡፡ እሳቸውም፣ ‹‹ለአላህ፣ ለመጽሀፉ፣ ለመልዕክተኛው፣ ለሙስሊሞች መሪዎችና ለህዝበ - ሙስሊሙ ነው፡፡›› አሉ፡፡

ጠበራኒ ሁዘይፋን ጠቅሶ እንደዘገበው፣ የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ብለዋል፡-

- ‹‹የሙስሊሞች ጉዳይ የማያሳስበው ሰው ከእነሱ አይደለም፡፡ ሲያነጋና ሲያመሽ ለአላህ፣ ለመልዕክተኛው፣ ለመጽሀፉ፣ ለመሪው፣ ለብዙሃኑ ሙስሊም መካሪ ያልሆነ ሰው ከሙስሊሞች አይደለም፡፡››

አላህ ይህ ስራ ሙስሊሞችን የሚጠቅም፣ ጥረቱም ፍጹም የሱን ምንዳ ለማግኘት ተብሎ የተሰራ እንዲያደርገው፣ ድሎት ካለበት ጀነት የመግባት ዕድልን እንዲያጎናጽፈን ምክንያት እንዲያደርገውም እሱን እንጠይቀዋለን፡፡ እሱ ሰሚና ምላሽ ሰጪ ነውና ለእኛ በቂያችን ነው፡፡ ምን ያማረ መመኪያ ነው!

# የሀጅና የዑምራ ግዴታነትና እነሱን ለመፈጸም የመትጋት አስፈላጊነት

ሀጅና ዑምራ የግዴታ ተግባራዊ ሊሆኑ የሚገባቸው መሆናቸውን በማስረጃ አጣቅሶ ማቅረብና እነሱን ለመፈጸምም መትጋት አስፈላጊ መሆኑ ከታወቀ፣ ብዙኃኑ ሙስሊሞች ማወቅ ያለባቸው ነገር አለ፡፡ ከሁሉም በፊት ግን እኔንና እናንተን አላህ ሀቁን ለማወቅና ለመከተል ዕድሉን ይግጠመን፡፡

አላህ በባሪያዎቹ ላይ ካዕባን እንዲጎበኙ ግዴታ አድርጎባቸዋል፡፡ ከኢስላም ማዕዘናት መካከልም አንዱ አድርጎታል፡፡ አላህ በቁርኣን እንዲህ ይላል፡-

- ﴿وَلِلَّهِ عَلَى ٱلنَّاسِ حِجُّ ٱلۡبَيۡتِ مَنِ ٱسۡتَطَاعَ إِلَيۡهِ سَبِيلٗاۚ وَمَن كَفَرَ فَإِنَّ ٱللَّهَ غَنِيٌّ عَنِ ٱلۡعَٰلَمِينَ ٩٧﴾

« ... ለአላህም በሰዎች ላይ ወደ እርሱ መሄድን በቻለ ሁሉ ላይ ቤቱን መጎብኘት ግዴታ አለባቸው፡፡ የካደም ሰው አላህ ከዓለማት ሁሉ የተብቃቃ ነው፡፡» (ኣሊ-ዒምራን፣ 97)፡፡

ሙስሊም በትክክለኛ የሀዲስ ዘገባው ኢብኑ ዑመርን ጠቅሶ እንደዘገበው፣ የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ብለዋል፡-

- «ኢስላም በአምስት ማዕዘናት የተገነባ ነው፡፡ ከአላህ ሌላ የሚመለክ አምላክ አለመኖሩንና ሙሀመድ የአላህ መልዕክተኛ መሆናቸውን መመስከር፣ ሶላት መስገድ፣ ዘካ ማውጣት፣ ረመዳንን መጾምና ጥብቅ የሆነውን ቤቱን (ካዕባን) መጎበኘት ነው፡፡»

ሰዒድ ደግሞ ሱነኑ (የሀዲስ ጥራዙ) ላይ ዑመር ኢብኑል ኸጣብ እንዲህ ማለታቸውን አውስቷል፡-

- ‹‹ወደ እነዚህ ከተሞች መልዕክተኞችን መላክን አሰብኩኝ፡፡ እነሱም የትኛው ሰው የገንዘብ አቅም እንዳለው እንዲለዩና ሀጅ በማያደርጉ ሰዎች ላይ ደግሞ ሙስሊሞች አይደሉምና፣ ሙስሊሞች አይደሉምና ጂዝያ (ሙስሊም ያልሆኑ ሰዎች የሚከፍሉት ግብር) እንዲጣልባቸው፡፡››

ከዐሊይ እንደተዘገበውም፣ ዐሊይ እንዲህ ብለዋል፡-

- ‹‹ሀጅ የማድረግ አቅም እያለው ሀጅ ያላደረገ ሰው፣ የሁዲ ወይም ክርስቲያን ሆኖ ከመሞት ሌላ አማራጭ የለውም፡፡›› (ቲርሚዚ የዘገበው)፡፡

ስለሆነም ሀጅ ማድረግ እየቻለ ሀጅ ያላደረገ ሰው ሀጅ ለማድረግ መጣጣር ይኖርበታል፡፡ ኢብኑ ዐባስ እንዳስተላለፉት፣ የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ አሉ፡-

- ‹‹ሀጅ (ግዴታ የሆነውን) ለማድረግ ተቻኮሉ፡፡ ከመካከላችሁ አንድኛችሁ እሱን ወደ ፊት ምን እንደሚገጥመው አያውቅምና፡፡›› (አህመድ የዘገበው)፡፡

ቀጣዩ ቁርኣናዊ ማስረጃ እንደሚያመለክተው፣ አንድ ሰው ሀጅ የማድረግ አቅም ሲኖረው፣ ወዲያዉኑ ሀጅ የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡

- ﴿وَلِلَّهِ عَلَى ٱلنَّاسِ حِجُّ ٱلۡبَيۡتِ مَنِ ٱسۡتَطَاعَ إِلَيۡهِ سَبِيلٗاۚ وَمَن كَفَرَ فَإِنَّ ٱللَّهَ غَنِيٌّ عَنِ ٱلۡعَٰلَمِينَ ٩٧﴾

« ... ለአላህም በሰዎች ላይ ወደ እርሱ መሄድን በቻለ ሁሉ ላይ ቤቱን መጎብኘት ግዴታ አለባቸው፡፡ የካደም ሰው አላህ ከዓለማት ሁሉ የተብቃቃ ነው፡፡» (ኣሊ-ዒምራን፣ 97)፡፡

የአላህ መልዕክተኛ በዲስኩራቸው ቀጣዩን ሃሳብ ገልጸዋል፡-

«ሰዎች ሆይ! አላህ በእናንተ ላይ ሀጅ እንድታደርጉ ግዴታ ስላደረገባችሁ፣ ሀጅ አድርጉ ...» (ሙስሊም የዘገበው)፡፡

ዑምራ የግዴታ መፈጸም እንዳለበት ከሚያመላክቱት ሀዲሳዊ መረጃዎች መካከል የሚከተሉት ተጠቃሽ ናቸው፡-

የአላህ መልዕክተኛ ጂብሪል ስለ ኢስላም በጠየቃቸው ጊዜ እንዲህ አሉ፡-

- «... ሶላትን ልትሰግድ፣ ዘካ ልታወጣ፣ ቤቱን (ካዕባን) ልትጎበኝ፣ ዑምራ ልታደርግ፣ ጀናባ ስትሆን ገላህን ልትታጠብ፣ ዉዱህን አሟልተህ ልታደርግ፣ ረመዳንን ልትጾም ነው» (ኢብኑ ኹዘይማና ዳረልቁጥኒይ ኢብኑ ዑመርን ጠቅሰው የዘገቡት፡፡) ዳረልቁጥኒይ ይህ ሀዲስ የዘገባ ሰንሰለቱ የተረጋገጠና ትክክለኛ ነው ብሏል፡፡
- ዓኢሻ፣ «የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! በሴቶች ላይ ጂሃድ የማድረግ ግዴታ አለባቸውን?» አለቻቸው፡ ፡ እሳቸውም፣ «በእነሱ ላይ መጋደል የሌለበት የሆነ ሀጅንና ዑምራን ማድረግ ነው ያለባቸው» አሉ፡፡ (አህመድና ኢብኑ ማጃህ በትክክለኛ የዘገባ ሰንሰለት ዘግበውታል)፡፡

አንድ ሰው ሀጅና ዑምራን በህይወት ዘመኑ አንድ ጊዜ ብቻ ማድረግ ነው ግዴታ የሚሆንበት፡፡ የአላህ መልዕክተኛ በትክክለኛ የሀዲስ ዘገባ እንዲህ ይላሉ፡-

- «(ከዚህ) የጨመረ ሰው ለሱ ሱና ይሆንለታል፡፡»

ሀጅንና ዑምራን ከአንድ ጊዜ በላይ ደጋግሞ ማድረጉ ሱና ነው፡፡

በትክክለኛ ሀዲስ እንደተረጋገጠውና አቡ ሁረይራ እንዳስተላለፉት፣ የአላህ መልእክተኛው እንዲህ አሉ፡-

- «ከአንድ ዑምራ እስከ አንድ ዑምራ ድረስ ያሉት፣ በመካከላቸው ያለውን ወንጀል እንዲሰረዝ ያስደርጋሉ፡፡ ጥሩ ሀጅ ጀነት እንጂ ሌላ ምንዳ የለውም፡፡» (ቡኻሪ ዘግበታል)፡፡

# ከወንጀል መመለስና ከበደሎች የመውጣት ግዴታነት

አንድ ሰው ሀጅ ወይም ዑምራ ለማድረግ ቁርጠኛ ከሆነ ቤተሰቦቹንና ጓደኞቹን ልዕልናና ልቅና የተገባውን አላህ እንዲፈሩ አደራ ማለት ይወደድለታል፡፡ ይህም አደራ የአላህን ትዕዛዝ እንዲፈጽሙና የከለከለውን እንዲከለከሉ መምከር ነው፡፡

ሀጅ ወይም ዑምራ አድራጊው ሰዎች ላይ ያለውን ገንዘብ (ወይም ሌላ ንብረት) እና በእሱ ላይ ያለበትን ዕዳ መጻፍ አለበት፡፡ ይህንም ሲያደርግ ሰዎችን ማስመስከር አለበት፡፡ በተጨማሪም ከሁሉም አይነት ወንጀሎች በሚገባ ወደ አላህ ንስኃ ለመግባት (ለመቶበት) መጣጣር ግዴታ አለበት፡፡ አላህ በቁርኣኑ እንዲህ ይላል፡-

- ﴿وَتُوبُوٓاْ إِلَى ٱللَّهِ جَمِيعًا أَيُّهَ ٱلْمُؤْمِنُونَ لَعَلَّكُمْ تُفْلِحُونَ ٣١﴾

«ምዕመናን ሆይ! ትድኑ ዘንድ ሁላችሁም ወደ አላህ (ንስኃ በመግባት) ተጸጸቱ» (አን-ኑር፣ 31)፡፡

ንስኃ የመግባት (ወደ አላህ የመመለስ) ትክክለኛ ገጽታ ከወንጀል ራስን ማውጣትና ወንጀል መስራትን አሁን መተው ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ቀድሞ ከተሰራው ስራም መጸጸትና ወደ ቀድሞው ወንጀል ላለመመለስ ቁርጠኛ መሆንንም ያካትታል፡፡ ንስኃ የገባው ሰው ሰዎችን በድሎ ከሆነ ለምሳሌ የሰው ህይወት ላይ አደጋ አድርሶ ከሆነ ወይም ከገንዘብና ከክብር ጋር የተገናኘ ነገር ከሆነም ነገሩን ወደ ባለቤቱ መመለስ አለበት፡፡ ስለሆነም ወደ መንገድ ከመሄዱ በፊት ባጠፋው ነገር ይሁንታ ማግኘት አለበት፡

፡ በትክክለኛ የሀዲስ ዘገባ እንደተረጋገጠው የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ አሉ፡-

- «አንድ ሰው የወንድሙን ክብር ነክቶ ከሆነ ወይም ሌላን ነገር ፈጽሞበት ከሆነ፣ ዲናርና ድርሃም በማይገኝበት አጋጣሚ ከመድረሱ በፊት፣ ዛሬውኑ ለጥፋቱ ማካካሻ ይፈልግ፡፡ ለእሱ መልካም ስራ ካለው፣ በሰራው በደል ልክ መልካም ስራው ይያዝበታል፡፡ እሱ መልካም ስራ ከሌለው ደግሞ፣ እሱ የበደለው ሰው ወንጀል ተይዞ፣ ከእሱ ላይ ይጫንበታል፡፡» (ቡኻሪ ዘግቦታል)፡፡

ለሀጅና ለዑምራው ጉዞው በሀቅ ተሰርቶ ከተገኘው (ሀላል) ገንዘቡ ቀለቡን ማሰናዳት አለበት፡፡ ከአላህ መልዕክተኛ በትክክለኛ የሀዲስ ዘገባ እንደተረጋገጠው፣ እሳቸው እንዲህ ብለዋል፡-

- «እናንተ ሰዎች ሆይ! አላህ መልካም ነው፡፡ ስለሆነም እሱ መልካምን እንጂ፣ ሌላን አይቀበልም፡፡» (ሙስሊም የዘገበው)፡፡

ጦበራኒ አቢ ሁረይራን ጠቅሶ እንደዘገበው፣ የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ብለዋል፡-

- «አንድ ሰው በጥሩ ገንዘቡ ሀጅ ለማድረግ (ከቤቱ) ሲወጣና ከመጓጓዣው መወጣጫ እርካብ ላይ እግሩን ሲያሳርፍ፣ ‹ለብበይከ አልላሁምመ ለበይከ› (አላህ ሆይ! ትዕዛዝህን ለመፈጸም ሙሉ ዝግጁ ነኝ) ብሎ ይጣራል፡፡ ከሰማይ የሆነ ተጣሪ ደግሞ፣ ‹ለብበይከ ወሰዕደይከ (አላህ ሀጅህን ደጋግሞ ተቀበለህ)፤ ስንቅህ በሀቅ ተሰርቶ ከተገኘ ገንዘብ የተሰናዳ (ሀላል) ነው፤ መጓጓዣህ በሀቅ ተሰርተ ከተገኘ ገንዘብ የተዘጋጀ ነው፤ ሀጅህ ተቀባይነት ያለው እንጅ፣ ወንጀል ጎታች አይደለም› ብሎ ይጣራል (ጥሪውን በጥሪ ይመልሳል)፡

፡ በመጥፎ ገንዘቡ ሀጅ ለማድረግ (ከቤቱ) ሲወጣና ከመጓጓዣው መወጣጫ እርካብ ላይ እግሩን ሲያሳርፍ ደግሞ፣ ‹ለብበይክ አልላሁምመ ለብበይክ› (አላህ ሆይ! ትዕዛዝህን ለመፈጸም ሙሉ ዝግጁ ነኝ) ብሎ ይጣራል፡ ፡ ከሰማይ የሆነ ተጣሪ ደግሞ፣ ‹ላ ለብበይከ ወላ ሰዕደይከ› (አላህ ሀጅ ለማድረግ ያሳየኸውን ዝግጁነት አይቀበለውም)፤ ስንቅህ በሀቅ ተሰርቶ ከተገኘ ገንዘብ የተሰናዳ አይደለም፤ መጓጓዣህ በሀቅ ተሰርተ ከተገኘ ገንዘብ የተዘጋጀ አይደለም፤ ሀጅህ ተቀባይነት የሌለው ነው› ብሎ ይጣራል (ጥሪውን በጥሪ ይመልሳል)፡፡››

ሀጅ የሚያደርግ ሰው የሰውን ገንዘብ መጠየፍና እነሱን ከመጠየቅ መራቅ አለበት፡፡ የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ብለዋል፡-

- ‹‹ከልመና የተጠበቀውን ሰው አላህ ጥብቅ ያደርገዋል፡፡ እሱ ዘንድ ባለው ነገር የተብቃቃንም አላህ ያብቃቃዋል፡ ፡›› እንዲሁም፣

- ‹‹አንድ ሰው ሰዎችን ከመለመን ካልተወገደ፣ በዕለተ-ትንሳኤ ግንባሩ ላይ ቁራጭ ስጋ እንኳ የሌለው ሆኖ ይመጣል (ይቀሰቀሳል)፡፡›› (ቡኻሪ ዘግቦታል)፡፡

ሀጅና ዑምራ አድራጊው በሀጅና በዑምራ ስራዎቹ ከአላህ ዘንድ ምንዳንና መጪውን ዓለም (ዳረል አኺራን) ፈልጎ መፈጸም፣ በእነዚህ የላቁ ቦታዎች ላይም ደግሞ አላህ በሚወዳቸው ንግግሮችና ስራዎች ወደ አላህ መቃረብ አለበት፡፡ እሱ ከምንም በላይ መጠንቀቅ ያለበት በሀጅ ስራው ጠፊዋን ዱንያ ሽቶ ሀጅ ለማድረግ ተፍ ተፍ ማለትን ነው፡፡ ለይዩልኝና ለይስሙልኝ እንዲሁም ለጉራ ብሎ ሀጅ ከማድረግ መጠንቀቅም ይኖርበታል፡ ፡ እነዚህ ነገሮች እጅግ በጣም እኩይ ምኞቶች ሲሆኑ፣ ስራ ዋጋ ቢስና ተቀባይነት እንዳይኖረው አስተዋጽኦም አድራጊ ናቸው፡፡ አላህ በቁርኣኑ እንዲህ ይላል፡-

- ﴿مَن كَانَ يُرِيدُ ٱلۡحَيَوٰةَ ٱلدُّنۡيَا وَزِينَتَهَا نُوَفِّ إِلَيۡهِمۡ أَعۡمَٰلَهُمۡ فِيهَا وَهُمۡ فِيهَا لَا يُبۡخَسُونَ ١٥ أُوْلَٰٓئِكَ ٱلَّذِينَ لَيۡسَ لَهُمۡ فِي ٱلۡأٓخِرَةِ إِلَّا ٱلنَّارُۖ وَحَبِطَ مَا صَنَعُواْ فِيهَا وَبَٰطِلٞ مَّا كَانُواْ يَعۡمَلُونَ ١٦﴾

‹‹ቅርቢቱን ህይወትና ጌጧን የሚሹ የሆኑትን ሰዎች ስራዎቻቸውን (ምንዳዉን) በእርሷ ውስጥ ወደ እነሱ እንሞላላቸዋለን፡፡ እነሱም በእርሷ ውስጥ ምንም አይጎድልባቸውም፡፡ እነዚያ እነርሱ በመጨረሻይቱ ዓለም ለእነሱ ከእሳት በቀር የሌላቸው ናቸው፡፡ የሰሩትም ስራ በእርሷ ውስጥ ተበላሸ፡፡ (በቅርቢቱ ዓለም) ይሰሩት የነበሩትም በጎ ስራ ብልሹ ነው፡፡›› (ሁድ፣ 16-15)፡፡

በሌላ የቁርኣን አንቀጽ አላህ፣

- ﴿مَّن كَانَ يُرِيدُ ٱلۡعَاجِلَةَ عَجَّلۡنَا لَهُۥ فِيهَا مَا نَشَآءُ لِمَن نُّرِيدُ ثُمَّ جَعَلۡنَا لَهُۥ جَهَنَّمَ يَصۡلَىٰهَا مَذۡمُومٗا مَّدۡحُورٗا ١٨ وَمَنۡ أَرَادَ ٱلۡأٓخِرَةَ وَسَعَىٰ لَهَا سَعۡيَهَا وَهُوَ مُؤۡمِنٞ فَأُوْلَٰٓئِكَ كَانَ سَعۡيُهُم مَّشۡكُورٗا ١٩﴾

‹‹ቸኳይቱን ዓለም (በስራው) የሚፈልግ ሰው ለእርሱ በእርሷ ውስጥ የሻነውን (ጸጋ) ለምንሻው ሰው እናስቸኩልለታለን፡፡ ከእዚያም ለእርሱ ገሀነምን (መኖሪያ) አድርገንለታል፡፡ ተወቃሽ፣ ብራሪ ሆኖ ይገባታል፡፡ መጨረሻይቱንም ዓለም የፈለገ ሰው እርሱ አማኝ ሆኖ ለእርሷ (ተገቢ) ስራዋን የሰራው ሰው እነዚህ ስራቸው የተመሰገነ ይሆናል›› (አል-ኢስራእ፣ 18-19) ይላል፡፡

ከአላህ መልዕክተኛ እንደተረጋገጠው፣ አላህ (በሀዲሰል ቁድስ) እንዲህ ይላል፡-

- ‹‹ጥራት የተገባው አላህ እንዲህ አለ፡- ‹እኔ ከመጋራት የተብቃቃሁኝ ነኝ፡፡ አንድ ሰው በሰራው ስራ ላይ ሌላን አካል ከእኔ ጋር ካጋራ፣ እሱንና ሺርኩን እተውለታለሁ›፡፡ ›› (ሙስሊም ዘግቦታል)፡፡

በተጨማሪም ሀጅ የሚያደርግ ሰው መንገድ ሲገባ ምርጥ የሆኑትን አላህን የሚታዘዙ፣ የሚፈሩና የዲን ዕውቀት ያላቸውን ሰዎች መጎዳኘት ያስፈልገዋል፡፡ በአንጻሩ ቂላቂሎችንና አፈንጋጮችን ከመጎዳኘት መጠንቀቅ ይኖርበታል፡፡ እግረ መንገዱንም ኢስላም ስለ ሀጅና ስለ ዑምራ ያስተማረውን ነገር መማር ይኖርበታል፡፡ በጉዳዩም ላይ ግንዛቤ ሊኖረው ይገባል፡፡ የሚሰራውን ስራ በቅጡ ያውቀው ዘንድ በጉዳዩ ላይ ግር ያለውን ነጥብ መጠየቅ ይገባዋል፡፡

ጉዞ ለመጀመር መጓጓዣ ላይ ማለትም እንስሳት፣ መኪና፣ አየር ላይ ወይም ሌሎች መጓጓዣዎች ላይ ከወጣ ጥራትና ምስጋና የተገባውን አላህን ስሙን ማውሳት ይወደድለታል፡፡ ከዚያም ሶስት ጊዜ፣ ‹‹አላሁ አክበር›› ይላል፡፡ ከዚያም እንዲህ ይላል፡-

- ﴿سُبۡحَٰنَ ٱلَّذِي سَخَّرَ لَنَا هَٰذَا وَمَا كُنَّا لَهُۥ مُقۡرِنِينَ ١٣ وَإِنَّآ إِلَىٰ رَبِّنَا لَمُنقَلِبُونَ ١٤﴾

‹‹ሱብሃነልለዚ ሰኸረለና ሃዛ ወማኩንና ለሁ ሙቅሪኒነ፤ ወኢንና ኢላ ረብቢና ለሙንቀሊቡን›› (አዝ-ዙኽሩፍ፣ -13 14)፡፡ (ትርጉም ‹‹ ... ያ ይህንን የማንችለው ስንሆን፣ ለእኛ ያገራልን ጌታ ጥራት ይገባው፡፡ እኛም በእርግጥ ወደ ጌታችን ተመላሾች ነን (እንድትሉ)፡፡››)

ይህንንም ተጨማሪ ዱዓእ ይላል፡-

- « ሱብሃነልለዚ ሰኸረለና ሃዛ ወማኩንና ለሁ ሙቅሪኒነ፤ ወኢንና ኢላ ረብቢና ለሙንቀሊቡን፤

- «اللهم إِنا نسئلك في سفرنا هذا البر والتقوي ومن العمل ما ترضي اللهم هون علينا سفرنا هذا وطوي عنا بعده اللهم انت الصاحب في السفر والخليفة في الاهل اللهم اني أعوذبك من وعثاء السفر وكابة المنظر وسوء المنقلب في المال والاهل»

  አልላሁምመ ኢንና ነስአሉከ ፊ ሰፈሪና ሃዛል ቢርረ ወትተቅዋ፤ ወሚነል ዐመሊ ማ ተርዷ፤ አልላሁምመ ሀውዊን ዐለይና ሰፈረና ሃዛ፤ ወጥዊ ዐንና ቡዕደሁ፤ አላልሁምመ አንተስሳሂቡ ፊስሰፈሪ፤ ወልኸሊፈቱ ፊል አህሊ፤ አልላሁምመ ኢንኒ አዑዙ ቢከ ሚን ወዕሣኢስሰፈሪ፤ ወከኣበቲል ሙንዞሪ፤ ወሱኢል ሙንቀለቢ ፊልማሊ ወልአህሊ፡፡» (ትርጉም፡-ያ ይህንን የማንችለው ስንሆን ለእኛ ያገራልን ጌታ ጥራት ይገባው፡፡ እኛም በእርግጥ ወደ ጌታችን ተመላሾች ነን (እንድትሉ)፡፡ አላህ ሆይ! እኛ በመንገዳችን መልካምን መስራትን፣ አንተን መፍራትንና የምትወደውን ስራ መስራትን - እንድትገጥመን እንጠይቀሃለን፡፡ አላህ ሆይ! ይህን መንገዳችንን ገር አድርግልን፡ ፡ ሩቁንም አሳጥርልን፡፡ አላህ ሆይ! አንተ በመንገዳችን ጓዳችን ነህ፡፡ ለቤተሰቦቻችን ደግሞ ምትክ - ጠባቂ- ነህ፡፡ አላህ ሆይ! እኔ ከጉዞ ውጣ ውረድ፣ ከአመለካከት ለውጥና በገንዘብና በቤተሰብ ላይ መጥፎ ነገር ተከስቶ (ወደ ቤቴ) ከመመለስ በአንተ እጠበቃለሁ፡፡) (ሙስሊም፣ ኢማሙ አህመድና ቲርሚዚ ዘግበውታል፡፡) ይህ ሀዲስ ትክክለኛ ለመሆኑ ሙስሊም ኢብኑ ዑመርን ጠቅሶ ዘግቦታል፡፡

ተጓዥ በመንገድ ላይ ዚክር፣ ዱዓእ፣ ኢስቲግፋር፣ አላህን በዱዓ መማጸንን፣ መልዕክቱን እያስተነተነ ቁርኣን መቅራትን (ማንበብን) ማብዛትና የህብረት ሶላትንም ጠብቆ መስገድ ላይ ትኩረት ማድረግ

አለበት፡፡ ምላሱን ከፍሬ ፈርስኪ ወሬ መጠበቅ፣ ከማይመለከተው ነገር ጣልቃ ከመግባትና በቀልድ ድንበር ከማለፍ ራሱን መጠበቅ አለበት፡፡ እንዲሁም ምላሱን ሀሰት ከመናገር፣ ከሀሜት፣ ነገርን ወዲያና ወዲህ ከመውሰድ፣ በማንኛውም ሰው፣ በጓደኛውና በሌሎች ሙስሊም ወንድሞቹ ላይ ከመሳለቅም ምላሱን መጠበቅ ይኖርበታል፡፡

ለጓደኞቹ መልካም ነገርን መስራትን፣ እነሱን ከመተናኮል መራቅን፣ በተቻለ መጠን ጥበብ በተሞላበት መንገድና በመልካም ግሳጼ እነሱን በመልካም ነገር ከማዘዝና ከመጥፎ ነገር መከልከልን መፈጸም ይገባዋል፡፡

# ሀጅ አድራጊው «ሚቃት» ላይ ሲደርስ የሚሰራው ስራ

በሀዲስ እንደተዘገበው፣ ሀጅ አድራጊው «ሚቃት» (ሀጅ ወይም ዑምራ ለማድረግ ኢህራም የሚደረግባቸው ቦታዎች ናቸው፡፡) ላይ ሲደርስ ገላውን መታጠብና ሽቶ መጠቀም (መቀባት) ይወደድለታል፡፡ የአላህ መልዕክተኛ ኢህራም ሲያደርጉ ልቅ ካልሆነ ልብስ ራሳቸውን አርቀው ገላቸውን ይታጠቡ ነበር፡፡ ቡኻሪና ሙስሊም በትክክለኛ ዘገባቸው ዓኢሻን ጠቅሰው እንደዘገቡት፣ ዓኢሻ እንዲህ ትላለች፡-

- «የአላህ መልዕክተኛ ኢህራም ሊያደርጉ ሲሉ ሽቶ እቀባቸዋለሁ፡፡ የሀጅን ስራ ጨርሰው ጦዋፍ ከማድረጋቸው በፊትም እንዲሁ ሽቶ እቀባቸዋለሁ፡፡»

የአላህ መልዕክተኛ፣ ዓኢሻ የወር አበባ ላይ እያለችና ለዑምራ ስራ አስባና ተዘጋጅታ (ሀርማ) እያለች ገላዋን እንድትታጠብና ለሀጅ ስራም እንድትሃርም አዘዋታል፡፡ እንዲሁም የአላህ መልዕክተኛ አስማእ ቢንቱ ዑመይስ ዙል ሁለይፋ ላይ በወለደችበት አጋጣሚ ገላዋን እንድትታጠብና በጨርቅ (ቁራጭ) ደሟን እንድትቆጣጠር፣ ከዚያም ኢህራም እንድታደርግ አዘዋታል፡፡ የአላህ መልዕክተኛ ዓኢሻንና አስማእን እንዳዘዙት ሁሉ፣ አንድ ሴት ወደ «ሚቃት» ከደረሰችና በአጋጣሚም የወር አበባ ደም ከተከሰተባት ወይም የወሊድ ደም ላይ ከሆነች ገላዋን ታጥባ ከሰዎቹ ጋር ኢህራም ማድረግና ካዕባ ላይ አንድ ሀጅ የሚያደርግ ሰው የሚያደርገውን ተግባር መፈጸም እንዳለበት መማር ይቻላል፡፡ በዚህ ሁኔታ የማትፈጽመው ጦዋፍ ማድረግን ብቻ ነው፡፡

ኢህራም ማድረግ የፈለገ ሰው ቀድሞ ቀመሱንና ጥፍሩን ማሳጠር፣ ብልቱ አካባቢ ያለውንና የብብቱን ጸጉር ማስወገድ ይወደድለታል፡፡ በዚህም አስፈላጊ በሆነበት ጊዜ ጸጉሩን ማስወገድ ይቻለዋል፡፡ ከኢህራም በኋላ ጸጉሩን መቁረጥ (መላጩት) ክልክል ስለሆነ፣ በዚህ ጊዜ ይህን ማድረጉ ተገቢ ነው፡፡ የአላህ መልዕክተኛ በሁሉም ጊዜያት እነዚህን ነገሮች በቅጡ መጠበቅን (መላጨትንና ማሳጠርን) አስተምረዋል፡፡ ሙስሊም አቢ ሁረይራን ጠቅሶ እንደዘገበው፣ የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ አሉ፡-

- ‹‹ያልተበረዙ ጤናማ ተፈጥሯዊ መልኮች አምስት ናቸው፡፡ (እነሱም) መገረዝ፣ የብልት አካባቢን ጸጉር ማስወገድ (መላጨት)፣ ቀድሞ ቀመስን ማሳጠር፣ ጥፍርን መቁረጥና የብብት ጸጉርን ማስወገድ ናቸው፡፡››

በትክክለኛ የሙስሊም ዘገባ አነስ እንዲህ አስተላልፈዋል፡-

- ‹‹(የአላህ መልዕክተኛ) ለእኛ ቀድሞ ቀመስን የምናሳጥርበትን፣ ጥፍራችንን የምንቆርጥበትንና የብብት ጸጉርን የምናስወግድበትን ጊዜ አድርገውልናል፡፡››

በሌላ የነሳኢ ዘገባ ደግሞ፣

- ‹‹ለእኛ ቀድሞ ቀመስን የምናሳጥርበት፣ ጥፍራችንን የምንቆርጥበትንና የብብት ጸጉርን የምናስወግድበትን ጊዜ ወስነውልናል፡፡›› ሲሉ፣ ይህንኑ መረጃ ደግሞ አህመድ፣ አቡ ዳውድና ቲርሚዚ፣ ነሳኢ በዘገበበት መንገድ ዘግበውታል፡፡

ይሁን እንጂ በኢህራም ወቅት የወንድም ሆነ የሴት የራስ ጸጉርን መቁረጥ አልተደነገገም፡፡ ጺምን ግን በማንኛውም ወቅት (በሀጅና ከሀጅ ውጪ) መላጨትም ሆነ መቁረጥ አይፈቀድም፡፡ እንዲያውም ጺምን ማሳደግና ማብዛቱ ነው ግዴታ የሚሆነው፡፡

ቡኻሪና ሙስሊም በትክክለኛ ዘገባቸው ኢብኑ ዑመርን ጠቅሰው እንደዘገቡት፣ የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ አሉ፡-

- «ጣኦት አምላኪዎችን ተቃረኑ! ጺማችሁን አሳድጉ፤ ቀድሞ ቀመሳችሁን አሳጥሩ፡፡»

ሙስሊም አቢ ሁረይራን ጠቅሶ እንደዘገበው፣ የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ አሉ፡-

- «ቀድሞ ቀመስን አሳጥሩ፤ ጺምን ልቀቁት (አሳድጉት)፤ እሳት አምላኪዎችን (መጁሶችን) ተጻረሩ፡፡»

ብዙ ሰዎች ሱናውን ተጻረው፣ ኢስላም ስለ ጺም ያስተማረውን አስተምህሮ ሊዋጉ በመቻላቸው በዚህ ዘመን መከራ በርክቷል፡ ፡ ከሃዲዎችንና ሴቶችን መመሳሰልን በመውደዳቸውም ኢስላምን እየተዋጉት ይገኛሉ፡፡ በተለይም አስተማሪዎችና ተማሪዎች በዚሁ ችግር ተዘፍቀው ይገኛሉ፡፡

እኛ ለአላህ ነን፤ ወደ እሱ ተመላሾች ነን፡፡ ምንም እንኳ ብዙዎቹ ችላ ቢሉትም አላህ ሙስሊሞችን ሱናውን መሰረት አድርገው እንዲሰሩና በእሱም ላይ ጽናት እንዲኖራቸው፣ እንዲሁም ወደ እሱም ዳዕዋ እንዲያደርጉና ቅኑን መንገድ እንዲመራቸው አላህን እንጠይቀዋለን፡፡ አላህ በቂያችን ነው፡፡ እሱ ምን ያምር መጠጊያ ነው! ብልሃትና ሀይል የእሱ እንጅ የማንም አይደሉም፡፡ እሱ ከፍ ያለና ታላቅ ነው፡፡

ከዚያም ወንዱ የኢህራም ልብስ (ኩታና ሸርጥ) ይለብሳል፡፡ ሁለቱ ልብሶች ንጹህና ነጫጭ ቢሆኑና ሸፍን ባልሆነ ጫማም ኢህራም ቢያደርግ ይወደዳል፡፡ የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ብለዋልና፡-

- «አንድኛችሁ በሸርጥ፣ በኩታና ሸፍን ባልሆነ ጫማ ኢህራም ያድርግ፡፡» (ኢማሙ አህመድ የዘገበው)፡፡

ሴት ግን ልብሱ ጥቁርም ይሁን አረንጓዴ ወይም ከእነዚህ ውጪ ቀለሙ ሌላ በሆነ በፈለገችው ልብስ ኢህራም ማድረግ ይፈቀድላታል፡፡ ይሁን እንጅ በአለባበሷ ከወንዶች ጋር ከመመሳሰል መጠንቀቅ ይኖርባታል፡፡ እንዲሁም በኢህራም ጊዜ በፊት መሸፈኛ ልብስ ፊቷን መሸፈን (ኒቃብ መልበስ)፣ የእጅ ጓንት ማድረግ አይፈቀድላትም፡፡ ምክንያቱም የአላህ መልዕክተኛ ኢህራም ያደረገች ሴት ኒቃብና ጓንት እንዳትለብስ ከልክለዋልና፡፡

ቢሆንም ግን ‹‹ኒቃብ›› ባልሆነ ልብስ ፊቷን መሸፈንና መዳፎቿንም ጓንት ባልሆነ ልብስ መሸፈን ይኖርባታል፡፡ አንዳንድ ሰዎች፣ ‹‹በኢህራም ወቅት ሴት አረንጓዴ ወይም ጥቁር ልብስ እንጅ ሌላ መልበስ የለባትም›› ብለው የሚያንጸባርቁት አቋም፣ ኢስላማዊ ዕውቀትን መሰረት ያደረገ አይደለም፡፡

አንድ ሰው ገላውን ታጥቦ ከጨረሰ፣ ሌላን ተጨማሪ ንጽህና ከጠበቀ እንዲሁም የኢህራም ልብስ ከለበሰ በኋላ ሀጅ ወይም ዑምራ ሊያደርግ እንደፈለገ በልቡ ያስባል፡፡ የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ብለዋል፡-

- ‹‹ስራዎች በኒያዎች ነው ተቀባይነት የሚኖራቸው፡፡ እያንዳንዱ ሰውም ባሰበው ልክ ያገኛል፡፡›› (ቡኻሪ የዘገበው)፡፡

አንድ ሰው በዚህ አጋጣሚ በልቡ ያሳደረውን በንግግር ሊገልጸው በኢስላም ተደንግጓል፡፡ ለምሳሌ፡- ሀሳቡ ሀጅ ማድረግ ከሆነ፣ ‹‹ለብበይክ ሀጀን›› ወይም ‹‹አልላሁምመ ለብበይከ ሀጀን›› ይላል፡፡ የአላህ መልዕክተኛ በዚህ መንገድ ነው የፈጸሙት፡፡ ሀጅንና ዑምራን በአንድ ላይ አጣምሮ ማድረግ ካሰበ፣ ‹‹አልላሁምመ ለበይክ ዑምረተን ወሀጀን›› ይላል፡፡ ሀሳቡን በንግግር መግለጹ እጅግ በጣም የተሻለ የሚሆነው ከእንስሳት ጀርባ፣ ከመኪና ላይ ወይም ከሌላ የመጓጓዣ ላይ ሲወጣ

ነው፡፡ ምክንያቱም የአላህ መልዕክተኛ ሃሳባቸውን በንግግር የገለጹት፣ ከመጓጓዣቸው ጀርባ ላይ ከወጡ በኋላ ነውና፡ ፡ ከዚያም ወደ ‹‹ሚቃት›› (ኢህራም ወደሚደረግበት ቦታ) ጉዞ ያደርጋል፡፡ ይህ እንግዲህ እጅግ በጣም ትክክለኛው የሊቃውንት አቋም ነው፡፡

ይሁን እንጅ ከአላህ መልዕክተኛ እንደተገኘው በልብ የታሰበውን ነገር በንግግር የሚገለጸው፣ በኢህራም አጋጣሚ እንጅ፣ በሌላ አጋጣሚ መፈጸም አለበት የሚል ኢስላማዊ መልዕክት የለም፡ ፡ በሶላትና በጠዋፍ እንዲሁም በሌሎች ቦታዎች ላይ በልብ የታሰበውን በንግግር መግለጽ አያስፈልግም፡፡ ለምሳሌ፡- አንድ ሰው፣ ‹‹ነወይቱ ከዛ ወከዛ››፣ ‹‹ነወይቱ አን አጡፈ ከዛ›› ብሎ በንግግር ሊገልጽ አይገባውም፡፡ እንዲያውም በልብ የታሰበውን ነገር በንግግር መግለጹ አዲስ መጤ ዒባዳ (ቢድዓ) ነው፡፡ ድምጽን ከፍ አድርጎ ደግሞ መግለጹ እጅግ በጣም አስቀያሚና ወንጀል ነው፡፡ ዒባዳን ለመፈጸም (እላይ ከተወሳው ውጪ) ሃሳብን በንግግር መግለጽ በኢስላም የተደነገገ ነገር ቢሆን ኖሮ፣ የአላህ መልዕክተኛ በተግባር ወይም በንግግር ይገልጹትና ያብራሩት ነበር፡፡ ለተግባራዊነቱም ቀደምት ደጋግ ሙስሊሞች ቀዳሚ ነበሩ፡ ፡ በመሆኑም ድርጊቱ ከነቢዩና ከባልደረቦቻቸውም ያልተገኘ በመሆኑ ጉዳዩ አዲስ መጤ ዒባዳ (ቢድዓ) መሆኑ ታውቋል፡፡ በእርግጥም የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ይላሉ፡-

- ‹‹የነገሮች መጥፎነታቸው፣ አዲስ መጤ ዒባዳ መሆናቸው ነው፡፡ ሁሉም አዲስ መጤ ዒባዳ ደግሞ ጥመት ነው፡፡›› (ሙስሊም የዘገበው)፡፡

የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ብለዋል፡-

- ‹‹በዚህ ጉዳያችን (በኢስላም) የሌለን አዲስ ነገር ያመጣ ሰው፣ ያመጣው (አዲስ) ነገር ተመላሽ ነው፡፡›› (ቡኻሪና ሙስሊም)፡፡

በሌላ የሙስሊም ዘገባ የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ብለዋል፡-

- ‹‹የእኛ ትዕዛዝ የሌለበትን ስራ የሰራ ሰው፣ ስራው ተመላሽ ነው፡፡››

# የኢህራም መፈጸሚያ ቦታቸው (ሚቃት) እና ወሰናቸው

አምስቱ የኢህራም መፈጸሚያ ቦታዎች፡-

አንደኛ. ዙል ሁለይፋ፡- ይህ የኢህራም ማድረጊያ ቦታ መዲና አካባቢ ላሉ ሰዎች የሚያገለግል ሲሆን፣ ዛሬ ሰዎች ‹‹አብያር ዓሊ›› ብለው ይጠሩታል፡፡

ሁለተኛ፡- ጁህፋ፡- ይህ የኢህራም ማድረጊያ ቦታ ሻም አካባቢ ለሚኖሩ ሰዎች የሚያገለግል ነው፡፡ ዛሬ ጁህፋ ህልውናው ያከተመለት መንደር ሲሆን፣ ‹‹ራቢግ›› ከሚባል ቦታ ቀጥሎ የሚገኝ ቦታ ነው፡፡ ዛሬ ሰዎች ራቢግ ላይ ኢህራም ያደርጋሉ፡፡ በራቢግ ኢህራም ያደረገ ሰው፣ ጁህፋ ላይ ኢህራም እንዳደረገ ነው፡፡ ምክንያቱም ራቢግ ከጁህፋ ብዙም አይርቅምና ነው፡፡

ሶስተኛ. ቀርነል መናዚል፡- ይህ የኢህራም ቦታ ነጅድ አካባቢ ለሚኖሩ ሰዎች የሚያገለግል ቦታ ነው፡፡ ዛሬ ይህ ቦታ ‹‹አስሰይል›› ተብሎ ይታወቃል፡፡

አራተኛ. የለምለም፡- ይህ የኢህራም ቦታ ደግሞ የመን አካባቢ ለሚኖሩ ሰዎች ኢህራም ማድረጊያ ሆኖ የሚያገለግል ቦታ ነው፡፡

አምስተኛ. ዛቱ ዒርቅ፡- ይህ የኢህራም ቦታ ኢራቅ አካባቢ ለሚኖሩ ሰዎች ኢህራም ማድረጊያ ሆኖ የሚያገለግል ቦታ ነው፡፡

እነዚህን የጠቀስናቸውን የኢህራም መፈጸሚያ ቦታዎች የአላህ መልእክተኛ ናቸው የኢህራም ማድረጊያ ቦታዎች ያደረጓቸው፡፡ በእነዚህ የኢህራም ቦታዎች አካባቢ ኗሪ ያልሆነና በእነሱ አካባቢ የሚያልፍ ከሆነ፣ ቦታዎቹ ላይ ኢህራም ያደርጋል፡፡ ኢህራምም የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡ አንድ ሰው ሀጅ ወይም ዑምራ ለማድረግ አስቦ ምናልባት በየብስ፣ በአየር (ወይም በሌላ መንገድ)

በእነሱ ላይ ሲያልፍ በእነሱ ላይ ኢህራም ካላደረገ፣ ስህተት ፈጽሟል ያስብላል፡፡

እላይ ያወሳነው ሃሳብ በቀጣዩ የአላህ መልዕክተኛ ንግግር ውስጥ ስለሚጠቃለል ነው ሃሳቡን ያንጸባረቅ ነው፡፡ የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ብለዋል፡-

- «እነሱ ለእነሱ ናቸው፡፡ የአካባቢውም ሰው ያልሆነና ሀጅና ዑምራ ለማድረግ ፈልጎ በእነሱ ላይ ካለፈም፣ በእነሱ ላይ ኢህራም ያደርጋል፡፡» (ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል፡፡)

ሀጅ ወይም ዑምራ ማድረግ አስቦ በአየር ወደ መካ የሚሄድ ሰው ገላውን መታጠብና ሌሎች አስፈላጊ ነገሮችን አየር ላይ ከመውጣቱ በፊት ማከናወን ይኖርበታል፡፡ ኢህራም ማድረጊያው ላይ ቀረብ ሲል ደግሞ ለዚህ ተግባር የሚውለን ልብስ (ሽርጡንና ኩታውን) ይለብሳል፡፡ ጊዜው በቂ (ሰፊ) ከሆነ፣ በዑምራ ጊዜ የሚባለውን (ተልቢያ) ይላል፡፡ ነገር ግን ጊዜው ጠባብ ከሆነ ደግሞ በሀጅ ጊዜ የሚባለውን (ተልቢያ) ይላል፡፡ ለዚህ ተግባር የሚውለን ልብስ ከመጓጓዣው ላይ ከመውጣቱ (ከመሳፈሩ) በፊት ወይም ኢህራም ከማድረጊያው ቦታ ሳይቀርብ ቢለብስ ችግር የለውም፡፡ ነገር ግን ለኢህራም ማድረጊያ ቦታው ትይዩ ካልሆነ ወይም ካልቀረበ በቀር፣ ወደ ሀጅና ወደ ዑምራ ስራ መግባቱን በማሰብ የሚባለውን ተልቢያ ማለት በዚህ ጊዜ አያስፈልግም፡ ፡ ምክንያቱም የአላህ መልእክተኛ ኢህራም ያደረጉት ኢህራም ማድረጊያ ቦታ ላይ ብቻ ነውና፡፡ በሌሎቹ ኢስላማዊ ጉዳዮች ላይ የአላህን መልእክተኛ መከተል እንዳለብን ሁሉ፣ በዚህም ህዝበ-ሙስሊሙ መንገዳቸውን መከተል አለበት፡፡ ምክንያቱም አላህ በቁርኣን እንዲህ ይላል፡-

- ﴿ لَّقَدْ كَانَ لَكُمْ فِي رَسُولِ ٱللَّهِ أُسْوَةٌ حَسَنَةٌ لِّمَن كَانَ يَرْجُواْ ٱللَّهَ

وَٱلۡيَوۡمَ ٱلۡأٓخِرَ وَذَكَرَ ٱللَّهَ كَثِيرٗا ﴿٢١﴾

‹‹ለእናንተ አላህንና የመጨረሻውን ቀን የሚከጅል ለሆነው ሰው፣ አላህንም በብዙ ለሚያወሳ፣ በአላህ መልዕክተኛ መልካም መከተል አላችሁ›› (አል-አህዛብ፣ 21)፡፡

የአላህ መልእክተኛ በመሰናበቻው ሀጅ ላይ እንዲህ ብለዋል፡-

- ‹‹የሀጅ አፈጻጸም ስርዓቱን ከእኔ ውሰዱ፡፡››

አንድ ሰው ሀጅ ወይም ዑምራ ማድረግ ሳይፈልግ ነገር ግን ነጋዴ፣ እንጨት ለቃሚ፣ ፖስተኛ ወይም ሌላ ተግባር የሚፈጽም ሆኖ ወደ መካ ቢገባ፣ በራሱ ፈቃድ ኢህራም ቢያደርግ እንጅ፣ ወደ መካ እንደገባ ኢህራም ማድረግ አይጠበቅበትም፡፡ ምክንያቱም ቀደም ብሎ በተጠቀሰው ሀዲስ የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ብለዋልና፡-

- ‹‹እነሱ ለእነሱ ናቸው፡፡ የአካባቢውም ሰው ያልሆነና ሀጅና ዑምራ ለማድረግ ፈልጎ በእነሱ ላይ ካለፈም፣ በእነሱ ላይ ኢህራም ያደርጋል፡፡››

ከዚህ ሀዲስ እንደምንረዳው ኢህራም በሚደረግባቸው ቦታዎች ላይ ሀጅ ወይም ዑምራ ማድረግ ሳይፈልግ፣ ወደ መካ የገባ ሁሉ የግዴታ ኢህራም ማድረግ አይጠበቅበትም፡፡ አላህ ይህን ነገር ለባሪያው እዝነት ሲል ያደረገው ነገር ነው፡፡ በዚህ ነገር እሱ ምስጋናና ውዳሴ ይገባዋል፡፡

እላይ ያነሳነውን ሃሳብ የሚያጠናክር ሌላ ነጥብ ደግሞ፣ የአላህ መልዕክተኛ የመካ ከተማን ሲከፍቱ ኢህራም አለማድረጋቸው ነው፡፡ እንዲያውም ከጭንቅላታቸው ላይ የብረት ቆብ ደፍተው ነበር ወደ መካ የገቡት፡፡ ይህ ማለት ደግሞ የአላህ መልዕክተኛ በጊዜው ሀጅ ወይም ዑምራ ለማድረግ አለመፈለጋቸውን ነው የሚያመላክተው፡፡ በሌላ መልኩ የአላህ መልዕክተኛ በጊዜው የፈለጉት መካን መክፈትና በውስጧ ያለውን የባዕድ አምልኮ

ማስወገድ ነው፡፡

ይሁን እንጅ መኖሪያው ከአምስቱ የኢህራም ማድረጊያ ቦታዎች ውጪ የሆነ ሰው፣ ለምሳሌ የጂዳ፣ የኡሙ ሰለም፣ የበህራ፣ የሸሽራኢዕ፣ የቢድር፣ የመስቱራና የመሳሰሉት አካባቢ ነዋሪ የግዴታ ከአምስቱ የኢህራም ማድረጊያ ቦታዎች ወደ አንዱ መሄድ አይጠበቅበትም፡፡ መኖሪያው በራሱ እንደ ኢህራም ቦታ ነው የሚቆጠረው፡፡ ስለሆነም ባለበት ቦታ ለሀጅ ወይም ለዑምራ ኢህራም ለማድረግ ይችላል፡፡

ነገር ግን አንድ ሰው ከኢህራም ማድረጊያ ቦታዎች ውጪ ሌላ መኖሪያ የሚኖረው ከሆነ፣ ሁለት አማራጭ ይኖረዋል፡፡ ከፈለገ ኢህራም ማድረጊያ ቦታዎች ላይ ኢህራም ያደርጋል፡፡ ወይም ደግሞ ለቤቱና ለመካ ቅርብ ወደ ሆነው የኢህራም ማድረጊያ ቦታ ላይ ኢህራም ሊያደርግ ይችላል፡፡ ይህ ጉዳይ በቀጣዩ አጠቃላይ የአላህ መልዕክተኛ መልዕክት ስር ሊጠቃለል ይችላል፡፡ የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ብለዋል፡-

- «ከእነሱ አካባቢ ውጪ የሆነው ሰው፣ ለሀጅ ወይም ለዑምራ ኢህራም የሚያደርግበት - ተልቢያ የሚያደርግበት- እዛው እቤቱ አካባቢ ነው፡፡ ሌላው ቀርቶ የመካ ነዋሪዎች ኢህራም የሚያደርጉት መካ ላይ ነው፡፡» (ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል)፡፡

ይሁን እንጅ ሀረም ውስጥ ሆኖ ዑምራ ማድረግ የፈለገ ሰው፣ መጀመሪያ ከሀረም ውጪ መውጣት ይጠበቅበታል፡፡ ከዚያም ለዑምራ ኢህራም ያደርጋል፡፡ ምክንያቱም ዓኢሻ ዑምራ ለማድረግ ስትፈልግ፣ የአላህ መልዕክተኛ ወንድሟን አብዱረህማንን ከሀረም ውጪ ይዟት እንድሄድና እዛው ኢህራም እንድታደርግ አዘዋታልና፡ ፡ ይህ ማለት ደግሞ ዑምራ ማድረግ የሚፈልግ ሰው ሀረም ውስጥ ኢህራም ማድረግ አይችልም ማለት ነው፡፡ ኢህራም የሚያደርገው ከሀረም ውጪ እንጅ፡፡

ይህ ሀዲስ ቀደም ብሎ በኢብኑ ዐባስ የተላለፈውን ሀዲስ ዉሱን የሚያደርግ ሲሆን፣ የአላህ መልዕክተኛ፣ «ሌላው ቀርቶ የመካ ሰዎች መካ ላይ (ለኢህራም) ተልቢያ ያደርጋሉ» የሚለው የነቢዩ ንግግር ሃሳቡ ሀጅን እንጅ፣ ዑምራን የሚመለከት አይደለም፡ ፡ ዑምራ ላይ ኢህራም ማድረግ የሚቻል ቢሆን ኖሮ፣ የአላህ መልዕክተኛ ዓኢሻ ሀረም ላይ ኢህራም እንድታደርግ ይፈቅዱላት ነበር፡፡ ከሀረም ውጪ እንድትሄድም አያደርጓትም ነበር፡፡ ይህ ደግሞ ግልጽ ጉዳይ ነው፡፡ አላህ ይዘንላቸውና ይህ ነጥብ የብዙሃኑ ሙስሊም ሊቃውንት አቋምም ነው፡፡ ለአማኞች ደግሞ ሁሉንም አቅፎ የሚይዝላቸው ነጥብ ይሄው ነው፡፡ ምክንያቱም ሁለቱንም ሀዲሶች አካቶ በመያዙና በሁለቱም ነቢያዊ መልዕክቶች የመስራት ዕድልንም ስለሚሰጥ ነው፡፡ መልካሙንም ነገር አጎናጻፊው አላህ ነው፡፡

አንዳንድ ሰዎች ሀጅ ካደረጉ በኋላ ከተንዒም ወይም ከጀዕራና ወይም ከሌላ ቦታ ላይ ዑምራ ማብዛታቸው፣ ለሚያደርጉት ዑምራ ኢስላማዊ ማስረጃ የለውም፡፡ እንዲያውም ማስረጃዎቹ የሚያመለክቱት ከሀጅ በኋላ ዑምራ አለማድረግን ነው፡፡ ምክንያቱም የአላህ መልዕክተኛና ባልደረቦቻቸው (ረ. ዐ) ከሀጅ በኋላ ዑምራ  አላደረጉምና ነው፡፡ ምናልባት ዓኢሻ ዑምራ ያደረገችው፣ ከአላህ መልዕክተኛ ጋር ወደ መካ በገባችበት ጊዜ በወር አበባ ምክንያት ዑምራ ባለማድረጓ ነው፡፡ ስለሆነም መጀመሪያ፣ በመጀመሪያው ዑምራ ምትክ ሌላ ዑምራ ለማድረግ የአላህ መልዕክተኛን ፈቃድ ጠየቀች፡፡ የአላህ መልዕክተኛም ጥያቄዋን ተቀበሏት፡፡ በዚህም ጊዜ ሁለት ዑምራ የማድረግ ዕድል አገኘች፡፡

- አንደኛው ከሀጅ ጋር ያደረገችው ሲሆን፣
- ሁለተኛው ደግሞ ብቻዋን ያደረገችው ነው፡፡

ከቀረቡት ማስረጃዎች አንጻርና ለሙስሊሞች ጉዳዩን ሰፋ

ለማድረግ፣ እንደ ዓኢሻ ችግር የገጠመው ሰው ከሀጅ በኋላ ዑምራ ቢያደርግ ብዙም ችግር የለውም፡፡ ለነገሩ ሀጅ አድራጊዎች ሀጅ ካደረጉ በኋላ መካ ሲገቡ ካደረጉት ዑምራ ውጪ ሌላ ዑምራ ማድረጋቸው በብዙሃኑ ሙስሊም ላይ ችግር ይፈጥራል፡፡ ምክንያቱም ቅኑን መንገድ መጻረሩ እንዳለ ሆኖ፣ በሀጅ ጊዜ የሰዎች መጨናነቅ እንዲኖርና በዚህም ምክንያት ብዙ አደጋ እንዲከሰት አስተዋጽኦ ያደርጋል፡፡ መልካሙን ነገር አጎናጻፊው አላህ ነው፡፡

# ከሀጅ ወራት ውጪ ኢህራም ማድረጊያ ቦታዎች ላይ መድረስ

ከሀጅ ወራት ውጪ ኢህራም ማድረጊያ ቦታዎች (ወደ ሚቃት) የአደራረሱ ሁኔታ ሁለት ገጽታዎች አሉት፡፡

አንደኛው፡- ከሀጅ ወራት ውጪ በሆኑ ወቅቶች መድረስ ነው፡ ፡ ለምሳሌ በረመዳን፣ በሻዕባን፣ ወዘተ ሊደርስ ይችላል፡፡ በዚህ ሁኔታ ሱናው፣ አንድ ሰው በልቡ ዑምራ ማድረጉን ያስብና ሃሳቡን «ለብበይከ ዑምረተን» ወይም «አልላህምመ ለብበይከ ዑምረተን» በማለት ይገልጸዋል፡፡ ከዚያም ነቢዩ ተልቢያ ባደረጉበት መንገድ ማለትም፤

- لبيك اللهم لبيك لبيك لا شريك لا لك لبيك ان الحمد ونعمت لك والملك لا شريك لك

- «ለብበይከ አላሁምመ ለብበይክ፤ ለብበይክ ላሽሪከ ለከ ለብበይክ፤ ኢንነል ሐምደ ወንኒዕመተ ለከ፤ ወልሙልከ፤ ላሽሪከ ለከ» ይላል፡፡ (ትርጉም፡- ጥሪህን ተቀብያለሁ፤ አምላኬ ሆይ! ጥሪህን ተቀብያለሁ፡፡ ጥሪህን ተቀብያለሁ፤ ላንተ አጋር የለህም፤ ጥሪህን ተቀብያለሁ፤ ምስጋናና ጸጋ ላንተ ነው፤ ንግስናም ላንተ ነው፤ ላንተ አጋር የለህም፡፡)

ይህን ተልቢያና አላህን ማውሳት (ዚክር) በተደጋጋሚ ማለት ይጠበቅበታል፡፡

ካዕባ ሲደርስ ተልቢያውን ያቋርጣል፡፡ ከዚያም ካዕባን ሰባት ጊዜ ይዞራል፡፡ ከመቃመ ኢብራሂም ኋላ ላይም ሁለት ረከዓ ሶላት ይሰግዳል፡፡ ቀጥሎም ወደ ሶፋ በመሄድ በሶፋና በመርዋ መካከል ሰባት ጊዜ ይመላለሳል፡፡ ከዚያም ጸጉሩን ይላጨዋል ወይም

ያሳጥረዋል፡፡ በዚህም መንገድ ዑምራው ይጠናቀቃል፡፡ በዑምራ ጊዜም ገደብ የተጣሉበት ነገሮች ሁሉ አሁን ይነሳሉ (የተፈቀዱ ይሆናሉ)፡፡

ሁለተኛው፡- በሀጅ ወራት ማለትም በሸዋል፣ በዙል ቂዕዳና በመጀመሪያዎቹ የዙል ሂጃ አስር ቀናት ውስጥ ኢህራም ማድረጊያ ቦታዎች ላይ መድረስ ነው፡፡ በዚህ ጊዜ ሶስት ምርጫዎች ይኖራሉ፡፡ እነሱም ሀጅን ለብቻ፣ ዑምራን ለብቻ ማድረግና ሁለቱን (ማለትም ሀጅንና ዑምራን) አንድ ላይ አጣምሮ ማድረግ ነው፡፡ ምክንያቱም የአላህ መልዕክተኛ በዙልቂዕዳ ወር በመሰናበቻው ሀጅ ላይ ባልደረቦቻቸውን እነዚህን ሶስት አማራጮች አቅርበውላቸዋል፡፡

ይህ ከመሆኑ ጋር «ሀድይ» የሚያቀርበው የሌለው ሰው ሱናው መጀመሪያ ዑምራ ማድረግ ነው፡፡ ከዚያም ቀደም ብለን እንዳወሳነው ከሀጅ ወራት ውጪ ኢህራም ማድረጊያ አካባቢዎች የደረሰ ሰው የሚሰራውን ተግባር ይፈጽማል፡፡ ምክንያቱም የአላህ መልዕክተኛ ባልደረቦቻቸው ወደ መካ ለመግባት በቀረቡ ጊዜ፣ ኢህራማቸውን ዑምራ እንዲያደርጉ አዘዋቸዋል፡፡ ይህንንም መካ ላይ አረጋግጠውታል፡፡ በዚህም ጦዋፍና ሰዕይ አደረጉ፤ ጸጉራቸውንም አሳጠሩና ተፈቱ (ስራቸውን አጠናቀቁ)፡፡ ይህን ያደረጉት የአላህን መልዕክተኛ ትዕዛዝ ተግባራዊ ከማድረግ አንጻር ነው፡፡ ይህን ከማድረግ የተቆጠበው «ሀድይ» የያዘው ሰው ብቻ ነው፡፡ «ሀድይ» የያዘው ሰው የአላህ መልዕክተኛ እርድ እስከሚፈጸምበት ቀን (ዙልሂጃ አስረኛው ቀን) ድረስ እንዲቆይ ያዙት ነበር፡፡ ለነገሩ «ሀድይ» ለያዘው ሰው ሱናው፣ ሀጅንና ዑምራን በአንድ ላይ አጣምሮ ኢህራም ማድረጉ ነው፡፡ ምክንያቱም የአላህ መልዕክተኛ ሀድይ ይዘው በመጡበት ጊዜ ይህንኑ ነው ያደረጉት፡፡ ከባልደረቦቻቸው መካከልም ሀድይ የያዘውንና በዑምራ የሀረመውን፣ ከዑምራው ጋር ሀጅን ጨምሮ ተልቢያ እንዲያደርግ አዘዋል፡፡ የሚፈታውም (ስራውን የሚያጠናቀው) ሙሉ ለሙሉ በእርዱ ቀን ይሆናል፡፡ በሀጅ ብቻ ኢህራም ያደረገውም፣ የሚያቀርበው ሀድይ ካለው፣ እሱም በእርዱ

ቀን እስኪፈታ ድረስ በኢህራሙ መቆየት ይጠበቅበታል፡፡ ይህ ማለት በአንድ ኢህራም ሀጅንና ዑምራን አጣምሮ እንደሚፈጽመው ሰው ማለት ነው፡፡

ከዚህ ላይ ግን መታወቅ ያለበት፣ ሀጅን ብቻ ለማድረግ ኢህራም ያደረገ ወይም ሀጅንና ዑምራን በአንድ ላይ ለማድረግ ኢህራም ያደረገ ሰው የሚያቀርበው ሀድይ ከሌለው፣ በኢህራሙ ሊቆይ አይገባውም፡፡ እንዲያውም ሱናው ኢህራሙን ዑምራ ማድረግና ከዚያም ጦዋፍና ሰዕይ ማድረግ ነው፡፡ በመጨረሻም ጸጉሩን በማሳጠር የዑምራውን ስራ ያጠናቅቃል፡፡ ይህ ማለት ከባልደረቦቻቸው መካከል የሚያቀርበው ሀድይ የሌለውን ሰው እንዳዘዙት ማለት ነው፡ ፡ ምናልባት ኢህራም አድራጊው ዘግይቶ መካ ይደርስና ሀጅ ያልፈዋል ብለው ካልፈሩ በቀር እንጅ፣ በዚህ ሁኔታ በኢህራሙ ላይ መቆየቱ ችግር የለውም። አላህ እጅግ በጣም አዋቂ ነው።

ኢህራም አድራጊው የሀጅ ወይም የዑምራ ስራው በበሽታ፣ ጠላትን በመፍራት ወይም በሌላ ምክንያት ተግባሩ ይደናቀፋል ብሎ ከሰጋ፣ እንዲህ ይላል፡-

- ‹‹ፈኢን ሀበሰኒ ሃቢሱን፤ ፈመሐሊ ሀይሡ ሀበስተኒ፡፡›› (ትርጉሙ፡- /በኢህራም ስራ ላይ እያለሁ/ አደናቃፊ ነገር ከገጠመኝ፣ ስራዬ የሚቋጨው እዛው እክል ከገጠመኝ ቦታ ላይ ነው)፡፡

ዷባዕ ቢንት ዙበይር (ረ. ዐ) ለአላህ መልዕክተኛ እንዲህ አለቻቸው፡-

- ‹‹አንቱ የአላህ መልዕክተኛ እኔ ሀጅ ማድረግ እፈልጋለሁ፡፡ ነገር ግን እኔ በሽተኛ ነኝ፡፡›› የአላህ መልዕክተኛም እንዲህ እንድትል አዘዟት፡- ‹‹ሀጅሽን አድርጊ፡፡ ነገር ግን ስራዬ

የሚቋጨው ችግር ካጋጠመኝ ቦታ ላይ ነው፡፡» (ቡኻሪና ሙስሊም የዘገቡት)፡፡

የዚህ ቅድመ ሁኔታ ጥቅሙ፡- አንድ ለሀጅ ወይም ለዑምራ ኢህራም ያደረገ ሰው የሐጅ ወይም የዑምራ ስራውን እንዳያሟላ በሽታ ቢገጥመው ወይም ጠላት እንዳይጓዝ ቢከለክለው ከኢህራሙ መፈታት (የኢህራም ስራውን ሊያቋርጥ) ይችላል፡፡ በዚህ አጋጣሚ ለተከሰተው ነገር ክፍተት መሙሊያም በእሱ ላይ ምንም ነገር (ለምሳሌ ማካካሻ) አይጠበቅበትም፡፡

# የህጻን ልጅ ሀጅ

ህጻናት ሀጅ ቢያደርጉ፣ እነሱ ያደረጉት ሀጅ ትክክለኛ ሀጅ ነው፡፡ ሙስሊም በትክክለኛ ዘገባው ኢብኑ ዐባን ጠቅሶ እንደዘገው፣ አነቢዩ ዘንድ አንድ ሴት ህጻን ልጅ ከፍ አድርጋ በመያዝ፣

- ‹‹ይህ ህጻን ልጅ ሀጅ ማድረግ ይችላልን?›› ብላ ጠየቀቻቸው፡፡ እሳቸውም፣ ‹‹አዎ! ለአንቺም ምንዳ አለሽ›› አሏት፡፡

ቡኻሪ በትክክለኛ ዘገባው አስሳኢብ ኢብኑ የዚድን ጠቅሶ እንደዘገበው፣ አስሳኢብ እንዲህ ይላል፡-

- ‹‹እኔ የሰባት ዓመት ልጅ ሆኜ ከአላህ መልዕክተኛ ጋር ሀጅ አስደርገውኛል፡፡››

ይህ ሀጅ ግን ወደ ፊት ለሚጠብቀው የግዴታ ሀጅ ምትክ አይሆንም፡፡ ልክ እንደዚሁ በቁጥጥር ስር ያሉ አገልጋዮች (ባሪያዎች) ሀጅ ማድረጋቸው ምንም ችግር የለውም፡፡ ኢብኑ ዐባስ ባስተላለፉት ሀዲስ የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ብለዋል፡-

- ‹‹ማንኛውም ህጻን ሀጅ ካደረገ፣ አቅመ - አዳም ሲደርስ ሌላ ሀጅ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡ ማንኛውም አገልጋይ (ባሪያ) ሀጅ ካደረገና ከዚያም ከባርነቱ ነጻ ከወጣ፣ በእሱ ላይ ሌላ ሀጅ የማድረግ ሃላፊነት አለበት፡፡›› (ኢብኑ አቢ ሸይባና በይሀቂ ‹‹ሀሰን›› በሆነ የዘገባ ሰንሰለት ዘግበውታል፡፡)

ህጻኑ ገና ብዙም ጥሩና መጥፎውን ያልለየ ከሆነ፣ አሳዳሪው ኢህራም ማድረግን ሊያስብለት (ሊነይትለት)፣ ተገቢውንም ልብስ

ሊያለብሰውና ስለእሱም ተልቢያውንም ሊልለት ይገባል፡፡ በዚህም ህጻኑ ሙህሪም ይሆናል፡፡ ኢህራም ያደረገው ልጅ ትልቅ ሰው የሚከለከለውን ነገር ይከለከላል፡፡ ሴቷም ልክ እነደዚሁ ገና አቅመ - ሄዋን ካልደረሰች አሳዳሪዋ ኢህራምና ተልቢያ ያደርግላታል፡፡ በዚህም ሙህሪም ትሆናለች፡፡ እሷም ኢህራም ያደረገችው ትልቋ ሴት የምትከለከለውን ነገር ትከለከላለች፡፡ በጦዋፍ ጊዜ ልብሷና ሰውነቷም እንደዚሁ ንጹህ ሊሆን ይገባል፡ ፡ ምክንያቱም ጦዋፍ ከሶላት ጋር ስለሚመሳሰል ነው፡፡ ለጦዋፍ ንጽህናን (ጦሃራ) መጠበቅ ደግሞ ለትክክለኛነቱ መስፈርት ነው፡፡

ህጻናቱ ነፍስ ያወቁና ኢህራም ያደረጉት በአሳዳሪዎቻቸው ፈቃድ ከሆነ፣ ገላ መታጠብና ሽቶ መጠቀምን የመሳሰሉ የኢህራም ስራዎች ከሰሩ፣ አሳዳሪዎቻቸው ማለትም አባቶቻቸው፣ እናቶቻቸው ወይም ሌሎች ጉዳዮቻቸውን የሚያስተናብሩላቸው ከሆነ፣ አሳዳሪዎቻቸው እነሱ ሊሰሩት ያቃታቸውን ድንጋይ እንደመወርወር (ረምይ) እና የመሳሰሉ ነገሮችን ሲያግዟቸው፣ ከዚህ ውጪ ያሉ የሀጅና የዑምራ ስራዎችን ለምሳሌ ዐረፋ ላይ መቆም፣ ሚና እና ሙዝደሊፋ ላይ ማደር፣ ጦዋፍና ሰዕይ ማድረግ የመሳሰሉ ስራዎችን በራሳቸው መወጣት አለባቸው፡፡

ጦዋፍ ማድረግ ካልቻሉ ስለነሱ አሳዳሪያቸው ተሸክመዋቸው ጦዋፍና ሰዕይ ያደርጉላቸዋል፡፡ በዚህ ሁኔታ እጅግ በጣም የተሻለው፣ ጦዋፍና ሰዕይ የሚያስደርጋቸው ሰው የሱን ጦዋፍና ሰዕይ ከእነሱ ጋር አለማጋራቱ ነው፡፡ ይህ ማለት ራሱን ችሎ ጦዋፍና ሰዕይ ያደርጋል ማለት ነው፡፡ ይህን ማድረጉ ዒባዳውን የተሟላ ያደርግለታል፡፡ በቀጣዩም ምርጥ ነቢያዊ ሀዲስ ለመስራት ዕድል ያገኛል፡፡ የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ይላሉ፡-

- «የሚያጠራጥርህን ነገር ትተህ፣ ወደማያጠራጥርህ ነገር ሂድ (አድላ)፡፡» (ቲርሚዚና ነሳኢ የዘገቡት)

ህጽኑን የተሸከመው ሰው ጦዋፍና ሰዕይ የሚያደርገው ለህጻኑ

አስቦ ከሆነ፣ በትክክለኛው አቋም መሰረት ህጻኑ ራሱ እንዳደረገ ይቆጠርለታል፡፡ ምክንያቱም ቀደም ብሎ በተጠቀሰው ሀዲስ ለአላህ መልዕክተኛ ስለ ህጻኑ ልጅ የጠየቀችውን ሴት፣ የአላህ መልዕክተኛ እሷ ለራሷ ብላ ጦዋፍ እንደምታደርግለት አልጠየቋትም፡፡ ይህ ነገር ደግሞ ግዴታ ቢሆን ኖሮ፣ የአላህ መልዕክተኛ ይገልጹት ነበር፡፡ መልካሙን ነገር አጎናጻፊው አላህ ነው፡፡

ነፍስ ያወቁ ልጆች ወደ ጦዋፍ ስራ ከመግባታቸው በፊት ከቆሻሻ (ከነጃሳ) ነገር ራሳቸውን ንጹህ ማድረግ አለባቸው፡፡ ዉዱእ እንዲያደርጉም ይታዘዛሉ፡፡ ልክ እንደ አዛውንቱ ሰውዮ በህጻናቱም ላይም ኢህራም የማድረግ ግዴታ የለባቸውም፡፡ ይህን ሃላፊነት የሚወጣው አሳዳሪያቸው ነው፡፡ እንዲያውም ይህ ተግባር ግዴታ አይደለም፡፡ እሱ ይህን ከሰራው ምንዳ አለው፡፡ ከተወውም ችግር የለውም፡፡ አላህ እጅግ በጣም አዋቂ ነው፡፡

# በኢህራም ወቅት የሚፈቀዱና የሚከለከሉ ነገሮች ማብራሪያ

አንድ ሰው ወንድም ይሁን ሴት ኢህራም ካደረገ በኋላ ጸጉሩን፣ ወይም ጥፍሩን መቁረጥ የለበትም፡፡ እንዲሁም ሽቶ መቀባት አይፈቀድለትም፡፡ በተለይ ለወንድ በአጠቃላይ የተሰፋ ልብስ መልበስ አይፈቀድለትም፡፡ ይህ ማለት በዘወትር እንደሚለበሰው ሆኖ፣ የተሰፋና የተዘጋጀ መሆን የለበትም ማለት ነው፡፡ በዚህም እንደ ቀሚስ ወይም ከፊሉ ቀሚስ የሆነ፣ ካኔቴራ፣ ሱሪ፣ ሽፍን ጫማ፣ የእግር ሹራብ (ካልሲ) መልበስ አይፈቀድም፡፡ ነገር ግን ልቅ ሽርጥ ያላገኘ ሰው ሱሪ ሊለብስ፣ ነጠላ ጫማ ያላገኘ ሰው ያልተቆረጠ ሽፍን ጫማ ሊያደርግ ይፈቀድለታል፡፡ ቡኻሪና ሙስሊም በትክክለኛ ዘገባቸው ኢብኑ ዐባስን ጠቅሰው እንዳስተላለፉት፣ የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ብለዋል፡-

- «ነጠላ ጫማዎችን ያላገኘ ሰው ሽፍን ጫማዎችን ይልበስ፡፡ ሽርጥ ያላገኘ ሰው ሱሪ ይልበስ፡፡»

ይሁንእንጅበኢብኑዑመርየተላለፈውና«ሽፍንጫማዎችንመልበስ ከፈለገ ሽፍን ጫማዎችን መቁረጥ አለበት» የሚለው ሀዲስ፣ በሌላ ሀዲስ የተሻረ ነው፡፡ ምክንያቱም የአላህ መልዕክተኛ መዲና ላይ እያሉ፣ ኢህራም ያደረገ ሰው ስለሚለብሰው ልብስ በተጠየቁበት ጊዜ በዚህ መንገድ ነው ያዘዙት፡፡ እንዲሁም የአላህ መልዕክተኛ ዐረፋ ላይ ዲስኩር ባደረጉበት ጊዜ ነጠላ ጫማ በሌለበት ጊዜ፣ ሽፍን ጫማ መልበስ እንደሚፈቀድ ገልጸዋል፡፡ በዚህ አጋጣሚ ሽፍን ጫማዎቹን መቁረጥ እንደሚያስፈልግ አላዘዙም፡፡ የአላህ መልዕክተኛ ዐረፋ ላይ ያደረጉትን ዲስኩር ተገኝቶ ያዳመጠ ሰው፣ እሳቸው መዲና ላይ የሰጡትን መልስ አላዳመጠም፡፡ ማብራሪያ

በሚያስፈልግበት ጊዜ ማዘግየት አይፈቀድም፡፡ በኡሱሉል ሀዲስና ፊቅህ እንደሚታወቀው ሽፍን ጫማን መቁረጥ የሚያዘው ሀዲስ (በሌላ ሀዲስ) መሻሩ ተረጋግጧል፡፡ ለነገሩ መቁረጥ ግዴታ ቢሆን ኖሮ፣ የአላህ መልዕክተኛ ያብራሩት ነበር፡፡ አላህ እጅግ በጣም አዋቂ ነው፡፡

ኢህራም ላደረገ ሰው ከቁርጭምጭሚቱ በታች የሆነ ጫማ መልበስ፣ እንዲሁም ሽርጥን ማሸረጥና በገመድና በመሰል ነገር ማሰር ይፈቀድለታል፡፡ ይህ የሚፈቀደው ተግባሮቹ እንዳይፈጸሙ የሚከለክል ማስረጃ ካለመገኘቱ አንጻር ነው፡፡ እንዲሁም ኢህራም ያደረገ ሰው አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ገላውንና ጸጉሩን ሊታጠብና ቀስ አድርጎም ሊያከው ይፈቀድለታል፡፡

ሴት ፊቷን መሸፈኛ ሆኖ የሚያገለግል (የተሰፋ) እንደ ቡርቁዕና ኒቃብ እንዲህም ለእጇ ደግሞ ጓንት (የእጅ ሹራብ) መልበስ አይፈቀድላትም፡፡ የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ብለዋል፡-

- ‹‹ሴት ፊቷን መሸፈኛ ሆኖ የሚያገለግል (ኒቃብ) እና የእጅ ጓንቶችን መልበስ አይፈቀድላትም፡፡››

ይሁን እንጅ ለዚኸው ጉዳይ ተብሎ ከተዘጋጀው የፊት መሸፈኛ ልብስ ውጪ እንዲሁም ቀሚስ፣ ሱሪ፣ ሽፍን ጫማ፣ የእግር ሹራብ (ካልሲ) እና የመሳሰሉትን ብትለብስ ችግር የለውም፡፡ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ጉፍታዋን (ሻሽዋን) ፊቷ ላይ ልትለቀው ትችላለች፡፡ ፊቷን እስካላሰረችው ድረስ ጉፍታዋ ፊቷን ቢነካውም ችግር የለውም፡፡ ዓኢሻ እንዲህ ትላለች፡-

- ‹‹እኛ ኢህራም ላይ ሆነን ከአላህ መልዕክተኛ ጋር በነበርንበት ጊዜ፣ መጓጓዣ ላይ የነበሩ ሰዎች እኛ በነበርንበት አካባቢ ሲያልፉና እኛ ዘንድ ሲድርሱ፣ ከመካከላችን አንዷ ጂልባቧን ከራሷ (ከጭንቅላቷ) ወደ ፊቷ ትለቀው ነበር፡፡ ተጓዡ ቡድን እኛን አልፎ ሲሄድ፣

ፊታችንን እንገልጠው ነበር፡፡» (አቡ ዳውድና አህመድ ዘግበውታል፡፡)

አቡ ዳውድና ኢብኑ ማጃህ እንዲሁም በተመሳሳይ ሁኔታ ዳረል ቁጥኒይ ኡሙ ሰለማን ጠቅሰው እንደዘገቡት፣ አንድ ሴት እጇን በልብሷ ወይም በሌላ መሰል ነገር ብትሸፍነው ችግር የለውም፡፡

ሴት ባዕድ ወንዶች ባሉበት አጋጣሚ ከሆነች ፊቷንና እጆቿን መሸፈን ግዴታ አለባት፡፡ ምክንያቱም እሷ ከእነሱ ራሷን መሰተር ያለባት (ዐውራ) ስለሆነች ነው፡፡ አላህ በቁርኣኑ እንዲህ ይላል፡-

- «(የውስጥ) ጌጦቻቸውንም ለባሎቻቸው ... ካልሆነ በስተቀር አይግለጡ፡፡» (አን-ኑር፣ 31)፡፡

ሴቶች ካላቸው ውበት አንጻር የፊት ገጽታቸውና መዳፋቸው በጣም ውበት ያላቸው ለመሆኑ ምንም ጥርጥር የለውም፡፡ በተለይ የፊት ገጽታቸው እጅግ በጣም የላቀ ውበት ያለው ነው፡፡ አላህ በቁርኣን እንዲህ ይላል፡-

- «ዕቃንም (ለመዋስ) በጠየቃችኋቸው ጊዜ፣ ከመጋረጃ ኋላ ሆናችሁ ጠይቋቸው፡፡ ይህ ለልቦቻችሁ፣ ለልቦቻቸውም የበለጠ ንጽህና ነው፡፡» (አል-አህዛብ፣ 53፡፡)

ብዙዎቹ ሴቶች ከጉፍታቸው በታች የሚያደርጉትን ሻሽ ለፊታቸው መሸፈኛ አድርገው መጠቀማቸው፣ እኛ እስከምናውቀው ድረስ ይህ ድርጊታቸው ኢስላማዊ ዕውቀትን መሰረት ያደረገ አይደለም፡፡ ይህ ጉዳይ በኢስላም የተደነገገ ቢሆን ኖሮ፣ የአላህ መልዕክተኛ ለህዝበ - ሙስሊሙ ይገልጹት ነበር፡፡ እንዲሁም በጉዳዩ ላይ ዝምታ የሚፈቀድበት አልነበረም- ተብራርቶ ይገለጽ ነበር እንጅ፡፡

ኢህራም ያደረጉበትን ልብስ በመቆሸሹ ወይም በሌላ ነገር ምክንያት መታጠብ ቢያስፈልገው ማጠብና (አስፈላጊም ከሆነ) ልብሱን

በሌላ የኢህራም ልብስ መቀየር ይቻላል፡፡ ይሁን እንጅ የኢህራም ልብሱን ዘዕፈራን (ጥሩ መዓዛ ያለው ሽቶ) ወይም ወረስ (ለልብስ መንከሪያ የሚያገለግል ነገር) ማስነካት አይፈቀድም፡፡ ምክንያቱም ኢብኑ ዑመር (ረ. ዐ) በዘገቡት ሀዲስ የአላህ መልዕክተኛ ድርጊቱን ከልክለዋልና፡፡

ኢህራም ያደረገ ሰው መጥፎ ንግግርን፣ ወንጀልን (ፊስቅ) እና ክርክርን መተው አለበት፡፡ አላህ በቁርአኑ እንዲህ ይላል፡-

- ﴿ٱلْحَجُّ أَشْهُرٌ مَّعْلُومَٰتٌ ۚ فَمَن فَرَضَ فِيهِنَّ ٱلْحَجَّ فَلَا رَفَثَ وَلَا فُسُوقَ وَلَا جِدَالَ فِى ٱلْحَجِّ ۗ﴾

  ‹‹ሀጅ (ጊዜያቱ) የታወቁ ወሮች ናቸው፡፡ በእነርሱም ውስጥ ሀጅን (እንዲሰራ) ነፍሱን ያስገደደ ሰው በሀጅ ውስጥ ሴትን መገናኘት፣ ማመጽም፣ ክርክርም የለም፡፡›› (አል-በቀራ፣ 197)፡፡

ቡኻሪና ሙስሊም አቡ ሁረይራን ጠቅሰው በትክክለኛ ዘገባ እንደዘገቡት፣ የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ብለዋል፡-

- ‹‹ይህን ቤት የጎበኘ ሰው ሴትን መገናኘትንና ማመጽን ካላንጸባረቀ ልክ እናቱ እንደወለደችው ሆኖ (ወደ ቤቱ፣ ሀገሩ) ይመለሳል፡፡››

‹‹ረፈሥ›› የሚለው ቃል ለግብረ ስጋ ግንኙነት፣ መጥፎ ለሆነ ንግግርና ተግባር ትርጉም ይውላል፡፡ ‹‹ፉሱቅ›› የሚለው ቃል ደግሞ ለወንጀል፣ ለሙግት፣ በሀሰት ለመከራከር ወይም ጥቅም ለሌለው ነገር ትርጉም ይውላል፡፡ ይሁን እንጅ ሀቅን ይፋ ለማድረግና ለሀሰት ምላሽ ለመስጠት ተገቢ በሆነ መንገድ የሚከናወን ክርክር፣ የሚጠቅም ከመሆኑም ሌላ ሙስሊሞች ተግባራዊ እንዲያደርጉት ታዘዋል፡፡ አላህ በቁርአኑ እንዲህ ይላል፡-

- ﴿ ٱدْعُ إِلَىٰ سَبِيلِ رَبِّكَ بِٱلْحِكْمَةِ وَٱلْمَوْعِظَةِ ٱلْحَسَنَةِ ۖ وَجَـٰدِلْهُم بِٱلَّتِى هِىَ أَحْسَنُ ۚ ﴿١٢٥﴾ ﴾

«ወደ ጌታህ መንገድ በብልሃትና በመልካም ግሳጼ (በመልካም ቃል) ጥራ፡፡ በዚያችም እርሷ መልካም በሆነችው (ዘዴ) ተከራከራቸው ... ፡፡» (አን-ነህል፣ 125)፡፡

ኢህራም ያደረገ ወንድ ጭንቅላቱን ከሱፍ ወይም ከጥጥ ከተሰራ ባርኔጣ፣ ኮፍያ፣ ጥምጣምና መሰል ነገር መሸፈን የለበትም፡፡ ፊቱንም እንዲሁ በሆነ ነገር መሸፈን የለበትም፡፡ ሙስሊም በዘገበው ሀዲስና ቡኻሪና ሙስሊም በትክክለኛነቱ በተስማሙበት የሀዲስ ዘገባ የአላህ መልዕክተኛ በዕለተ ዐረፋ ከመጓጓዣው ላይ ወድቆ ለሞተው ሰው እንዲህ ብለዋልና፡-

- «በውሃና በሲድር እጠቡት፡፡ በልብሱም ገንዙት (ከፍኑት)፡፡ በዕለተ ትንሳኤ ተልቢያ እያደረገ እንዲቀሰቀስ፣ ጭንቅላቱንና ፊቱን አትሸፍኑት፡፡»

ቢሆንም ግን አንድ ሰው በመኪና ጣራ፣ በጸሀይ ጥላ (የቀኑ ጊዜ ሲቀያየር በሚፈጠረው ጥላ) ወይም በድንኳንና በዛፍ ጥላ ቢጠለል ችግር የለውም፡፡ በትክክለኛ ዘገባ እንደተረጋገጠው፣ የአላህ መልዕክተኛ «ጀምረተል ዐቀባ»ን ሲወረዉሩ በልብስ ተጠልለዋል፡፡ በሌላ በትክክል በተረጋገጠ ሀዲስም፣ ለአላህ መልዕክተኛ ነሚራ ላይ ድንኳን ተጥሎላቸው ነበር፡፡ በእሷ ውስጥም በዐረፋ ዕለት ጸሀይዋ ዘንበል እስከምትል ድረስ ቆይተዋል፡፡

ኢህራም ባደረጉ ወንዶችና ሴቶች ላይ የየብስ እንስሳን አድኖ መግደል፣ ለዚህም ትብብር ማድረግ፣ ከቦታቸውም ማሳደድ ክልክል ነው፡፡ እንዲሁም ጋብቻ መፈጸም፣ የግብረ ስጋ ግንኙነት ማድረግ፣ ሴትን ለጋብቻ ማጨት፣ ከሴቶች ጋር በስጋዊ ስሜት መነካካት ክልክል ነው፡፡ ዑስማን በዘገበው ሀዲስ የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ

ይላሉ፡-

- «ኢህራም ያደረገ ሰው ጋብቻ አይፈጽምም፤ አያጋባምም፤ ለጋብቻም አያጭም፡፡» (ሙስሊም የዘገበው፡፡)

ኢህራም አድራጊው ረስቶ ወይም ሳያውቅ ልቅ ያልሆነ ልብስ ቢለብስ፣ ጭንቅላቱን ቢሸፍነው፣ ሽቶ ቢጠቀም ለሰራው ጥፋት ማካካሻ (ፊድያ) አያስፈልገውም፡፡ ይሁን እንጅ ይህን ድርጊቱን ሲያስታውስ ወይም ሲያውቅ ወዲያዉኑ እንዲወገድ ያደርገዋል፡፡ ልክ እንደዚሁ አንድ ኢህራም አድራጊ ረስቶ ወይም ሳያውቅ ጸጉሩን ቢላጨው ወይም የተወሰነውን ጸጉሩን ቢያስወግደው ወይም ጥፍሩን ቢቆርጠው እንደ ትክክለኛው አቋም፣ ለሰራው ጥፋት ማካካሻ (ፊድያ) አያስፈልገውም፡፡

ኢህራም ያደረገም ይሁን ያላደረገ፣ ሴትም ትሁን ወንድ ሙስሊም ሀረም ክልል ውስጥ የዱር እንስሳትን ማደን፣ እንዲታደኑ በመሳሪያም እገዛ በማድረግ ወይም ያሉበትን በመጠቆምና ተመሳሳይ ተግባር በመፈጸም መተባበርና ከቦታቸው ማሳደድ፣ ሀረም ክልል ውስጥ የሚገኝ ዛፍንና አረንጓዴ ተክልን መቁረጥ እንዲሁም ወድቆ የተገኘን ነገር ለባለቤቱ ለመስጠት (ለማድረስ) ካልሆነ በስተቀር ማንሳትም ክልክል ነው፡፡ የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ይላሉ፡-

- «ይቺ ሀገር (መካ) እስከ ዕለተ ትንሳኤ ድረስ እርም ናት፡፡ ስለሆነም ዛፏ አይቆረጥም፤ አራዊቷ አይታደንም፤ ሳሯ አይቆረጥም፤ በእሷ ውስጥ ወድቆ የተገኘውም፣ የጠፋህ ለሚል ሰው ካልሆነ በቀር ማንሳት አይፈቀድም፡፡» (ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል፡፡)

«ሙንሺድ» ማለት ጠፍቶ የተገኘውን ነገር (የጠፋህ የሚል) አሳዋቂ ማለት ነው፡፡ «ኸላ» ማለት እርጥብ ሳር ነው፡፡ ሚና እና ሙዝደሊፋ የሀረም ክልል ውስጥ የሚካተቱ ሲሆኑ፣ ዐረፋ ግን በሀረም ክልል ውስጥ አይካተትም፡፡

# መካና መስጂደል ሀራም ሲገባ የሚፈጸሙ ተግባሮች ማብራሪያቸው

ለሀጅ ኢህራም ያደረገው ሰው መካ እንደደረሰ ወደ መካ ከመግባቱ በፊት ገላውን መታጠብ ይወደድለታል፡፡ ምክንያቱም የአላህ መልዕክተኛ ይህንን ሰርተውታልና፡፡መስጂደል ሀራም ሲደርስ፣ ቀኝ እግሩን ያስቀድምና

- بسم الله والصلاة والسلام علي رسول الله أعوذ بالله العظيم وبوجه الكريم و سلطانه القديم من الشيطان الرجيم اللهم الفتح لي أبواب رحمتك

«ቢስሚላሂ ወስሶላቱ ወስሰላም ዐላ ረሱሊላህ፡፡ አዑዙ ቢላሂልዐዚም፤ ወቢወጅሂሂል ከሪም፤ ወሱልጧኒሂል ቀዲም ሚነሽሸይጧኒረጂም፤ አልላሁምመፍተህሊ አብዋበ ረሕመቲከ፡፡» (ትርጉም፡- በአላህ ስም እጀምራለሁ፡፡ ሰላምና እዝነት በአላህ መልዕክተኛ በሆኑት ላይ ይሁን፡፡ ታላቅ በሆነው አላህ፣ በተከበረው ፊቱ፣ መጀመሪያ በሌለው ስልጣኑ ከተረገመው ሰይጣን እጠበቃለሁ፡፡ አላህ ሆይ! የእዝነት በራፎችህን ለእኔ ክፈትልኝ፡፡)

ይህን ዱዓ ሌሎች መስጂዶች ላይም ሲገባ ተግባራዊ ያደርገዋል፡፡ እኔ እስከማውቀው ድረስ ከአላህ መልዕክተኛ ዘንድ የተረጋገጠ ወደ መስጂደል ሀራም ብቻ ሲገባ  የሚባል ዚክር የለም፡፡

በሀጅ ወቅት ዑምራ ማድረግና በዚያው ጊዜ ሀጅ መፈጸምን የሚያከናውን (ሙተመቲዕ) ወይም ዑምራ አድራጊ ከሆነ፣ ወደ ካዕባ ሲደርስ፣ ሲለው የነበረውን ተልቢያ፣ ጦዋፍ ከመጀመሩ በፊት ያቋርጠዋል፡፡ ከዚያም ሀጀረል አስወድን ፊት ለፊቱ በማድረግ

ለእሱ ሰላምታ ያቀርባል፡፡ ነገሮች ምቹ ከሆኑለት እሱን ይስመዋል፡
፡ ሀጀረል አስወድን ለመሳም ብሎ ሰዎችን በማጨናነቅ ማስቸገር የለበትም፡፡ ሀጀረል አስወድን ሰላም ሲል፣ «ቢስሚላሂ አላሁ አክበር» ወይም «አላሁ አክበር» ይላል፡፡ እሱን ለመሳም ከተቸገረ በዱላ (በዘንግ) ወይም በመሰል ነገር ሰላምታ ያቀርብና ዱላዉን ወይም ዘንጉን መልሶ ይስመዋል፡፡ አሁንም በዱላ (በዘንግ) ወይም በመሰል ነገር ሰላምታ ማቅረብ ካልቻለ፣ በዱላ (በዘንግ) ወይም በመሰል ነገር ወደ እሱ ያመላክትና «አላሁ አክበር» ይላል፡፡ በዚህ ሁኔታ ያመላከተበትን ነገር መሳም አይጠበቅበትም፡፡

ምንም እንኳ በጦዋፍ ላይ ንግግር የሚፈቀድ ቢሆንም፣ ጦዋፉ ጤናማ እንዲሆን ጦዋፍ አድራጊው ገላውን መታጠብና ዉዱእ ማድረግ አለበት፡፡ በጦዋፍ ጊዜ ካዕባን በስተቀኝ በኩል አድርጎ ጦዋፍ ይጀምራል፡፡ በዚህም ጊዜ፣

- اللهم ايمانا بك و تصديق بكتابك ووفاءً بعهدك والتباع لسنة نبيك محمدٍ

«አልላሁምመ ኢማነን ቢከ፤ ወተስዲቀን ቢኪታቢከ፤ ወወፋአን ቢዐህዲከ፤ ወትቲባዓን ሊሱንነቲ ነቢይከ ሙሀመዲን (ሶ. ዐ. ወ)» ይላል፡፡ (ትርጉም፡- አላህ ሆይ! በአንተ አምኜ፣ በመጽሀፍህ እውነት ብዬ፣ ቃል ኪዳንህን ለመሙላት ብዬ፣ የመልዕክተኛህን ሙሀመድ መንገድ ለመከተል ብዬ (ጦዋፍ አደርጋለሁ)፡፡
) የሚለውን ዱዓ ቢል መልካም ነው፡፡ ምክንያቱም ይህ ዱዓ ከነቢዩ ዘንድ ተላልፏልና፡፡ በአጠቃላይ ሰባት ዙሮችን ይዞርና፣ በመጀመሪያው ጦዋፍ የመጀመሪያዎቹ ሶስት ዙሮች ላይ እርምጃ በተቀራረበት ሁኔታ ሮጥ ሮጥ ይላል፡፡ ቀሪዎቹን አራት ዙሮች ደግሞ ቀስ ባለ እርምጃ ይሸፍናቸዋል፡፡

ኢህራም ያደረገው ሰው በሀጅ ወቅት ዑምራ ማድረግና በዚያው ጊዜ ሀጅ መፈጸምን የሚያከናውን (ሙተመቲዕ) እና ዑምራ አድራጊ ቢሆን ወይም ሀጅን ብቻ (ኢፍራድ) ወይም ሀጅና

ዑምራን በአንድ ላይ አጣምሮ (ቂራን) የሚያደርግ ቢሆንም፣ የሚያደርገው ጠዋፍ እላይ በተጠቀሰው መንገድ ነው፡፡ ሁሉንም ዙር የሚጀምረውና የሚጨርሰው ሀጀረል አስወድ ላይ ነው፡፡

«ረምል» ማለት እርምጃ በተቀራረበ ሁኔታ ሮጥ ሮጥ ማለት ነው፡ ፡

በጠዋፍ ጊዜ ብቻ የኩታውን መካከለኛ ክፍል በቀኝ ትከሻ በታች እንዲሁም የኩታውን ጫፍ በግራ ትከሻው አድርጎ ጠዋፍ ያደርጋል፡፡

ጠዋፍ በሚያደርግበት ጊዜ ምን ያህል ጠዋፍ እንዳደረገ ከተጠራጠረ እርግጠኛ የሆነበትን ቁጥር በመያዝ ጠዋፉን ይቀጥላል፡፡ ለምሳሌ አራት ዙር ወይስ ሶስት ዙር ነው ጠዋፍ ያደረኩት የሚል ጥርጣሬ ካደረበት፣ ሶስት ነው ያደረኩት በማለት ቀሪውን ጠዋፍ አሟልቶ ይጨርሳል፡፡ በሰዕዩም ላይ ከተጠራጠረ እርግጠኛ የሆነበትን ቁጥር በመያዝ ሰዕዩን ይቀጥላል፡፡ ጠዋፉን እንዳጠናቀቀ የጠዋፉን ሁለት ረከዓ ሶላት ከመስገዱ በፊት ኩታውን ትከሻው ላይ በማድረግ ደረቱ ላይ ይለቀዋል፡፡

ሊነቀፍና ማስጠንቀቂያ ሊደረግበት የሚገባው ጉዳይ ሴቶች ጌጣቸውን አድርገውና ጥሩ መዓዛ ያለው ነገር ተጠቅመው ጠዋፍ የማድረጋቸው ሁኔታ ነው፡፡ ሴቶች ማንኛውም ባዕድ አካል ሊመለከታቸው የሚገቡ አካላት አይደሉም፡፡ ስለሆነም ከሌላ ባዕድ አካል መሰተር (መከለል) ግዴታቸው ነው፡፡ በጠዋፍና በሌሎች አጋጣሚዎች ሴቶች ከባዕድ ወንዶች ጋር በሚቀላቀሉበት ሁኔታ ጌጣቸውን መጠቀም አይገባቸውም፡፡ ምክንያቱም እነሱ ማንኛውም ባዕድ አካል ሊመለከታቸው የማይገቡና ውበታቸው ሰዎችን በቀላሉ ለአደጋ (ዝሙት) የሚያጋልጥ ነውምና ነው፡፡ አንድት ሴት አላህ ከሰጣት ውበት መካከል ለእይታ ግልጽ የሆነው የአካሏ ክፍል የፊት ገጽታዋ ነው፡፡ ስለሆነም ይህን ውበቷን

ለቅርብ ዘመዷ ካልሆነ በስተቀር ለባዕድ ወንድ ማሳየት የለባትም፡፡ አላህ በቁርኣን እንዲህ ይላል፡-

- ﴿وَلَا يُبْدِينَ زِينَتَهُنَّ إِلَّا لِبُعُولَتِهِنَّ أَوْ ءَابَآئِهِنَّ﴾

«(የውስጥ) ጌጦቻቸውንም ለባሎቻቸው ... ካልሆነ በስተቀር አይግለጡ፡፡» (አን-ኑር፣ 31፡፡)

ሴቶች ሀጀረል አስወድን ለመሳም ፊታቸውን ሲገልጡ ባዕድ ወንዶች የሚያዩዋቸው ከሆነ፣ ፊታቸውን መግለጥ አይፈቀድላቸውም፡፡ በዚኸው ምክንያት ሀጀረል አስወድን ለመሳም ምቹና ሰፊ ቦታ ካላገኙ ሀጀረል አስወድን ለመሳም ብለው ከወንዶች ጋር መጋፋት አይፈቀድላቸውም፡፡ ከዚህ ይልቅ ከወንዶች ኋላ ሆነው ጦዋፍ ማድረግ ነው የሚገባቸው፡፡ በዚህ ከወንዶች ጋር ግፊት በሚበዛበት ሁኔታ ካዕባ አካባቢ ጦዋፍ ማድረጋቸው፣ በላጭና እጅግ በጣም ምንዳ ያለው ነው፡፡

እርምጃ በተቀራረበ ሁኔታ ሮጥ ሮጥ ማለትና የኩታን መካከለኛ ክፍል በቀኝ ትከሻ በታች እንዲሁም የኩታውን ጫፍ በግራ ትከሻው በላይ ማድረግ በጦዋፍ ጊዜ እንጅ በሌላ ቦታ ተግባራዊ እንዲሆን ሸሪዓው አላስተማረም፡፡ «ሰዕይ»ም ላይ ቢሆን ይህን ማድረግ አልተደነገገም፡፡ ሴቶችም ይህን እንዲያደርጉ ሸሪዓው አላስተማረም፡፡ የአላህ መልዕክተኛ እርምጃ በተቀራረበ ሁኔታ ሮጥ ሮጥ ማለትና የኩታን መካከለኛ ክፍል በቀኝ ትከሻ በታች እንዲሁም የኩታውን ጫፍ በግራ ትከሻው በላይ ማድረግ መካ በገቡበት ጊዜ በመጀመሪያው የጦዋፍ ዙር ጊዜ ነው ተግባራዊ ያደረጉት፡፡

በጦዋፍ ጊዜ ገላን መታጠብና ዉዱእ ማድረግ ተገቢ ነው፡፡ እንዲሁም ጦዋፍ አድራጊው ለጌታው አጎብዳጅና ተንበርካኪ መሆን ይገባዋል፡፡ በዚህ ጊዜ ዚክርና ዱዓ ማብዛት ይወደድለታል፡

፡ የተወሰነ የቁርኣን ክፍልም ቢቀራ ጥሩ ነው፡፡ ነገር ግን በዚህ ጦዋፍና በሌሎች የጦዋፍ አጋጣሚዎች እንዲሁም ሰዕይ ላይ የሚባል የተለየ ዚክርና ዱዓ ሸሪዓው አላስተማረም፡፡ ይሁን እንጅ ይህ አንዳንድ ሰዎች ለእያንዳንዱ ጦዋፍ ወይም ሰዕይ አድርገው የሚጠቀሙበት ልዩ ዚክርና ዱዓ መሰረት የለሽ ነው፡፡ ይልቅ ኢስላም ካስተዋወቃቸው ዚክርና ዱዓ የተመቸውን መጠቀሙ ነው በቂ የሚሆነው፡፡

ኢህራም አድራጊው ለሩክነል የማኒ ትይዩ ሲሆን፣ ሩክነል የማኒን በቀኝ እጁ ይነካዋል፡፡ እንዲህም ይላል፡- ‹‹ቢስሚላሂ ወላሁ አክበር፡፡›› ሩክነል የማኒን ግን በቀጥታ መሳም የለበትም፡ ፡ እሱን መንካት የሚቸገር ከሆነ፣ ትቶት ጦዋፉን መቀጠል ነው ያለበት፡፡ በሩክነል የማኒ ትይዩ ሲሆን በሆነ ነገር ወደ እሱ ማመላከትና ‹‹አላሁ አክበር›› ማለት አያስፈልገውም፡ ፡ እኛ እስከምናውቀው ድረስ እንዲህ አይነቱ ተግባር ከአላህ መልዕክተኛ ዘንድ አልተረጋገጠም፡፡ ጦዋፍ የሚያደርገው ሰው በሩክነል የማኒና በሀጀረል አስወድ መካከል ሲደርስ፣

- ﴿ رَبَّنَآ ءَاتِنَا فِي ٱلدُّنۡيَا حَسَنَةٗ وَفِي ٱلۡأٓخِرَةِ حَسَنَةٗ وَقِنَا عَذَابَ ٱلنَّارِ ٢٠١ ﴾

  ‹‹ረብበና ኣቲና ፊድዱንያ ሀሰነተን ወፊል ኣኺረቲ ሀሰነተን ወቂና ዐዛበንናር›› (አል-በቀራ፣ 201)፡፡ ማለት ይወደድለታል፡ ፡ (ትርጉም፡- ጌታችን ሆይ! በምድረ ዓለም ደግን ነገር (ጼጋን)፣ በመጨረሻይቱም አገር ደግን ነገር (ገነትን) ስጠን፡፡)

ለሀጀረል አስወድ ትይዩ በሆነበት አጋጣሚ ሁሉ እሱን በእጁ ይነካዋል፤ ይስመዋልም፡፡ ‹‹አላሁ አክበር››ም ይላል፡፡ እሱን በእጁ መንካትና መሳም ካልተመቻቸለት፣ ወደ እሱ ትይዩ በሆነ ቁጥር ወደ እሱ ማመላከትና ‹‹አላሁ አክበር›› ማለት ብቻ ነው የሚጠበቅበት፡፡

አንድ ሰው በተለይም የሰው መጨናነቅ በሚከሰትበት ጊዜ ከ‹‹ዘምዘም ውሃ››ው ኋላ ጦዋፍ ቢያደርግ ችግር የለውም፡፡ የመስጂዱ ሁሉም ስፍራ የጦዋፍ ቦታ ነውና ሌላው ቀርቶ በመስጂዱ ዳር ዳር አካባቢ እንኳ ጦዋፍ ቢያደርግ ጦዋፉ ትክክለኛ ነው፡፡ ነገሮች ምቹ የሚሆኑ ከሆነ፣ ካዕባ አካባቢ ጦዋፍ ማድረግ ከሌላ ቦታ ከማድረግ በላጭ ነው፡፡

አሁንም ነገሮች ምቹ የሚሆኑ ከሆነ፣ ጦዋፉ እንደተጠናቀቀ መቃመ ኢብራሂም ኋላ ላይ ሁለት ረከዓ ሶላት ይሰግዳል፡፡ ነገር ግን በሰው መጨናነቅና በሌላ መሰል ምክንያት መቃመ ኢብራሂም ኋላ መስገድ ካልቻለ፣ በየትኛውም የመስጂዱ ክልል ውስጥ መስገዱ በቂ ይሆናል፡፡ ሶላቱንም ሲሰግድ፣ በመጀመሪያው ረከዓ ከፋቲሃ ምዕራፍ በኋላ የአል-ካፊሩን ምዕራፍ፣ በሁለተኛው ረከዓ ደግሞ የአል-ኢኽላስን ምዕራፍ ይቀራል፡፡ ከዚያም ሶፋ እስከሚደርስ ድረስ ቀስ ብሎ በሚኬድበት ቦታ ቀስ ብሎ የሚሄድ ሲሆን፣ ፈጠን ፈጠን ተብሎ በሚኬድበት ቦታ ደግሞ ፈጠን ብሎ ይሄዳል፡፡ የአላህ መልዕክተኛ ተግባራዊ ስላደረጉት፣ ይህንንም ዙሩን ሲሄድም ሲመለስም ሰባት ጊዜ ተግባራዊ ያደርጋል፡፡ የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ብለዋል፡-

- ‹‹የሀጅ አፈጻጸም ስርዓታችሁን ከእኔ ውሰዱ (ያዙ)፡፡››

ከዚያም በበሩ ይወጣና ወደ ሶፋ ተራራ ይሄዳል፡፡ ወደ ሶፋ ሲጠጋ ወደ ሶፋ ተራራ ይወጣል ወይም ደግሞ እሱ ዘንድ ይቆማል፡፡ ለነገሩ የሚቻል ከሆነ ወደ ሶፋ ተራራ መውጣቱ በጣም የበለጠ ነው፡፡ ሶፋ ላይ የመጀመሪያውን ዙር ሰዕይ ሲጀምር፣ ቀጣዩን የቁርአን አንቀጽ ይላል፡-

- ﴿ إِنَّ ٱلصَّفَا وَٱلۡمَرۡوَةَ مِن شَعَآئِرِ ٱللَّهِۖ فَمَنۡ حَجَّ ٱلۡبَيۡتَ أَوِ ٱعۡتَمَرَ فَلَا جُنَاحَ عَلَيۡهِ أَن يَطَّوَّفَ بِهِمَاۚ وَمَن تَطَوَّعَ خَيۡرٗا فَإِنَّ ٱللَّهَ شَاكِرٌ عَلِيمٌ

(١٥٨)

«ኢንነ ሶፋ ወልመርወተ ሚን ሸዓኢሪላሂ፤ ፈመን ሐጅጀል በይተ አዊዕተመረ ፈላ ጁናሐ ዐለይሂ አንየጥጦውወፈ ቢሂማ፤ ወመን ተጦውወዓ ኸይረን ፈኢንነላሃ ሻኪሩን ዐሊም፡፡» (አል-በቀራ፣ 158፡፡)

(ትርጉም፡- ሶፋና መርዋ ከአላህ (ትዕዛዝ መፈጸሚያ) ምልክቶች ናቸው፡፡ ቤቱን (ካዕባን) በሀጅ ወይም በዑምራ ስራ የጎበኘ ሰው በሁለቱ (መካከል) በመመላለሱ በእርሱ ላይ ኃጢአት የለበትም፡፡ መልካምንም ስራ በፈቃደኝነት የሰራ ሰው (አላህ ይመነዳዋል)፡፡ አላህ አመስጋኝ አዋቂ ነው፡፡)

ሶፋ ላይ በሚሆንበት ጊዜ ወደ ቂብላ መዞርና፣ አላህን ማመስገንና ተክቢራ ማለት ይወደዳል፡፡ ስለሆነም እንዲህ ይላል፡-

- لا اله الا الله والله اكبر لا اله الا الله وحده لا شريك له له الملك وله الحمد يحي و يميت وهو علي كل شيءٍ قدير لا اله الا الله وحده انجز وعده ونصر عبده و هزم الاحزاب وحده

«ላ ኢላሃ ኢልለልላህ፤ ወልላሁ አክበር፤ ላ ኢላሃ ኢልለልላህ፤ ወሕደሁ ላሸሪከ ለሁ፤ ለሁል ሙልኩ ወለሁል ሐምዱ፤ ዩሕዩ ወዩሚቱ፤ ወሁወ ዐላ ኩሊ ሸይኢን ቀዲር፡፡ ላ ኢላሃ ኢልለልላሁ ወህደሁ፤ አንጀዘ ወዕደሁ፤ ወነሶረ ዐብደሁ፤ ወሀዘመል አሕዛበ ወሕደሁ፡፡» (ትርጉም፡- ከአላህ በቀር ሌላ አምላክ የለም፡፡ አላህ ታላቅ ነው፡፡ ከአላህ በቀር ሌላ አምላክ የለም፡፡ አንድ ነው፡፡ አጋር የለውም፡፡ ንግስና ለእሱ የተገባ ነው፡፡ ምስጋናም ለእሱ ነው፡፡ እሱ ህያው አድራጊና ገዳይ ነው፡፡ እሱ በሁሉም ነገር ላይ ቻይ ነው፡፡ ከአላህ በቀር ሌላ አምላክ የለም፡፡ አንድ ነው፡፡ ቃሉን ሞልቷል፤ ባሪያውን ረድቷል፤ የጠላትን ጭፍራ ብቻውን አሸንፏል፡፡)

እጁን ወደ ላይ በማንሳት የገራለትን ዱዓ ሶስት ጊዜ እየደጋገመ ያደርጋል፡፡ ከዚያም ይወርድና ወደ መርዋ ይጓዛል፡፡ በዚህ ጊዜ እስከ መጀመሪያው ምልክት (ዐለመል አወል) ድረስ ጉዞውን ይቀጥልና እስከ ሁለተኛው ምልክት (ዐለመሥሣኒ) ድረስ ሮጥ ሮጥ ይላል፡፡ ሴት ግን በሁለቶቹ ምልክቶች መካከል መሮጥ አያስፈልጋትም፡፡ ምክንያቱም እሷ ባዕድ ሊመለከታት የማይገባ (ዐውራ) ነችና፡፡ እሷ ማድረግ የሚገባት ሁሉንም ሰዕይ፣ ፍጥነት በሌለበት እርምጃ መፈጸም ነው ያለባት፡፡

ሶፋ ላይ እንደደረሰ ወይ ወደ ሶፋ ተራራ ይወጣል ወይም ደግሞ እሱ ዘንድ ይቆማል፡፡ ለነገሩ የሚቻል ከሆነ ወደ ሶፋ ተራራ መውጣቱ በጣም የበለጠ ነው፡፡ በዚህ ጊዜ ቀድሞ የቀራውን የቁርኣን አንቀጽ ማለትም (ኢንነ ሶፋ ወልመርወተ ሚን ሸዓኢሪላህ) የሚለውን ሳይጨምር፣ ሶፋ ላይ የሰራውንና ያለውን ነገር ሁሉ ደግሞ ይሰራዋል፤ ይለዋል፡፡ የቁርኣን አንቀጹ የሚባለው ሶፋ ላይ በሚደረገው እንቅስቃሴ የመጀመሪያው ዙር ላይ ብቻ ነው፡፡

ከዚያም የአላህን መልዕክተኛ ተግባር ከመከተል አንጻር ሶፋ እስኪደርስ ድረስ ሰባቶቹንም ዙሮች ቀስ ብሎ በሚኬድበት ቦታ ቀስ በማለትና ፈጠን ብሎ በሚኬድበት ቦታ ላይ ፈጠን በማለት ተግባራዊ ያደርጋል፡፡ የአላህ መልእክተኛ እንዲህ ብለዋል፡-

- «የሀጅንና የዑምራን አፈጻጸም ስርዓት ከእኔ ያዙ (ውሰዱ)፡፡» (ሙስሊም የዘገበው፡፡)

ሀጅን ወይም ዑምራን የሚፈጽም ሰው ሰዕይ በሚያደርግበት ጊዜ ዚክርና ዱዓ ማብዛት አለበት፡፡ በዚህ ጊዜም ገላውን መታጠብና ዉዱእ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡ ይሁን እንጅ ገላውን ሳይታጠብና ዉዱእ ሳያደርግ ሰዕይ ቢያደርግ ችግር የለውም፡፡ ልክ እንደዚሁ አንዲት ሴት ከጦዋፍ በኋላ የወር አበባ ወይም የወሊድ ደም ቢከሰትባት፣ ባለችበት ሁኔታ ሰዕይ ብታደርግ ችግር የለውም፡

፡ ምክንያቱም ቀደም ብሎ እንደተገለጸው ሰዕይ ለማድረግ ገላ መታጠብና ዉዱእ ማድረግ የሚወደድ ተግባር እንጅ፣ ለሰዕዩ እንደ ቅድመ-ሁኔታ የሚቆጠር አይደለም፡፡

ሀጅን ወይም ዑምራን የሚፈጽም ሰው ሰዕዩን እንደፈጸመ ጸጉሩን ይላጫላል ወይም ያሳጥራል፡፡ ለወንድ ግን ጸጉሩን መላጨቱ በጣም በላጭ ነው፡፡ ጸጉሩ መላጨቱን ትቶ ቢያሳጥረውም ጥሩ ነው፡፡ ይሁን እንጅ በሀጅ ጊዜ ቀሪውን ጸጉሩን ይላጨዋልና ለሀጅ ወደ መካ የሚመጣበት አጋጣሚ ቅርብ ከሆነ ጸጉሩን ከመላጨቱ ይልቅ ማሳጠሩ ነው በላጩ፡፡ ምክንያቱም የአላህ መልዕክተኛ ከባልደረቦቻቸው ጋር በዙል ሂጃ ወር ወደ መካ በመጡበት ጊዜ ከባልደረቦቻቸው መካከል «ሀድይ» ያላያዘ ሰው ከሀጅ ስራው ተፈቶ (ስራውን ቋጭቶ) ጸጉሩን እንዲያሳጥር አዘዋልና፡፡ በዚህ ሁኔታ የአላህ መልዕክተኛ ባልደረቦቻቸውን እንዲላጩ አላዘዙም፡ ፡

ጸጉር በሚያጥርበት ጊዜ ሁሉንም የጸጉሩን ክፍል ማሳጠር እንጅ፣ ልክ የጸጉሩን ክፍል ከፊሉን ላጭቶ ከፊሉን መተው እንደማይችል ሁሉ፣ ከፊሉን አሳጥሮ ከፊሉን መተውም በቂ አይደለም፡፡ ይሁን እንጅ ሴት ልጅ ጸጉሯን ማሳጠር እንጅ፣ መላጨት አይፈቀድላትም፡ ፡ ይህን ስታደርግ ጸጉሯን ሰብሰብ አድርጋ በመያዝ የጸጉሯን የአንድ ጣት አንድ ሶስተኛ መጠን ያህል የሚሆነውን ትቆርጠዋለች፡፡ ከዚህ መጠን በላይ መቁረጥ የለባትም፡፡

ዑምራ አድራጊው ይህን ቀደም ብለን ያወሳነውን ነገር ከፈጸመ ምስጋና ለአላህ ይሁንና ዑምራው ተሟልቶ ተፈጽሟል፡፡ ከዚህ በኋላ በዑምራው ጊዜ እንዳያከናውናቸው ማዕቀብ ተጥለውበት የነበሩትን ነገሮች አሁን የማድረግ መብት ይኖረዋል፡፡ ነገር ግን "ሀድይ" የያዘ ሰው ከሀጅና ከዑምራው በአንድ ላይ እስኪፈታ ድረስ ባለበት (በኢህራሙ) ይቆያል፡፡ ኢህራም ሲያደርግ ሀጅን ብቻ ወይም ሀጅንና ዑምራን በአንድ ላይ ለማድረግ ያሰበ ከሆነ፣

ኢህራሙን ሀጅና ዑምራን በሀጅ ወራቶች እንደሚያደርገው (ሙተመቲዕ) ሰው ማድረግ ሱና ይሆንለታል፡፡ ነገር ግን በዚህ ሁኔታ "ሀድይ" የሚያቀርብ መሆን የለበትም፡፡ ምክንያቱም የአላህ መልዕክተኛ ባልደረቦቻቸውን በዚህ ሁኔታ ነው ያዘዙት፡፡ የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ይላሉ፡- ‹‹እኔ ሀድይ የያዝኩ ቢሆን ኖሮ፣ ከእናንተ ጋር እፈታ ነበር፡፡››

አንድት ሴት ለዑምራ ከሀረመች በኋላ የወር አበባ ወይም የወሊድ ደም ቢከሰትባት፣ ከወር አበባ ወይም ከወሊድ ደም ንጹህ እስከምትሆን ድረስ በካዕባ ላይ ጦዋፍ፣ በሶፋና በመርዋም ሰዕይ አታደርግም፡፡ ነገር ግን ከወር አበባ ወይም ከወሊድ ደም ንጹህ ከሆነች ጦዋፍ፣ በሶፋና በመርዋም እንቅስቃሴ (ሰዕይ) ማድረግ ብቻ ሳይሆን ጸጉሯንም ታሳጥራለች፡፡ በዚህ ሁኔታ ዑምራዋ ምሉዕ ይሆናል፡፡

ይሁን እንጅ ከወር አበባ ወይም ከወሊድ ደም ከየውመትተርዊያ (የዙል ሂጃ ስምንተኛው ቀን) በፊት ንጹህ ካልሆነች፣ ካለችበት ቦታ ሆና ሀጅ ለማድረግ ኢህራም ታደርጋለች፡፡ ከሰዎች ጋርም ወደ ሚና ትሄዳለች፡፡ በዚህ ሁኔታም ሀጅና ዑምራን አጣምራ እንደምታደርገው (ቃሪና) ሆነች፡፡ በዚህም አንድ ሀጅ አድራጊ የሚያደርገውን እንደ ዐረፋ ላይ መቆም፣ መሽዐርም ላይ መገኘት፣ ድንጋዮችን መወርወር፣ በሙዝደሊፋና በሚና ላይ ማደር፣ ሀድይን መሰዋት (ማረድ)፣ ጸጉርን ማሳጠር የመሳሰሉ ተግባሮችን ትፈጽማለች፡፡ ከወር አበባ ወይም ከወሊድ ደም ንጹህ ከሆነች ካዕባ ላይ አንድ ጊዜ ብቻ ጦዋፍ ታደርጋለች፡፡ አንድ ጊዜ ብቻም በሶፋና በመርዋ ሰዕይ ታደርጋለች፡፡ ይህም ተግባሯም ለሁሉም ሀጇና ዑምራዋ በቂዋ ይሆናል፡፡ ዓኢሻ በዘገበችው ሀዲስ መሰረት፣ እሷ ለዑምራ ከሀረመች በኋላ የወር አበባ ደም እንደተከሰተባት የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ብለዋታል፡-

- ‹‹ሀጅ አድራጊ የሚያደርገውን አድርጊ፡፡ ነገር ግን ከወር

አበባ ደም እስከምትጠሪ ድረስ በካዕባ ላይ ጦዋፍ እንዳታደርጊ፡፡» (ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል፡፡)

የወር አበባ ወይም የወሊድ ደም ላይ ያለች ሴት በመስዋዕት ቀን (የውመንነሕር) ድንጋይ ከወረወረች፣ ጸጉሯን ካሳጠረች፣ ሽቶና የመሳሰሉት በኢህራም ምክንያት መጠቀማቸው ክልክል የሆኑት ነገሮች ሁሉ (ከባሏ ጋር የግብረ ስጋ ግንኙነት ሲቀር እንጅ) አሁን መጠቀም ትችላለች፡፡ ከባሏ ጋር የግብረ ስጋ ግንኙነት ማድረግ የሚፈቀድላት፣ እንደ ሌሎቹ ከወር አበባ ወይም ከወሊድ ደም ጠርተው ሀጃቸውን ጦዋፍና ሰዕይ በማድረግ እንደቋጬት ነው፡፡

# በዙል ሂጃ ወር ስምንተኛው ቀን ኢህራም ማድረግና ወደ ሚና መሄድ

በየውመትተርዊያ፣ በዙል ሂጃ ስምንተኛው ቀን ላይ መካ ላይ ያሉና የተፈቱ (ዑምራ ያደረጉ) እንዲሁም ከመካ ነዋሪዎች መካከልም በሀጅ ኢህራም ማድረግ የፈለጉ ሰዎች፣ በዚህ ቀን እቤታቸው ለሀጅ ኢህራም ሊያደርጉ ይችላሉ፡፡ ምክንያቱም የአላህ መልዕክተኛ ባልደረቦች በአላህ መልዕክተኛ ትዕዛዝ አብጦህ ከሚባለው ቦታ ላይ ሆነው ሀጅ ለማድረግ ኢህራም አድርገዋልና፡፡ በዚህ ጊዜ የአላህ መልዕክተኛ ባልደረቦቻቸውን ካዕባ ላይ ሄደው ኢህራም እንዲያደርጉ ወይም ወደ አል-ሚዛብ እንዲሄዱ አላዘዟቸውም፡ ፡ እንዲሁም ከሚና ሲወጡ የመሰናበቻ ጦዋፍ (ጦዋፈል ወዳዕ) እንዲያደርጉም አላዘዟቸውም፡፡ ይህ ሁሉ በኢስላም የተደነገገ ቢሆን ኖሮ፣ የአላህ መልዕክተኛ ባልደረቦቻቸውን ያስተምሯቸው ነበር፡፡ ሁሉም መልካም ነገር ያለው የአላህን መልዕክተኛና ባልደረቦቻቸውን (ረ. ዐ) በመከተል ነው፡፡

ሀጅ ለማድረግ ያሰበ ሰው ሚቃት ላይ ገላውን መታጠብ፣ በአጠቃላይም ንጽህናውን መጠበቅ፣ ሽቶ መጠቀም እንደሚወደድለት ሁሉ፣ ኢህራም ላይም እነዚህን ነገሮች መጠቀም ይወደድለታል፡፡ ሀጅ የሚያደርጉ ሰዎች ከኢህራም በኋላ በዙል ሂጃ ወር ስምንተኛው ቀን ላይ ከቀትር በፊት ወይም በኋላ ወደ ሚና መሄድ ሱና ይሆንላቸዋል፡፡ በዚህም ጊዜ «ጀምረተል ዐቀባ»ን እስኪወረዉሩ ድረስ ተልቢያ ያበዛሉ፤ ሚና ላይም ዙህርን፣ ዐሥርን፣ መግሪብን፣ ዒሻንና ሱብሂን ይሰግዳሉ፡፡ እንደሱናው ከሆነ ሁሉንም ቁጥራቸው ተቀንሶ የሚሰገዱ ሶላቶችን አንድ ላይ ሳይሰበስቡ (በአንድ ጊዜ ሁለቱን ሶላቶች ሳይሰግዱ) ቁጥራቸውን ቀንሰው (አራቱን ረከዓ ሁለት በማድረግ) በጊዜያቸው ይሰግዳሉ፡

፡ የመግሪብና የሱብሂ ሶላቶች ግን ቁጥራቸው ተቀንሶ የሚሰገዱ ሶላቶች አይደሉም፡፡

ሶላቶቹ ቁጥራቸውን ቀንሶ መስገዱ፣ ሶላቱን ሰጋጆቹ የመካና የሌላ አካባቢ ሰዎች በመሆናቸውና ባለመሆናቸው ልዩነት የለውም፡ ፡ ምክንያቱም የአላህ መልዕክተኛ የመካና የሌላ አካባቢ ሰዎችን በሚና፣ በዐረፋና በሙዝደሊፋ ቁጥራቸውን ቀንሰው ሶላቶቹን (የዙህርን፣ የዐስርንና የዒሻን ሶላቶችን) መርተው ሲያሰግዱ፣ የመካን ሰዎች ሶላታቸውን ሞልተው እንዲሰግዱ አላዘዟቸውም፡ ፡ ሞልቶ መስገዳቸውም ግዴታ ቢሆን ኖሮ፣ ጉዳዩን ለእነሱ ያብራሩት ነበር፡፡

ከዚያም ጸሀይ ከወጣ በኋላ በዐረፋ ቀን (በዙል ሂጃ ወር ዘጠነኛው ቀን) ከሚና ወደ ዐረፋ ይጓዛል፡፡ የአላህ መልዕክተኛ ተግብረውታልና ነገሮች ምቹ ከሆኑ ጸሐይ ዘንበል እስከሚል ድረስ ነሚራ አካባቢ ላይ አረፍ ማለትና ጸሀይም ዘንበል ስትል ኢማሙ ወይም ምክትሉ ከወቅቱ ሁኔታ ጋር ሊስማማ የሚችል ማለትም በሀጅ ላይ ሊከናወኑ እንዲሁም ተያያዥ ጉዳዮችን አንስቶ ዲስኩር (ኹጥባ) ማድረጉ ሱና ነው፡፡ በዚህ አጋጣሚም ሀጅ አድራጊዎች አላህን እንዲፈሩ፣ በሁሉም ስራቸው አላህን ብቻ ፍጹም አንድ አድርገው እንዲያመልኩ፣ ሁሉንም ዒባዳ ለእሱ ብቻ አስበው እንዲያከናውኑ ጥሪ ያደርግላቸዋል፤ አላህ የከለከለውን ነገር እንዳይዳፈሩም ያስጠነቅቃቸዋል፤ የአላህን መልዕተኛ ምሳሌ በማድረግ ቁርኣንና ሱናን በሁሉም የህይወት ዘርፍ መመሪያቸው በማድረግ ጥብቅ እንዲሉ አደራ ይላቸዋል፡፡ ከዚህ በኋላ ሙስሊም ጃቢርን ጠቅሰው በዘገቡት ሀዲስ የአላህ መልዕክተኛው እንደፈጸሙት፣ በመጀመሪያው የሶላት ጊዜ፣ በአንድ አዛንና ኢቃም የዙህርና የዐሥርን ሶላቶች ቁጥራቸውን ቀንሰው በተመሳሳይ ጊዜ ይሰግዳሉ፡፡

ከዚያም ሰዎች ዐረፋ ላይ ይቆማሉ፡፡ በጥን ዑረና  የተባለው

ቦታ ሲቀር እንጅ፣ ሁሉም የዐረፋ ክልል መቆሚያ ቦታ ነው፡፡ ነገሮች ምቹ የሚሆኑ ከሆነ ወደ ጀበሉ ረህማን አቅጣጫ መዞር ይወደዳል፡፡ ነገሮች ምቹ ካልሆኑ ደግሞ እሱ ወደ አቅጣጫ መዞር አያስፈልግም፡፡ በዚህ አጋጣሚ (በዐረፋ) ሀጅ አድራጊው አላህን መዘከር፣ እሱን መለመን (ዱዓእ) እና ቀልቡን ሰብሰብ አድርጎ ወደ እሱ መማጸን ላይ መጣጣር (መታገል) ይኖርበታል፡፡ ዱዓእ በሚያደርግበት ጊዜ እጁን ወደ ላይ ያነሳል፡፡ ተልቢያ ወይም ከቁርኣን የተወሰነ መጠን ያህል ቢቀራ ጥሩ ነው፡፡

- «ላ ኢላሃ ኢልለላህ ወሕደሁ ላሸሪከ ለሁ፤ ለሁልሙልኩ ወለሁል ሐምዱ፤ ዩሕዪ ወዩሚቱ ወሁወ ዐላ ኩሊ ሸይኢን ቀዲር» (ትርጉም፡- ከአላህ ሌላ በእውነት የሚመመለክ አምላክ የለም፤ እሱ አንድና አጋር የሌለው ነው፤ ንግስናና ምስጋና ለሱ ነው፤ እሱ ሕያውና ሙት አድራጊ ነው፤ እሱ በሁሉም ነገር ቻይ ነው፡፡) የሚለውን ዚክር ማብዛት ይጠበቅበታል፡፡

ቲርሚዚ ዐምር ኢብኑ ሹዐይቢን፣ ዐምር ደግሞ አባቱን፣ አባቱ ደግሞ አያቱን ጠቅሶ እንደዘገበው፣ የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ብለዋል፡-

- «በላጩ ዱዓእ በዕለተ ዐረፋ የሚደረገው ዱዓእ ነው፡፡ እኔና ከእኔ በፊት የነበሩት የአላህ መልዕክተኞች ከተናገሩት ንግግር በላጩ ላ ኢላሃ ኢልለላህ ወሕደሁ ላሸሪከ ለሁ፤ ለሁልሙልኩ ወለሁል ሐምዱ፤ ወሁወ ዐላ ኩሊ ሸይኢን ቀዲር የሚለው ንግግር ነው፡፡»

ሙስሊም በትክክለኛ ዘገባ ሰሙራ ኢብኑ ጁንዱብን ጠቅሶ እንደዘገበው፣ የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ብለዋል፡-

- «ከአላህ ዘንድ እጅግ በጣም ተወዳጅ ንግግሮች አራት ናቸው፡፡ (እነሱም፡-) ሱብሃነላህ፣ ወልሐምዱሊላህ፣ ወላኢላሃ ኢልለላህ፣ ወላሁ አክበር፡፡»

ቀልብን ሰብሰብና አላህን ፈራ አድርጎ እነዚህን ዚክሮች ማብዛት አስፈላጊ ነው፡፡ እንዲሁም ሸሪዓው ያስተማራቸውን በሁሉም ጊዜ የሚባሉ ዚክሮችና ዱዓዎች በብዛት ማለት ያስፈልጋል፡፡ በተለይም በዚህ ልዩ ቦታና የላቀ ዕለት ጥቅል መልዕክት በውስጣቸው የያዙ ዱዓዎችን ማለት ያስፈልጋል፡፡ ከእነዚህ ዱዓዎችም መካከል የሚከተሉት ተጠቃሽ ናቸው፡፡

# የተለያዩ ምርጥ ዱዓዎች

በትክክለኛ የሀዲስ ዘገባ የአላህ መልእክተኛ እንዲህ ብለዋል፡- ‹‹ከአላህ ዘንድ ተወዳጅ ንግግሮች አራት ናቸው፡፡ እነሱም፡-

- سُبْحَـــانَ اللهِ

ሱብሃነላሂ፣

- وَالْحَمْــــــدُ للهِ

አልሀምዱሊላሂ፣

- وَلَا إِلَــهَ إِلَّا اللهُ

ላኢላሃ ኢለላህ እና

- وَاللهُ أَكْــــبَرُ

አላሁ አክበር ናቸው፡፡››

- سُبْحَانَ اللّٰهِ وَبِحَمْدِهِ، سُبْحَانَ اللّٰهِ الْعَظِيم لَّآ إِلَٰهَ إِلَّآ أَنتَ سُبْحَٰنَكَ إِنِّي كُنتُ مِنَ ٱلظَّٰلِمِينَ.

ሱብሃነላሂ ወቢሃምዲሂ ሱብሃነላሂል ዐዚም፤ ላኢላሃ ኢልላ አንተ ሱብሃነከ ኢንኒ ኩንቱ ሚነዟሊሚን፡፡

‹‹ጥራትና ምስጋና ለአላህ ይገባው፤ ታላቅ ለሆነው አላህ ጥራት ይገባው፡፡››

- لَا إِلَهَ إِلَّا اللهُ، وَلَا نَعْبُدُ إِلَّا إِيَّاهُ، لَهُ النِّعْمَةُ، وَلَهُ الْفَضْلُ،

وَلَهُ الثَّنَآءُ الْحَسَنُ، لَا إِلَهَ إِلَّا اللهُ مُخْلِصِينَ لَهُ الدِّينَ، وَلَوْ كَرِهَ الْكَافِرُونَ

ላኢላሃ ኢለላህ፤ ወላነዕቡዱ ኢልላ ኢያሁ፤ ለሁንኒዕመቱ፣ ወለሁል ፈድሉ፣ ወለሁሥሠናኡል ሀሰን፤ ላኢላሃ ኢልለላህ፤ ሙኽሊሲነ ለሁድዲን፤ ወለው ከሪሃል ካፊሩን፡፡

‹‹ከአላህ በስተቀር አምልኮ የሚገባው ሌላ አምላክ የለም፡፡ እርሱን እንጂ ሌላ አካልን አንገዛም፡፡ ጸጋ የእርሱ ነው፤ ትሩፋትም ለእርሱ ነው፤ መልካም ውዳሴ የሚገባው ለእርሱ ነው፡፡ ከአላህ በቀር ሌላ አምላክ የለም፤ ከሀዲዎች ቢጠሉም፣ እምነታችንን ለእሱ አጥርተናል፡፡››

- لَا حَوْلَ وَلَا قُوَّةَ إِلَّا بِاللَّهِ

ላሃውለወላ ቁውወተ ኢልላ ቢላህ፡፡ ‹‹ብልሃትና ሃይል የሚገኘው በአላህ እገዛ ነው፡፡››

- رَبَّنا آتنا في الدنيا حسنة وفي الآخرة حسنة وقنا عذاب النار

ረብበና ኣቲና ፊድዱንያ ሀሰነተን ወፊል ኣኺረቲ ሀሰነተን ወቂና ዐዛበንናር፡፡

‹‹ጌታዬ ሆይ! በዚህ ዓለምና በመጪው ዓለም መልካምን ነገር ስጠን፤ ከእሳት ቅጣትም ጠብቀን፡፡››

- اللَّهُمَّ أَصْلِحْ لِي دِينِي الَّذِي هُوَ عِصْمَةُ أَمْرِي، وَأَصْلِحْ لِي دُنْيَايَ الَّتِي فِيهَا مَعَاشِي، وَأَصْلِحْ لِي آخِرَتِي الَّتِي فِيهَا مَعَادِي، وَاجْعَلِ الْحَيَاةَ زِيَادَةً لِي فِي كُلِّ خَيْرٍ، وَالْمَوْتَ رَاحَةً

لِي مِنْ كُلِّ شَرٍّ

አላህምመ አስሊህ ሊ ዲኒ አለዚ ሁወ ዒስሙቱ አምሪ፤ ወአስሊህ ሊ ዱንያዩ አልለቲ ፊሃ መዓሺ፤ ወአስሊህ ሊ ኣኺረቲ አልለቲ ፊሃ መዓዲ፤ ወጅዐሊል ሀያተ ዚያደተንሊ ፊ ኩልሊ ኸይር፤ ወልመውተ ራሀተን ሊ ሚን ኩልሊ ሸርር፡፡

«አላህ ሆይ! የጉዳዩ ተገን የሆነውን ሃይማኖቴን አብጅልኝ፤ በእሷ መኖሪያዬ የሆነችውን ይችን ዓለም አብጅልኝ፤ መመለሻዬ የሆነችውን መጪዋን አለም አብጅልኝ፤ በህይወት መቆየቴን ለመልካም ስራ ጭማሪ አደርግልኝ፤ ህልፈቴን ደግሞ ከመጥፎ ስራ መገላገያ አድርግልኝ፡፡»

- أَعُوذُ بِاللَّهِ مِنْ جَهْدِ الْبَلَاءِ، وَدَرَكِ الشَّقَاءِ، وَسُوءِ الْقَضَاءِ، وَشَمَاتَةِ الأَعْدَاءِ.

አዑዙ ቢላሂ ሚን ጀህዲል በላእ፤ ወደርኪ ሸሸቃእ፤ ወሱኢል ቀዷእ፤ ወሸማተቲል አዕዳእ፡፡

«ከመጥፎ መከራ፣ ከዝቅጠት ጥመት፣ ከመጥፎ ውሳኔ፣ ከጠላት ደስታ በአንተ እጠበቃለሁ፡፡»

- اللَّهُمَّ إِنِّي أَعُوذُ بِكَ مِنَ الْهَمِّ وَالْحَزَنِ، وَمِنَ الْعَجْزِ وَالْكَسَلِ، وَمِنَ الْجُبْنِ وَالْبُخْلِ، وَمِنَ الْمَأْثَمِ وَالْمَغْرَمِ، وَمِنْ غَلَبَةِ الدَّيْنِ وَقَهْرِ الرِّجَالِ

አላሁምመ ኢንኒ አዑዙ ቢከ ሚነል ሀምሚ፤ ወልሁዝኒ፤ ወሚነል ዐጅዚ ወልከሰሊ፤ወሚነል ጁብኒ ወልቡኽሊ፤ ወሚነል መእሠሚ ወልመግረሚ፤ ወሚን ገለበቲድደይኒ ወቀህሪርሪጃል

‹‹አላህ ሆይ! ከጭንቀት፣ ከሀዘን፣ ከመሳን፣ ከስንፍና፣ ከፍርሃት፣ ከስስት፣ ከወንጀል፣ ከዕዳ፣ ከማይወጡት ዕዳና ከወንዶች ሸንፈት በአንተ እጠበቃለሁ።

- أَعُوذُ بِكَ اللَّهُمَّ مِنَ الْبَرَصِ، وَالْجُنُونِ، وَالْجُذَامِ، وَمِنْ سَيِّءِ الْأَسْقَامِ.

አዑዙ ቢከ አላሁምመ ሚነል በረሲ፣ ወልጁኑኒ፣ ወልጁዛሚ፣ ወሚን ሰይይኢል አስቃሚ

‹‹አላህ ሆይ! ከስጋ ደዌ፣ ከእብደት፣ ከቁምጥና፣ ከመጥፎ በሽታ በአንተ እጠበቃለሁ።››

- اللَّهُمَّ إِنِّي أَسْأَلُكَ الْعَفْوَ وَالْعَافِيَةَ فِي الدُّنْيَا وَالآخِرَةِ

አላሁምመ ኢንኒ አስአሉከል ዐፍወ ወል ዓፊየቲ ፊድዱንያ ወል ኣኺራ

‹‹አላህ ሆይ! ምህረትንና ጤንነትን በአለማዊ ህይወቴና በመጪው ዓለም እጠይቅሃለሁ።››

- اللَّهُمَّ إِنِّي أَسْأَلُكَ الْعَفْوَ وَالْعَافِيَةَ، فِي دِينِي وَدُنْيَايَ، وَأَهْلِي وَمَالِي

አላሁምመ ኢንኒ አስአሉከል ዐፍወ ወል ዓፊየቲ ፊ ዲኒይ፣ ወዱንያዬ፣ ወአህሊይ፣ ወማሊይ

‹‹አላህ ሆይ! ምህረትንና ጤንነትን በሃይማኖቴ፣ በአለማዊ ህይወቴ፣ በቤተሰቦቼና በገንዘቤ እጠይቅሃለሁ።››

- اللَّهُمَّ اسْتُرْ عَوْرَاتِي، وَآمِنْ رَوْعَاتِي، وَاحْفَظْنِي مِنْ بَيْنِ يَدَيَّ وَمِنْ خَلْفِي، وَعَنْ يَمِينِي، وَعَنْ شِمَالِي، وَمِنْ فَوْقِي، وَأَعُوذُ بِعَظَمَتِكَ أَنْ أُغْتَالَ مِنْ تَحْتِي

አላሁምመስቱር ዐውራቲ፤ ወኣምሚርረውዓቲ፤ ወህፊዝኒ ሚንበይኒ የደይዬ፣ ወሚን ኸልፊ፣ ወዐን የሚኒ፣ ወዐን ሺማሊ፣ ወሚን ፈውቂ፤ ወዐኡዙ ቢዐዞመቲከ አን ኡግታለ ሚን ተህቲ

‹‹አላህ ሆይ! ነውሮቼን ሸፍንልኝ፤ ፍርሃቴን አስወግድልኝ፤ አላህ ሆይ! ከበስተፊቴ ጠብቀኝ፤ ከበስተኋላየም ጠብቀኝ፤ ከስሬም እንዳልሞት በልዕልናህ እጠበቃለሁ፡፡››

- اللَّهُمَّ اغْفِرْ لِي خَطِيئَتِي وَجَهْلِي وَإِسْرَافِي فِي أَمْرِي وَمَا أَنْتَ أَعْلَمُ بِهِ مِنِّي

አላሁምመግፊርሊ ኸጢኣቲ፣ ወጀህሊ፣ ወኢስራፊ ፊአምሪ፤ ወማአንተ አዕለሙ ቢሂ ሚንኒ

‹‹አላህ ሆይ! ወንጀሌን፣ አለማወቄን፣ በጉዳዮ ድንበር ማለፌን፣ ከእኔ ይልቅ አንተ በምታውቀውም ነገሬ ምህረት አድርግልኝ፡፡››

- اللَّهُمَّ اغْفِرْ لِي جِدِّي وَهَزْلِي، وَخَطَئِي وَعَمْدِي، وَكُلُّ ذلِكَ عِنْدِي

አላሁምመግፊርሊ ጂዲይ፣ ወሀዝሊይ፣ ወኸጢኣቲይ፣ ወዐምዲይ፣ ወኢስራፊ፣ ወኩሉዛሊከ ዒንዲይ

‹‹አላህ ሆይ! ምሬንም፣ ቧልታዬንም፣ ወንጀሌንም፣ እያወኩ የሰራሁትን ስህተቴንም፣ ማባከኔንም፣ እኔ ዘንድ ያለውንም ሁሉ ምህረት አድርግልኝ፡፡››

- اللَّهُمَّ اغْفِرْ لِي مَا قَدَّمْتُ وَمَا أَخَّرْتُ، وَمَا أَسْرَرْتُ وَمَا أَعْلَنْتُ، وَمَا أَنْتَ أَعْلَمُ بِهِ مِنِّي، أَنْتَ الْمُقَدِّمُ وَأَنْتَ الْمُؤَخِّرُ وَأَنْتَ عَلَى كُلِّ شَيْءٍ قَدِيرٌ

አላሁምመግፊርሊ ማቀድደምቱ፣ ወማአኸኸርቱ፣ ወማአስረርቱ፣ ወማአዕለንቱ፣ ወማአንተ አዕለሙ ቢሂ ሚንኒ፤ አንተል ሙቀዲሙ፤ ወአንተል ሙአኺሩ፤ ወአንተ ዐላ ኩሊ ሸይኢን ቀዲር

‹‹አላህ ሆይ! ባስቀደምኩት፣ ባዘገየሁት፣ በደበቅኩት፣ ይፋ ባደረኩት፣ ከእኔ ይልቅ አንተ ከምታውቀው ነገር ምህረት አድርግልኝ፤ አንተ አስቀዳሚው፣ አዘግይው፣ አንተ በሁሉም ነገር ላይ ቻይ ነህ፡፡››

- اللَّهُمَّ إِنِّي أَسْأَلُكَ الثَّبَاتَ فِي الأَمْرِ، وَالْعَزِيمَةَ عَلَى الرُّشْدِ، وَأَسْأَلُكَ شُكْرَ نِعْمَتِكَ وَحُسْنَ عِبَادَتِكَ، وَأَسْأَلُكَ قَلْباً سَلِيماً وَلِسَاناً صَادِقاً، وَأَسْأَلُكَ مِنْ خَيْرِ مَا تَعْلَمُ، وَأَعُوذُ بِكَ مِنْ شَرِّ مَا تَعْلَمُ، وَأَسْتَغْفِرُكَ لِمَا تَعْلَمُ إِنَّكَ عَلَّامُ الْغُيُوبِ.

አላሁምመ ኢኒ አስአሉከሠባተ ፊልአምሪ፤ ወልዐዚመተ ዐለርሩሽዲ፤ ወአስአሉከ ሹክረ ኒዕመቲከ፤ ወሁስነ ዒባደቲከ፤ ወአስአሉከ ቀልበን ሰሊማ፤ ወሊሳነን ሷዲቃ፤ ወአስአሉከ ሚን ኸይሪ ማተዕለሙ፤ ወአዑዙ ቢከ ሚን ሸርሪ ማተዕለሙ፤ ወአስተግፊሩከ ሊማ ተዕለሙ፤ ኢንነከ ዐልላሙል ጉዩብ

‹‹አላህ ሆይ! በጉዳዮ ጽናትን፣ በቅኑ መንገድ ቁርጠኝነትን እጠይቅሃለሁ፤ እንዲሁም በዋልክልኝ ጸጋህ ማመስገንንና መልካም ዒባዳህን እጠይቅሃለሁ፤ ደህነኛ ቀልብን፣ እውነተኛ ምላስን እጠይቅሃለሁ፤ አንተ ከምታውቀው መልካም ነገር እጠይቅሃለሁ፤ አንተ ከምታውቀው መጥፎ ነገር በአንተ እጠበቃለሁ፤ አንተ ከምታውቀው ነገር ምህረት እጠይቃለሁ፡፡ አንተ ድብቁን ነገር አዋቂ ነህ፡፡››

- اللَّهُمَّ رَبَّ النَّبِيِّ مُحَمَّد - عَلَيْهِ الصَّلَاةُ وَالسَّلَامُ - اغْفِرْ لِي ذَنْبِي وَأَذْهِبْ غَيْظَ قَلْبِي، وَأَعِذْنِي مِنْ مُضِلَّاتِ الْفِتَنِ مَا أَبْقَيْتَنِي.

አላሁምመ ረብበንነቢይዪ ሙሀመዲን (ዐለይሂስሶላቱ ወስሰላም) አልሁምመግፊርሊ ዘንቢ፤ ወዝሀብ ገይዞ ቀልቢ፤ ወአዒዝኒ ሚን ሙዶልላቲል ፊተኒ ማአብቀይተኒ

«አላህ ሆይ! (ሰላምና እዝነት በእሳቸው ላይ ይስፈን ባቸውና) የነቢዩ ሙሀመድ ጌታ ነህ፤ አላህ ሆይ! ለወንጀሌ ምህረት አድርግልኝ፤ የቀልቤን ድንድንና አስወግድልኝ፤ እስካቆየኸኝ ድረስም፣ ከአጥማማኒ ፈታኝ ነገሮች ጠብቀኝ፡፡»

- اللَّهُمَّ رَبَّ السَّمَوَاتِ وَرَبَّ الْأَرْضِ وَرَبَّ الْعَرْشِ الْعَظِيم، رَبُّنَا وَرَبُّ كُلِّ شَيْءٍ، فَالِقُ الْحَبِّ وَالنَّوَى، مُنْزِلُ التَّوْرَاةِ وَالْإِنْجِيلِ وَالْقُرْآنِ، أَعُوذُ بِكَ مِنْ شَرِّ كُلِّ شَيْءٍ أَنْتَ آخِذٌ بِنَاصِيَتِه، أَنْتَ الْأَوَّلُ فَلَيْسَ قَبْلَكَ شَيْءٌ، وَأَنْتَ الْآخِرُ فَلَيْسَ بَعْدَكَ شَيْءٌ، وَأَنْتَ الظَّاهِرُ فَلَيْسَ فَوْقَكَ شَيْءٌ، وَأَنْتَ الْبَاطِنُ فَلَيْسَ دُونَكَ شَيْءٌ، اقْضِ عَنِّي الدَّيْنَ وَأَغْنِنِي مِنَ الْفَقْرِ

አላህምመ ረብቢስሰማዋቲ፣ ወረብቢልአርዲ፣ ወረብቢል ዐርሺል ዐዚም፤ ረብቡና ወረብቡ ኩልሊ ሸይኢን፤ ፋሊቂል ሀብቢ ወንነዋ፤ ሙንዚሊትተወራቲ፣ ወልኢንጂሊ፣ ወልቁርኣኒ፤ አንተል አውወሉ፤ ወለይሰ ቀብለከ ሸይኡን፤ ወአንተል ኣኺሩ፤ ፈለይሰ በዕደከ ሸይኡን፤ ወአንተዟሂሩ ፈለይሰ ፈውቀከ ሸይኡን፤ ወአንተል ባጢኑ ፈለይሰ ዱነከ ሸይኡን፤ ኢቅዲ ዐንኒድደይነ፤ ወአግኒኒ ሚነልፈቅሪ

«አላህ ሆይ! የሰባቱ ሰማያትና የግዙፉ ዐርሽ ጌታ ነህ፤ የእኛም ሁሉም ነገሮች ጌታ ነህ፤ ፍሬን፣ በቆልትን ፈልቃቂ፣ ተውራትንና ኢንጂልን እንዲሁም ፉርቃንን ያወረድከው አምላክ ነህ፤ በቁጥጥርህ ስር ካለው ሁሉ ነገር ክፋት በአንተ እጠበቃለሁ፤ አላህ ሆይ! አንተ የመጀመሪያ ነህ፤ ከአንተ በሁዋላ ምንም ነገር

አልነበረም፤ አንተ የመጨረሻ ነህ፤ ከአንተ በሁዋላ ምንም ነገር አይኖርም፤ አንተ ግልጽ ነህ፤ ከአንተ በላይ ምንም ነገር የለም፤ አንተ ስውር ነህ፤ ከአንተ ውጪ ምንም ነገር የለም፤ ዕዳችንን አቃልልን፤ ከድህነትም ገላግለን፡፡»

- اللَّهُمَّ أَعْطِ نَفْسِي تَقْوَاهَا ، وَزَكِّهَا أَنْتَ خَيْرُ مَنْ زَكَّاهَا ، أَنْتَ وَلِيُّهَا وَمَوْلَاهَا

አላሁምመ አዕጢ ነፍሲ ተቅዋሃ፤ ወዘክኪሃ አንተ ኸይሩ መንዘክካሃ፤ አንተ ወልይዩሃ ወመውላሃ

«አላህ ሆይ! ለነፍሴ ፍርሃተ-አላህን አጎናጽፋት፤ አንተ በላጩ አጥሪዋ ነህና አጥራት፤ አንተ የነፍሴ አለቃዋና አሳዳሪዋ ነህና፡፡»

- اللَّهُمَّ إِنِّي أَعُوذُ بِكَ مِنَ الْعَجْزِ ، وَالْكَسَلِ ، وَأَعُوذُ بِكَ مِنْ عَذَابِ الْقَبْرِ

አላህምመ ኢንኒ አዑዙቢከ ሚነል ዐጅዚ ወልከሰሊ፤ ወአዑዙቢከ ሚነልጁብኒ፣ ወልሀረሚ፣ ወልቡኽሊ፤ ወአዑዙቢከ ሚን ዐዛቢልቀብሪ

«አላህ ሆይ! ከመሳንና ከስንፍና፣ ከፍርሃት፣ ከመጃጀት፣ ከስስት፣ ከገሀነም እሳት በአንተ እጠበቃለሁ፡፡»

- اللَّهُمَّ لَكَ أَسْلَمْتُ ، وَبِكَ آمَنْتُ ، وَعَلَيْكَ تَوَكَّلْتُ ، وَإِلَيْكَ أَنَبْتُ ، وَبِكَ خَاصَمْتُ ، أَعُوذُ بِعِزَّتِكَ أَنْ تُضِلَّنِي ، لَا إِلَهَ إِلَّا أَنْت .أَنْتَ الْحَيُّ الَّذِي لَا يَمُوتُ وَالْجِنُّ وَالْإِنْسُ يَمُوتُونَ

አላሁምመ ለከ አስለምቱ፤ ወቢከ ኣመንቱ፤ ወዐለይከ ተወከከልቱ፤ ወኢለይከ አነብቱ፤ ወቢከ ኻሶምቱ፤ አዑዙ ቢዒዝዘቲከ አንቱዲልለኒ፤ ላኢላሃ ኢልላ አንተ፤ አንተል

ሀይዩ፤ አለዚ ላየሙቱ፤ ወልጂንኑ ወልኢንሱ የሙቱን፡፡

‹‹አላህ ሆይ! ለአንተ እጄን ሰጠሁ፤ በአንተ አመንኩ፤ በአንተ ላይ ተመካሁ፤ ወደ አንተ (ተጸጽቼ) ተመለስኩ፤ በአንተ (ማስረጃ) ሞገትኩ፡፡ በአንተ ታላቅነት እንዳታጠመኝ እጠበቃለሁ፤ ከአንተ ሌላ የሚመለክ የለም፤ አንተ የማትሞት ህያው ነህ፤ ጂኒዎችና ሰዎች ግን ይሞታሉ፡፡››

- اللَّهُمَّ إِنِّي أَعُوذُ بِكَ مِنْ عِلْمٍ لَا يَنْفَعُ، وَمِنْ قَلْبٍ لَا يَخْشَعُ، وَمِنْ نَفْسٍ لَا تَشْبَعُ، وَمِنْ دَعْوَةٍ لَا يُسْتَجَابُ لَهَا

አላሁምመ ኢንኒ አዑዙቢከ ሚን ዒልሚን ላየንፈዕ፤ ወሚንቀልቢን ላየኽሸዕ፤ ወሚን ነፍሲን ላተሸበዕ፤ ወሚን ደዕወቲን ላዩስተጃቡ ለሃ፡፡

‹‹አላህ ሆይ! ከማይጠቅም ዕውቀት፣ አንተን ከማይፈራ ቀልብ፣ ከማትጠግብ ነፍስና ተቀባይነት ከሌለው ዱዓ በአንተ እጠበቃለሁ፡፡››

- اللَّهُمَّ جَنِّبْنِي مُنْكَرَاتِ الْأَخْلَاقِ، وَالْأَعْمَالِ وَالْأَهْوَاءِ وَالْأَدْوَاءِ

አላሁምመ ጀንኒብኒ ሙንከራቲል አኽላቂ፣ ወልአዕማሊ፣ ወልአህዋኢ፣ ወልአድዋኢ፡፡

‹‹አላህ ሆይ! ከእኩይ ስነ ምግባር፣ ከመጥፎ ስራ፣ ከእኩይ ስሜትና ከመጥፎ በሽታ በአንተ እጠበቃለሁ፡፡››

- اللَّهُمَّ أَلْهِمْنِي رُشْدِي، وَأَعِذْنِي مِنْ شَرِّ نَفْسِي

አላሁምመ አልሂምኒ ሩሽዲ፤ ወአዒዝኒ ሚን ሸርሪ ነፍሲ፡፡

‹‹አላህ ሆይ ቅኑን መንገድ አመላክተኝ፤ ከነፍሴ እኩይነትም

ጠብቀኝ፡፡››

- اللَّهُمَّ اكْفِنِي بِحَلَالِكَ عَنْ حَرَامِكَ، وَأَغْنِنِي بِفَضْلِكَ عَمَّنْ سِوَاكَ

አላሁምመክፊኒ ቢሀላሊከ ዐን ሀራሚከ፤ ወአግኒኒ ቢፈድሊከ ዐምመን ሲዋከ፡፡

‹‹አላህ ሆይ! ከእርሙ ነገር ይልቅ በፍቅዱ ነገር መብቃቃትን ስጠኝ፤ በአንተ ትሩፋትም ከአንተ ውጪ ያለን አካል ከመለመን አብቃቃኝ፡፡››

- اللَّهُمَّ إِنِّي أَسْأَلُكَ الْهُدَى وَالتُّقَى، وَالْعَفَافَ وَالْغِنَى

አላሁምመ ኢንኒ አስአሉከል ሁዳ፣ ወትቱቃ፣ ወልዐፋፈ፣ ወልጊና፡፡

‹‹አላህ ሆይ! ቅኑን መንገድ፣ አንተን መፍራትን፣ መጥራራትንና መብቃቃትን እጠይቅሃለሁ፡፡››

- اللَّهُمَّ إِنِّي أَسْأَلُكَ الْهُدَى والسَّدَادَ

አላሁምመ ኢንኒ አስአሉከል ሁዳ፣ ወሰሰዳደ፡፡

‹‹አላህ ሆይ! ቅኑንና ትክክለኛውን መንገድ እንድትመራኝ እጠይቅሃለሁ፡፡››

- اللَّهُمَّ إِنِّي أَسْأَلُكَ مِنَ الْخَيْرِ كُلِّهِ عَاجِلِهِ وَآجِلِهِ مَا عَلِمْتُ مِنْهُ وَمَا لَمْ أَعْلَمْ، وَأَعُوذُ بِكَ مِنَ الشَّرِّ كُلِّهِ عَاجِلِهِ وَآجِلِهِ مَا عَلِمْتُ مِنْهُ وَمَا لَمْ أَعْلَمْ، وَأَسْأَلُكَ مِنْ خَيْرِ مَا سَأَلَكَ مِنْهُ عَبْدُكَ وَنَبِيُّكَ مُحَمَّدٌ .وَأَعُوذُ بِكَ مِنْ شَرِّ مَا اسْتَعَاذَ مِنْهُ عَبْدُكَ وَنَبِيُّكَ مُحَمَّدٌ

አላሁምመ ኢንኒ አስአሉከ ሚነል ኸይሪ ኩሊህ፤ ዓጂሊሂ፣ ወአጂሊሂ፤ ማዐሊምቱ ሚንሁ ወማለም አዕለም፤ ወአዑዙቢከ ሚነሸርሪ ኩሊህ ዓጂሊሂ፣ ወአጂሊሂ፤ ማዐሊምቱ ሚንሁ ወማለም አዕለም፤ ወአስአሉከ ሚን ኸይሪን፤ ማሰአለከ ሚንሁ ዐብዱከ፣ ወነቢይዩከ ሙሀመዱን (ሰ. ዐ. ወ)፤ ወአዑዙ ቢከ ሚን ሸርሪ መስተዓዘ ሚንሁ ዐብዱከ ወነብቢዩከ መሀመዱን (ሰ. ዐ. ወ)፡፡

«አላህ ሆይ! አሁንና ዘግይቶም፣ ካወቅኩትና ከማላውቀው እንዲሁም ከሁሉም መልካም ነገር አንተን እጠይቃለሁ፡፡ አሁንና ዘግይቶም፣ ካወቅኩትና ከማላውቀው እንዲሁም ከሁሉም መጥፎ ነገር በአንተ እጠበቃለሁ፡፡ ከመልካም ነገሮችም ባሪያህ የሆኑት ነቢዩ ሙሀመድ የጠየቁህን እኔም እጠይቅሃሉ፡፡ ከመጥፎ ነገሮችም ባሪያህ የሆኑት ነቢዩ ሙሀመድ እንድትጠብቃቸው ከጠየቁህ ነገርም እኔም እጠይቅሃለሁ፡፡»

- اللَّهُمَّ إِنِّي أَسْأَلُكَ الْجَنَّةَ وَمَا قَرَّبَ إِلَيْهَا مِنْ قَوْلٍ أَوْ عَمَلٍ، وَأَعُوذُ بِكَ مِنَ النَّارِ وَمَا قَرَّبَ إِلَيْهَا مِنْ قَوْلٍ أَوْ عَمَلٍ ، وَأَسْأَلُكَ أَنْ تَجْعَلَ كُلَّ قَضَاءٍ قَضَيْتَهُ لِي خَيْرًا

አላሁምመ ኢንኒ አስአሉከል ጀንነተ ወማ ቀርረበ ኢለይሃ ሚን ቀውሊን አው ዐመሊን፤ ወዐኡዙ ቢከ ሚነንናሪ ወማቀረበ ኢለይሃ ሚን ቀውሊን አው ዐመሊን፤ ወአስአሉከ አንተጅዐለ ኩልለ ቀዷኢን ቀዶይተሁ ሊ ኸይራ፡፡

«አላህ ሆይ! ወደ ጀነትና ወደ እሷ የሚቃርብ የሆነ ንግግርንና ስራን እጠይቅሃለሁ፡፡ አላህ ሆይ! ወደ እሳትና ወደ እሷ የሚቃርብ የሆነን ንግግርና ስራን በአንተ እጠበቃለሁ፡፡»

- لَا إِلَهَ إِلَّا اللَّهُ وَحْدَهُ لَا شَرِيكَ لَهُ ، لَهُ الْمُلْكُ وَلَهُ الْحَمْدُ ، يُحْيِي وَيُمِيتُ بِيَدِهِ الْخَيْرُ ، وَهُوَ عَلَى كُلِّ شَيْءٍ قَدِيرٌ.

سُبْحَانَ اللّه ، وَالْحَمْدُ للّه ، وَلَا إِلَهَ إِلَّا اللّهُ ، وَاللّه أَكْبَرُ ، وَلَا حَوْلَ وَلَا قُوَّةَ إِلَّا بِاللّهِ الْعَلِيِّ الْعَظِيم.

ላኢላሃ ኢልላለህ፤ ለሁል ሙልኩ ወለሁል ሀምዱ ወሁወ ዐላ ኩልሊ ሸይኢን ቀዲር፤ ሱብሃነላሂ፤ ወልሀምዱሊላሂ፤ ወላኢላሃ ኢለላህ፤ ወላሁ አክበር፤ ወላሃውለ ወላቁተ ኢልላ ቢላሂል ዐዚም፡፡

«ከአላህ ሌላ አምላክ የለም፤ ንግስናና ምስጋና በሁሉም ነገር ላይ ቻይ ለሆነው አላህ ነው፡፡ ከጉድለት መጥራትና ምስጋና ለአላህ ይገባው፤ ከአላህ ሌላ አምላክ የለም፤ አላህ ታላቅ ነው፤ ከታላቁ አላህ ውጪ ሀይልና ብልሃት ያለው የለም፡፡»

- اللَّهُمَّ صَلِّ عَلَى مُحَمَّد وَعَلَى آلِ مُحَمَّد كَمَا صَلَّيْتَ عَلَى إِبْرَاهِيمَ وَعَلَى آلِ إِبْرَاهِيمَ إِنَّكَ حَميدٌ مَجِيدٌ، وَبَارِكْ عَلَى مُحَمَّد وَعَلَى آلِ مُحَمَّد كَمَا بَارَكْتَ عَلَى إِبْرَاهِيمَ، وَعَلَى آلِ إِبْرَاهِيمَ إِنَّكَ حَمِيدٌ مَجِيدٌ

አላሁምመ ሶልሊ ዐላ ሙሀመድ፤ ወዐላ ኣሊ ሙሀመድ፤ ከማ ሶልለይተ ዐላ ኢብራሂም፣ ወዐላ ኣሊ ኢብራሂም፤ ኢንነከ ሀሚዱን መጂድ፤ ወባሪክ ዐላ ሙሀመድ፤ ወዐላ ኣሊ ሙሀመድ፤ ከማ ባረክተ ዐላ አብራሂም፣ ወዐላ ኣሊ ኢብራሂም ኢንነከ ሀሚዱን መጂድ፡፡

«አላህ ሆይ! በኢብራሂምና በኢብራሂም ቤተሰቦች ላይ እዝነትህን እንዳሰፈንከ ሁሉ፣ በሙሀመድ ላይና በሙሀመድ ቤተሰቦች ላይ እዝነትህን አስፍን፡፡ አንተ ምስጉን የላቅክ ነህና፡፡ አላህ ሆይ! በኢብራሂምና በኢብራሂም ቤተሰቦች ላይ ረድኤትህን እንዳደረክ ሁሉ፣ በሙሀመድና በቤተሰቦቹ ላይ ረድኤትህን አድርግ፡፡ አንተ ምስጉንና የላቅክ ነህና፡፡»

- رَبَّنا آتنا في الدنيا حسنة وفي الآخرة حسنة وقنا عذاب النار

ረበና ኣቲና ፊድዱንያ ሀሰነተን፤ ወፊልኣኺረቲ ሀሰነተን፤ ወቂና ዐዛበንናር፡፡

«ጌታችን፣ በዚህ ዓለም መልካምን ነገር ስጠን፤ በመጪውም ዓለም መልካምን ነገር ስጠን፤ ከእሳት ቅጣት ጠብቀን፡፡»

በዚህ ትልቅ ኢስላማዊ የሀጅ ስነ ስርዓት አጋጣሚ ሀጅ አድራጊው ቀደም ብለን የጠቀስናቸውን አዝካርና ዱዓዎች እየደጋገሙ ማለት ይወደድለታል፡፡ በውስጡም ዚክሮችን፣ ዱዓዎችንና በነቢዩ ላይ ሶለዋት ማድረስን የያዘን ሁሉ በዚህ አጋጣሚ ማለት ያስፈልጋል፡፡ ዱዓም ላይ ብርትት (ጽንት) ማለትና ከዱንያና ከኣኺራ መልካም ነገሮችም አላህን መጠየቅ አለበት፡፡ በእሳቸው ላይ የአላህ እዝነትና ሰላምታ ይሁንና የአላህ መልእክተኛ ዱዓ ሲያደርጉ ሶስት ሶስት ጊዜ ደጋግመው ነበር፡፡ ስለሆነም በዱዓ አደራረግ የእሳቸውን መንገድ መከተል ተገቢ ነው፡፡

በዚህ ትልቅ አጋጣሚ ሙስሊም ጌታውን ፈሪ፣ ለእሱ ተናናሽ፣ ተንበርካኪና አደግዳጊ መሆን ይጠበቅበታል፡፡ የአላህን እዝነትና ምህረት እንዲሁም ቁጣውንና የእሳት (ቅጣቱን) መፍራት አለበት፡፡ ራሱን (ነፍሱን) መተሳሰብ፣ ወደ አላህ የገባውን ንስኃ (ተውባ) ደጋግሞ ማደስ ይኖርበታል፡፡ ምክንያቱም ይህ ዕለት ታላቅ ዕለትና ግዙፍ የሆነ የሰዎች ስብስብም ነው፡፡ አላህም ለባሪያዎቹ ቱሩፋቱን የሚለግስበትም ዕለት ነው፡፡ አላህ በባሪያዎቹ ሁኔታ በመደሰቱም መላኢካ በክስተቱ እንዲደመሙ ይጋብዛቸዋል፡፡ ብዙ ሰዎችም ከእሳት ቅጣት ነጻ የሚሆኑበት ነው፡፡ ሰይጣን በበድር ዘመቻ የታየበትን ሁኔታ ሳጨምር፣ እጅግ በጣም ተሸናፊ፣ ኢምንትና ወራዳ ሆኖ የሚታይበት በዚህ የዐረፋ ዕለት ነው፡፡ ይህ የሆነው ሰይጣን አላህ በዕለቱ ለባሪያዎቹ ያለውን ቸርነትና

እነሱ የሚውልላቸውን ጸጋ በማየቱ ነው፡፡ እንዲሁም በብዛት ባሪያዎቹን ከእሳት ቅጣት ነጻ ሲያደርግና ለጥፋታቸው ምህረት ሲያደርግላቸው በማየቱም ጭምር ነው፡፡

ሙስሊም በትክክለኛ ዘገባው ዓኢሻን (ረ. ዐ) ጠቅሶ እንደዘገበው፣ የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ብለዋል፡-

- «ከቀናት ሁሉ አላህ ባሪያውን ከእሳት ቅጣት ነጻ የሚያደርግበት እንደ ዕለተ ዐረፋ የለም፡፡ አላህ በዚህ ጊዜ ወደ ባሪዎቹ ይቀርባል፡፡ በባሪያዎቹ ሁኔታ በመደሰቱም መላኢካ በክስተቱ እንዲደመሙ ይጋብዛቸዋል፡፡ እንዲህም ይላል፡- ‹እነዚህ ምን ፈልገው ነው (የተሰበሰቡት)?› »

ስለሆነም በዚህ ታላቅ ቀን አላህን መልካምን ነገር ከልባቸው ሊጠይቁት፣ ጠላታቸውን ሰይጣንን ሊያዋርዱት፣ ብዙ ዚክርና ዱዓእ እንዲሁም ወደ አላህ ንስኃ መግባትና እሱን ከሁሉም አይነት ወንጀሎችና ስህተቶች ምህረት መጠየቅን በማብዛት ሰይጣን እንዲያዝን ሊያደርጉት ይገባል፡፡

ሀጅ አድራጊዎች በዚህ ትልቅ አጋጣሚ ጸሀይ እስከምትገባ ድረስ አላህን ፈርተው በዚክርና በዱዓእ ሊባትሉ ይገባቸዋል፡፡ ጸሀይ ከገባች በኋላ ደግሞ ውስጣቸውና ውጫቸው ረጋ ብሎ ተልቢያ በማብዛት ወደ ሙዝደሊፋ ይጓዛሉ፡፡ እንደ አላህ መልዕክተኛ ተግባር በዚህ ጊዜ ምቹ በሆነበት ሁኔታ ፈጠን ብለው ይጓዛሉ፡ ፡ ነገር ግን ጸሀይ ከመግባቷ በፊት ወደ ሙዝደሊፋ መሄድ አይፈቀድም፡፡ ምክንያቱም የአላህ መልዕክተኛ ዐረፋ ላይ የቆሙት ጸሀይ እስክትገባ ድረስ ነውና፡፡ የአላህ መልዕክተኛ እንዲህም ብለዋል፡

- « ... ከእኔ የሀጅና የዑምራ አፈጻጸም ስነ ስርዓትን ልትይዙ ... ፡፡»

የአላህ መልዕክተኛ ይህንኑ ስለሆነ የፈጸሙት ሀጅ አድራጊዎቹ ሙዝደሊፋ የደረሱት በመግሪብ ሶላትም ይሁን በዒሻ ሶላት ሙዝደሊፋ እንደደረሱ ወዲያዉኑ በአንድ አዛንና በሁለት ኢቃም መግሪብን ሶላትን ሶስት ረክዓና ዒሻን ሶላትን ደግሞ ሁለት ረክዓ ይሰግዳሉ፡፡

ከብዙኃኑ ሙስሊሞች መካከል አንዳንዶቹ ከሶላት በፊት ሙዝደሊፋ ከደረሱበት ጊዜ ጀምሮ ለውርወራ የሚያስፈልጋቸውን ድንጋይ ይሰበስባሉ፡፡ እንደ ብዙዎቹ አስተሳሰብ ይህ ስራቸው በኢስላም የተደነገገ አድርገው ያስባሉ፡፡ ይሁን እንጅ ተግባራቸው የኢስላም መሰረት የሌለው ነው፡፡ የአላህ መልዕክተኛ ከመሽዐር ወደ ሚና ከተንቀሳቀሱ በኋላ እንጅ፣ ከዚያ ውጪ ለውርወራ ድንጋይ እንዲሰበሰብ አላዘዙም፡፡ አንድ ሰው የትም ባገኘው ድንጋይ መወርወር ስለሚችል፣ የግዴታ ሙዝደሊፋ ብቻ ባገኘው ጠጠር መወርወር አለብህ አይባልም፡፡ እንዲያውም ሚና ባገኘው ጠጠር ለውርወራ ሊጠቀምበት ይችላል፡፡

የአላህን መልዕክተኛ ድርጊት ከመከተል አንጻር፣ በዚህ ቀን ለ‹‹ጀምረተል ዐቀባ›› ውርወራ የሚሆኑ ሰባት ድንጋዮችን መያዝ ሱና ነው፡፡ አንድ ሰው በሶስቶቹ ቀናት ደግሞ በየቀኑ ሀያ አንድ ጠጠሮችን ሚና ላይ ይሰበስባል፡፡ በዚህም ሶስቱን የድንጋይ ውርወራ አይነቶች ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

ለውርወራ የሚጠቀምበትን ጠጠር ማጠቡ አይወደድም፡፡ እንዲያውም ምንም አይነት እጥበት ሳያስፈልግ ነው ውርወራው የሚካሄደው፡፡ ምክንያቱም ‹‹የአላህ መልዕክተኛ ለውርወራ የሚያገለግል ጠጠርን አጠቡ›› የሚል ከአላህ መልዕክተኛም ይሁን ከባልደረቦቻቸው የተገኘ መረጃ የለም፡፡

ዓኢሻ፣ ኡሙ ሰለማና ሌሎች በዘገቡት ሀዲስ መሰረት ሀጅ አድራጊዎቹ በዚህ ሌሊት ሙዝደሊፋ ላይ ያድራሉ፡፡ አቅመ ደካማ የሆኑ እንደ ሴቶች፣ ህጻናትና ሌሎች በሌሊቱ የመጨረሻ ክፍል

ወደ ሚና ሊጓዙ ይችላሉ፡፡ ነገር ግን ሌሎቹ ሀጅ አድራጊዎች ሙዝደሊፋ ላይ አድረውና ቆይተው የፈጅርን ሶላትም እዛው ሰግደው ወደ ሚና መንቀሳቀሳቸው የግድ ነው፡፡ ከዚያም እስኪማልድ ድረስ መሽዐረል ሐራም ላይ ቆመው ወደ ቂብላ በመዞር አላህን ያወሳሉ፣ ተክቢራና ዱዓእ ያበዛሉ፡፡ በዚህ ጊዜ ዱዓእ ላይ እጅን ወደ ላይ ማንሳት ይወደዳል፡፡ ለነገሩ ግን በዚህ ቦታ ቆመው የሚፈጽሙትን ተግባር ሙዝደሊፋ ላይ ቢፈጽሙት በቂ ይሆንላቸዋል፡፡

በዚህ ሁኔታ ወደ መሽዐረል ሀራም መቃረብም ሆነ ወደ ላይ መውጣት ግዴታ የለባቸውም፡፡ ምክንያቱም ሙስሊም ጃቢር ኢብኑ ዐብደላህን ጠቅሶ በዘገበው ሀዲስ፣ የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ብለዋል፡-

- «እኔ እዚህ (መሽዐረል ሀራም ላይ) ቆሜያለሁ፡፡ (የሙዝደሊፋ) ሁሉም ቦታ መቆሚያ ነው፡፡»

በጣም ከነጋጋ በኋላና ጸሀይ ከመውጣቷ በፊት ወደ ሚና ይሄዳሉ፡፡ በጉዟቸውም ላይ ተልቢያ እያበዙ መሄድ ያስፈልጋል፡፡ «ሙሀስሲር» ከሚባለው ቦታ ሲደርሱ (አላህ በዝሆን ባለቤቶች ላይ ቁጣውን የገለጸበት ቦታ ስለሆነ) ትንሽ ፈጠን ፈጠን ብሎ መሄድ ይወደዳል፡፡

ሚና ላይ «ጀምረተል ዐቀባ» ዘንድ እንደደረሱ ተልቢያ ማለታቸውን ያቋርጣሉ፡፡ ከደረሱበት ጊዜ ጀምሮም አከታትለው ሰባት ጠጠሮችን ይወረውራሉ፡፡ እያንዳንዱን ጠጠር እንደወረወሩም እጅን ማንሳትና ተክቢራ ማለት ያስፈልጋል፡፡ ከአላህ መልዕክተኛ ተግባር አንጻር ካዕባን በግራው፣ ሚናን ደግሞ በቀኙ በማድረግ «በጥነል ዋዲ» ላይ ሆኖ ይወረውራል፡፡ የተወረወረው ጠጠር ከቦታው ላይ እስካረፈ ድረስ በሌላ ጎን ላይ ሆኖ ጠጠሩን ቢወረውረው ችግር የለውም፡፡ በውርወራው ጊዜ የተወረወረው ጠጠር ከቦታው ላይ መድረሱ እንጅ፣ ከቦታው

አርፎ እዛው መቀመጡ እንደ ቅድመ ሁኔታ አይቆጠርም፡ ፡ ለምሳሌ፡- አንድ ሰው የወረወረው ጠጠር ከቦታው ካረፈ በኋላ ነጥሮ ከቦታው ወጥቶ ሌላ ቦታ ቢያርፍ፣ እንደ ዑለሞቹ ግልጽ አቋም መሰረት የዚህ ሰው ውርወራ ትክክል ነው፡፡ ይህን አቋም ካንጸባረቁት ዑለሞች መካከል ኢማሙ አን-ነወዊ አንዱ ናቸው፡፡ ይህን አቋማቸውንም ‹‹ሙሀዝዘብ›› በሚባለው መጽሀፋቸው ማብራሪያ ላይ አስፍረውታል፡፡ ጠጠር ሲባል ለውርወራ የሚያገለግለው ሲሆን፣ ከአንድ ፍሬ ትንሽ ከፍ ያለ ነው፡፡

የውርወራው ስነ ስርዓት ከተጠናቀቀ በኋላ ሀድዩን ያርዳል ወይም ይሰዋል፡፡ ወደ ቂብላ አድርጎ በሚያርድበት ጊዜም፣ ‹‹ቢስሚላሂ ወላሁ አክበር፤ አልላሁምመ ሀዛ ሚንከ ወለከ›› (ትርጉም፡- በአላህ ስም እጀምራለሁ፡፡ አላህም ታላቅ ነው፡፡ አላህ ሆይ! ይህ ከአንተ የተገኘና ወደ አንተ ነው) ማለት ይወደድለታል፡፡

በአስተራረድ በኩል ሱናው ግመል ከሆነ የፊት እግሩ ይታሰርና በቁሙ (ሳይጋደም) ይታረዳል፡፡ ከብትና ፍየል (በግ) ደግሞ በግራ ጎናቸው ተጋድመው ይታረዳሉ፡፡ በእርድ ጊዜ እንስሳቱን ወደ ቂብላ ሳያዞሩ ቢታረዱ፣ ሱናው ቀረ እንጅ፣ እርዱ ተቀባይነት ያለው ነው፡፡ ምክንያቱም በእርድ ጊዜ እንስሳቱን ወደ ቂብላ አዙሮ ማረድ ሱና እንጅ፣ ግዴታ አይደለምና፡፡ እርዱን ያቀረበው ሰው ካረደው እንስሳ፣ የተወሰነ ስጋ መብላቱ የተወደደ ነው፡፡ ከስጋውም ለሌሎች መስጠትና ስጋውንም ለምጽዋት ማድረግም የሚወደድ ተግባር ነው፡፡ አላህ በቁርአኑ እንዲህ ይላል፡-

- ﴿ فَكُلُوا۟ مِنْهَا وَأَطْعِمُوا۟ ٱلْبَآئِسَ ٱلْفَقِيرَ ﴿٢٨﴾ ﴾

‹‹ ... ከእርሷም ብሉ፤ ችግረኛ ድሃንም አብሉ፡፡›› (አል-ሀጅ፣ 28)፡፡

እንደ ትክክለኛው የዑለሞች አቋም መሰረት እርድ የሚከናወንበት

ጊዜ የሚቆይበት የጊዜ ርዝመት በአያመተሽሪቅ ሶስተኛው ቀን ላይ ጀምሮ እስከ ጸሀይ መግባት ድረስ ይቆያል፡፡ ይህ ማለት የእርድ ጊዜው፣ የሚታረድበት ዕለት (የውመነህር) እና ከእሱ በኋላ ሶስት ቀናትን የሚጨምር ይሆናል፡፡

ከእርድ በኋላ ሀጅ አድራጊው ጸጉሩን ይላጨዋል ወይም ያሳጥረዋል፡፡ ይሁን እንጅ መላጨቱ እጅግ በጣም በላጭ ነው፡፡ ምክንያቱም የአላህ መልዕክተኛ ጸጉራቸውን ለላጩት ሶስት ጊዜ አላህ እንዲያዝንላቸውና እንዲምራቸው ዱዓ ያደረጉ ሲሆን፣ ነገር ግን ጸጉራቸውን ላሳጠሩት አንድ ጊዜ ብቻ ነው አላህ እንዲያዝንላቸውና እንዲምራቸው ዱዓ ያደረጉላቸው፡፡ ጸጉርን በማሳጠር ጊዜ ከፊሉን የጸጉር ክፍል ብቻ ማሳጠር አይፈቀድም፡፡ ይልቅ ሁሉም የጸጉር ክፍል ነው ማጠር ያለበት፡፡ ሴት በአንጻሩ ጸጉሯን ሰብሰብ አድርጋ በመያዝ የጸጉሯን የአንድ ጣት አንድ ሶስተኛ መጠን ያህል በታች የሚሆነውን ትቆርጠዋለች፡፡

«ጀምረተል ዐቀባ» ከተወረወረ በኋላ እንዲሁም ጸጉሩን ከመላጨትና ከማሳጠር በኋላ ከሚስቱ ጋር የግብረ ስጋ ግንኙነት ማድረግ ሲቀር፣ ሀጅ አድራጊው ላይ ተጥሎ የነበረው ማዕቀብ (ተከልክሎ የነበረው ነገር) ይነሳለትና ሁሉንም ነገር ማድረግ ይፈቀድለታል፡፡ ይህ ክልከላ ተነስቶ ሀጅ አድራጊው የተፈቀደለትን ነገር ማድረግ ሲችል፣ «የመጀመሪያው መፈታት» (አትተሐሉሉል አወል) ይባላል፡፡ ከዚህ መፈታት በኋላ ሀጅ አድራጊው ሽቶ መጠቀም (መቀባት)፣ «ጦዋፈል ኢፋዷ» ለማድረግ ወደ መካ መሄድ ይፈቀድለታል፡፡ ዓኢሻ እንዲህ ትላለች፡-

- «እኔ የአላህን መልዕክተኛ ኢህራም ከማድረጋቸው በፊትና ከሀጅ ስራ ተፈተው (ስራቸውን ከቋጩ በኋላ) ካዕባን ጦዋፍ ከማድረጋቸው በፊት ሽቶ እቀባቸው ነበር፡፡» (ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል፡፡)

ይህ ጦዋፍ ጦዋፈል ኢፋዷ እና ጦዋፈ ዚያራ ይባላል፡፡ ይህ ጦዋፍ

የሀጅ ስራ ካለሱ የማይሟላበት የሀጅ ማዕዘን ነው፡፡ አላህም በሀጅ ምዕራፍ ቁጥር 29 ላይ ያወሳውም ይህንኑ ጦዋፍ ነው፡፡ አላህ እንዲህ ይላል፡-

- ﴿ ثُمَّ لْيَقْضُوا۟ تَفَثَهُمْ وَلْيُوفُوا۟ نُذُورَهُمْ وَلْيَطَّوَّفُوا۟ بِٱلْبَيْتِ ٱلْعَتِيقِ ﴿٢٩﴾ ﴾

‹‹ከዚያም (እንደ ጸጉርና ጥፍር ያሉትን) ትርፍ አካላቸውንና እድፋቸውን ያስወግዱ፤ ስለቶቻቸውንም ይሙሉ፤ በጥንታዊዉም ቤት ይዞሩ፡፡›› (አል-ሀጅ፣ 29)፡፡

ጦዋፍ አድርጎ ሁለት ረከዓ ሶላት ከመቃመ ኢብራሂም ኋላ ላይ ከሰገደ በኋላ በሀጅ ወቅት ዑምራ ማድረግና በዚያው ጊዜ ሀጅ መፈጸምን የሚያከናውን (ሙተመቲዕ) ከሆነ፣ በሶፋና በመርዋ መካከል ሰዕይ ያደርጋል፡፡ ይህ ሰዕዩ ግን ለሀጁ ሲሆን፣ የመጀመሪያው ሰዕዩ ደግሞ ለዑምራው ይሆናል፡፡ ዓኢሻ በዘገበችው ሀዲስ መሰረት በጣም ትክክለኛ እንደሆነው የዑለሞች አቋም፣ በዚህ ሁኔታ አንድ ሰዕይ ብቻ ማድረግ በቂ አይደለም፡፡ ዓኢሻ (ረ. ዐ) እንዲህ ትላለች፡-

- ‹‹ከአላህ መልዕክተኛ ጋር ወደ ሀጅ ሄድን ... የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ አሉ፡- ‹ሀድይ የያዘ ሰው ሀጅን ከዑምራ ጋር ለመፈጸም ተልቢያ ያድርግ፡፡ ከሁሉም የሀጅና የዑምራ ስራ ሙሉ ለሙሉ እስኪጨርስ ድረስ፣ የሀጅና የዑምራ ስራው ሙሉ ለሙሉ አይጠናቀቁም፡፡› ... በዑምራ ተልቢያ (ዑምራን ለመፈጸም ያሰቡት) ያደረጉት፣ በካዕባ ጦዋፍ፣ በሶፋና መርዋ ሰዕይ ያደርጋሉ፡፡ ከዚያም ስራቸውን ያጠናቅቃሉ፡፡ ከሚና ከተመለሱ በኋላ ግን ለሀጃቸው ሌላ ጦዋፍ ያደርጋሉ፡፡›› (ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል፡፡)

ዓኢሻ፣ «ከሚና ከተመለሱ በኋላ ለሀጅ ሌላ ጦዋፍ ያደርጋሉ» ስትል፣ ለዚህ ሀዲስ እንደተሰጠው ትክክለኛ ትርጓሜ መሰረት፣ «በሶፋና በመርዋ ጦዋፍ ማድረግ» ማለቷ ነው፡፡ ዓኢሻ ለማለት የፈለገችው፣ «ጦዋፈል ኢፋዷ ነው» ያሉ ሰዎች ሃሳባቸው ትክክል አይደለም፡፡ ምክንያቱም «ጦዋፈል ኢፋዷ» ሁሉም የሚሰራው የሀጅ ማዕዘንና እነሱም የተገበሩት ተግባር ነው፡፡ የእሷ ንግግር የሚመለከተው በሀጅ ወቅት ዑምራ ማድረግና በዚያው ጊዜ ሀጅ መፈጸምን የሚያከናውነውን (ሙተመቲዕ) ሰው ነው፡፡ ይህ ደግሞ የሀጅ ስራውን ለማሟላት ከሚና ከተመለሰ በኋላ ለሁለተኛ ጊዜ በሶፋና በመርዋ መካከል ጦዋፍ ማድረግ ነው፡፡ ምስጋና ለአላህ ይሁንና ጉዳዩ ግልጽ ነው፡፡ የብዙኃኑ ሙስሊም ሊቃውንትም አቋምም ነው፡፡

ይህ ሃሳብ ትክክል ለመሆኑ ተጨማሪ ማስረጃውም ቡኻሪ በትክክለኛው የሀዲስ ጥራዙ ተጨማሪ («ተዕሊቅ») አድረጎ በማያሻማ መልኩ ዘግቦታል፡፡ ኢብኑ ዐባስ (ረ. ዐ) በሀጅ ወቅት ዑምራ ስለማድረግና በዚያው ጊዜ ሀጅ መፈጸምን ስለማከናወን (ሙትዓ) ተጠየቁ፡፡ እንዲህም አሉ፡-

- «ሙሃጂሮች፣ አንሷሮችና የነቢዩ ባለቤቶች ሀጅን ለመፈጸም ሃሳባቸውን ገለጹ (ኢህላል) አደረጉ፡፡ እኛም ይህንኑ አደረግን፡፡ ወደ መካ እንደሄድን የአላህ መልዕክተኛ ፡- ‹ሀድይ የያዘ ሰው ሲቀር እንጅ፣ ሀጅ ለማከናወን ያደረጋችሁትን ሃሳብ (ኢህላል) ለዑምራ አድርጉት› አሉ፡፡ እኛም በካዕባ ጦዋፍ፣ በሶፋና መርዋ ሰዕይ አደረግን፤ ከሴቶቻችንም ደረስን (ግብረ ስጋ ግንኙነት አደረግን)፤ ልብሳችንንም ለበስን፡፡ የአላህ መልዕክተኛም ‹ሀድይ የያዘ ሰው ሀድዩ ከቦታው እስኪደርስ ድረስ የሀጅ ስራው ሙሉ ለሙሉ አይጠናቀቅም› (አይፈታም) አሉ፡፡ ከዚያም በዙል ሂጃ ስምንተኛው ቀን ላይ የምሽት ጊዜ ወደ ሀጅ ስራ ለመግባት ሃሳባችንን እንድንገልጽ (ኢህላል እንድናደርግ)

ታዘዝን፡፡ የሀጅ ስራንም እንደጨረስን መጣንና ካዕባን ጦዋፍ አደረግን፤ በሶፋና በመርዋም ሰዕይ አደረግን፡፡»

በዚህ ማስረጃ መሰረትና የማስረጃው ግልጽ የሆነው መልዕክቱ፣ በሀጅ ወቅት ዑምራ ማድረግና በዚያው ጊዜ ሀጅ እየፈጸ ያለ ሰው (ሙተመቲዕ) ሁለት ጊዜ ሰዕይ እንደሚያደርግ ነው፡፡ ትክክለኛውን ነገር የሚያውቀው እጅግ በጣም አዋቂው አላህ ነው፡፡

ሙስሊም ጃቢርን ጠቅሶ የዘገበው ሀዲስና «የአላህ መልዕክተኛና ባልደረቦቻቸው በሶፋና በመርዋ አንድ ጊዜ የመጀመሪያ ጦዋፍ እንጅ ሌላ ጦዋፍ አላደረጉም» የሚለው ሃሳብ ከአላህ መልዕክተኛ ባልደረቦች መካከል ሀድይ የያዘውን ነው የሚል፣ መልዕክት ያዘለ ነው፡፡ ምክንያቱም እነሱ በአንድ ላይ የሀጅንና የዑምራን ተግባር ሙሉ ለሙሉ እስኪያጠናቅቁ ድረስ በሀጅና በዑምራ ተግባራቸው (ኢህራማቸው) ቆይተዋልና ነው፡፡ እነሱ የሀጅና የዑምራ ተግባራቸውን ያጠናቀቁ እንኳ ቢሆኑም፣ የአላህ መልዕክተኛ ደግሞ ዑምራን ከሀጅ ስራ ጋር ለማከናወን ተልቢያ አድርገዋል፡ ፡ ሀድይ የያዘ ሰውም ሀጅን ከዑምራ ጋር ለማከናወን ሃሳቡን እንዲገልጽና፣ የሀጅንና የዑምራን ስራ ሙሉ ለሙሉ ማጠናቀቅ የሚቻለውም፣ ሁሉንም ተግባሮች ሙሉ ለሙሉ መፈጸም ሲቻል ነው፡፡ ነገር ግን ቀደም ብሎ የተወሳው ጃቢር ያስተላለፈውና ሌሎች ትክክለኛ ሀዲሶች እንደሚያመላክቱት፣ ሀጅና ዑምራን በአንድ ሃሳብ (ኒያ) አጣምሮ የሚያደርግ (ቃሪን) ሰው በእሱ ላይ ያለበት ነገር አንድ ጊዜ ብቻ ሰዕይ ማድረግ ነው፡፡

ልክ እንደዚሁ የሀጅን ተግባር የሀጅ ወቅት እስኪያበቃ ድረስ ሀጅን ብቻ ለማድረግ ኢህራም ያደረገ ሰው (ሙፍሪድ) እና እስከ እንስሳት ማረጃው ዕለት (የውመንነሕር) ድረስ በኢህራሙ የቆየ ሰው፣ በእሱ ላይ አንድ ሰዕይ ብቻ ነው ያለበት፡፡ ሀጅና ዑምራን በአንድ ሃሳብ (ኒያ) አጣምሮ የሚያደርግ (ቃሪን) ሰውና የሀጅን ተግባር የሀጅ ወቅት እስኪያበቃ ድረስ ሀጅን ብቻ ለማድረግ

ኢህራም ያደረገ ሰው (ሙፍሪድ) ከ‹‹ጦዋፈል ቁዱም›› (የመግቢያ ጦዋፍ) በኋላ ሰዕይ ካደረጉ፣ ከ‹‹ጦዋፈል ኢፋዷ›› በኋላ ሰዕይ ማድረግ አይጠበቅባቸውም፡፡ ይህ ጉዳይ እንግዲህ ዓኢሻ፣ ኢብኑ ዐባስና ጃቢር የዘገቧቸውን ሀዲሶች በአንድ ላይ በማጣመር ሀዲሶቹ ስሙሙ እንዲሆኑ የማድረግ ሂደት ነው፡፡ ይህ ሲሆን ደግሞ በሀዲሶቹ መካከል እርስ በርስ የመልዕክት መጣረስ እንዳይከሰት ያደርጋል፡፡ እንዲሁም ያለምንም ልዩነት በሀዲሶቹ የመስራት ዕድልን ይሰጣል፡፡

የሀዲሶቹን ጥምረት (ጀምዕ) ከሚደግፉ ነገሮች አንዱ ዓኢሻና ኢብኑ ዐባስ  የዘገቧቸው ሀዲሶች ሁለቱም ትክክለኛ ሀዲሶች መሆናቸው ነው፡፡ ሁለቱም ሀዲሶች በሀጅ ወቅት ዑምራ ለማድረግና በዚያው ጊዜ ሀጅን ለመፈጸም ለሚያስብ ሰው (ሙተመቲዕ) ሁለተኛ ሰዕይ የማድረግ ግዴታ እንዳለበት ያረጋግጣሉ፡፡ ይሁን እንጅ ጃቢር የዘገበው ሀዲስ ግልጽ መልዕክቱ ይህን መልዕክት ይቃረናል፡፡

የሀዲስን ትምህርት በሁለንተናዊ ዘርፉ የሚጠናው ‹‹ሙስጦለሐልሀዲስ›› እና በዒልመል ኡሱል የትምህርት  ዘርፍ እንደተረጋገጠው፣ አንድን መረጃ ተግባራዊ ለማድረግ ሁለት የማይስማሙ መልዕክቶች ሲጣረሱ፣ አንድን መልዕክት ትክክለኛነቱን የሚያረጋግጠው መረጃ (ሙሥቢት) መልዕክቱን ከሚቃረነው መረጃ (ነፍይ) በቀዳሚነት ተግባራዊ ይሆናል፡፡ ከጉድለት የጠራውና ከፍ ያለው አላህ ለትክክለኛው መንገድ መሪ ነው፡፡ ሀይልና ብልሃት ከአላህ እንጅ ከሌላ ወገን ዘንድ የለም፡፡

# ሀጅ አድራጊው እንስሳት በሚታረድበት ዕለት የሚሰራቸው በላጭ ተግባራት

ሀጅ አድራጊው እንስሳት (ግመል፣ በሬ፣ ፍየል) በሚታረድበት ዕለት ቀጣዮቹን አራት ተግባሮች በቅደም ተከተል ተግባራዊ ያደርጋል፡፡ እነሱም፡-

አንደኛ. በመጀመሪያ ‹‹ጀምረተል ዐቀባ››ን በመወርወር ይጀምራል፡፡

ሁለተኛ. እንስሳት ማረድ (ነሕር)

ሶስተኛ. ጸጉርን መላጨት ወይም ማሳጠር እና

አራተኛ. ካዕባን ጦዋፍ ማድረግ ሲሆን፣ ‹‹ሙተመቲዕ›› ለሆነ ሰው ከጦዋፍ በኋላ ሰዕይ ማድረግ ነው፡፡ እንደዚሁም ‹‹ሙፍሪድ›› እና ‹‹ቃሪን›› ለሆኑ ሰዎች ‹‹ጦዋፈል ቁዱም›› ሲያደርጉ ሰዕይ ካላደረጉ፣ አሁን ጦዋፍ ያደርጋሉ፡፡

ከአላህ መልዕክተኛ የማግራራት ማረጋገጫ በመገኘቱ እነዚህ አራት ነገሮች ቅደም ተከተላቸው እለፍ ተቀደም ሆነው ተግባራዊ ቢደረጉ ችግር የለውም፡፡ እንደዚሁም ሰዕይ ከጦዋፍ ቀድሞ ተግባራዊ ቢሆንም ችግር የለውም፡፡ ምክንያቱም እነዚህ ነገሮች እንስሳት በማረጃው ዕለት (የውመንነሕር) የሚፈጸሙ ተግባሮች ናቸውና፡፡ ጉዳዩ ከአላህ ባልደረባ ንግግር ውስጥ የተካተተ ነው፡፡ ቡኻሪ ዐብደላ ኢብኑ ዐምር ኢብነል ዓስን ጠቅሶ እንደዘገበው፣ የአላህ መልዕክተኛ በዕለቱ አራቱ ነገሮች ቅደም ተከተላቸው እየተቀያየረ ተግባራዊ በመደረጋቸው ሲጠየቁ፣ እንዲህ አሉ፡-

- «ስራው ችግር የለውም፡፡»

ይህ የቅደም ተከተል አማራጭ የተቀመጠው፣ ነገሮቹ በመርሳትና ባለማወቅ ቅደም ተከተላቸው የሚዛባበት ሁኔታ የሚጠበቅ ስለሆነ ነው፡፡ እንዲሁም በነገሮቹ ላይ የማግራራትና የማቅለል ስራም ለመስራት ነው፡፡ አቡ ዳውድ ኡሳማ ኢብኑ ሹረይኪን ጠቅሶ በትክክለኛ ዘገባ እንዳረጋገጠው፣ የአላህ መልዕክተኛ ከጦዋፍ በፊት ሰዕይ ስላደረገ ሰው ተጠይቀው ሲመልሱ እንዲህ ብለዋል፡-

- «...ችግር የለውም፡፡»

ከዚህ ነቢያዊ መልዕክት ግልጽ እንደሚሆነው፣ ጉዳዩ ያለምንም ጥርጥር ሁሉን አቀፍ ከሆነው ጉዳይ ውስጥ ገብቷል፡፡ ትክክለኛውን ነገር አጎናጻፊው አላህ ነው፡፡

አንድ ሀጅ አድራጊ ከሀጅ ስራ አፈጻጸሙ በሙሉ የሚያጠናቅቀው ቀጣዮቹን ሶስት ነገሮች ተግባራዊ ሲደርግ ነው፡፡ እነሱም፡-

አንደኛ. «ጀምረተል ዐቀባ»ን መወርወር

ሁለተኛ. ጸጉሩን መላጨት ወይም ማሳጠር

ሶስተኛ. ቀደም ብሎ ከተወሱት ነገሮች ቀጥሎ ጦዋፈል ኢፋዷ እና ሰዕይ ማድረግ ነው፡፡ አንድ ሀጅ አድራጊ እነዚህን ሶስት ነገሮች ከፈጸመ፣ ከዚህ በፊት በኢህራም ምክንያት ቀደም ብሎ የተከለከላቸው ከሚስቱ ጋር ግብረ ስጋ ግንኙነት ማድረግ፣ ሽቶ መጠቀምና ሌሎች ነገሮችን ሁሉ አሁን መስራት ይፈቀድለታል፡፡ (ይህ «አትተሐሉሉሥሣኒ ወልአኺር» ይባላል፡፡) ከእነዚህ ውስጥም ሁለቱን ነገሮች ከፈጸመ፣ ከሚስቱ ጋር ግብረ ስጋ ግንኙነት ማድረግ ሲቀር እንጅ፣ ቀደም ብሎ የተከለከላቸው ነገሮችን ሁሉ መስራት አሁን ይፈቀዱለታል፡፡ ይህ ሁኔታ «አትተሐሉሉል አወል» (የመጀመሪያ መፈታት) ይባላል፡፡

ሀጅ አድራጊ የዘምዘም ውሃን መጠጣትና ከውሃውም መያዝ (መሸከም) ይወደዳል፡፡ ጠቃሚ ዱዓእን ማድረግ የቻለ ሰው ዱዓ ቢያደርግ ጥሩ ነው፡፡ ከአላህ መልዕክተኛ እንደተዘገበው፣ የዘምዘም ውሃ ለጠጣው ሰው ሁሉ ጠቃሚ ነው፡፡ ሙስሊም አቢ ዘርን ጠቅሶ እንደዘገበው፣ የአላህ መልዕክተኛ ስለ ዘምዘም ውሃ እንዲህ ብለዋል፡-

- «የዘምዘም ውሃ የሚጣፍጥ ምግብ ነው፡፡»

አቡ ዳውድ በዘገበው ሀዲስ ደግሞ፣ የአላህ መልዕክተኛ ስለ ዘምዘም ውሃ እንዲህ ብለዋል፡-

- «ለበሽታ ፍቱን መድኃኒት ነው፡፡»

ከጦዋፈል ኢፋዷና ከሰዕይ በኋላ ሰዕይ ማድረግ የግዴታ ያለበት ሀጅ አድራጊ፣ ወደ ሚና በመሄድ እዛው (ሚና ላይ) ሶስት ቀን ከነሌሊቱ ይቆያል፡፡ ጸሀይ ዘንበል ካለች በኋላ በሶስቱ ቀናት በየዕለቱ ሶስቱን የጠጠር ውርወራ አይነቶች ተግባራዊ ያደርጋል፡፡ በውርወራው ጊዜ የውርወራውን ቅደም ተከተል መጠበቅ ግዴታ ነው፡፡ በውርወራው ጊዜ የውርወራው ቅደም ተከተል የሚከተለውን ይመስላል፡-

- መጀመሪያ ጀምረተል ኡላን ይወረዉራል፡- ጀምረተል ኡላ መስጂደል ኸይፍ አጠገብ የምትገኝ ሲሆን፣ ተከታታይነት ባለው መንገድ ሰባት ጠጠሮችን ይወረውራል፡፡ በእያንዳንዱ ጠጠር ውርወራ እጁን ወደ ላይ ያነሳል፡፡ ከእሷ ቀደም ማለቱ ሱና ሲሆን፣ እሷንም በግራው ያደርጋታል፡፡ በውርወራው ጊዜ ወደ ቂብላ ከመዞሩ በተጨማሪ አላህን ሲበዛ መፍራትና እጁን በማንሳት ዱዓእ ማብዛት ይኖርበታል፡፡

- ቀጥሎም እንደ መጀመሪያው «ጀምረተሥሣኒያ»ን

ይወረውራል፡፡ ከውርወራው በኋላ ትንሽ ቀደም ማለት ሱና ነው፡፡ በውርወራው ጊዜ እሷን በስተቀኙ ያደርጋል፡፡ በውርወራው ጊዜ ወደ ቂብላ ከመዞሩ በተጨማሪ እጁን በማንሳት ዱዓእ ማብዛት ይኖርበታል፡፡

- ከዚያም «ጀምረተሥሣሊሣ»ን ይወረውራል፡፡ በዚህ ጊዜ እሷ ዘንድ አይቆምም፡፡

በመጀመሪያው ቀን እንደ ወረወረው ሁሉ በያመተሽሪቅ በሁለተኛው ቀን ላይ ጸሀይ ዘንበል ካለች በኋላ ውርወራውን ይቀጥላል፡፡ የአላህን መልእክተኛ ምሳሌ ከማድረግ አንጻር «ጀምረተል ኡላ»ን እና «ጀምረተሥሣኒያ»ን በወረወረበት መንገድ ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

በአያመተሽሪቅ በመጀመሪያዎቹ ሁለት ተከታታይ ቀናት ላይ ጠጠሮችን መወርወር ከሀጅ ግዴታዎች መካከል አንዱ ግዴታ ነው፡፡ እንዲሁም እንስሳትን ውሃ የሚያጠጡ፣ የሚጠብቁ፣ አቅመ ደካሞች፣ ወዘተ ላይ ግዴታ አይደለም እንጅ፣ በሌላው ላይ በመጀመሪያዎቹ ሁለት ተከታታይ ቀናት ላይ ሚና ላይ ማደር ከሀጅ ግዴታዎች መካከል አንዱ ግዴታ ነው፡፡

ከዚያም በተወሱት ሁለት ተከታታይ ቀናት ጠጠሮችን ከወረወሩ በኋላ ቸኩሎ ሚናን መልቀቅ የፈለገ ሰው ጸሀይ ከመግባቷ በፊት መልቀቅ ይፈቀድለታል፡፡ ይሁን እንጅ ሚና ላይ መዘግየትና ሶስተኛውን ሌሊት ማደር የፈለገ ሰው በጊዜውም ጠጠሮችን ከወረወረ እጅግ በጣም በላጭና ምንዳውም እጅግ በጣም የላቀ ነው፡፡ አላህም እንዲህ ብሏል፡-

- ﴿ ۞ وَٱذۡكُرُواْ ٱللَّهَ فِيٓ أَيَّامٖ مَّعۡدُودَٰتٖۚ فَمَن تَعَجَّلَ فِي يَوۡمَيۡنِ فَلَآ إِثۡمَ عَلَيۡهِ وَمَن تَأَخَّرَ فَلَآ إِثۡمَ عَلَيۡهِۖ لِمَنِ ٱتَّقَىٰۗ وَٱتَّقُواْ ٱللَّهَ

﴿وَٱعۡلَمُوٓاْ أَنَّكُمۡ إِلَيۡهِ تُحۡشَرُونَ ٢٠٣﴾

«በተቆጠሩ ቀኖችም ውስጥ (በሚና ጠጠሮችን ስትወረውሩ) አላህን አውሱ፡፡ በሁለቱ ቀኖችም ውስጥ (በመሄድ) የተቻኮለ ሰው በእርሱ ላይ ሀጢአት የለበትም፡፡ (ይህም) አላህን ለፈራ ሰው ነው፡፡» (አል-በቀራ፣ 203)፡፡

የአላህም መልዕክተኛ እሳቸው ሳይቸኩሉ፣ የቸኮሉ ሰዎች ሚናን ለቀው እንዲሄዱ ፈቅደዉላቸዋል፡፡ እንዲያውም የአላህ መልዕክተኛ ባለመቸኮላቸው ሚና ላይ እስከ አስራ ሶስተኛው ቀን ቆይተው ጸሀይ ዘንበል ካለች በኋላ ጠጠሮችን ወርወረው የዙህርን ሶላት ከመስገዳቸው በፊት ሚናን ለቀው ሄደዋል፡፡

ጠጠር መወርወርን ለማይችል ህጻን አሳዳሪው ጀምረተል ዐቀባንና ሌሎቹን ውርወራዎች የእሱን ከወረወረ በኋላ ስለ ህጻኑ ሆኖ ሊወረውርለት ይችላል፡፡ ልክ እንደዚሁ ጠጠር መወርወርን ለማትችል ህጻን አሳዳሪዋ ጀምረተል ዐቀባንና ሌሎቹን ውርወራዎችን የእሱን ከወረወረ በኋላ ስለ ህጻኗ ሆኖ ሊወረውርላት ይችላል፡፡ ጃቢር (ረ. ዐ) እንዲህ ብሏል፡-

- «ከአላህ መልዕክተኛ ጋር ሀጅ አደረግን፡፡ ከእኛም ጋር ሴቶችና ህጻናት ስለነበሩ፣ ስለ እነሱ ተልቢያ (የሀጅ ዘክር) አልን፤ ስለ እነሱም ጠጠሮችን ወረወርን፡፡» (ኢብኑ ማጃህ ዘግቦታል፡፡)

በሽተኛ፣ አዛውንትና እርጉዝ ሴት አቅመ ደካማ በመሆናቸው ጠጠሮችን መወርወር ካልቻሉ ስለ እነሱ ሆኖ ጠጠሮችን የሚወረውርላቸው ሰው ሊወክሉ ይችላሉ፡፡ አላህ በቁርኣን እንዲህ ይላል፡፡-

- ﴿فَٱتَّقُواْ ٱللَّهَ مَا ٱسۡتَطَعۡتُمۡ ١٦﴾

«አላህንም የቻላችሁትን ያህል ፍሩት ... » (አት-ተጋቡን፣ 16፡ ፡)

እነዚህ አቅመ ደካሞች በጠጠሮች ውርወራ ጊዜ ሰው በሙብዛቱ የሠው መጨናነቅ ስለሚከሰት እነሱ በራሳቸው ጠጠሮችን መወርወር አይችሉም፡፡ በጠጠር መወርወሪያ ጊዜ ጠጠሩ ካልተወረወረ፣ በሌላ ጊዜ የሚካካስ አይደለም፡፡ ስለሆነም በዚህ ሁኔታ በሌሎቹ ሰዎች በተቃራኒ፣ ጠጠሮችን የሚወረውርላቸው ሰው ሊወክሉ ይችላሉ፡፡

አንድ ሀጅ ወይም ዑምራ አድራጊ ሌላው ቀርቶ የሚያደርገው ሀጅ ወይም ዑምራ ግዴታ እንኳ ባይሆንም፣ ስለሚያደርገው ሀጅ ወይም ዑምራ ሰውን ለመተካት መጠየቅ የለበትም፡፡ ምክንያቱም የሚያደርገው ሀጅ ወይም ዑምራ ግዴታ እንኳ ባይሆንም ሀጁን ወይም ዑምራውን ከጀመረ የጀመረውን ሀጅ ወይም ዑምራ መጨረስ ግዴታ አለበት፡፡ አላህ በቁርኣን እንዲህ ይላል፡-

• ﴿ وَأَتِمُّوا۟ ٱلْحَجَّ وَٱلْعُمْرَةَ لِلَّهِ ﴿١٩٦﴾ ﴾

«ሀጅንና ዑምራን ለአላህ ሙሉ ... ፡፡» (አል-በቀራ፣ 196)፡፡

ጦዋፍና ሰዕይ የሚፈጸምበት ጊዜ፣ የጠጠር ውርወራ እንደሚካሄድበት ጊዜ፣ ጊዜው የሚያልፍ አይደለም፡፡

ይሁን እንጅ በዐረፋ ላይ መቆም፣ ሚናና ሙዝደሊፋ ላይ ማደር ያለ ጥርጥር ጊዜያቸው ሊያልፍ የሚችሉ ተግባሮች ናቸው፡ ፡ ነገር ግን በቀጥታ ጠጠር በሚወረወርበት ቦታ አንጻር አቅመ ደካሞች በችግርም ቢሆን በእነዚህ ቦታዎች (በዐረፋ፣ በሚናና በሙዝደሊፋ) ላይ ቦታ የሚያገኙበት አጋጣሚ ይኖራል፡፡ ከሌሎቹ የኢህራም ስራዎች አንጻር፣ ጠጠር ውርወራን መፈጸም ለማይችሉ ሰዎች፣ ተግባሩ በሌላ ሰው በምትክ ሊሸፈን የሚችል መሆኑን ከቀደምት ደጋግ ሰዎች መረጃ ተገኝቷል፡፡

ዒባዳዎች እንደወረዱ ተግባራዊ ይሆናሉ እንጅ፣ ማንኛውም ሰው ያለ ማስረጃ ብድግ ብሎ ሊደነግጋቸው አይችልም፡፡ ጠጠሮችን እንዲወረወር ውክልና የተሰጠው ሰው መጀመሪያ ለራሱ ከዚያም ውክልና ለሰጠው ሰው ሶስቱን ጠጠር ውርወራዎች ማከናወኑ የሚፈቀድ ተግባር ነው፡፡ ሁለቱም ማለትም ውክልና የሰጠውና የተቀበለው ሰው ተግባራቸው አንድ ነው፡፡

እንደ ትክክለኛው የዑለሞች አቋም፣ ግዴታ ነው የሚል ማስረጃ ባለመገኘቱና ተግባሩን በሚፈጽመው አካል ላይ ችግርና መከራ የሚያስከትል በመሆኑም፣ ጠጠሮችን እንዲወረወር ውክልና የተሰጠው ሰው መጀመሪያ የራሱን ጨርሶ ከዚያም ውክልና የሰጠውን ሰው የጠጠር ውርወራ ተግባር መፈጸሙ ግዴታ አይደለም፡፡ አላህ በቁርኣኑ እንዲህ ይላል፡-

- ﴿وَمَا جَعَلَ عَلَيۡكُمۡ فِي ٱلدِّينِ مِنۡ حَرَجٖۚ ٧٨﴾

« ... በእናንተም ላይ በሃይማኖቱ ውስጥ ምንም ችግር አላደረገባችሁም ... ፡፡» (አል-ሀጅ፣ 78)፡፡

አነስ ኢብኑ ማሊክ (ረ. ዐ) እንዳስተላለፉት፣ የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ አሉ፡-

- « ... አግራሩ፤ አታጠባብቁ ... ፡፡» (ቡኻሪና ሙስሊም የዘገቡት፡፡)

የአላህ መልዕክተኛ ባልደረቦች ለህጻናታቸውና ለአቅመ ደካሞቻቸው ጠጠር በወረወሩበት አጋጣሚ እንዲህ አይነት ተግባር መፈጸማቸው በመረጃነት የተገኘ መረጃ የለም፡፡ እነሱ እንዲህ አይነቱን ተግባር ፈጽመውት ቢሆን ኖሮ፣ መረጃው ወደ ቀጣዩ ትውልድ ይደርስ ነበር፡፡ መረጃውንም ወደ ቀጣዩ ትውልድ ለማድረስ ጥረት ይደረግ ነበር፡፡

# እንስሳት መስዋዕት ማድረግ ግዴታ የሚሆንበት ‹‹ሙተመቲዕ›› እና ‹‹ቃሪን››

ሀጅ አድራጊው ‹‹ሙተመቲዕ›› ወይም ‹‹ቃሪን›› ከሆነና መስጂደል ሐራም ላይ ካልተገኙት መካከል ከሆነ፣ አንድ ፍየል ወይም ሰባት ግመል ወይም ሰባት በሬ ለእርድ ማቅረብ ግዴታ ይሆናል፡ ፡ ለእንስሳቱ የሚወጣው ገንዘብ በሀላል መንገድ ተሰርቶ የተገኘ ጥሩ ገንዘብ መሆን አለበት፡፡ ምክንያቱም አላህ መልካም ነውና ከመልካም ነገር ውጪ ሌላን ነገር አይቀበልም፡፡

ሰዎችን መጠየቅን የሚነቅፉና የሚያነዉሩ እንዲሁም በአንጻሩ ሰዎችን መጠየቅን ችላ ያለ ሰው የተወደሰ መሆኑን የሚያወሱ ብዙ ነቢያዊ ሀዲሶች ከነቢዩ ተላልፈዋል፡፡ አንድ ሙስሊም በስጦታም ይሁን በሌላ መልክ ከነገስታትም ሆኑ ከሌሎች ሰዎች የእነሱን ገንዘብ ከመሻት መራቅ አለበት፡፡ አላህ እሱን ገንዘቡን ለራሱ ጉዳይ እንዲያውለው ካገራለት፣ የሰዎችን እጅ ከማየት መታቀብ ይኖርበታል፡፡

‹‹ሙተመቲዕ›› ወይም ‹‹ቃሪን›› የሆነ ሰው ሀድይ ማቅረብ የሚሳነው ከሆነ ሶስት ቀናትን በሀጅ ቀናት እንዲሁም ሰባቱን ቀናት ወደ ቤተሰቦቹ ሲመለስ መጾም ግዴታ አለበት፡፡ ሶስት ቀናትን በሚጾምበት ጊዜ ምርጫ ይኖረዋል፡፡ ከፈለገ እንስሳት ለእርድ ከሚቀርቡበት ቀን በፊት ሊጾም፣ ወይም በሶስቶቹ የአያመተሽሪቅ ቀናት ሊጾም ይችላል፡፡ አላህ እንዲህ ብሏል፡-

- ﴿ وَأَتِمُّوا۟ ٱلْحَجَّ وَٱلْعُمْرَةَ لِلَّهِ ۚ فَإِنْ أُحْصِرْتُمْ فَمَا ٱسْتَيْسَرَ مِنَ ٱلْهَدْىِ ۖ وَلَا تَحْلِقُوا۟ رُءُوسَكُمْ حَتَّىٰ يَبْلُغَ ٱلْهَدْىُ مَحِلَّهُۥ ۚ فَمَن كَانَ مِنكُم مَّرِيضًا أَوْ بِهِۦٓ أَذًى مِّن رَّأْسِهِۦ

فَفِدْيَةٌ مِّن صِيَامٍ أَوْ صَدَقَةٍ أَوْ نُسُكٍۚ فَإِذَآ أَمِنتُمْ فَمَن تَمَتَّعَ بِٱلْعُمْرَةِ إِلَى ٱلْحَجِّ فَمَا ٱسْتَيْسَرَ مِنَ ٱلْهَدْيِۚ فَمَن لَّمْ يَجِدْ فَصِيَامُ ثَلَٰثَةِ أَيَّامٍ فِى ٱلْحَجِّ وَسَبْعَةٍ إِذَا رَجَعْتُمْۗ تِلْكَ عَشَرَةٌ كَامِلَةٌۗ ﴿١٩٦﴾

‹‹ ... እስከ ሀጅ በዑምራ የተጣቀመ ሰው ከሀድይ የተገራውን (መሰዋት) አለበት፡፡ ያላገኘም ሰው ሶስት ቀኖችን በሀጅ ወራት፣ ሰባትም በተመለሳችሁ ጊዜ መጾም አለበት፡፡ ይህቺ ሙሉ አስር (ቀናት) ናት፡፡ ይህም (ህግ) ቤተሰቦቹ ከቅዱሱ መስጂድ አቅራቢያ ላልሆኑ ነው ... ፡፡›› (አል-በቀራ፣ 196)፡፡

ቡኻሪ በትክክለኛው ዘገባው ዓኢሻንና ኢብኑ ዑመርን ጠቅሶ እንደዘገበው፣ ሁለቱ የአላህ መለዕክተኛ ባልደረቦች እንዲህ አሉ፡-

- ‹‹ሀድይ የሚያቀርበው ያጣ ሰው በቀር እንጅ፣ አያመተሸሪቅን (የዙል ሂጃ 11፣ 12 እና 13 ቀናት) እንዲጾሙ፣ የማግራራት ፈቃድ አልተደረገም፡፡››

ይህ መልዕክት ከአላህ መልዕክተኛ የመጣ ያህል ነው ቦታ የሚሰጠው፡፡ ለማንኛውም በዕለተ ዐረፋ ላይ ጾሙን የፈታ ሆኖ እንዲውል፣ የሶስቱን ቀናት ጾም ከዐረፋ ዕለት ቀደም አድርጎ መጾም ነው የሚገባው፡፡ ምክንያቱም የአላህ መልዕክተኛ በዕለተ ዐረፋ ሳጾሙ ቆመው ነው የዋሉት፡፡ እንዲሁም በዕለተ ዐረፋ መጾምን ከልክለዋል፡፡ በዚህ ቀን ሳይጾሙ መዋል በዚክርና በዱዓእ ንቁ ሆነው እንዲውሉ ያደርጋል፡፡

የሚጾሙትን ሶስቱን ቀናት ተከታታይ ወይም የተለያዩ አድርጎ መጾም ይቻላል፡፡ እንዲሁም ሰባቱ ቀናት የግዴታ ተከታትለው መጾም የለባቸውም፡፡ እንዲያውም ተከታትለው ወይም ተለያይተው ሊጾሙ ይችላሉ፡፡ ምክንያቱም አላህ እንዲሁም መላዕክተኛው ቀናቱ ተከታትለው እንዲጾሙ እንደ ቅድመ ሁኔታ ያስቀመጡት ነገር የለም፡፡ በላጩ ሰባቱን ቀናት ወደ ቤተሰብ

እስኪመለሱ ድረስ ማዘግየቱ ነው፡፡ አላህ እንዲህ ብሏል፡-

﴿وَسَبۡعَةٍ إِذَا رَجَعۡتُمۡۗ﴾

- « ... ሰባትም በተመለሳችሁ ጊዜ ... » (አል-በቀራ፣ 196፡፡)

ሀድይ ለማቅረብ አቅም የተሳነው (ገንዘብ የሌለው) ሰው ነገስታትን ወይም ሌሎች ባለስልጣናትን ለሀድይ ገንዘብ ከሚለምን ለእሱ መጾሙ ይሻለዋል፡፡ ነገር ግን አንድ ሰው ካለምንም ልመና ስጦታ ወይም በሌላ የእርዳታ መንገድ ገንዘብ ካገኘ፣ በዚህ መንገድ የተገኘው ገንዘብ ችግር የለውም፡፡ እንዲሁም አንድ ሰው እሱ ለሌላ ሰው ሀጅ ቢያደርግና ውክልና የሰጡት ሰዎችም ሀጅ ከሚያደርግበት ገንዘብ መካከል ሀድይ የሚገዛበትን ገንዘብ እንደቅድመ ሁኔታ ያላስቀመጠ ከሆነም፣ በዚህ መንገድ የተገኘው ገንዘብ ችግር የለውም፡፡ ይሁን እንጅ አንዳንድ ሰዎች በተወሰኑ ሰዎች ስም የሀድይ ገንዘብ ለማግኘት መንግስትን ወይም ሌሎች አካላትን መጠየቃቸው ውሸታም ናቸው፡፡ ይህ ድርጊት ያለምንም ጥርጥር ክልክልና በሀሰተኛ መንገድ ገንዘብ መብላት ነው፡፡ እኛንና ሙስሊሞችን ከእንዲህ አይነቱ ተግባር አላህ ይጠብቀን፡፡

# ሀጃጆችና ሌሎች ሰዎችን በመልካም የማዘዝና ከመጥፎ የመከልከል ግዴታ

ሀጅ በሚያደርጉና በሌሎች ሰዎች ላይ ከሁሉም በላይ ግዴታ ካለባቸው ነገሮች መካከል አንዱ በመልካም ነገር ማዘዝና ከመጥፎ ነገር መከልከል ነው፡፡ አላህ በቁርኣኑና መልዕክተኛውም በሱናቸው በገለጹበት መንገድ ግዴታ ሶላቶችን ጠብቆ መስገድም ሌላው ግዴታቸው ነው፡፡ ብዙዎቹ የመካና የሌላ አካባቢ ነዋሪዎች የግዴታ ሶላቶችን መስጂድ ላይ ከመስገድ ፋንታ፣ መስጂዶችን ችላ ብለው ከቤታቸው መስገዳቸው፣ ስህተትና ሸሪዓውን የሚጻረር ተግባር ነው፡፡ ከዚህ ተግባራቸው መከልከል አለባቸው፡፡ ሰዎች ወደ መልካም ነገር ሲጠሩ፣ መስጂድ ላይ ሶላትን በህብረት እንዲሰግዱ ማዘዝ ተገቢ ነው፡፡

ዐብደላህ ኢብኑ ኡሚ መክቱም ማየት የተሳነው (አይነ ስውር) እና ቤቱም ከመስጂዱ ሩቅ ሆኖ እያለ፣ የአላህ መልእክተኛን እቤቱ እንዲሰግድ ፈቃድ ጠየቃቸው፡፡ እሳቸውም የሚከተለውን ምላሽ መስጠታቸው ተረጋግጧል፡፡ አቢ ሁረይራ እንዳስተላለፉት፣ የአላህ መልእክተኛ እንዲህ ብለዋል፡-

«هَلْ تَسْمَعُ النِّدَاءَ بِالصَّلَاةِ؟ قَالَ: نَعَمْ. قَالَ فَأَجِبْ، مَا أَجِدُ لَكَ رُخْصَةً»

‹‹አዛን ትሰማለህን?›› አሉት፡፡ እሱም፣ ‹‹አዎ›› አለ፡፡ እሳቸውም፣ ‹‹ለጥሪው ምላሽ ስጥ (ወደ መስጂድ ና)›› አሉት፡፡ በሌላ የቡኻሪና የሙስሊም ዘገባ፣ አቢሁረይራን ጠቅሰው እንደዘገቡት፣ የአላህ መልእክተኛ ለኢብኑ ኡሚ መክቱም፡- ‹‹(በዚህ ጉዳይ) ለአንተ ከቤትህ የምትሰግድበት ፈቃድ አላገኘሁልህም›› ብለውታል፡፡

እንዲሁም ቡኻሪና ሙስሊም አቢ ሁረይራን ጠቅሰው በዘገቡት ሌላ የሀዲስ ዘገባ ደግሞ፣ የአላህ መልእክተኛ እንዲህ ብለዋል፡-

«لَقَدْ هَمَمْتُ أَنْ آمُرَ بِالصَّلَاةِ فَتُقَامَ، ثُمَّ آمُرَ رَجُلًا فَيَؤُمَّ النَّاسَ، ثُمَّ أَنْطَلِقَ إِلَى رِجَالٍ لَا يَشْهَدُونَ الصَّلَاةَ، فَأُحَرِّقَ عَلَيْهِمْ بُيُوتَهُمْ بِالنَّارِ»

«ሶላት ይሰገድ ዘንድ ትዕዛዝ ማስተላለፍን፣ ከዚያም ሶላትን የሚመራ ሰው ሰዎቹን ሶላቱን እንዲያሰግዳቸው ማዘዝን፤ ከዚያም የህብረትን ሶላት (መስጂድ) ላይ ወደማይገኙ ወንዶች ዘንድ በመሄድ ቤታቸውን በእሳት ማቃጠልን አሰብኩ» አሉ፡፡

ኢብኑ ማጂህ ኢብኑ ዐባስን ጠቅሶ በዘገበው መሰረት፣ የአላህ መልእክተኛ እንዲህ ብለዋል፡-

«مَنْ سَمِعَ النِّدَاءَ فَلَمْ يَأْتِ ، فَلَا صَلَاةَ لَهُ إِلَّا مِنْ عُذْرٍ»

«የአዛንን ጥሪ ሰምቶ ወደ መስጂድ ያልመጣ ሰው፣ (መስጂድ የማያስመጣው ሸሪዓዊ) ምክንያት እስከሌለው ድረስ፣ ሶላቱ ተቀባይነት የለውም፡፡»

በሌላ ትክክለኛ የሙስሊም ዘገባ መሰረት፣ ኢብኑ መስዑድ እንዲህ ብሉዋል፡- «ነገ (በዕለተ-ቂያማ) ሙስሊም ሆኖ፣ አላህን መገናኘትን የሚያስደስተው ሰው፣ የአዛን ጥሪ በሰማባቸው ቦታዎች ሁሉ እነዚህን አምስት ሶላቶችን ጠብቆ ይስገድ፡፡ አላህ ለነቢያችሁ ቅኑን መንገድ ደንግጎላቸዋል፤ እነዚህ ሶላቶች ከቅኑ መንገድ መካከል ተጠቃሽ ናቸው፡፡ ወደ ሁዋላ የሚቀረው ሰው ከቤቱ እንደሚሰግደው፣ እናንተ ከቤታችሁ ከሰገዳችሁ፣ የነቢያችሁን ፈለግ (ሱና) ተዋችሁ ማለት ነው፡፡ እናንተ የነቢያችንን ፈለግ (ሱና) ከተዋችሁ ደግሞ ትጠማላችሁ፡፡ አንድ ሰው ዉዱኡን

አሳምሮ ካደረገ በሁዋላ፣ ከእነዚህ መስጂዶች ወደ አንድ መስጂድ ይሄዳል፡፡ በዚህም አላህ በተራመደው እርምጃ ልክ ምንዳ ይጽፍለታል፤ ደረጃውም ከፍ ይላል፤ ወንጀሉም ይረግፍለታል፡ ፡ እኛ እንደታዘብነው ከህብረት ሶላት (ከጀመዓ ሶላት) ወደ ሁዋላ የሚቀረው፣ ሙናፊቅነቱ በግልጽ የሚታወቅበት እንጂ ሌላ አይደለም፡፡ የሆነ ሰው በሁለት ሰዎች ተደግፎ (መራመድ በቅጡ ባለመቻሉ) ወደ መስጂድ ይመጣ ነበር፡፡ ከዚያም ለሶላት በሶፍ መካከል ይቆማል፡፡››

ሀጅ በሚያደርጉና በሌሎች ሰዎች ላይ አላህ እርም ካደረገው ነገር መራቅ ይኖርባቸዋል፡፡ ይህም ከዝሙት፣ ከአንድ አይነት ጾታዊ ግንኙነት (ሊዋጥ)፣ ከስርቆት፣ ከወለድ (ሪባ)፣ የየቲምን ገንዘብ ከሙብላት፣ ከማጭበርበር፣ አደራን ከሙብላት፣ አስካሪን መጠጥ ከመጠጣት፣ ከማጨስ፣ ልብስን (ለወንድ) ከቁርጭምጪሚት በታች ከማድረግ፣ ከኩራት፣ ከምቀኝነት፣ ከዩይልኝ፣ ከሀሜት፣ ነገር ከማዋሰድ፣ በሙስሊም ከመሳለቅ፣ በሲዲዎች፣ በጊታር፣ በማሲንቅ፣ የመሳሰሉትን የሙዚቃ መሳሪያ መጠቀምና ሙዚቃንና መዝሙር በሬድዮና በሌሎች ነገሮች ከማዳመጥ፣ ቼዝ፣ ዳማና ቁማር ከመጫወት፣ የሰው ልጅንና ሌሎች ህይወት ያላቸውን ነገሮች (እንስሳት) ፎቶ ግራፍ ከማንሳት፣ ፎቶ ግራፍ እንዲነሱም ፈቃደኛም ከመሆን ከመሳሰሉት ተግባሮች መራቅ አለባቸው፡፡ እነዚህ ሁሉ አላህ በሁሉም ቦታና ዘመን የከለከላቸው መጥፎ ነገሮች ናቸው፡፡

ሀጅ የሚያደርጉና የበይቱላህ አል-ሀራም ነዋሪዎች ከሌላው ሰው በፊት እነሱ እነዚህን መጥፎ ነገሮች ሌላውን ሰው ሊከለክሉ ይገባቸዋል፡፡ ምክንያቱም በዚህ አማን በሆነ ሀገር የሚሰራ ወንጀል፣ ሌላ ቦታ ከሚሰራው ወንጀል የበለጠ ሲሆን፣ ቅጣቱም እጅግ በጣም የበረታ ነው፡፡ አላህ በቁርአን እንዲህ ይላል፡-

﴿وَمَن يُرِدْ فِيهِ بِإِلْحَادٍ بِظُلْمٍ نُّذِقْهُ مِنْ عَذَابٍ أَلِيمٍ﴾

‹‹ ...በመዘንበል በዳይ ሆኖ (ማንኛውንም ነገር)፣ የሚፈልግ ሰው፣ ከአሳማሚ ቅጣት እናቀምሰዋለን›› (አል-ሀጅ፣ 25)፡ ፡ አላህ በዚህ በተከበረ ቦታ ወንጀልን ለመስራት የፈለገን (ያሰበን) ሰው እንደዚህ ከዛተበት፣ ወንጀልን በሰራው ሰው ላይ የሚያደርስበት ቅጣት ምን ያህል ሊሆን ነው? ያለ ጥርጥር ቅጣቱ በጣም ትልቅና ብርቱ ነው፡፡ ከዚህ መጠ ንቀቅ ያስፈልጋል፡፡ ከሌሎቹም ወንጀሎች እንዲሁ መጠን ቀቅ ያስፈልጋል፡፡

ሀጅ የሚያደርጉ ሰዎች የሀጁን ሽልማት እንዲሁም ከወንጀሎች ምህረት የሚያገኙት፣ ከእነዚህ እላይ ከጠቀስናቸውና ከሌሎቹ አላህ ከከለከላቸው ወንጀሎች ሲጠነቀቁ ነው፡፡ ነቢዩ በሀዲሳቸው እንዲህ ብለዋል፡-

«مَنْ حَجَّ فَلَمْ يَرْفُثْ ، وَلَمْ يَفْسُقْ ، رَجَعَ كَيَوْمَ وَلَدَتْهُ أُمُّهُ»

‹‹ሀጅ ያደረገ ሰው፣ (በሀጅ ሰራው ወቅት) እርባና ቢስ (እንቶ ፈንቶ) ወሬ ካላወጋና ወንጀል ካልሰራ፣ ልክ እናቱ እንደወለደችው ሆኖ (ከወንጀል ነጻ ሆኖ) ይመለሳል፡፡››

ከእነዚህ በጣም መጥፎ ስራዎች መካከል ሙታንን መለመን፣ በጭንቅ ጊዜ እነሱን መማጸን፣ በእነሱ መሳል (ነዝር)፣ ለእነሱ ማረድ (መስዋት)፣ አላህ ዘንድ ያማልዱኛል ብሎ መከጀል ወይም በሽተኛን ያድኑልኛል ወይም የራቀውን ይመልሱልኛል፤ ወዘተ ብሎ መከጀል አላህ የከለከለው ትልቅ ሺርክ ነው፡፡ ይህ የጃሂሊያዎቹ ሙሽሪኮች እምነት ነው፡፡

አላህ መልእክተኞችን ልኳል፤ መጥፎን ነገር ለመንቀፍና ለመከልከልም መጽሀፍ አውርዷል፡፡ ስለሆነም እያንዳንዱ ሀጅ አድራጊና ሌላውም ከእነዚህ ወንጀሎች መጠንቀቅ አለበት፡፡ ከዚህ በፊትም መጥፎ ነገር ሰርቶ ከሆነ ወደ አላህ መመለስ (መቶበት) ይኖርበታል፡፡ ከቶበተም በሁዋላም እንደ አዲስ ሀጅ

ማድረግ አለበት፡፡ ምክንያቱም ትልቅ ሺርክ የተሰራን መልካም ስራ ሁሉ ስለሚያበላሽ ነው፡፡ አላህ በቁርአን እንዲህ ይላል፡-

﴿وَلَوْ أَشْرَكُواْ لَحَبِطَ عَنْهُم مَّا كَانُواْ يَعْمَلُونَ﴾

« ... ባጋሩም ኖሮ፣ ይሰሩት የነበሩት ከእነሱ በታበሰ ነበር» (አል-አንዓም፣ 88)፡፡

ከትንሹ ሺርክ አይነቶች መካከል ደግሞ ከአላህ ውጪ ባለ ነገር መማል፣ በነቢዩ፣ በካዕባ፣ በአደራ፣ በሌሎች ነገሮች መማል ትንሽ ሺርክ ናቸው፡፡ የዩልኝ፣ የይስሙልኝ፣ አንተና አላህ ከሻችሁ (ማሻ አላህ ወሺእተ) ማለት፣ አንተና አላህ ባትኖሩ እኮ (ለውለልላሁ ወአንተ) ማለት፣ ይህ ከአንተና ከአላህ ነው ማለት፣ ሌሎችንም መሰል አገላለጾች መጠቀም የትንሹ ሺርክ መገለጫ ናቸው፡፡ ከእነዚህ ንቅፍ ሺርካዊ ነገሮች መጠንቀቅ የግዴታ ነው፡፡ ሰዎችም እነዚህን ነገሮች እንዳይሰሩዋቸው መመካከር ግዴታ ነው፡፡

ኢብኑ ዑመር ባስተላለፉት ሀዲስ እንደተረጋገጠው፣ የአላህ መልእክተኛ እንዲህ ይላሉ፡-

«مَنْ حَلَفَ بِغَيْرِ اللّٰهِ فَقَدْ كَفَرَ أَوْ أَشْرَكَ»

«ከአላህ ሌላ ባለ ነገር የማለ ሰው፣ በእርግጥ ካደ ወይም ሺርክ ሰራ፡፡» (አህመድና ቲርሚዚ በትክክለኛ የዘገባ ሰንሰለት ዘግበውታል)፡፡ ኢብኑ ዑመር በትክክለኛ የሀዲስ ዘገባ እንዳስተላለፉት፣ የአላህ መልክተኛ እንዲህ ብለዋል፡-

«مَنْ كَانَ حَالِفًا فَلْيَحْلِفْ بِاللّٰهِ أَوْ لِيَصْمُتْ»

«አንድ ሰው የሚምል ከሆነ፣ በአላህ ይማል፤ ወይም ዝም ይበል፡፡» (ቡኻሪና ሙስሊም የዘገቡት)፡፡ እንዲሁም ደግሞ የአላህ መልእክተኛ እንዲህ ብለዋል፡-

«مَنْ حَلَفَ بِالْأَمَانَةِ فَلَيْسَ مِنَّا»

‹‹በአደራ የማለ ሰው፣ ከእኛ አይደለም (ትክክለኛ ሙስሊም አይደለም)፡፡›› (አቡ ዳውድ የዘገበው)፡፡

እንዲሁም በሌላ የኢማሙ አህመድ ዘገባም፣ የአላህ መልእክተኛ እንዲህ ብለዋል፡-

«أَخْوَفُ مَا أَخَافُ عَلَيْكُمُ الشِّرْكُ الأَصْغَرُ»

«እኔ እጅግ በጣም የምፈራላችሁ ነገር፣ ትንሹን ሺርክ ነው፡፡»

የአላህ መልእክተኛ ስለ ትንሹ ሺርክ ምንነት ሲጠየቁ፣ እሱ፣ ‹‹ይዩልኝ ነው›› አሉ፡፡ በሌላ ዘገባ የአላህ መልእክተኛ እንዲህ ብለዋል፡-

«لَا تَقُولُوا :مَا شَـآءَ اللّٰهُ وَ شَـآءَ فُلَانٌ، وَلَكِنْ قُولُوا : مَا شَـآءَ اللّٰه ، ثُمَّ شَـآءَ فُلَانٌ»

‹‹አላህና እገሌ ስለፈለጉ (ይህን ሰሩት) አትበሉ፡፡ ነገር ግን አላህ ከዚያም እገሌ ስለፈለገ (ይህን ሰራው) በሉ፡፡››

ኢብኑ ዐባስ እንዳስተላለፉትና ነሳኢይ በዘገበው ሀዲስ፣ የሆነ ሰው ለአላህ መልእክተኛ፣

‹‹በአላህና በመልእክተኛው መልካም ፈቃድ (ሆነ)›› አላቸው፡፡ የአላህ መልእክተኛም፣

«أَجَعَلْتَنِـي لِلّٰهِ نِدًّا ، بَلْ مَا شَـآءَ اللّٰهُ وَحْدَهُ»

‹‹አንተ እኔን ለአላህ አቻ ታደርገኛለህን? ይልቅ አላህ ብቻውን መልካም ፈቃዱ ሆነ›› በል አሉት፡፡

እነዚህ ነቢያዊ ሀዲሶች የአላህ መልእክተኛ ለተውሂድ ከፍተኛ ጥንቃቄና ጥበቃ የሚያደርጉ መሆናቸውንና ኡማቸውንም ከትልቁና ከትንሹ ሺርክ ያስጠነቀቁ ለመሆናቸውን ማሳያዎች

ናቸው፡፡ የዚህም ጥረታቸው ዓላማ ሙስሊሙ ህብረተሰብ ኢማኑ ጤናማ ሆኖ ከአላህ ቅጣት መድህን እንዲያገኝ ነው፡፡ እንዲሁም አላህን እንዲቆጣ ከሚያደርጉ ሰበቦችም እንዲርቅ ነው፡፡ በዚህም አላህን እጅግ በጣም የላቀ ምንዳቸውን ይስጣቸው፡፡ የአላህ መልእክተኛ የአላህን መልእክት በሚገባ አደረሱ፤ አስፈራሩ፡፡ ለአላህና ለባሪዎቹ መክረዋል፡፡ በእሳቸው ላይ እዝነትና ሰላም እስከ እለተ ትንሳኤ ድረስ ይስፈንባቸው፡፡

ሀጅ ከሚያደርጉ አዋቂዎችና አማን በሆነችው የአላህ ከተማ (መካ) እንዲሁም የአላህ እዝነት ይስፈንባቸውና በተከበሩት የአላህ መልዕክተኛ ከተማ (መዲና) በሚኖሩ ሰዎች ላይ አላህ ለሰዎች የደነገገውን ነገር ማስተማር ግዴታ አለባቸው፡፡ እነዚህ አካሎችም አላህ ከከለከለው የሺርክና የወንጀል አይነቶች እንዲርቁ እነሱን ሊያስፈራሩዋቸው ግዴታ አለባቸው፡፡ ሰዎች ከጨለማው ወደ ብርሃኑ ይወጡ ዘንድም ሃሳባቸውን በማስረጃም ሊገልጹትና አጥጋቢ አድርገውም ሊያብራሩት ግዴታ አለባቸው፡፡ ስለሆነም አላህ በእነሱ ላይ ግዴታ ያደረገባቸውን ኢስላምን ለሰዎች የማድረስና የማብራራት ግዴታ አለባቸው፡፡ አላህ በቁርኣኑ እንዲህ ይላል፡-

﴿وَإِذْ أَخَذَ ٱللَّهُ مِيثَٰقَ ٱلَّذِينَ أُوتُوا۟ ٱلْكِتَٰبَ لَتُبَيِّنُنَّهُۥ لِلنَّاسِ وَلَا تَكْتُمُونَهُۥ﴾

« ... አላህ የእነዚያን መጽሀፉን የተሰጡትን ቃል ኪዳን ለሰዎች በእርግጥ ታብራሩታላችሁ፤ አትደብቁትምም ... » (ኣሊ-ዒምራን፣ 187)፡፡

እንደዚህ አንቀጽ መልእክት ከሆነ፣ የመጽሀፍ ባለቤቶች ሀቅን በመደበቅ የሰሩትን ጥፋት (በደል)፣ የኡማው ሊቃውንት እነሱም በተራቸው አሁን ወይም ወደ ፊት ለሚገኝ ጥቅም ብለው፣ ኢስላማዊ ሃላፊነታቸውን ዘንግተው ይህን መንገድ እንዳይከተሉ

ማስጠንቀቂያ ነው፡፡ አላህ በቁርኣኑ እንዲህ ይላል፡-

﴿ إِنَّ ٱلَّذِينَ يَكۡتُمُونَ مَآ أَنزَلۡنَا مِنَ ٱلۡبَيِّنَٰتِ وَٱلۡهُدَىٰ مِنۢ بَعۡدِ مَا بَيَّنَّٰهُ لِلنَّاسِ فِي ٱلۡكِتَٰبِ أُوْلَٰٓئِكَ يَلۡعَنُهُمُ ٱللَّهُ وَيَلۡعَنُهُمُ ٱللَّٰعِنُونَ ١٥٩ إِلَّا ٱلَّذِينَ تَابُواْ وَأَصۡلَحُواْ وَبَيَّنُواْ فَأُوْلَٰٓئِكَ أَتُوبُ عَلَيۡهِمۡ وَأَنَا ٱلتَّوَّابُ ٱلرَّحِيمُ ﴾

‹‹እነዚያ ከአንቀጾችና ከቅን መምሪያ ያወረድነውን ለሰዎች በመጽሀፉ ከገለጽነው በኋላ የሚደብቁ፣ እነዚያ አላህ ይረግማቸዋል፤ ረጋሚዎችም ሁሉ ይረግሙዋቸዋል›› (አል-በቀራ፣ 159)፡፡

ቁርኣናዊ ማስረጃዎችና ነቢያዊ ሀዲሶች እንደሚያስረዱት፣ ወደ አላህ መንገድ ጥሪ ማድረግና ሰዎች የተፈጠሩለትን ዓላማ ማመላከት ወደ አላህ በጣም የላቀ ቅርበትና ኢስላማዊ ግዴታ ነው፡ ፡ ይህ ድርጊትም እስከ እለተ ትንሳኤ ድረስ የአላህ መልእክተኞችና የተከታዩቻቸው መንገድ ነው፡፡ አላህ በቁርኣን እንዲህ ይላል፡-

﴿ وَمَنۡ أَحۡسَنُ قَوۡلٗا مِّمَّن دَعَآ إِلَى ٱللَّهِ وَعَمِلَ صَٰلِحٗا وَقَالَ إِنَّنِي مِنَ ٱلۡمُسۡلِمِينَ ›› ﴾

‹‹ወደ አላህ ከጠራና መልካምንም ከሰራ፣ እኔ ከሙስሊሞች ነኝ ካለም ሰው ይበልጥ ቃሉ ያማረ ማን ነው?›› (ፉሲለት፣ 33)፡፡ በሌላ የቁርኣን አንቀጽም፡-

﴿ قُلۡ هَٰذِهِۦ سَبِيلِيٓ أَدۡعُوٓاْ إِلَى ٱللَّهِۚ عَلَىٰ بَصِيرَةٍ أَنَا۠ وَمَنِ ٱتَّبَعَنِيۖ وَسُبۡحَٰنَ ٱللَّهِ وَمَآ أَنَا۠ مِنَ ﴾

‹‹ይህቺ መንገዴ ናት፤ ወደ አላህ እጠራለሁ፤ እኔም የተከተለኝም ሰው፣ በግልጽ ማስረጃ ላይ ነን፤ ጥራትም ለአላህ ይገባው፤ እኔም ከአጋሪዎቹ አይደለሁም በል›› (ዩሱፍ፣ 108)፡፡

አቢ መስዑድ እንዳስተላለፉት፣ የአላህ መልእክተኛ እንዲህ ብለዋል፡-

«مَنْ دَلَّ عَلَى خَيْرٍ فَلَهُ مِثْلُ أَجْرِ فَاعِلِهِ»

‹‹በመልካም ነገር ያመላከተ ሰው፣ ለእሱ መልካሙን ነገር እንደሰራው ሰው አምሳያ ምንዳ አለው፡፡›› በሌላ ትክክለኛ የሙስሊም ዘገባ፣ የአላህ መልእክተኛ ለዐሊይ (ኢብኑ አቢ ጧሊብ) እንዲህ ብለውታል፡-

«لَأَنْ يَهْدِيَ اللهُ بِكَ رَجُلًا وَاحِدًا خَيْرٌ لَكَ مِنْ حُمْرِ النَّعَمِ»

‹‹በአንተ ምክንያት አላህ አንድን ሰው ቅኑን መንገድ ቢመራው፣ ለአንተ ከቀይ ግመል (ምጽዋት ከመስጠት) የበለጠ ነው፡፡›› የዚህን ሀዲስ ትክክለኛነት ቡኻሪና ሙስሊም በጋራ ተስማምተውበታል፡ ፡ በዚህ ርዕስ ጉዳይ የሚያትቱ ነቢያዊ ሀዲሶች በርካታ ናቸው፡፡

እንደ እውነታው ከሆነ የእውቀት ባለቤቶችና አማኞች ወደ አላህ መንገድ (ወደ ኢስላም) ጥሪ ለማድረግ የሚያደርጉትንና ሰዎችን መድህን ወደሚያገኙበት ሰበብ ማመላከት የሚያደርጉትንም ጥረት ማጠናከርና የጥፋት ምክንያቶችንም ማስጠንቀቅ ይገባቸዋል፡ ፡ በተለይም በዚህ ዘመን ስሜትን መከተል ባየለበት፣ አፍራሽ አመለካከቶችና ጥመትን የሚሰብኩ ጠሪዎች (መግለጫዎች፣ ማስታወቂያዎች) በተስፋፉበት ሰዎችን ከመጥፎ ነገሮች ማስጠንቀቅ ተገቢ ነው፡፡ ነገር ግን ወደ ቅኑ መንገድ (ወደ ኢስላም) ጥሪ የሚያደርጉ ሰዎች ቁጥር አናሳ ነው፡፡ በተቃራኒው ግን ከህደትና ሁሉን ነገር ፍቅድ የሚያደርገው ወገን አቁዋም (ኢባሂያ) ጥሪ አድራጊዎች አያሌ ናቸው፡፡ አጋዣችን አላህ ነው፡፡ ብልሃትና ሀይል፣ ከፍ ያለና ታላቅ የሆነው የእሱ የአላህ ብቻ ነው፡፡

# አላህን በመገዛት ስንቅ መሰነቅ

ሀጅ ለሚያደርጉ ሰዎች መካ እስከቆዩበት ጊዜ ድረስ አላህን ማውሳት፣ እሱን መታዘዝና መልካም መስራት ይወደድላቸዋል፡ ፡ በሀረም ውስጥ መልካም ስራ እጥፍ ድርብ ሆኖ የሚመዘገብ በመሆኑ ሶላትን፣ በካዕባ ጦዋፍንና በአላህ መልዕክተኛው ላይ ሶለዋትን ማብዛት ያስፈልጋል፡፡ በተቃራኒውም ሀረም ውስጥ መጥፎ ስራ እጥፍ ድርብ ሆኖ የሚመዘገብበት ቦታ ነው፡፡

ሀጅ አድራጊዎች ከመካ መውጣት ሲፈልጉ ካዕባ የሀጅ የመጨረሻ መሰናበቻ ይሆንላቸው ዘንድ ካዕባ ላይ ‹‹ጦዋፈል ወዳዕ›› (የመሰናበቻ ጦዋፍ) ማድረግ ግዴታ አለባቸው፡፡ በዚህ ጊዜ የወር አበባ ደምና የወሊድ ደም የተከሰተባቸው ሴቶች እነሱ ‹‹ጦዋፈል ወዳዕ›› (የመሰናበቻ ጦዋፍ) ማድረግ ግዴታ የለባቸውም፡፡ ኢብኑ ዐባስ እንዲህ ይላል፡-

- ‹‹ሰዎች (በሀጅና በዑምራ ስራ) የመጨረሻ መሰናበቻቸው ካዕባ ላይ እንዲሆን ታዘዋል፡፡ ይሁን እንጅ ይህ ግዴታ የወር አበባ ደም በተከሰተባት ላይ ተቃሎላታል (ግዴታው ተነስቶላታል)፡፡›› (ቡኻሪና ሙስሊም ዘገባው ትክክል ነው ብለዋል፡፡)

ሀጅ አድራጊው ካዕባን ከተሰናበተ በኋላ ከመስጂድ መውጣት ከፈለገ፣ ወደ ፊት ይሄዳል እንጅ፣ የኋልዮሽ እየተራመደ ከመስጂድ መውጣት የለበትም፡፡ ይህ አይነቱ ድርጊት ከአላህ መልዕክተኛ አልተወሰደምና፡፡ እንዲያውም አዲስ መጤ ዒባዳ (ቢድዓ) ነው፡፡ ዓኢሻ ባስተላለፈችው፣ የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ብለዋል፡-

- ‹‹የእኛ ትዕዛዝ የሌለበትን ስራ የሰራ ሰው፣ ስራው ተመላሽ ነው፡፡›› (ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል፡፡)

እንዲሁም፣ ዒርባድ ኢብኑ ሳሪያ ባስተላለፈው፣ የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ብለዋል፡-

- ‹‹አዳዲስ መጤ ነገሮችን አደራችሁን፡፡ አዲስ ሁሉ መጤ ዒባዳ ነው፡፡ አዲስ መጤ ዒባዳ ሁሉ ጥመት ነው፡፡›› (ኢማሙ አህመድና አቡ ዳውድ ዘግበውታል፡፡)

አላህ በሃይማኖታችን ጽናትን እንዲሰጠንና ዲኑን ከሚጻረሩ ወገኖች እንዲጠብቀን እንጠይቀዋለን፡፡ እሱ ቸርና ለጋስ ነው፡፡

# ጉብኝት፣ ህጉና ስርዓቱ

መዲና የሚገኘውን የነቢዩን መስጂድ ከሀጅ በፊትና በሁዋላ መጎብኘት (ዚያራ) ሱና ነው፡፡ አቡ ሁረይራ እንዳስተላለፉት፣ የአላህ መልእክተኛ እንዲህ ብለዋል፡-

«صَلَاةٌ فِي مَسْجِدِي هَذَا ، خَيْرٌ مِنْ أَلْفِ صَلَاةٍ فِيمَا سِوَاهُ، إِلَّا الْمَسْجِدَ الْحَرَامَ»

‹‹መስጂደል ሀራም የተሰገደው ሶላት ሲቀር፣ ከዚህ ከእኔ (መዲና) መስጂድ አንድ ሶላት መስገድ፣ ከሌላው መስጂድ አንድ ሶላት ከመስገድ በአንድ ሽ ሶላት የበለጠ ነው፡፡›› (ቡኻሪና ሙስሊም የዘገቡት)፡፡

ኢብኑ ዑመር እንዳስተላለፉት፣ ደግሞ፣ የአላህ መልእክተኛው እንዲህ ብለዋል፡-_

«صَلَاةٌ فِي مَسْجِدِي هَذَا أَفْضَلُ مِنْ أَلْفِ صَلَاةٍ فِيمَا سِوَاهُ، إِلَّا الْمَسْجِدَ الْحَرَامَ»

‹‹መስጂደል ሀራም (የተሰገደው ሶላት) ሲቀር፣ ከዚህ ከእኔ መስጂድ አንድ ሶላት መስገድ፣ ከሌላው መስጂድ በአንድ ሽ ሶላት በላጭ ነው፡፡›› (ሙስሊም የዘገበው)፡፡ አብደላህ ኢብኑ ዙበይር እንዳስተላለፈው፣ የአላህ መልእክተኛ እንዲህ ብለዋል፡-

«صَلَاةٌ فِي مَسْجِدِي هَذَا أَفْضَلُ مِنْ أَلْف صَلَاة فيمَا سوَاهُ إِلَّا الْمَسْجِدَ الْحَرَامَ ، وَصَلَاةٌ فِي الْمَسْجِدِ الْحَرَامِ أَفْضَلُ مِنْ مِائَةِ صَلَاةٍ فِي مَسْجِدِي هَذَا»

‹‹መስጂደል ሀራም (የተሰገደው ሶላት) ሲቀር፣ ከዚህ ከእኔ መስጂድ አንድ ሶላት መስገድ፣ ከሌላው መስጂድ በአንድ ሽ ሶላት በላጭ ነው፡፡ መስጂደል ሀራም የሚሰገደው ሶላት፣ ከዚህ (መስጂደ-ነበዊ) ከሚሰገደው ሶላት በመቶ ሶላት በላጭ ነው፡፡›› (አህመድ፣ ኢብኑ ኹዘይማና ኢብኑ ሂባን ዘግበውታል)፡፡

ጃቢር እንዳስተላለፉት፣ የአላህ መልእክተኛ እንዲህ ብለዋል፡-

«صَلَاةٌ فِي مَسْجِدِي هَذَا أَفْضَلُ مِنْ أَلْفِ صَلَاةٍ فِيمَا سِوَاهُ، إِلَّا الْمَسْجِدَ الْحَرَامَ ، وَصَلَاةٌ فِي الْمَسْجِدِ الْحَرَامِ أَفْضَلُ مِنْ مِائَةِ أَلْفِ صَلَاةٍ فِيمَا سِوَاهُ»

‹‹ከእኔ መስጂድ አንድ ሶላት መስገድ፣ ከሌላው መስጂድ አንድ ሶላት ከመስገድ በአንድ ሽ ሶላት በላጭ ነው፡፡ መስጂደል ሀራም (ከሚሰገደው ሶላት) ሲቀር እንጂ፡፡ መስጂደል ሀራም የሚሰገደው አንድ ሶላት ከሌላ ቦታ ከሚሰገደው አንድ ሶላት፣ በመቶ ሽ ሶላት በላጭ ነው፡፡›› (አህመድና ኢብኑ ማጃህ ዘግበውታል)፡፡

የነቢዩን መስጂድ ለመጎብኘት የፈለገው ሰው ወደ መስጂዱ ደርሶ፣ እንዲሁም ወደ መስጂዱ ሲገባ ቀኝ እግሩን ማስቀደም ይወደድለታል፡፡ ሲገባም እንዲህ ይላል፡-

«بِسْمِ اللّٰهِ وَالصَّلَاةُ وَالسَّلَامُ عَلَى رَسُولِ اللّٰهِ، أَعُوذُ بِاللّٰهِ الْعَظِيمِ وَبِوَجْهِهِ الْكَرِيمِ، وَسُلْطَانِهِ الْقَدِيمِ، مِنَ الشَّيْطَانِ الرَّجِيمِ، اللَّهُمَّ افْتَحْ لِي أَبْوَابَ رَحْمَتِكَ»

‹‹ቢስሚላሂ፤ ወሰላሙ ዐላ ረሱሊላሂ፤ አዑዙ ቢላሂል ዐዚም፤ ወቢወጅሂሂል ከሪም፤ ወሱልጡዋኒሂል ቀዲም፤ ሚነሽይጧኒረጂም፡፡››

‹‹በአላህ ስም፣ ሰላም በአላህ መልእክተኛ ላይ ይስፈን፤ ታላቅ በሆነው አላህ፣ በተከበረው ፊቱና መጀመሪያ በሌለው ስልጣኑ አሳሳች ከሆነው ሰይጣን እጠበቃለሁ፡፡›› (አህመድ ኢብኑ ማጃህ ዘግበውታል)፡፡

«اللَّهُمَّ افْتَحْ لِي أَبْوَابَ رَحْمَتِكَ»

‹‹አላሁምመፍተህሊ አብዋበ ረህመቲከ፡፡›› ‹‹አላህ ሆይ! የእዝነት በሮችህን ክፈትልኝ፡፡›› (አህመድ ኢብኑ ማጃህ ዘግበውታል)፡፡ ይህ ማለት ከሌላው መስጂድ ሲገባ የሚለውን ዱዓ ይላል ማለት ነው፡፡ ወደ ነቢዩ መስጂድ (የመዲናው መስጂድ) ለመግባት የተለየ ዱዓ የለም፡፡

ወደ መስጂዱ የገባ ሰው ሁለት ረከዓ ሶላቶችን ይሰግዳል፡፡ ከዱንያና ከአኺራ በወደደው ምርጥ በሆኑ ነገሮች ዱዓ ያደርጋል፡ ፡ እነዚህን ሁለት ረከዓዎች ከላቀው ‹‹ረውዷ›› ላይ ከሰገዳቸው በላጭ ይሆንለታል፡፡ አብደላህ ኢብኑ ዘይድ አል-ማዚኒ እንዳስተላለፈው፣ የአላህ መልእክተኛ እንዲህ ይላሉ፡-

«مَا بَيْنَ بَيْتِي وَمِنْبَرِي رَوْضَةٌ مِنْ رِيَاضِ الْجَنَّةِ»

> ‹‹በእኔ ቤትና በሚንበሬ (የኹጥባ ማድረጊያ ወንበሬ) መካከል ከጀነት የሆነ ጨፌ (ረውዷ) አለ፡፡›› (ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል)፡፡

ሶላት ከሰገደ በሁዋላ የአላህን መልእክተኛ ቀብር፣ የባልደረቦቻቸውን ማለትም የአቡበክርን፣ የዑመርን ቀብሮች ይጎበኛል፡፡ በአላህ መልእክተኛ ትይዩ (ፊት ለፊት) ስርዓት ባለው መንገድና ድምጽን ዝቅ አድርጎ ይቆማል፡፡ ከዚያም በነቢዩ ላይ እዝነትና ሰላም እሳቸው ላይ ይሁንና በእሳቸው ላይ እንዲህ ብሎ ሰላምታ ያቀርባል፡-

«السَّلَامُ عَلَيْكَ يَا رَسُولَ اللَّهِ وَرَحْمَةُ اللَّهِ وَبَرَكَاتُهُ»

«አሰላሙ ዐለይከ ያ ረሱለላሂ፤ ወረህመቱላሂ ወበረካቱህ፡ ፡» አቡ ሁረይራ እንዳስተላለፉት፣ የአላህን መልእክተኛ እንዲህ ይላሉ፡-

«مَامِنْ أَحَدٍ يُسَلِّمُ عَلَيَّ إِلَّا رَدَّ اللّٰهُ عَلَيَّ رُوحِي، حَتَّى أَرُدَّ عَلَيْهِ السَّلَامَ»

«ማንኛውም ሙስሊም በእኔ ላይ ሰላምታ ካቀረበ፣ አላህ ነፍሴን ይመልሳትና ሰላምታውን እመልሳለሁ፡፡» (አቡ ዳውድ ዘግቦታል)፡፡

ጉብኝት የሚያደርገው ሰው የሚከተለውን ሰላምታ ቢያቀርብ ምንም ችግር የለውም፡-

«السَّلَامُ عَلَيْكَ يَا نَبِيَّ اللّٰه، السَّلَامُ عَلَيْكَ يَاخِيرَةَ اللّٰه مِنْ خَلْقه، السَّلَامُ عَلَيْكَ يَاسَيِّدَ الْمُرْسَلِينَ وَإِمَامَ الْمُتَّقِينَ، أَشْهَدُ أَنَّكَ قَدْ بَلَّغْتَ الرِّسَالَةَ، وَأَدَّيْتَ الْأَمَانَةَ، وَنَصَحْتَ الْأُمَّةَ، وَجَاهَدْتَ فِي اللّٰهِ حَقَّ جِهَادِهِ»

«አስሰላሙ ዐለይከ ያ ነቢይየላህ፤ አሰላሙ ዐለይከ ያ ኺረተ ሚን ኸለቂሂ፤ አሰላሙ ዐለይከ ያ ሰይይደል ሙርሰሊን፤ ወኢማሚል መትተቂን፤ አሽሀዱ አንነከ በለግተርሪሳላ፤ ወአድደይተል አማና፤ ወነሶህተል ኡምማ፤ ወጃሃድተ (ሲነበብ - ወጃሀተ) ፊላሂ ሀቅቀ ጂሃዲህ፡፡»

«አንተ የአላህ ነቢይ ሆይ! ሰላም በአንተ ላይ ይስፈን፤ አንተ ምርጥ ፍጡር ሆይ! በአንተ ላይ ሰላም ይስፈን፤ የመልእክተኞች አለቃ ሆይ! በአንተ ላይ ሰላም ይስፈን፤ የአላህን ፈሪዎች መሪ፣ አንተ መልእክተ-ኢስላምን ማድረስክን፣ አደራህን ማድረስክን፣ ኡማውን መምከርህን፣ ለአላህ ብለህ እውነተኛውን ትግል ማድረግህን እመሰክራለሁ» ብሎ ሰላምታ ቢያቀርብ ችግር የለውም፡፡ ምክንያቱም ይህ ሁሉ ባህሪያታቸው (መገለጫቸው)

ነውና ነው፡፡

በእሳቸው ላይ እዝነትና ሰላም ያደርሳል፤ ዱዓ ያደርጋል፡፡ በሸሪዓው እዝነትንና ሰላምን አንድ ላይ አጣምሮ መግለጹ የተወሰነ በመሆኑ ይህንኑ አካሄድ ተግባራዊ ያደርጋል፡፡ አላህ በቁርኣኑ እንዲህ ይላል፡-

﴿ إِنَّ ٱللَّهَ وَمَلَٰٓئِكَتَهُۥ يُصَلُّونَ عَلَى ٱلنَّبِيِّۚ يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ صَلُّواْ عَلَيۡهِ وَسَلِّمُواْ تَسۡلِيمًا ﴾

«አላህና መላእክቱ በነቢዩ ላይ የአክብሮት እዝነትን አውርዱ፤ የማክበር ሰላምታን ሰላም በሉ» (አል-አህዛብ፣ 56)፡፡ ከዚያም በአቡ በክርና በዑመር ላይ ሰላምታ ያቀርባል፡፡ ለሁለታቸውም ዱዓ ያደርግላቸዋል፡፡ ስራቸውንም አላህ እንዲወድላቸው እሱን ይለምንላቸዋል፡፡

ዐብደላህ ኢብኑ ዑመር በአላህ መልእክተኛና በጉዋደኞቻቸው (ባልደረቦቻቸው) ላይ ሰላምታ ካቀረበ፣ ብዙ ጊዜ ከሚከተለው ሰላምታ ወጪ ሌላ አይጨምርም ነበር፡- «አሰላሙ ዐለይከ ያረሱሉላህ፤ አሰላሙ ዐለይከ ያ አባ በክር፤ አሰላሙ ዐለይከ ያአበታሁ፡፡»

«አንተ የአላህ ነቢይ ሆይ! ሰላም በአንተ ላይ ሰላም ይስፈን! አንተ አቡ በክር ሆይ! ሰላም በአንተ ላይ ሰላም ይስፈን! አንተ አባቴ ሆይ! ሰላም በአንተ ላይ ሰላም ይስፈን!» (በይሃቂ ዘግበታል)፡፡ ከዚያም ከቦታው ይንቀሳቀሳል፡፡

ይህ ለወንድ ብቻ የተደነገገ የዚያራ (የጉብኝት) አደራረግ ስነ ስርዓት ነው፡፡ ሴቶች ቀብርን የመጎብኘት መብት የላቸውም፡፡ ይህም ኢብኑ ዐባስ እንዳስተላለፉት፣ የአላህ መልእክተኛ «መቃብርን የሚጎብኙ ሴቶች፣ መቃብርን መስጂዶችና መብራት ማብሪያ የሚያደርጉም የአላህ እርግማን ይውረድባቸው፡፡» ብለዋል፡፡

(አቡዳውድ፣ ቲርሚዚ፣ ነሳኢና ኢብኑ ማጃህ ዘግበውታል፡፡)

ወደ መዲና ከተማ ሄዶ በነቢዩ መስጂድ ላይ ሶላት ለመስገድና ዱዓ ለማድረግ ማሰብ፣ እንዲሁም በሌሎች መስጂዶች ላይ እንዲተገበር የተደነገገ ነገር ሁሉ ለመፈጸም ማሰብ፣ ቀደም ብሎ በተጠቀሱት ሀዲሶች ላይ በሁሉም ላይ የተደነገገ ጉዳይ ነው፡፡ የመዲናውን መስጂድ የሚጎበኝ ሰው ያለውን ትልቅ ምንዳ ከመጠቀም አንጻር አምስቱን የግዴታ ሶላቶች በመዲናው መስጂድ ላይ ቢሰግድ ጥሩ ነው፡፡ አሁንም ያለውን ትልቅ ምንዳ ከመጠቀም አንጻርም በመስጂዱ ዚክርና ዱዓ እንዲሁም ትርፍ (ሱና) ሶላቶችን ማብዛት ሱና ነው፡፡

ቀደም ብሎ በትክክለኛ የሀዲስ ዘገባ የቦታው ደረጃ ላቅ ያለ መሆኑ ተወስቱዋል፡፡ በላቀው ረውዷ (ረውደቱ ሸሪፍ) ላይ ትርፍ ሶላቶችን ማብዛት ይወደዳል፡፡ የአላህ መልእክተኛ እንዲህ ይላሉ፡-

«مَا بَيْنَ بَيْتِي وَمِنْبَرِي رَوْضَةٌ مِنْ رِيَاضِ الْجَنَّةِ»

‹‹በእኔና በሚንበሬ (በመቀመጫዬ) ላይ ከጀነት የሆነ ጨፌ አለ፡፡››

የግዴታ ሶላቶችን በተመለከተ ለጎብኚውና ለሌላው ሰው ወደ መስጂዱ ቀደም ብሎ ለመግባትና የመጀመሪያውን ሶፍ (መስመር) ለመያዝ መጣጣር አለባቸው፡፡ ሌላው ቢቀር የመጀመሪያው ሶፍ እንኳዋ ባይገኝ የዋናው ሶፍ ተቀጽላ የሆነውን የመጀመሪያው ሶፍ ለማግኘት መጣጣር ያስፈልጋል፡፡ በትክክለኛ የሀዲስ ዘገባ፣ የአላህ መልእክተኛ በመጀመሪያ ሶፍ ጉዳይ ላይ አጽንኦት ሰጥተው ግፊት ማድረጋቸውን አቡ ሁረይራ እንደሚከተለው ዘግበዋል፡-

«لَوْ يَعْلَمُ النَّاسُ مَا فِي النِّدَآءِ وَالصَّفِّ الْأَوَّلِ ثُمَّ لَمْ يَجِدُوا إِلَّا أَنْ يَسْتَهِمُوا عَلَيْهِ لَاسْتَهَمُوا»

‹‹ሰዎች በአዛንና በመጀመሪያ ሶፍ (ሰልፍ) ያለውን ምንዳ ቢያውቁና

(እሱን ለማግኘት) ዕጣ ከመጣጣል ውጪ ሌላ አማራጭ የሌላቸው ቢሆን ኖሮ፣ ዕጣ ይጣጣሉ ነበር፡፡» (ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል)፡፡ የአላህ መልእክተኛ ተመሳሳይ መልእክት ያለው ሃሳብ ለባልደረቦቻቸው በሚከተለው መንገድ ገልጸዋል፡፡ አቢ ሰዒድ አል-ኹድሪይ እንዳስተላለፈው፣ የአላህ መልእክተኛ እንዲህ ብለዋል፡-

«تَقَدَّمُوا فَأْتَمُّوا بِي وَلْيَأْتَمَّ بِكُمْ مَنْ بَعْدَكُمْ وَلَا يَزَالُ الرَّجُلُ يَتَأَخَّرُ عَنِ الصَّلَاةِ حَتَّى يُؤَخِّرَهُ اللَّه».

«ወደ ፊት ቀደም በሉ፤ በእኔ ተመሩ (ተከተሉ)፤ ከእናንተ ሁዋላ ያለው በእናንተ ይመራ፡፡ ሰዎች ከሶላት ከመዘግየት አይወገዱም፣ አላህ እነሱን ወደ ሁዋላ የሚያስቀራቸው ቢሆን እንጂ፡፡» (ሙስሊም የዘገበው)፡፡

ዓኢሻ እንዳስተላለፈችው፣ የአላህ መልእክተኛ እንዲህ ብለዋል፡-

«لَا يَزَالُ الرَّجُلُ يَتَأَخَّرُ عَنِ الصَّفِّ الْمُقَدَّمِ حَتَّى يُؤَخِّرَهُ اللَّه فِي النَّارِ»

«ሰዎች ከመጀመሪያ ሶፍ (መስመር) ከመዘግየት አይወገዱም፣ አላህ በእሳት ውስጥ የሚያዘገያቸው ቢሆን እንጂ፡፡» በሌላ የሀዲስ ዘገባ እንደተረጋገጠውም፣ የአላህ መልእክተኛ እንዲህ አሉ፡-

«أَلَا تَصُفُّونَ كَمَا تَصُفُّ الْمَلَائِكَةُ عِنْدَ رَبِّهَا قَالُوا: يَارَسُولَ اللَّه! وَكَيْفَ تَصُفُّ الْمَلَائِكَةُ عِنْدَ رَبِّهَا؟ قَالَ: يُتِمُّونَ الصُّفُوفَ الأُوَلَ، وَيَتَرَاصُّونَ فِي الصَّفِّ»

«መላኢካዎች ጌታቸው ዘንድ ሶፍ (ሰልፍ) እንደሚይዙት፣ እናንተም ሶፍ (ሰልፍ) አትይዙምን?» እኛም፣ የአላህ መልእክተኛ ሆይ! መላኢካዎች እጌታቸው ዘንድ እንዴት ብለው ነው ሶፍ (ሰልፍ) የሚይዙት? አልናቸው፡

፡ እሳቸውም፣ «የመጀመሪያውን ሶፍ (ሰልፍ) የሚሞሉ ሲሆኑ፣ በየመስመሩ መካከል ክፍተት የሌለው (የተጠጋጋ) የሆነ ሶፍ (ሰልፍ) ይሰራሉ፡፡» (ሙስሊም የዘገበው)፡፡

ይህን ነቢያዊ መልእክት የሚመለከቱ ብዙ ነቢያዊ ሀዲሶች አሉ፡፡ መልእክቶቹም የእሳቸውን መስጂድ ጥንታዊ ይዞታና አሁን ከተስፋፋ በኋላ ያለውን ሁኔታ የሚመለከቱ ናቸው፡፡ በትክክለኛው የሀዲስ ዘገባ እንደተረጋገጠው፣ የአላህ መልእክተኛ ባልደረቦቻቸውን የሶፉን (የሰልፉን) ቀኝ አቅጣጫ ያለውን እንዲይዙ ግፊት ያደርጉ ነበር፡፡ እንደሚታወቀው በመዲናው መስጂድ በመጀመሪያው ይዞታ በቀኝ በኩል ያለው የመጀመሪያው ሶፍ የሚገኘው ከረውዷው ውጪ ነው፡፡ ይህ ማለት ደግሞ በሶፉ መጀመሪያ የቀኝ አቅጣጫ ላይ ትኩረት ማድረግ ከላቀው ረውዳ የበለጠ ትኩረት የሚደረግበት መሆኑን ማወቅ ይቻላል፡፡ በመጀመሪያው ሶፍና በሶፉ የቀኝ አቅጣጫ ላይ አጽዕኖት መስጠት፣ ረውዷው ላይ አጽዕኖት ከመስጠት የላቀ ነው፡፡ በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ላይ የመጡ ሀዲሶችን በትኩረት የቃኘ ሰው፣ ያነሳነው ነጥብ ግልጽ መሆኑን ይረዳል፡፡ አላህ መልካምን ነገር አጎናጻፊ ነው፡፡

ለአንድ ሰው እንኩዋ ሀጀረል አስወድን በእጁ ማበስ ወይም መሳም ወይም መዞር የሚፈቀድ አይደለም፡፡ ምክንያቱም ይህ ተግባር ከቀደምት ደጋግ ሙስሊሞች ከአንዱ ዘንድ እንኳ አልተገኘም፡፡ እንዲያውም ተግባሩ አዲስ ፈጠራ (ቢድዓ) እና ንቅፍ ነው፡፡

አንድ ሰው ጉዳዩ መፍትሄ እንዲያገኝ ወይም ከጭንቁ ለመገላገል ወይም በሽተኛው እንዲድን ፈልጎ የአላህን መልእክተኛ መጠየቅ የለበትም፡፡ ምክንያቱም እነዚህ ሁሉ ጉዳዮች ከአላህ ዘንድ ሊጠየቁ የሚገባቸው እንጂ፣ ከሌላ ፍጡር ሊጠየቁ የሚገቡ አይደሉም፡፡ አንድ ሰው ጉዳዩን ከሙታን የሚጠይቅ ከሆነ ድርጊቱ ሽርክ (ጣኦት አምልኮ)፣ ከአላህ ውጪ ያለን ነገር ማምለክ ነው፡፡

ኢስላም በሁለት መሰረቶች ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ እነሱም፡-

አንደኛው፡- እሱን ብቻውን እንጂ፣ ሌላን ፍጡር ላያመልክ ነው፡፡

ሁለተኛው፡- የሚመልከውም አላህና የአላህ መልእክተኛ በደነገጉት መንገድ ብቻ ነው፡፡ ይህ የ

«لَا إِلَهَ إِلَّا اللَّه، مُحَمَّدٌ رَسُولُ اللَّهِ»

«ላ ኢላሃ አልለላህ፤ ሙሀመዱን ረሱሉላህ» የሚለው ሃሳብ ትርጉም ነው፡፡

እንደዚሁም አንድ ሰው ነቢዩን ምልጃ ሊጠይቅ አይፈቀድለትም፡ ፡ ምክንያቱም ይህ ነገር ለአላህ ብቻ የተገባ ነውና ነው፡፡ ምልጃ ከእሱ እንጂ ከሌላ ወገን አይፈቀድም፡፡ አላህ በቁርአኑ እንዲህ ይላል፡-

﴿قُل لِّلَّهِ ٱلشَّفَـٰعَةُ جَمِيعًاۖ﴾

«ምልጃ መላውም የአላህ ብቻ ነው» (አዝ-ዙመር፣ 44)፡፡ ሰዎች እንዲህ ይላሉ፡-

«اللَّهُمَّ شَفِّعْ فِيَّ نَبِيَّكَ، اللَّهُمَّ شَفِّعْ فِيَّ مَلَائِكَتَكَ، وَعِبَادَكَ الْمُؤْمِنِينَ، اللَّهُمَّ شَفِّعْ فِيَّ أَفْرَاطِي«

«አላሁምመ ሸፍፊዕ ፊይዩ ነቢይየከ፤ አላሁምመ ሸፊዕ ፊይዩ መላኢከተከ፤ ወዒባዲከል ሙእሚኒን፤ አላሁምመ ሸፊዕ ፊይዩ አፍራጢ፡፡»

«አላህ ሆይ! የነቢይህን፣ የመላኢካህን፣ የአማኝ ባሪያዎችህንና የህጻናቱን ምልጃ እንድትሰጠኝ እጠይቅሃለሁ፡፡» (አዱረሩ ስሰኒያ ፊል አጅዊበቲ ነጅዲያ 1፣ 218)፡፡ ሌሎችም መሰል ዱዓዎችም አሉ፡፡

ሙታን ምንም አይነት ነገር ሊጠየቁ አይገባም፡፡ ምልጃም ከእነሱ ወይም ከሌላ ሊጠየቅ አይገባም፡፡ አንቢያእ ሆኑም አልሆኑም ከእነሱ ምልጃ መጠየቅ ተገቢ አይደለም፡፡ እንዲህ አይነቱ ተግባር በኢስላም አልተደነገገም፡፡ ምክንያቱም ሟች ሸሪዓው በልዩ ሁኔታ ካስቀመጠው ውጪ፣ የሟች ስራው በእርግጠኝነት ተቋዋርጡዋል፡፡ አቡ ሁረይራ እንዳስተላለፉት፣ የአላህ መልእክተኛ እንዲህ ብለዋል፡-

«إِذَا مَاتَ ابْنُ آدَمَ انْقَطَعَ عَمَلُهُ إِلَّا مِنْ ثَلَاثٍ: صَدَقَةٍ جَارِيَةٍ أَوْ عِلْمٍ يُنْتَفَعُ بِهِ أَوْ وَلَدٍ صَالِحٍ يَدْعُو لَهُ»

«የሰው ልጅ ሲሞት ቁዋሚ ሶደቃ ወይም ጠቃሚ የሆነ ዕውቀት ወይም ለእሱ አላህን የሚለምንለት መልካም ልጅ ካለው በቀር እንጂ፣ ስራው ሁሉ ይቋረጣል፡፡ (ሙስሊም የዘገበው)፡፡

የአላህ መልዕክተኛ በህይወት እያሉና በዕለተ ቂያማ ወደ አላህ ምልጃ ማቅረብ ስለሚችሉ ለእሳቸው ምልጃ ይፈቀዳል፡፡ በዚህም ነቢዩ ሰዎችን ሊማልዱ እነሱ የጠየቁዋቸውን ጥያቄዎች ይዘው ወደ ጌታቸው ይቀርባሉ፡፡

እንደሚታወቀው በዱንያ ምልጃ በእሳቸው ብቻ የሚወሰን ሳይሆን፣ አጠቃላይና ለሌላውም የሚፈቀድ ነው፡፡ ስለሆነም አንድ ሙስሊም ለወንድሙ (በህይወት ላለ ወንድሙ)፡- «በዚህ፣ በዚህ ጉዳይ ጌታዬን ማልድልኝ» ሊል ይችላል፡፡ ይህም ማለት «አላህን ለምንልኝ» ሊል ይችላል ማለት ነው፡፡ ስለሆነም አንድ ሰው የሆነ ሰው በሚፈቀድ መንገድ አላህን እንዲማልድለት (እንዲጠይቅለት) ከጠየቀው፣ ተጠያቂው ለወንድሙ አላህን ምልጃ ሊጠይቅለት ይችላል፡፡

ይሁን እንጂ አላህ በቁርኣን

﴿مَن ذَا ٱلَّذِى يَشۡفَعُ عِندَهُۥٓ إِلَّا بِإِذۡنِهِۦ﴾

«... ያ እርሱ ዘንድ በፈቃዱ ቢሆን እንጂ፣ የሚያማልደው ማነው?» (አል-በቀራ፣ 255) እንዳለው የዕለተ ቂያማ ማንኛውም ሰው አላህ ፈቅዶለት ካልሆነለት በስተቀር፣ የማማለድ አቅም የለውም፡፡ የሞት ሁኔታ ልዩ የሆነ ሁኔታ ነው፡፡ ይህን ሁኔታ የሰው ልጅ ከሞት በፊት፣ ከመቀስቀስ በኋላና ከሞት መነሳት በኋላ ካለው ሁኔታ ጋር ማመሳሰል አይገባም፡፡ ምክንያቱም የሰው ልጅ ህይወቱ በማለፉ (በመሞቱ) ስራው ሁሉ ተቋርጧልና ነው፡፡ ይህ ማለት ሸሪዓው ቀጣይነት አላቸው ብሎ ከጠቀሳቸው የስራ ዓይነቶችን ሳይጨምር ማለት ነው፡፡ ይሁን እንጂ ከሙታን ምልጃ መጠየቅ ሸሪዓው «በሲቀር» ያስቀመጠው ነገር አይደደለም፡፡ ይህን ጉዳይ ይፈቀዳል ከሚል አጉል መላምት ጋር ማቆራኘትም አይፈቀድም፡፡

የአላህ መልዕክተኛ ከሞት በሁዋላ በቀብር ህያው (ሀያተን በርዘኺያ) እንደሆኑ ያለጥርጥር ይታወቃል፡፡ እንዲያውም ቀብር ላይ የሚያሳልፉት ህይወት ሰማዕታት (ሹሃዳእ) ከሚያሳልፉት ህይወት እጅግ በጣም የላቀ ህይወት ነው፡፡ ነገር ግን ይህ ህያውነት ከሞት በፊት ያለው የህያውነት ገጽታ ነጸብራቅ አይደለም፡፡ በዕለተ ቂያማ ያለውም የህያውነት ገጽታ ነጸብራቅም አይደለም፡፡ ይልቅ ይህን ከሞት በሁዋላ ያለው የህያውነት ገጽታ እውነታውንና እንዴትነቱን የሚያውቀው አላህ እንጂ ሌላ ማንም አይደለም፡፡ ስለሆነም ነው የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ያሉት፡-

«مَا مِنْ أَحَدٍ يُسَلِّمُ عَلَيَّ إِلَّا رَدَّ اللهُ عَلَيَّ رُوحِي حَتَّى أَرُدَّ عَلَيْهِ السَّلَامَ»

«አንድ እንኳ ሙስሊም በእኔ ላይ ሰላምታ ካቀረበ፣ ሰላምታውን እመልስ ዘንድ አላህ ነፍሴን ወደ እኔ ይመልስልኛል፡፡» (አህመድና አቡ ዳውድ የዘገቡት)፡፡

ማስረጃው እንደሚያስረዳው እሳቸው (ነቢዩ) ሙዋች ናቸው፡

፡ ነፍሳቸው አካላቸውን ተለይታለች፡፡ ነገር ግን ወደ እሳቸው ሰላምታ ሲቀርብላቸው፣ ነፍሳቸው ወደ እሳቸው ትመለሳለች፡፡ እሳቸው የሞቱ ለመሆናቸው የቁርኣንና የሱና ማስረጃዎች አሉ፡፡ በሊቃውንት ዘንድም እሳቸው የሞቱ ለመሆናቸው የጋራ አቋዋም አላቸው፡፡ ይህ ማለት ግን ቀብር ላይ ከሚኖራቸው የ‹‹ህያውነት›› ገጽታ (በርዘኸ) ጋር የሚጋጭ አይደለም፡፡ ‹‹የሰማዕታት ሞት›› በቁርኣን የተወሳውንና ቀብር ላይ የሚኖራቸውን የ‹‹ህያውነት›› ገጽታ የሚከለክላቸው አይደለም፡፡ አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ وَلَا تَحْسَبَنَّ ٱلَّذِينَ قُتِلُوا۟ فِى سَبِيلِ ٱللَّهِ أَمْوَٰتًۢا ۚ بَلْ أَحْيَآءٌ عِندَ رَبِّهِمْ يُرْزَقُونَ ›› ﴾

‹‹እነዚያን በአላህ መንገድ የተገደሉትን ሙታን አድርገህ አትገምታቸው፤ በእርግጥ እነርሱ እጌታቸው ዘንድ ህያዋን ናቸው፤ ይመገባሉ›› (ኣሊ-ዒምራን፣ 169)፡፡

በዚህ ጉዳይ ላይ ሀተታ ያበዛነው፣ ርዕሰ-ጉዳዩ አንገብጋቢ ስለሆነ ነው፡፡ በዚህ ርዕሰ-ጉዳይ ላይ በሙስሊሞች ዘንድ ብዙ ያልጠሩ (የተመሳሰሉ) ነገሮች ስላሉ ነው፡፡ በእነዚህም ያልጠሩ ነገሮች ምክንያት በሙስሊሙ አካባቢ ወደ ሺርክ (ከአላህ ወጪ ሙታንን ማምለክ) ጥሪ የማድረግ አዝማሚያ አካሄድ ነው የሚታየው፡፡ ለእኛና ለሁሉም ሙስሊሞች ሸሪዓውን ከሚነቅፉ ነገሮች እንድንርቅ ደህንነትን አላህን እንለምነዋለን፡፡ አላህ እጅግ በጣም አዋቂ ነው፡፡

የተወሰኑ ኀብኘዎች ከነቢዩ ቀብር ዘንድ ድምጻቸውን ከፍ ማድረጋቸው፣ እዚያም ላይ ረዘም ላለ ጊዜ መቆማቸው ኢ-ሸሪዓዊ አካሄድ ነው፡፡ ምክንያት አላህ የዚህን ኡማ አባላት ከነቢዩ ድምጽ በላይ ድምጻቸው ከፍ እንዳይልና፣ ጩኸታቸውም ከፊላቸው ለከፊላቸው እንደሚያደርጉት ጩኸት እንዳይሆን ከልክሉዋቸዋል፡፡ ድምጻቸውንም ዝቅ እንዲያደርጉ አላህ በቁርኣኑ

ግፊት አድርጎባቸዋል፡፡ አላህ በቁርኣኑ እንዲህ ይላል፡-

﴿ يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ لَا تَرۡفَعُوٓاْ أَصۡوَٰتَكُمۡ فَوۡقَ صَوۡتِ ٱلنَّبِيِّ وَلَا تَجۡهَرُواْ لَهُۥ بِٱلۡقَوۡلِ كَجَهۡرِ بَعۡضِكُمۡ لِبَعۡضٍ أَن تَحۡبَطَ أَعۡمَٰلُكُمۡ وَأَنتُمۡ لَا تَشۡعُرُونَ ۝٢ إِنَّ ٱلَّذِينَ يَغُضُّونَ أَصۡوَٰتَهُمۡ عِندَ رَسُولِ ٱللَّهِ أُوْلَٰٓئِكَ ٱلَّذِينَ ٱمۡتَحَنَ ٱللَّهُ قُلُوبَهُمۡ لِلتَّقۡوَىٰۚ لَهُم مَّغۡفِرَةٞ وَأَجۡرٌ عَظِيمٌ ﴾

‹‹እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ድምጾቻችሁን ከነቢዩ ድምጽ በላይ ከፍ አታድርጉ፤ ከፊላችሁም ለከፊሉ እንደሚጮህ በንግግር ለእርሱ አትጨሁ፤ እናንተ የማታውቁ ስትሆኑ ስራዎቻችሁ እንዳይበላሹ (ተከልከሉ)፡፡ እነዚያ በአላህ መልእክተኛ ዘንድ ድምጾቻቸውን ዝቅ የሚያደርጉ፣ እነዚህ እነዚያ አላህ ልቦቻቸውን ለፍርሃት የፈተናቸው ናቸው፡፡ ለእነሱም ምህረትና ታላቅ ምንዳ አላቸው›› (አል-ሁጁራት፣ 3-2)፡፡

ከነቢዩ ቀብር ዘንድ ረዘም ላለ ጊዜ መቆምና በተደጋጋሚ በእሳቸው ላይ ሰላምታ ማብዛት፣ የሰው መጨናነቅ (መገፋፋት)፣ የጫጫታ ብዛትና የድምጽ ከፍታ እቀብራቸው ላይ እንዲኖር አስተዋጽኦ ያደርጋል፡፡ ይህ ደግሞ አላህ ለሙስሊሞች በዚህ ግልጽ በሆኑ አንቀጾች ከደነገገው ህግ ጋር ይጋጫል፡፡ የአላህ መልእክተኞች የተከበሩ፣ ህያውና ሙዋች ናቸው፡፡ ስለሆነም አንድ አማኝ ከነቢዩ ቀብር ላይ የሸሪዐውን ስርዓት የሚጻረር ተግባር መፈጸም የለበትም፡፡ ልክ እንደዚሁ አንዳንድ የነቢዩን ቀብር የሚዘይሩና ሌሎች ሰዎች ፊታቸውን ወደ ቂብላ ዞረውና እጃቸውን ከፍ አድርገው በጣም ዱዓ ያበዛሉ፡፡ ይህ ሁሉ ድርጊት የነቢዩ ባልደረቦችንና መንገዳቸውን በቅን የተከሉ የቀደምት ደጋግ ሙስሊሞችን ድርጊት ተጻራሪ ነው፡፡ እንዲያውም አዲስ ፈጠራ ነው፡፡ የአላህ መልእክተኛ እንዲህ ይላሉ፡-

«عَلَيْكُمْ بِسُنَّتِي وَسُنَّةِ الْخُلَفَاءِ الرَّاشِدِينَ الْمَهْدِيِّينَ مِنْ بَعْدِي،

تَمَسَّكُوا بهَا ، وعَضُّوا عَلَيْهَا بالنَّوَاجذ ، وَإِيَّاكُمْ وَمُحْدَثَاتِ الْأُمُورِ فَإِنَّ كُلَّ مُحْدَثَةٍ بِدْعَةٌ ، وَكُلَّ بِدْعَةٍ ضَلَالَةٌ»

«በእኔና ከእኔ በሁዋል ቅኑን መንገድ በተመሩ ምትኮች ሱና (ፈለግ) አደራችሁን፡፡ ሱናውን አጥብቃችሁ ያዙ፤ በቅንጣጤያችሁ (በውሻ ክራንቻ ጥርሳችሁ ነክሳችሁ - መንገዳቸውን አጥብቃችሁ) ያዙ፡፡ አዳዲስ ፈጠራዎችን አደራችሁን! አዲስ ፈጠራ ሁሉ መጤ ነው፤ ሁሉም መጤ ደግሞ ጥመት ነው፡፡» (አቡ ዳውድና ነሳኢ ዘግበውታል)፡፡

ዓኢሻ እንዳስተላለፈችው፣ የአላህ የአላህ መልእክተኛ እንዲህ ብለዋል፡-

«مَنْ أَحْدَثَ فِي أَمْرِنَا هَذَا مَا لَيْسَ مِنْهُ فَهُوَ رَدٌّ»

‹‹በዚህ ጉዳያችን (በኢስላም) ከእሱ የሌለ አዲስ ነገር ይዞ የመጣ ሰው፣ ነገሩ (ያመጣው) ተመላሽ ነው፡፡›› (ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል)፡፡ በሌላ የሙስሊም ዘገባ ደግሞ፣ ‹‹የእኛ ትእዛዝ የሌለበት ስራን የሰራ፣ እሱ (ነገሩ) ተመላሽ ነው፡፡››

ዐሊይ ኢብኑል ሀሰን ዘይኑል ዓቢዲን የሆነ ሰው እነቢዩ ቀብር ዘንድ ዱዓ እያደረገ ተመለከቱት፤ ድርጊቱን ከለከለው፡፡ እሱም ከአባቴ፣ ከአያቴ ከዚያም ከአላህ መልእክተኛ የሰማሁትን ሀዲስ አልነግርህምን? አለው፡፡ የአላህ መልእክተኛ እንዲህ አሉ፡-

«لَا تَتَّخِذُوا قَبْرِي عِيدًا وَلَا بُيُوتَكُمْ قُبُورًا ، وَصَلُّوا عَلَيَّ فَإِنَّ تَسْلِيمَكُمْ يَبْلُغُنِي أَيْنَمَا كُنْتُمْ»

‹‹ቀብሬን የበዓል ቦታ አታድርጉት፡፡ ቤታችሁንም መቃብር አታድርጉት፡፡ የትም ቦታ ሆናችሁ የምታደርጉት ሰላምታ ለእኔ ይደርሰኛል፡፡›› (አል-ሀፊዝ ሙሀመድ ኢብኑ ዐብዱልዋሂድ አል-መቅዲሲይ ዘግቦታል)፡፡

የነቢዩን ቀብር የሚጎበኙ አንዳንድ ሰዎች በነቢዩ ላይ ሰላምታ ለማቅረብ ልክ የሶላት አቋቋም ስነ-ስርዓት የሚፈጽሙ ይመስል ከደረታቸው በላይ ወይም በታች ቀኝ እጃቸውን ከግራ እጃቸው አድርገው ዚያራ ያደርጋሉ፡፡ ይህ ሁኔታ በእሳቸው ላይ ሰላምታ ለማቅረብ ተብሎ የሚፈጸም ተገቢ ተግባር አይደለም፡፡ ይህ ለእሳቸው ብቻ ሳይሆን ለንጉሶችም ይሁን ለመሪዎች እንዲሁም ለሌሎችም ባላስልጣናት ሰላምታ ለማቅረብ ይህን አይነት መንገድ ተግባራዊ አድርጎ ዚያራ (ጉብኝት) ማድረግም የሚፈቀድ አይደለም፡፡ ምክንያቱም ሂደቱ ውርደትን፣ ፍርሃትንና አምልኮትን የሚገልጽ ነውና፡፡ እንዲህ አይነቱ «የውርደት ገጽታ» መገለጫ ደግሞ ለአላህ በቀር እንጂ ለሌላ አይገባም፡፡ ይህን ጉዳይ አል-ሃፊዝ አል-ሀጀር አል-ዐስቀላኒ «ፈትሁል ባሪእ» ከተባለው መጽሀፍ ላይ የተለያዩ ሊቃውንትን ጠቅሰው ዘክረውታል፡፡ የቀደምት ደጋግ ሙስሊሞችን ቅን መንገድ መከተል አላማው የሆነ ሰው በዚህ ላይ ያለውን ጉዳይ ካስተነተነው በጉዳዩ ላይና ዙሪያ ያለው እውነታ ጉልህ ሆኖ ይታየዋል፡፡

ነገር ግን ወደ ቅኑ የቀደምት ደጋግ ሙስሊሞች መንገድ ጥሪ የሚያደርጉ ዳዒዎች ላይ አጉል የእኔነት፣ ስሜትና ጭፍን ተከታይነትን መሰረት አድርጎ በእነሱ ላይ የሚነዛውን አጓጉል አሉባልታ፣ ለአላህ መተው ነው፡፡ ለእኛና በአጉል አሉባልታ ራሱን ለጠመደው ሰው አላህ ቅኑን መንገድ እንዲመራው፣ እንዲሁም እውነታውን ለሌሎች መግለጽን አላህ እንዲገጥመን እሱን እንለምነዋለን፡፡ አላህ ከጉድለት የጠራና መልካም ነገርን የሚጠየቀው እሱ ነው፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ አንዳንድ ሰዎች ከላቀው የነቢዩ ቀብር ፊት ለፊት ይሆኑና በሰላምታና በዱዓ አጋጣሚ ከንፈራቸውን ያንቀሳቅሳሉ፡፡ ይህ ሁሉ ነገር አዲስ መጤ (ቢድዓ) ነገር ነው፡፡ አንድ ሙስሊም አላህ ሳይፈቅድለት በዲኑ አዲስ ነገር ሊያመጣ አይገባም፡፡ ይህ ሰው በዚህ ስራው ለአላህ ወዳጅና መልካም

ተከታይ ከመሆን ይልቅ፣ ወደ ድርቅና የቀረበ ነው፡፡ ኢማሙ ማሊክ ይህን አይነቱንና ተመሳሳዩን ስራ ነቅፈውታል፡፡ እንዲሁም ብለዋል፡- «የሁዋለኛው ትውልድ (ኡማ) ስኬታማ የሚሆነው፣ የመጀመሪያው ትውልድ ስኬታማ የሆነበትን የስኬት መንገድ መከተል ሲችል ነው፡፡» (ቃዲ ዒያድ፣ ሺፋ፣ 1፣ 88)፡፡

እንደሚታወቀው የዚህ ኡማ የመጀመሪያው ትውልድ በጉዞው ስኬታማነትን የተጎናጸፈው በነቢዩ፣ በቅኖቹ ኸሊፋዎች፣ በተወዳጆቹ ባልደረቦች፣ በቅንነት በተከተሉት ተከታዬች መንገድ የተጓዘ ስለሆነ ነው፡፡ የዚህ ኡማ ማሳረጊያም ትውልድም ስኬታማ ጉዞን የሚጎናጸፈው፣ የመጀመሪያው ኡማ የሄደበትን ስኬታማ መንገድ የሙጥኝ ብሎ በመንገዱ ከተጉዋዘ ነው፡፡ አላህ ሙስሊሞችን በዱንያና በአኺራ መድህንና ደስታ እንዲሁም ልቅና የሚያገኙበትን ሁኔታ ይግጠማቸው፡፡ እሱ ለጋስና ቸር ነው፡፡

# ማሳሰቢያ

አንዳንድ ብዙም ኢስላማዊ እውቀት የሌላቸውና መሰሎቻቸው እንደሚያስቡት የነቢዩን ቀብር መጎብኘት ለሀጅ ስራ እንደ ግዴታ ወይም እንደ መስፈርት የሚያስቆጥረው አይደለም፡፡ የነቢዩን መስጂድ ለጎበኘና ለመስጂዱ ቅርብ ለሆነ ሰው ቀብሩን መጎብኘት የተወደደ እንጂ፣ ከሀጂ ጉዳይ ጋር የሚያገናኘው ምንም ነገር የለም፡፡ ከመዲና ከተማ ውጪ ያለ የሩቅ ሰው፣ ቀብሩን ለመጎብኘት አስቦና ለጉዞ ተሰናድቶ ቀብሩን ለመጎብኘት መምጣት የለበትም፡ ፡ ነገር ግን የነቢዩን መስጂድ ለመጎብኘት ከሩቅ ቢመጣ ችግር የለውም፡፡ ከመስጂድ ዚያራው በሁዋላ የተከበረውን ቀብር ለመዘየር ከቻለ አብሮ የሁለቱን ባልደረቦቻቸውን (የአቡበክርንና የዑመርን) ይጎብኛል፡፡ ምክንያቱም የሁለቱ ባልደረቦቻቸው ቀብር ጉብኝት ጉዳይ ከነቢዩ የቀብር ጉብኝት ጋር የተጎዳኘ ነውና፡፡ ለዚህም ቡኻሪና ሙስሊም አቡ ሁረይራን ጠቅሰው የዘገቡት ሀዲስ አለ፡፡ ይኸውም የሚከተለው ነው፡-

«لَا تُشَدُّ الرِّحَالُ إِلَّا إِلَى ثَلَاثَةِ مَسَاجِدَ: الْمَسْجِدِ الْحَرَامِ، وَمَسْجِدِي هَذَا، وَالْمَسْجِدِ الأَقْصَى»

‹‹አንድ ሰው ወደ ሶስት መስጂዶች (እነሱም)፡- ወደ መስጂደል ሀራም፣ ወደ ይህ የኔ መስጂድ (የመዲናው መስጂድ) እና ወደ መስጂደል አቅሷ የሚያደርገው ጉዞ ሲቀሩ እንጂ፣ ዒባዳን አስቦ መንገድ መግባት አይገባውም፡፡››

የእሳቸውንና የሌላውን ቀብር መጎብኘት በኢስላም የተደነገገ ቢሆን ኖሮ፣ የአላህ መልዕክተኛ ኡማውን ቀብራቸውን ይጎበኝ ዘንድ ያዙት ነበር፡፡ ቀብር በመጎብኘቱ የሚገኘውንም ደረጃ ያመላክቱ

ነበር፡፡ ምክንያቱም ነቢዩ ከማንም የላቁ፣ ለአላህ ብለው መካሪ፣ አዋቂ እንዲሁም አላህን ከማንም በላይ ፈሪ ናቸውና ነው፡፡ ኡማው ሊደርሰው የሚገባውን ነገር ሁሉ ግልጽ በሆነ መንገድ አድርሰዋል፡፡ ይህ ማለት ኡማውን በሁሉም መልካም ነገር ላይ አመላክተዋል፤ ከሁሉም እኩይ ነገርም አስጠንቅቀዋል፡፡ ከጠቀሱዋቸውም ሶስት መስጂዶች በቀርም ስንቅ ሰንቆና ለጉዞ ተሰናድቶ መንገድ መግባት ተገቢ እንዳልሆነ አስጠንቅቀዋል፡፡ ኢማሙ አህመድና አቡ ዳውድ በዘገቡት ሀዲስም የአላህ መልእክተኛ እንዲህ ብለዋል፡-

«لَا تَتَّخِذُوا قَبْرِي عِيدًا، وَلَا بُيُوتَكُمْ قُبُورًا، وَصَلُّوا عَلَيَّ فَإِنَّ صَلَاتَكُمْ تَبْلُغُنِي حَيْثُ كُنْتُمْ»

‹‹ቀብሬን የበዓል ቦታ አታድርጉት፤ ቤታችሁንም መቃብር አታድርጉት፡፡ የትም ቦታ ሆናችሁ የምታቀርቡት ሰላምታ ለእኔ ይደርሰኛል፡፡››

እንዲያው በደፈናው የነቢዩን ቀብር መጎብኘት በሸሪዓው የተፈቀደ ነው የሚለው አቋም፣ የነቢዩን ቀብር ‹‹በዓል›› አድርጎ እንዲያዝ በር ከፋች ነው፡፡ በዚህም ነቢዩ የጠሉት ማለትም በእሳቸው ጉዳይ ላይ ተስፈንጣሪና ድንበር አላፊ መሆን ላይ መውደቅ ይከሰታል፡፡ ለነገሩ የነቢዩን ቀብር መጎብኘት በሸሪዓው ተፈቀደ ነው በሚል (አጉል) አቋም ብዙ ሰዎች ተስፈንጣሪ (ከነቢዩ ሱና አፈንጋጭ) ሆነዋል፡፡

‹‹ወደ ነቢዩ ቀብር በመሄድ የእሳቸውን ቀብር መዘየር የሚፈቀድ ነው›› የሚል አቋም ያላቸው ወገኖች የሚያቀርቡት የሀዲስ ማስረጃ ሰነዱ (የዘገባ ሰንሰለቱ) ደካማ ከመሆኑ በላይ መሰረተ-ቢስ ነው፡፡ ሀዲሶቹም ደካማ ለመሆናቸው የሀዲስ ሊቃውንቱ እንደነ ዳረል ቁጥኒይ፣ በይሀቂ፣ ኢብኑ ሀጀርና ሌሎቹም አሳስበዋል፡፡ ስለሆነም ‹‹ይበቃል›› የሚለውን አቋም ለመደገፍ ለማስረጃነት የሚውሉት ‹‹ደካማ ሀዲሶች››፣ ከሶስቱ መስጂዶች በቀር ለጉዞ ተሰናድቶ መጉዋዝን የሚከለክለውን ‹‹ትክክለኛ ሀዲስ›› መቃረን

አይበቃላቸውም፤ አይፈቀድላቸውምም፡፡

አንተ አንባቢ ሆይ! አንተ ልታውቃቸውና እንድትጠነቀቃቸው እንዲሁም እንዳትሸነገልባቸው ይሆን ዘንድ የነቢዩን ቀብር መጎብኘት ይበቃል የሚል አቋዋም ያላቸው ሰዎች ለመረጃነት የተጠቀሙባቸው ደካማ ሀዲሶች የሚከተሉት ናቸው፡-

አንደኛ፡- ‹‹ሀጅ አድርጎ እኔን ያልጎበኘኝ ሰው፣ እኔን ችላ እንዳለኝ ነው፡፡››

ሁለተኛ፡- ‹‹ከሞትኩ በሁዋላ የጎበኘኝ ሰው፣ በህይወት እያለሁ እንደጎበኘኝ ነው፡፡››

ሶስተኛ፡- ‹‹እኔንና አባቴ ኢብራሂምን በአንድ አመት ውስጥ የጎበኘን፣ ከአላህ ዘንድ ጀነትን ዋስትና እገባለታለሁ፡፡››

አራተኛ፡- ‹‹ቀብሬን የጎበኘ ሰው፣ ለእሱ ምልጃዬ ተገቢ ሆነችለት፡፡››

እነዚህ ሁሉ በነቢዩ ስም የተወሱ ‹‹ሀዲሶች›› በእርግጥም ራሳቸው ነቢዩ ለመናገራቸው ማረጋገጫ ያልተገኘላቸው ናቸው፡፡ የሀዲስ ሊቃውንቱ አል-ሃፊዝ ኢብኑ ሀጀር ብዙ ዘገባ ያለውን ሀዲስ ካወሱ በሁዋላ፣ ‹‹ተልኺስ›› ላይ እንዲህ ብለዋል፡- ‹‹የዚህ ሀዲስ ሁሉም የዘገባ መንገዶች ደካሞች ናቸው›› ብለዋል፡፡ አል-ሃፊዝ አል-ዑቀይሊ ደግሞ፣ እንዲህ ብለዋል፡- ‹‹በዚህ ምዕራፍ ላይ (ርዕሰ-ጉዳዩን በሚዳስሰው) ምንም አይነት ትክክለኛ ዘገባ የለም፡፡›› እንዲህ ስለሆነም ሸይኹል ኢስላም ኢብኑ ተይሚያ፡- ‹‹እነዚህ ሀዲሶች ሁሉ መሰረተ-ቢስ (መውዱዕ) ናቸው›› ብሉዋል፡፡ ኢብኑ ተይሚያ በዒልም ባህር፣ ዕውቀትን በአዕምሮው ሸምድዶ የሚይዝና መረጃዎችን በሚገባ አዳርሶ የሚያስስ ሊቅ ነው፡፡

ለነገሩ በዚህ እየተነጋገርንበት ባለው ርእሰ ጉዳይ ላይ በትክክለኛ መረጃ የተረጋገጠ ነቢያዊ ሀዲስ ቢኖር ኖሮ፣ ከማንም በላይ

የነቢዩ ባልደረቦች ለስራዎቹ ቀዳሚዎች ነበሩ፡፡ ጉዳዩንም ለነቢዩ ኡማ ከማብራራታቸው በላይ ሰዎችም እሱን ይተገብሩት ዘንድ ጥሪ ያደርጉ ነበር፡፡ ምክንያቱም የነቢዩ ባልደረቦች ከአንቢያእ ቀጥሎ ምርጥ ትውልዶች ነበሩና ነው፡፡ ይህም ብቻ አይደለም፣ የአላህን የህግ ልክ (ድንበር)፣ አላህ ለፍጡራኑ ለምን እንደደነገገው በሚገባ አዋቂዎችም ነበሩምና ነው፡፡ የሰው ልጅ ለአላህ ቅን ታዛዥ እንዲሆን ፍጡራኑን በጣም መካሪዎች ናቸው፡፡ ታዲያ በዚህ ጉዳይ ላይ ከእነሱ ዘንድ አንድ እንኳዋ እዚህ ግባ የሚባል ማስረጃ አለመገኘቱ፣ ለጉዞ ተሰናድቶ የነቢዩን ቀብር ለመጎብኘት መንገድ መግባት ሸሪዓዊ መሰረት የሌለው ለመሆኑ በሚገባ አስረጅ ነው፡፡ በዚህ ጉዳይ የተዘገቡት ሀዲሶች ሁላቸውም ትክክለኛ ሀዲሶች ቢሆኑ ኖሮ፣ ምንም የጉዞ መሰናዳት ሳያስፈልግ ቀብራቸውን ብቻ መጎብኘት ይፈቀዳል የሚል አቋዋም መድረስ የግድ ነበር፡፡ አላህ ከፍ ያለ ነው፤ ጥራት ይገባውና ነገሮችን ከማንም በላይ አዋቂም ነው፡፡

# የቁባእ መስጂድንና በቂዕን መጎብኘት

የመዲና ከተማን ለሚጎበኝ ሰው እግረ መንገዱንም የቁባእን መስጂድ መጎብኘትና መስጂዱም ላይ ሶላት መስገድ ይወደዳል፡፡ ይህ ጉዳይ ቡኻሪና ሙስሊም አብደላህ ኢብኑ ዑመርን ጠቅሰው በዘገቡት ትክክለኛ ሀዲስ፣ ኢብኑ ዑመር እንዲህ ብለዋል፡-

«كَانَ النَّبِي  يزور مَسْجِد قُبَاء رَاكبًا وَمَاشيًا وَيصَلِّي فِيهِ رَكَعتَين»

‹‹የአላህ መልእክተኛ የቁባእ መስጂድን በእግራቸውና በመጓጓዣ በመሄድ ይጎበኙት ነበር፡፡ በመስጂዱም ሁለት ረከዓ ሶላት ይሰግዱ ነበር፡፡›› በሌላ የሀዲስ ዘገባ ደግሞ፣ ሠህል ኢብኑ ሁነይፌ እንዳስተላለፈው፣ የአላህ መልእክተኛ እንዲህ ብለዋል፡-

«مَنْ تَطَهَّرَ فِي بَيْتِهِ ثُمَّ أَتَى مَسْجِدَ قُبَاءٍ فَصَلَّى فِيهِ صَلاَةً كَانَ لَهُ كَأَجْرِ عُمْرَةٍ»

‹‹ከቤቱ ዉድእ አድርጎ ወደ ቁባእ መስጂድ የመጣ ሰው፣ እንዲሁም በመስጂዱም ሶላት የሰገደ ሰው፣ ዑምራ ተሰርቶ የሚገኘውን ምንዳ ያገኛል፡፡›› (ኢብኑ ማጃህ ዘግቦታል)፡፡

በተጨማሪም የበቂዕንና የሰማዕታትን (ሹሀዳእ) መቃብር እንዲሁም የሀምዛን ቀብር መጎብኘት ሱና ነው፡፡ ምክንያቱም ነቢዩ ቦታዎቹን (መቃብሮቹን) ይጎበኙዋቸው ስለ ነበር ነው፡፡ ለሟቾቹም ዱዓ ያደርጉ ነበር፡፡ አቡ ሁረይራ ባስተላለፉት ሀዲስ የአላህ መልእክተኛ እንዲህ ብለዋል፡-

«زُورُوا الْقُبُورَ فَإِنَّهَا تُذَكِّرُكُمُ الآخِرَةَ»

‹‹መቃብርን ጎብኙ፡፡ እነሱ መጪውን ዓለም ያስታዉሷችሁዋል፡፡›› (ሙስሊም ዘግበውታል)፡፡ ሰልማን ኢብኑ ቡረይዳ አባቱን ጠቅሶ እንደዘገበው፣ የአላህ መልእክተኛ ባልደረቦቻቸው መቃብርን ሲጎብኙ የሚከተለውን እንዲሉ ያስተምሩዋቸው ነበር፡-

«السَّلَامُ عَلَيْكُمْ أَهْلَ الدِّيَارِ مِنَ الْمُؤْمِنِينَ وَالْمُسْلِمِينَ، وَإِنَّا إِنْ شَآءَ اللّٰهُ بِكُمْ لَاحِقُونَ .نَسْأَلُ اللّٰه لَنَا وَلَكُمُ الْعَافِيَةَ»

‹‹አስሰላሙ ዓለይኩም፤ አህለድዲያሪ ሚነል ሙእሚኒነ ወል ሙስሊሚነ፤ ወኢንና ኢንሻአላሁ ቢኩም ላሂቁን፤ ነስአሉላሁ ለና ወለኩምል ዓፊያ፡፡››

‹‹በዚህ መካነ መቃብር የምትገኙ ምዕመናንና ሙስሊሞች ሆይ! ሰላም በእናንተ ላይ ይሁን፡፡ እኛ አላህ ሲፈቅድ ከእናንተ ጋር እንቀላቀላለን፡፡ ለእኛም ለእናንተም ደህንነቱን እንዲለግሰን አላህን እንማጸነዋለን፡፡›› ቲርሚዚ ኢብኑ ዐባስን ጠቅሶ በዘገበው ሀዲስ ደግሞ፣ የአላህ መልእክተኛ በመዲና መቃብር ሲያልፉ ወደ መቃብሩ ፊታቸውን አዙረው የሚከተለውን ብለዋል፡-

«السَّلَامُ عَلَيْكُمْ يَا أَهْلَ الْقُبُورِ، يَغْفِرُ اللّٰه لَنَا وَلَكُمْ؛ أَنْتُمْ سَلَفُنَا وَنَحْنُ بِالأَثَرِ»

‹‹አስሰላሙ ዓለይኩም ያ አህለል ቁቡሪ፤ የግፊሩላሁ ለና ወለኩም፤ አንቱም ሰለፉና ወነህኑ ቢል አሠር፡፡››

‹‹በዚህ መካነ መቃብር የምትገኙ ምዕመናንና ሙስሊሞች ሆይ! ሰላም በእናንተ ላይ ይስፈን፤ አላህ ለእኛና ለእናንተ ምህረቱን ይስጠን፤ እናንተ ቀዳሚዎች ስትሆኑ፣ እኛ ደግሞ ተከታዬች ነን፡፡››

ከእነዚህ ነቢያዊ ሀዲሶች መረዳት እንደሚቻለው፣ ሸሪዓው እውቅና የሰጠው የቀብር ጉብኘት አላማው፣ መጪውን አለም

ለማስታወስ፣ ለሙታን በጎ ለመዋልና እነሱን አላህ እንዲያዘንላቸው ዱዓ ለማድረግ ነው፡፡ ነገር ግን መቃብሩን የሚጎበኘው ሰው ከመቃብራቸው ዱዓ ለማድረግ፣ ከመቃብሩ ቁጭ ለማለት ወይም የሆነ ጉዳይ እንዲፈጸምለት እነሱን ለመጠየቅ ወይም የታመመ እንዲድንለት እነሱን ለመማጸን ወይም እነሱ አላህ ዘንድ ባላቸው ደረጃ (ክብር) ወይም መሰል ነገርን በመጠቀም እነሱን ለመጠየቅ ከሆነ፣ እንደዚህ አይነቱ የመቃብር ጉብኝት አዲስ መጤ፣ የሚነቀፍና አላህ እንዲሁም ነቢዩ ያልደነገጉት ተግባር ነው፡፡ ስራቸውን አላህ ይውደድላቸውና ቀደምት ደጋግ ሙስሊሞችም አልተገበሩትም፡፡ እንዲያውም ይህ አይነቱ ተግባር ነቢዩ የከለከሉት የወንጀል ተግባር ነው፡፡ የአላህ መልእክተኛ አህመድ በዘገበው ሀዲስ እንዲህ ይላሉ፡-

«زُورُوا الْقُبُورَ، وَلَا تَقُولُوا هُجْرًا»

‹‹መቃብርን ጎብኙ፡፡ ነገር ግን መጥፎ ነገር አትናገሩ፡፡››

እነዚህ ያወሳናቸው ነገሮች ሁሉ አዲስ መጤ (ቢድዓ) ናቸው፡፡ ነገር ግን ደረጃቸው የተለያየ ነው፡፡ ከፊሉ አዲስ መጤ (ቢድዓ) እንጂ፣ ሺርክ አይደሉም፡፡ ለምሳሌ አላህን ቀብር ላይ ሆኖ መለመን፣ አላህን በሙታን ደረጃ (ክብር) እና በመሰል ነገሮች መጠየቅ የቢድዓ ተግባሮች ናቸው፡፡ ከፊሎች ደግሞ ከትልልቅ ሺርክ የሚመደቡ ናቸው፡፡ ለምሳሌ፡- ሙታንን መለመን፣ በእነሱ መታዘዝና መሰል ተግባሮች ትልቅ ሺርክ ናቸው፡፡

ቀደም ብሎ ይህን የመሰል ነጥብ ተነስቶ እዚያ ላይ ዝርዝር ማብራሪያ ሰጥተናል፡፡ ስለሆነም ማንኛውም ሰው በዚህ ጉዳይ ላይ ንቁና ጥንቁቅ መሆን አለበት፡፡ ጌታህን መልካምን ነገርን መገጠምንና ለሀቁ መንገድ መመራትን ጠይቅ፡፡ እሱ ከጉድለት የጠራው ጌታ፣ ቅኑን መንገድ መሪና አጎናጻፊ ነው፡፡ ከእሱ ውጪ አምላክ የለም፤ ከእሱ ወጪም ጌታ የለ፡፡

ይህ በመጨረሻ ልንገልጸው የፈለግነው ነጥብ ነው፡፡ በመጀመሪያም በመጨረሻም ምስጋና ለአላህ ይሁን፡፡ በባሪያው፣ በመልእክተኛው፣ ከፍጡራኑ መካከል ምርጥ በሆኑት ሙሀመድ ላይ፣ በቤተሰቦቻቸው፣ በባልደረቦቻቸው እንዲሁም እስከ ዕለተ ትንሳኤ ድረስ መንገዳቸውን በሚገባ መልኩ ለተከተሉ ሁሉ የአላህ እዝነትና ሰላም ይስፈንባቸው፡፡

# ሰላምታ፣ ማስነጠስና በሽተኛን መጠየቅ

1. ዐብደላህ ኢብኑ ዐምር ኢብኑል ዓስ (ረ. ዐ) እንዳስተላለፉት፣ የሆነ ሰው የአላህ መልክተኛን፣ «ከኢስላም መልካሙ የትኛው ነው?» ብሎ ጠየቃቸው፡፡ እሳቸውም፣ «ምግብ ታበላለህ፤ ለምታውቀውም ለማታውቀውም ሰው ላይ ሰላምታ ታቀርባለህ» አሉት፡፡ (ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል)፡፡

2. አቢ ሁረይራ (ረ. ዐ) እንዳስተላለፉት፣ የአላህ መልእክተኛ እንዲህ ብለዋል፡- «እናንተ እስካለመናችሁ ድረስ ጀነት አትገቡም፤ እስካልተዋደዳችሁ ድረስም ደግሞ አላመናችሁም፡፡ እናንተ ከሰራችሁት ልትዋደዱበት የምትችሉትን ነገር ልጠቁማችሁን? በመካከላችሁ ሰላምታን አብዙ (አሰራጩ)፡፡» (አሰላሙ ዐለይኩም ተባባሉ፡፡) (ሙስሊም የዘገበው)፡፡

3. አቢ ሁረይራ (ረ. ዐ) እንዳስተላለፉት፣ የአላህ መልእክተኛ እንዲህ ብለዋል፡- « አንድ ሙስሊም በሌላው ሙስሊም ወንድሙ ላይ አምስት ነገሮች ግዴታ ይሆኑበታል፡፡ (እነሱም) ለሰላምታ ምላሽ መስጠት፣ ያስነጠሰው ሰው፣ አልሀምዱሊላሂ ሲል፣ የርሀሙከላህ ማለት፣ ለጥሪ ምላሽ መስጠት፣ በሽተኛን መጠየቅ፣ ሬሳን መሸኘት (መከተል)፡፡» (ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል)፡፡

4. አቢ ሁረይራ (ረ. ዐ) እንዳስተላለፉት፣ የአላህ መልእክተኛ እንዲህ ብለዋል፡- «አንድ ሙስሊም በሌላው ሙስሊም ላይ ያለው መብት (ሀቅ) ስድስት ነው»፡፡ የአላህ መልእክተኛ ሆይ! ምንድን ናቸው? ተባሉ፡፡ እሳቸውም፣ «ስታገኘው ሰላምታ ልታቀርብለት፣ ጥሪ ሲያደርግልህ፣ ለጥሪው አወንታዊ ምላሽ ልሰጥ፣ ምክር ሲጠይቅህ፣ ልትመክረው፣

አስነጥሶት አልሀምዱሊላሂ ሲል፣ የርሀሙከላህ ልትለው፣ ሲታመም ልታየውና ሲሞት ደግሞ ልትሸኘው ነው» አሉት፡፡ (ሙስሊም ዘግቦታል)፡፡

5. አቡ ሁረይ (ረ. ዐ) እንዳስተላለፉት፣ የአላህ መልእክተኛ እንዲህ ብለዋል፡- «አላህ የሚያስነጥሳቸውን ሰዎች ይወዳል፤ ማስፋሸግን ግን ይጠላል፡፡ አንድ ሰው ካስነጠሰው፣ አልሀምዱሊላሂ ይላል፡፡ እሱ አስነጥሶት አልሃምዱሊህ ሲል፣ ያስነጠሰው መሆኑን የሰማ ሁሉ እሱን የርሀሙከላህ ማለት ግዴታ አለባቸው፡፡ ማስፋሸግ የሰይጣን ተግባር ነው፡፡ አንድ ሰው ሲያስፋሽገው፣ በተቻለ መጠን ፍሽጊያውን ሊመልሰው (አፉን በእጁ ወይም በሌላ ነገር ሊያፍነው) ይገባል፡፡ አፉን ከፍቶ ሃ (ኣ) ካለ፣ በዚህ ስራው ሰይጣን ይስቅበታል፡፡» (ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል)፡፡

6. አቡ ሁረይራ (ረ. ዐ) እንዳስተላለፉት፣ የአላህ መልእክተኛ እንዲህ ብለዋል፡- «ማስፋሸግ ከሰይጣን ነው፡፡ አንድኛችሁ ካስፋሸገው፣ በተቻለ መጠን (አፉን) ይፈነው፡፡» (ሙስሊም ዘግቦታል)፡፡

7. አቢ ሰዒድ አል-ኹድሪ (ረ. ዐ) እንዳስተላለፉት፣ የአላህ መልእክተኛ እንዲህ ብለዋል፡- «አንድኛችሁ ሲያስፋሽገው፣ አፉን ይያዘው (ይፈነው)፡፡ (አፉን ካላፈነው) ሰይጣን ይገባል፡፡» (ሙስሊም ዘግቦታል)፡፡

8. አቡ ሁረይራ (ረ. ዐ) እንዳስተላለፉት፣ የአላህ መልእክተኛ እንዲህ ብለዋል፡-«አንድኛችሁ ሲያስነጥሰው፣ አልሀምዱሊላሂ ይበል፡፡ ወንድሙ ወይም ጉዋደኛው የርሀሙከላህ (አላህ ይዘንልህ) ይበለው፡፡ የርሀሙከላህ ሲለው፣ እሱ ደግሞ፣ የህዲኩሙላህ ወዩስሊሁ ባለኩም (አላህ ቅኑን መንገድ ይምራችሁ፤ ጉዳያችሁን ያብጅላችሁ) ይበለው፡፡» (ቡኻሪ ዘግቦታል)፡፡

9. አቡ ሙሳ አል-ዐሽዐሪይ የአላህ መልእክተኛ ሲናገሩ እንደሰሙት፣ የአላህ መልእክተኛ እንዲህ ብለዋል፡- «አንድኛችሁ ሲያስነጥሰው፣ አልሀምዱሊላሂ ካለ፣ የርሀሙከላህ ይበለው፡፡ እሱ ሲያስነጥሰው፣ አልሀምዱሊላሂ ካላለ፣ የርሃሙከላህ አይበለው፡፡» (ሙስሊም ዘግቦታል)፡፡

# አዝካሮችና ዱዓዎች

## በምትኛና ከእንቅልፍ በኋላ የሚባሉ ዚክሮችና ዱዓዎች

1. ሁዘይፋ (ረ. ዐ) እንዳስተላለፉት፣ የአላህ መልእክተኛ በሌሊት በጎናቸው ጋደም ካሉ (ከተኙ)፣ እጃቸውን ከጉንጫቸው በታች ያደርጉ ነበር፡፡ ከዚያም እንዲህ ይላሉ፡- ‹‹አልህምመ ቢስሚከ አሙቱ ወአህያ፡፡››

‹‹አላህ ሆይ! በአንተ ስም እሞታለሁ፤ ህያውም እሆናለሁ፡፡››

ከእንቅልፍ ሲነቁ ደግሞ፣ ‹‹አልሀምዱሊላሂ አልለዚ አህያና በዕደ ማ አማተና ወኢለይሂንኑሹር፡፡›› ‹‹ለእዚያ ከሞት በሁዋላ ህያው ላደረገን፣ ከዚያም ወደ እሱ የምንቀሰቀስ ለሆነው አላህ ምስጋና ይገባው፡፡›› ቡኻሪ አቢ ዘርን ጠቅሰው ተመሳሳይ የሆነ ዘገባ ዘግበዋል፡፡ በሌላ ዘገባም ሙስሊም እላይ የተወሳውን ሁዘይፋ ያስተላለፉትን የመሰለ ሀዲስ፣ በራእ ኢብኑ አዚብን ጠቅሶ ዘግቡዋል፡፡

2. ዓኢሻ (ረ. ዐ) እንዳስተላለፉት፣ የአላህ መልእክተኛ ሁል ጊዜ ወደ መኝታቸው ሲሄዱ፣ መዳፋቸውን ሰብሰብ አድርገው እፍ ይሉባቸዋል፡፡ ቁል ሁወ አልላሁ አሀድን፣ ቁል አዑዙ ቢረቢል ፈለቅንና ቁል አዑዙ ቢረቢናሲን ይቀራሉ፡፡ ከዚያም የቻሉትን ያህል በመዳፎቻቸው ሰውነታቸውን ያብሳሉ፡፡ ሲያብሱም የሚጀምሩት

ከጭንቅላታቸው ጀምሮ ፊታቸውን፣ ፊት ለፊት ያለውን አካላቸውን ነው፡፡ ይህን ድርጊት ሶስት ጊዜም ይሰሩታል፡፡

3. አቢ ሁረይራ (ረ. ዐ) እንዳስተላለፉት፣ የአላህ መልዕክተኛ የዘካ ንብረት እንዲጠብቅ ባደረጉት አጋጣሚ፣ የሆነ አካል ወደ እሱ መጣና ከዘካው የተወሰነ መውሰድ ጀመረ፡፡ ይህንንም ስራውን ለሁለተኛ ቀን ደገመው፡፡ በሶስተኛው ቀንም አቢ ሁረይራ፣ «አንተን ወደ አላህ መልእክተኛ ዘንድ ነው የማደርስህ» አለው፡፡ እሱም፣ «(ወደ አላህ መልእክተኛ) አትውሰደኝ፡፡ ይልቅ አላህ በእነሱ ሊጠቅምህ የሚችልበትን ቃላት ላስተምርህ» አለው፡፡ «ቃላቱ ምንድን ናቸው» አልኩት፡፡ እሱም፣ «ልትተኛ ስትል፣ አየተል ኩርስይ ቅራ (አንብብ) አንቀጹንም እስከምትጨርስ ድረስም ቅራ (አል-በቀራ፣ 255)፡፡ ይህን አንቀጽ ከቀራህ፣ ከአላህ ዘንድ የሆነ ጠባቂ ከአንተ ጋር አብሮ ከመሆን አይርቅም፡፡ እስከምታነጋ ድረስም፣ ሰይጣን ወዳንተ አይቀርብህም» አለ፡፡ የአላህ መልእክተኛ እንዲህ አሉ፡- «እውነት ነገረህ፤ እሱ ውሸታም ነው፡፡ እሱም ሰይጣን ነው፡፡» (ቡኻሪ ዘግቦታል)፡፡

﴿ ٱللَّهُ لَآ إِلَٰهَ إِلَّا هُوَ ٱلۡحَيُّ ٱلۡقَيُّومُۚ لَا تَأۡخُذُهُۥ سِنَةٞ وَلَا نَوۡمٞۚ لَّهُۥ مَا فِي ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَمَا
فِي ٱلۡأَرۡضِۗ مَن ذَا ٱلَّذِي يَشۡفَعُ عِندَهُۥٓ إِلَّا بِإِذۡنِهِۦۚ يَعۡلَمُ مَا بَيۡنَ أَيۡدِيهِمۡ وَمَا خَلۡفَهُمۡۖ
وَلَا يُحِيطُونَ بِشَيۡءٖ مِّنۡ عِلۡمِهِۦٓ إِلَّا بِمَا شَآءَۚ وَسِعَ كُرۡسِيُّهُ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضَۖ وَلَا
يَـُٔودُهُۥ حِفۡظُهُمَاۚ وَهُوَ ٱلۡعَلِيُّ ٱلۡعَظِيمُ ٢٥٥ ﴾

«አላህ ከእርሱ በቀር ሌላ አምላክ የለም፡፡ ህያው ራሱን ቻይ ነው፡፡ ማንገላጀትም እንቅልፍም አትይዘውም፤ በሰማያት ውስጥና በምድር ውስጥ ያለው ሁሉ የእርሱ ብቻ ነው፡፡ ያ እርሱ ዘንድ በፈቃዱ ቢሆን እንጂ የሚያማልድ ማነው? (ከፍጡሮች) በፊታቸው ያለውንና ከኋላቸው ያለውን ሁሉ ያውቃል፡፡ በሻውም ነገር እንጂ፣ ከእውቀቱ በምንም ነገር

አያካብቡም (አያውቁም)፡፡ መንበሩ ሰማያትንና ምድርን ሰፋ፡፡ ጥበቃቸውም አያቅተውም፡፡ እርሱም የሁሉ በላይ ታላቅ ነው» (አል-በቀራ፣ 255)፡፡

4. አቢ መስዑድ አል-አንሱዋሪ (ረ. ዐ) እንዳስተላለፉት፣ የአላህ መልእክተኛ እንዲህ ይላሉ፡- «ሁለት የአል-በቀራን ምዕራፍ የመጨረሻ ክፍል አንቀጾች ያነበበ ሰው፣ (ከመጥፎ ነገር) እነሱ ይበቁታል፡፡» (ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል)፡፡

5. በራእ ኢብኑ ዓዚብ (ረ. ዐ) እንዳስተላለፉት፣ የአላህ መልእክተኛ እንዲህ ይላሉ፡- «አንተ ወደ መኝታህ ስትሄድ፣ ለሶላት እንደምታደርገው ዉዱእ አድርግ፡፡ ከዚያም በቀኝ ጎንህ ጋደም በል፡፡ ከዚያም አላሁምመ አስለምቱ ነፍሲ ኢለይኪ፤ ወወጅጀህቱ ወጅሂ ኢለይከ፤ ወፈውወድቱ (ሲነበብ- ወፈውወቱ) አምሪ ኢለይከ፤ ወአልጀእቱ ዞህሪ አለይከ፤ ረግበተን ወረህበተን ኢለይክ፤ ላመልጀአ ወላ መንጃ ሚንከ ኢልላ ኢለይከ፤ አመንቱ ቢኪታቢከለዚ አንዘልተ፤ ወቢነቢይዪከለዚ አርሰልተ፤ ይህን ባልክበት ሌሊት ከሞትክ፣ አንተ በኢስላም ላይ ነው የሞትከው፡፡ እነዚህን ዱዓዎች በምትለው ነገር መጨረሻ አድርጋቸው፡፡»

«አላህ ሆይ! ወደ አንተ በመከጀልና በመፈለግ ነፍሴን ላንተ ሰጥቻለሁ፤ ፊቴንም ወደ አንተ አዙሬያለሁ፤ ጉዳዮን ሁሉ ላንተ ትቻለሁ፤ ጀርባዬንም ወደ አንተ አስጠግቻለሁ፤ ወደ አንተ ቢሆን እንጂ መጠጊያም ሆነ ነጻ መውጫ የለም፤ ባወረድከው መጽሀፍ አምኛለሁ፤ በላክከውም ነቢይም አምኛለሁ፡፡» (ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል)፡፡ በሌላ የሙስሊም ዘገባ ደግሞ፣ «እነዚህን ቃላት የንግግርህ መጨረሻ አድርጋቸው፡፡» ብለዋል፡፡

6. አቢ ሁረይራ (ረ. ዐ) እንዳስተላለፉት፣ የአላህ መልእክተኛ ወደ መኝታ ሲሄዱ «አላሁምመ ረብበ ስሰማዋቲ፣ ወረብበል

አርዲ፣ ወረብበል ዐርሺል ዐዚም፡፡ ረብበና ወረብበ ኩሊ ሸይኢን፤ ፋሊቂል ሀቢ ወንነዋ፤ ወሙንዝዚሊተውራቲ፣ ወልኢንጂሊ፣ ወልፉርቃኒ፤ አዑዙ ቢከ ሚን ሸርሪ ኩሊ ሸይኢን፤ አንተ ኣኺዙን ቢናሲየቲሂ፤ አላሁምመ አንተል አውወሉ፤ ወለይሰ ቀብለከ ሸይኡን፤ ወአንተል ኣኺሩ ፈለይሰ በዕደከ ሸይኡን፤ ወአንተዝዛሂሩ ፈለይሰ ፈውቀከ ሸይኡን፤ ወአንተል ባጢኑ ፈለይሰ ዱነከ ሸይኡን፤ ኢቅዲ ዐንነድደይነ፤ ወአግኒና ሚነልፈቅሪ፡፡»

«አላህ ሆይ! የሰባቱ ሰማያትና የግዙፉ ዐርሽ ጌታ ነህ፤ የእኛም ሁሉም ነገሮች ጌታ ነህ፤ ፍሬን በቆልትን ፈልቃቂ፣ ተውራትንና ኢንጂልን እንዲሁም ፉርቃንን ያወረድከው አምላክ ነህ፤ በቁጥጥርህ ስር ካለው ሁሉ ነገር ክፋት በአንተ እጠበቃለሁ፤ አላህ ሆይ! አንተ የመጀመሪያ ነህ፤ ከአንተ በሁዋላ ምንም ነገር አልነበረም፤ አንተ የመጨረሻ ነህ፤ ከአንተ በሁዋላ ምንም ነገር አይኖርም፤ አንተ ግልጽ ነህ፤ ከአንተ በላይ ምንም ነገር የለም፤ አንተ ስውር ነህ፤ ከአንተ ውጪ ምንም ነገር የለም፤ እዳችንን አቃልልን፤ ከድህነትም ገላግለን፡፡» (ሙስሊም የዘገበው)፡፡

7. የአማኞች እናት ሀፍሱዋ እንዲህ ይላሉ፡- የአላህ መልእክተኛ ሊተኙ ሲፈልጉ፣ ቀኝ እጃቸውን ከቀኝ ጉንጫቸው በታች ያደርጉታል፡፡ ከዚያም በሁዋላ ሶስት ጊዜ እንዲህ ይላሉ፡- «አላሁምመ ቂኒ ዐዛበከ የውመ ተብዐሡ ዒባደከ፡፡»

«አላህ ሆይ! ባሮችህን በምትቀሰቅስበት ቀን ከቅጣትህ ጠብቀኝ፡፡» (ኢማሙ አህመድና አቡ ዳውድ ዘግበውታል)፡፡

8. አነስ እንዳስተላለፉት፣ የአላህ መልእክተኛ ወደ መኝታ ቦታ ሲሄዱ እንዲህ ይሉ ነበር፡- «አልሀምዱሊላሂ አጥዐመና፣ ወሰቃና፣ ወከፋና፣ ወኣዋና፡፡ ፈከም ሚምመን ላካፊ ለሁ፤ ወላ ሙእዊየ፡፡»

«ላበላንና ላጠጣን፣ ላብቃቃንና ላስጠጋን አላህ ምስጋና ይገባው:: አብቃቂም፣ መጠጊያም የሌላቸው በርካታ ሰዎች አሉ::» (ሙስሊም ዘግቦታል)::

9. ዐብደላሁ ኢብኑ ዑመር (ረ. ዐ) እንዳስተላለፉት፣ የአላህ መልእክተኛ የሆነን ሰው ወደ መኝታ ቦታ ሲሄድ እንዲህ እንዲል አዘዙት፡- «አላሁምመ ኸልቅተ ነፍሲ፤ ወአንተ ተዋፍፋሃ፤ ለከ መማቱሃ ወምህያሃ፤ ኢን አህየይተሃ፣ ፈህፈዝሃ፤ ወኢን አመትተሃ፣ ፈግፊር ለሃ፤ አላህምመ ኢኒ አስአሉከልዓፊየተ::»

«አላህ ሆይ! አንተ ነፍሴን ፈጥረሃታል፤ ለሞትም የምታበቃት አንተው ነህ፤ ሞቱዋም ህይወቱዋም ላንተ ነው፤ በህይወት ካቆየሃት ጠብቃት፤ ለሞት ካበቃሃት ደግሞ ምህረትህን ለግሳት፤ አላህ ሆይ! ደህንነትን እጠይቅሃለሁ::» ኢብኑ ዑመር ይህን ሀዲስ፣ «የአላህ መልእክተኛ ሲናገሩት ሰምቻለሁ» ብለዋል:: (ሙስሊም ዘግቦታል)::

10. አቢ ሁረይራ (ረ. ዐ) እንዳስተላለፉት፣ የአላህ መልእክተኛ እንዲህ ብለዋል፡- «አንድኛችሁ ወደ መኝታው ሲሄድ፣ (ራቁቱን እንዳይተኛ) የውስጥ ልብስ (ቱታ፣ ፓንት፣ ወዘተ) ያድርግ:: መኝታው ላይ ምራቁን እትፍ ይበልበት፤ ቢስሚላሂም ይበል:: እሱ መኝታውን ከለቀቀው በሁዋላ ምን እንደተከሰተ ኢያውቅም:: መተኛት ከፈለገ፣ በቀኝ ጎኑ ጋደም ይበል:: እንዲህም ይበል፡- «ሱብሃነከላሁምመ ረብቢ ወደዕቱ ጀንቢ፣ ወቢከ አርፈዑሁ፤ ኢን አምሰክተ ነፍሲ፣ ፈግፊር ለሃ፤ ወኢን አርሰልተሃ፣ ፈህፈዝሃ ቢማ ተህፊዙ ቢሂ ዒባደከስሱዋሊሂን::»

«ጌታዬ ሆይ! በአንተ ስም ጎኔን አሳርፋለሁ፤ በአንተ ስምም አነሳዋለሁ፤ ነፍሴን ከያዝካት፣ እዘንላት፤ ከላክካት ደግሞ ቅን ባሪያዎችህን በምትጠብቅበት (መንገድ) ጠብቃት::» (ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል)::

11. ዐሊይ (ረ. ዐ) እንዳስተላለፉት፣ ፋጢማ (ረ.ዐ) የቤት ሰራተኛ ፈልጋ ወደ አላህ መልእክተኛ ዘንድ ሄደች፡፡ ነገር ግን የአላህን መልዕክተኛ አላገኘቻቸውም፡፡ ይሁን እንጂ የመጣችበትን ጉዳይ ለዓኢሻ አወሳችላት፡፡ ዓኢሻ የአላህ መልእክተኛ ሲመጡ፣ ጉዳዩን ነገረቻቸው፡፡ ዐልይ እንዲህ ይላል፡- ‹‹እኛ ተኝተን እያለ፣ የአላህ መልእክተኛ ወደ እኛ መጡ፡፡ እኔም ከመኝታዬ ልነሳ ስል፣ የአላህ መልእክተኛ፣ ‹እዛው ከነበረባችሁበት ቦታ ሁኑ› አሉንና በመካከላችንም ተቀመጡ፡፡ በዚህም ጊዜ የእግራቸው ቅዝቃዜ ደረቴን ይሰማኝ ነበር፡፡ እሳቸውም እንዲህ አሉ፡- ‹‹ለእናንተ ከቤት ሰራተኛ የበለጠ አላመላከታችሁምን? ወደ መኝታችሁ ስትሄዱ ወይም ከመኝታችሁ ጋደም ስትሉ ሱብሃነላህን ሰላሳ ሶስት ጊዜ፣ አልሀምዱሊላሂን ሰላሳ ሶስት ጊዜ፣ አላሁ አክበርን ሰላሳ ሶስት ጊዜ ማለታችሁ ከቤት ሰራተኛ ይበልጣል፡፡›› (ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል)፡፡

12. ዑባዳ ኢብኑ ሷሚት (ረ. ዐ) እንዳስተላለፉት፣ አላህ መልክተኛ እንዲህ ብለዋል፡- ‹‹በሌሊት ከእንቅልፉ ነቅቶ፣ ላኢላሃ አልለላህ ወህደሁ ላሸሪከ ለሁ፤ ለሁል ሙልኩ፤ ወለሁል ሀምዱ፤ ወሁወ ዐላ ኩሊ ሸይኢን ቀዲር፤ ወሱብሃነላህ፤ ወላኢላሃ ኢልለላህ፤ ወላሁ አክበር፤ ወላሀውለ ወላ ቁወተ ኢልላ ቢላሂ፤ ያለና ከዚያም አላሁምመግፊርሊ ‹‹ከአላህ ውጪ ሌላ አምላክ የለም፤ አንድ ነው፤ አጋር የለውም፤ ንግስና የእሱ ብቻ ነው፤ ምስጋናም ለእሱ ብቻ ነው፤ እርሱ በሁሉም ነገር ላይ ቻይ ነው፤ እሱ ጥራት ይገባው፤ ከአላህ ውጪ ሌላ አምላክ የለም፤ አላህ ታላቅ ነው፤ ብልሃትና ሀይል የአላህ ብቻ ነው፡፡ ጌታዬ ሆይ! ለወንጀሌ ምህረት አድርግልኝ›› ቢል ወይም ዱዓ ቢያደርግ ዱዓው ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡ ዉዱእ አድርጎም ሶላት ከሰገደ፣ ሶላቱ ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡›› (ቡኻሪ ዘግቦታል)፡፡

# የጧትና የማታ አዝካሮች (ውዳሴዎች)

1. አቢ ሁረይራ (ረ. ዐ) እንዳስተላለፉት፣ የአላህ መልእክተኛ እንዲህ ብለዋል፡- «ሲያነጋና ሲያመሽ መቶ ጊዜ ሱብሃነላህ ወቢሀምዲሂ ያለ ሰው፣ የዕለተ ትንሳኤ ዕለት ከእሱ በተሻለ የሰራ አንድ እንኳዋ የሚመጣ የለም፡፡ እንደ እሱ የሰራ ወይም ከእሱ በተሻለ መንገድ የሰራ ሲቀር፡፡» (ሙስሊም ዘግበታል)፡፡

2. ኢብኑ መስዑድ (ረ. ዐ) እንዳስተላለፉት፣ የአላህ መልእክተኛ ምሽት ሲመጣ (ላይ) እንዲህ ይሉ ነበር፡- «አምሰይና ወአምሰል ሙልኩ ሊላሂ፤ ወልሀምዱ ሊላሂ፤ ላኢላሃ ኢልለላህ ወህደሁ ላሸሪከ ለሁ፤ ለሁል ሙልኩ፣ ወለሁል ሀምዱ፣ ወሁወ ዐላ ኩል ሸይኢን ቀዲር፡፡ ረብቢ አስአሉከ ኸይረ ማፊሃዚሂልለይለቲ፤ ወኸይረ ማ ባዕደሃ፤ ወአዑዙ ቢከ ሚን ሸሽሪ ማፊሃዚሂልለይለቲ፤ ወሸርሪ ማበዕደሃ፤ ረብቢ አዑዙቢከ ሚነል ከሰሊ ወሱኡል ኪበሪ፤ ረቢ አዑዙ ቢከ ሚን ዐዛቢን ፊንናሪ፤ ወዐዛቢን ፊል ቀብሪ፡፡»

«እኛ አምሽተናል፤ ንግስናም የአላህ ሆኖ አምሽቱዋል፤ ምስጋና ለአላህ የተገባ ነው፤ ከአላህ ውጪ ሌላ አምላክ የለም፤ አንድ ነው፤ አጋር የለውም፤ ንግስና የእሱ ብቻ ነው፤ ምስጋናም ለእሱ ብቻ ነው፤ እርሱ በሁሉም ነገር ላይ ቻይ ነው፤ ጌታዬ ሆይ! በዚህ ሌሊት ውስጥ ያለውን መልካም ነገርና የቀጣዩን (የሌሊቱን) መልካም ነገር እጠይቅሃለሁ፡፡ ጌታዬ ሆይ!

ከስንፍናና ከከፋ እርጅና በአንተ እጠበቃለሁ፤ ጌታዬ ሆይ! ከእሳትና ከቀብር ውስጥ ቅጣት በአንተ እጠበቃለሁ፡፡»

ንጋት ላይ ደግሞ እንዲህ ይላል፡- «አስበህና ወአስበሀል ሙልኩ ሊላሂ .....» «እኛ አንግተናል፤ ...»

3. ሸዳድ ኢብኑ አውስ (ረ. ዐ) እንዳስተላለፉት፣ የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ብለዋል፡- «ከኢስቲግፋር (አላህን ምህረት ከመጠየቅ) የላቀው፣ አላሁምመ አንተ ረብቢ፤ ላኢላሃ ኢልላ አንተ፤ ወአነ ዐብዱከ፤ ወአነ ዐላ ዐህዲከ ወወዕዲከ መስተጦዕቱ፤ አዑዙ ቢከ ሚን ሸሸርሪ ማሶናዕቱ፤ አቡኡ ለከ፤ ቢኒዕመቲከ ዐለይዬ፤ ወአበኡ ቢዘንቢ፤ ፈግፊር ሊ፤ ፈኢንነሁ ላየግፊሩ ዘኑበ ኢልላ አንተ፡፡» «አላህ ሆይ! ጌታዬ አንተ ነህ፤ ከአንተ በስተቀር አምልኮት የሚገባው አምላክ የለም፤ ፈጥረኸኛል፤ እኔ ደግሞ ባሪያህ ነኝ፤ እኔ በምችለው ያህል ባንተ ቃል ኪዳንና ቀጠሮ ላይ ነኝ፤ ከሰራሁት ተንኮል ሁሉ በአንተ እጠበቃለሁ፤ ለዋልክልኝ ጸጋ እውቅና እሰጣለሁ፤ ከወንጀሌም ወደ አንተ እመለሳለሁ፤ ማረኝ፤ ያለ አንተ በቀር ወንጀሎችን የሚምር የለም፡፡»

የአላህ መልእክተኛ ጨምረው እንዲህ አሉ፡- «በዚህ ዚክር እርግጠኝነት ተሰምቶት ቀን ላይ ያለው ሰው፣ የምሽቱ ጊዜም ከመምጣቱ በፊት ከሞተ፣ እሱ የጀነት ሰው ነው፡፡»

4. ዐብደላህ ኢብኑ ሀቢብ (ረ. ዐ) አባታቸውን ጠቅሰው እንዳስተላለፉት፣ እንዲህ ይላሉ፡- «(የአላህ መልእክተኛ) ሶላት እንዲያሰግዱን ፈልገን፣ ዝናብ በሚጥልበት፣ ሀይለኛ ጨለማ ባለበት ሌሊት ወጣን፡፡ እሳቸውንም አገኘናቸው፡፡ እሳቸውም፣ ‹ሶላት አልሰገዳችሁንም› አሉን፡፡ እኔም ምንም ነገር አላልኩም፡፡ እሳቸውም፣ ‹በል› አሉኝ፡፡ እኔም ምንም ነገር አላልኩም፡፡ ከዚያም እሳቸው፣ ‹በል› አሉኝ፡፡ እኔም የአላህ መልእክተኛ ሆይ! ምንድን ነው የምለው? አልኩዋቸው፡፡

እሳቸውም፣ ‹ስታነጋና ስታመሽ ሶስት ሶስት ጊዜ ቁል ሁወ ላሁ አሀድ እና ሙዓወዘተይኒ (ቁል አዑዙ ቢረቢል ፈለቅንና ቁል አዑዙ ቢረቢንናስ በል፡፡ ይህን ማለትህ ከሁሉ ነገር እንድትጠበቅ ያደርግሃል›፡፡» (አቡ ዳውድ፣ ቲርሚዚና ነሳኢይ ሀሰን በሆነ የዘገባ ሰንሰለት - ሰነድ ዘግበውታል)፡፡

5. አቢ ሁረይራ (ረ. ዐ) እንዳስተላለፉት፣ አቢ በክር ሲዲቅ (ረ. ዐ)፣ «የአላህ መልእክተኛ ሆይ! በመሸና በነጋ ቁጥር፣ የምለው ነገር ይዘዙኝ» አሉ፡፡ የአላህ መልእክተኛ እንዲህ አሉ፡- «ቁሊ ላሁምመ ፋጢረ ስሰማዊቲ ወል አርዲ፤ ዓሊመል ገይቢ ወሸሸሃደቲ፤ ረብበ ኩልለ ሸይኢን ወመሊከሁ፤ አሽሀዱ አንልላኢላሀ ኢልላ አንተ፤ አዑዙቢከ ሚን ሸርሪ ነፍሲ፤ ወሸርሪ ሸሸይጣኒ ወሺርኪሂ፤ ወአን አቅተሪፍ ዐላ ነፍሲ፤ ሱኣን አው አጁርሩሁ ኢላ ሙስሊም፡፡»

«አላህ ሆይ! የሰማይና የምድር ፈጣሪ ነህ፤ የሩቁንና የቅርቡን የምታውቅ ነህ፤ የማንኛውም ነገር ጌታና ባለቤት ነህ፤ ከአንተ በስተቀር አምልኮት የሚገባው አምላክ እንደሌለ እመሰክራለሁ፤ ከነፍሴ፣ ከሰይጣንና ከጉዋዶቹ ተንኮልም በአንተ እጠበቃለሁ፤ በራሴ ላይ መጥፎ ነገር ከመፈጸምና ወደ ሌላው ሙስሊም ከማስተላለፍም በአንተ እጠበቃለሁ፡፡»

የአላህ መልእክተኛ፣ «ስታነጋና ስታመሽ እንዲሁም ለመተኛት ጋደም ስትል ይህን ዱዓ (ዚክር) በል» አሉት፡፡ (አህመድ፣ አቡ ዳውድ፣ ቲርሚዚ፣ ነሳኢይና ቡኻሪ ዘግበውታል)፡፡

6. ዑስማን ኢብኑ ዐፋን (ረ. ዐ) እንዳስተላለፉት፣ የአላህ መልእክተኛ እንዲህ አሉ፡- «ማንኛውም ሰው በየቀኑ በጧትና በማታ ‹ቢስሚላሂልለዚ ላየዱርሩ መዐ ኢስሚሂ ሸይኡን ፊል አርዲ ወላ ፊሰማእ፤ ወሁወ ስሰሚዑል ዐሊም› ሶስት ጊዜ አይልም፣ ምንም ነገር የማይጎዳው ቢሆን እንጂ፡፡»

‹‹በአላህ ስም (እጠበቃለሁ)፤ ከእርሱ ስም ጋር በምድርም ሆነ በሰማይ ያለ ነገር ሊጎዳ አይችልም፤ እርሱ ሰሚው አዋቂው ነው፡፡›› (ኢማሙ አህመድ፣ ቲርሚዚና ኢብኑ ማጃህ ዘግበውታል)፡፡ ቲርሚዚ አላህ ይዘንለትና የዚህን ሀዲስ ደረጃ ሀሱኑን ሶሂህ ነው ብሉዋል፡፡

7. የአላህ መልእክተኛ አገልጋይ የሆነው ሠውባን (ረ. ዐ) እንዳስተላለፈው፣ የአላህ መልእክተኛ እንዲህ ብለዋል፡- ‹‹ማንኛውም ሙስሊም ሲያነጋና ሲያመሽ ሶስት ጊዜ፣ ረዲይቱ ቢልላሂ ረብበን፤ ወቢል ኢስላሚ ዲነን፤ ወቢሙሀመደን (ሶ. ዐ. ወ) ነቢይየን፤ የሚል ሰው፣ አላህ በዕለተ ትንሳኤ ሊወደው ሀቅ (መብት) አለው፡፡››

‹‹በአላህ ጌትነት፣ በኢስላም ሃይማኖትነት፣ በነቢዩ ሙሀመድ ነቢይነት ወድጃለሁ፡፡›› (ኢማሙ አህመድ፣ አቡ ዳውድ፣ ኢብኑ ማጃህ ይህን ሀዲስ ሀሰን በሆነ የዘገባ ሰንሰለት - ሰነድ ዘግበውታል፡፡ አህመድ በዘገባው ግን ‹‹ሠውባን›› የሚለውን ስም አላወሳም፡፡ ነገር ግን ነሳኢይ አህመድ በዘገበበት መንገድ ‹‹የቀንና የሌሊት ስራ›› በሚለው ርዕስ ስር በሀዲሱ ጥራዝ ጠቅሶታል፡፡)

8. አቢ ሰዒድ አል-ኹድሪይ (ረ. ዐ) እንዳስተላለፉት፣ የአላህ መልእክተኛ እንዲህ አሉ፡- ‹‹ረዲይቱ ቢላሂ ረብበን፤ ወቢል ኢስላሚ ዲነን፤ ወቢ ሙሀመዲን ነቢይየን፤ ያለ ሰው፣ ለሱ ጀነት በቃችለት፡፡›› (ሙስሊም ዘግቦታል)፡፡

9. ዐባስ ኢብኑ ዐብዱል ሙጦሊብ (ረ. ዐ) እንዳስተላለፉት፣ የአላህ መልእክተኛ እንዲህ ብለዋል፡- ‹‹ረዲይቱ ቢላሂ ረብበን፤ ወቢል ኢስላሚ ዲነን፤ ወቢ ሙሀመዲን ረሱላ ያለ ሰው፣ የኢማንን ጣዕም አጣጥሙዋል፡፡››

10. አነስ (ረ. ዐ) እንዳስተላለፉት፣ የአላህ መልእክተኛ እንዲህ

ብለዋል፡- ‹‹ሲያነጋና ሲያመሽ፣ አላሁምመ ኢንኒ አስበህቱ ኡሽሂዱከ፣ ወኡሽሂዱ ሀመለተ ዐርሺከ፣ ወመላኢከቲከ፣ ወጀሚዓ ኸልቂከ፤ አንነከ አንተላሁ፤ ላኢላሃ ኢልላ አንተ፤ ወአንነ ሙሀመደን ዐብዱከ ወረሱሉከ፤ ያለ ሰው አላህ የዕለቱን አንድ አራተኛውን (ሩቡን) ክፍል ከእሳት ነጻ ያደርገዋል፡፡ ሁለት ወይም ሶስት ጊዜ ያለው ሰው፣ የዕለቱን ሶስት አራተኛ ክፍል አላህ ከእሳት ነጻ ያደርገዋል፡፡ አራት ጊዜ ያለው ሰው ደግሞ አላህ ከእሳት ነጻ ያደርገዋል፡፡››

‹‹አላህ ሆይ! አንተንና ዐርሽህን የተሸከሙ መላኢኮችህንና ፍጡራንህን ሁሉ በአጠቃላይ ሳስመሰክር አንግቻለሁ፤ አንተ አላህ ነህ፤ ከአንተ በስተቀር አምልኮት የሚገባው አምላክ የለም፤ አንድ ነህ፤ አጋር የለህም፤ ሙሀመድ ደግሞ ባሪያህና መልእክተኛህ ናቸው፡፡›› (አቡ ዳውድ ሀሰን በሆነ የዘገባ ሰንሰለት - ሰነድ ዘግበውታል፡፡ ነሳኢ ደግሞ በሀዲስ ጠራዛቸው ዐመሊል የውሚ ወልለይሊ በሚለው ምዕራፍ፣ ሀሰን በሆነ የዘገባ ሰንሰለት (ሰነድ) የሚከተለውን ዘግቡዋል፡-

‹‹ሲያነጋና ሲያመሽ፣ አላሁምመ ኢንኒይ አስበህቱ ኡሽሂዱከ፣ ወኡሽሂዱ ሀመለተ ዐርሺከ፣ ወመላኢከቲከ፣ ወጀሚዓ ኸልቂከ፤ አንነከ አንተልላሁ፤ ላኢላሃ ኢልላ አንተ፤ ወአንነ ሙሀመደን ዐብዱከ ወረሱሉከ፤ ያለ ሰው አላህ የዕለቱን አንድ አራተኛውን ክፍል ከእሳት ነጻ ያደርገዋል፡፡ አራት ጊዜ ያለ ሰው ደግሞ አላህ ዕለቱን ከእሳት ነጻ ያደርገዋል፡፡››

11. ዐብደላህ ኢብኑ ገናም (ረ. ዐ) እንዳስተላለፉት፣ የአላህ መልእክተኛ እንዲህ ብለዋል፡- ‹‹አንድ ሰው ሲያነጋ፣ አላህምመ ማ አስበሀ ቢ ሚን ኒዕመቲን፤ ፈሚንከ ወህደከ ላሸሪከ ለከ፤ ፈለከል ሀምዱ ወለከሸሹክር፤ ያለ ሰው የዕለቱን ምስጋና አሙዋልቱዋል፡፡ ይህንኑ ሲያመሽ ካለ፣ የምሽቱን ምስጋና አሙዋልቱዋል፡፡››

«አላህ ሆይ! ከእኔ ወይም ከፍጡራንህ በአንዱ ላይ ያነጋው ጸጋህ ከአንተ የተገኘ ነው፤ አንድ ነህ፤ አጋር የለህም፤ ምስጋና ለአንተ ነው፤ ውዳሴም የሚገባው ለአንተ ብቻ ነው፡፡» (ነሳኢና አቡ ዳውድ በሀዲስ ጠራዛቸው ዐመሊል የውሚ ወለይሊ በሚለው ምዕራፍ፣ ሀሰን በሆነ የዘገባ ሰንሰለት (ሰነድ) ዘግበውታል፡፡ ይህ ዘገባ የነሳኢይ ዘገባ ነው፡፡ ነገር ግን «ሂይነ ዩምሲ- ሲያመሽ» የሚለውን ሀሳብ አላወሳውም፡፡ ኢብኑ ሂባን ደግሞ ነሳኢይ ኢብኑ ዐባስን ጠቅሶ በዘገበው መንገድ በተመሳሳይ ሁኔታ ዘግቦታል)፡፡

12. ዐብደላህ ኢብኑ ዑመር (ረ. ዐ) እንዳስተላለፉት፣ የአላህ መልእክተኛ ሲያነጋና ሲያመሽ እነዚህን ዱዓዎች አይተዋቸዉም ነበር፡- «አላሁምመ ኢንኒይ አስአሉከል ዓፊየተ፤ ፊ ድዱንያ ወል ኣኺራ፤ አላሁምመ ኢንኒይ አስአሉከል ዐፈወ፣ ወልዓፊየተ ፊ ዲኒ፣ ወዱንያየ፣ ወአህሊ፣ ወማሊ፤ አላሁምመስቱር ዐውራቲ፤ ወኣምሚን ርረውዓቲ፤ አላሁምመህፈዝኒ ሚን በይኒ የደዬ፣ ወሚን ኸልፊ፣ ወዐን የሚኒ፣ ወዐን ሺማሊ፣ ወሚን ፈውቂ፤ ወአዑዙ ቢዐዞመቲከ አን ኡግታለ ሚን ተህቲ፡፡»

«አላህ ሆይ! በዚህም ሆነ በተከታዩ አለም ምህረትንና ጤንነትን እጠይቃለሁ፤ አላህ ሆይ! ምህረትንና ጤንነትን በእምነቴ፣ በአለማዊ ህይወቴ፣ በቤተሰቦቼና በገንዘቤ እጠይቅሃለሁ፤ አላህ ሆይ! ነውሮቼን ሸፍንልኝ፤ ፍርሃቴን አስወግድልኝ፤ አላህ ሆይ! ከበስተፊቴ ጠብቀኝ፤ ከበስተኋላየም ጠብቀኝ፤ ከስሬም እንዳልሞት በልዕልናህ እጠበቃለሁ፡፡» (ኢማሙ አህመድ ሙስነድ ላይ ሀዲሱን ያወሱት ሲሆን፣ ይህንኑ ሀዲስ አቡ ዳውድ፣ ነሳኢይና ኢብኑ ማጂህ ዘግበውታል፡፡ ሃኪም ደግሞ ሀዲሱን ትክክለኛ ነው ብለዋል)፡፡

13. አቢ ሁረይራ (ረ. ዐ) የአላህ እንዳስተላለፉት፣ መልእክተኛ

እንዲህ ብለዋል፡- «ላኢላሀ ኢለላህ፤ ወህደሁ ላሸሪከ ለሁ፤ ለሁልሙልኩ ወለሁል ሀምዱ፤ ወሁወ ዐላ ኩሊ ሸይኢን ቀዲር፤ ሲያነጋ አስር ጊዜ ያለው ሰው መቶ ምንዳ ሲመዘገብለት፣ መቶ ወንጀል ደግሞ ይታበስለታል፡፡ ባሪያን ነጻ የማውጣት ያህል ነው፤ በዕለቱም እስከሚመሽ ድረስ ጥብቅ ይሆናል፡ ፡ አንድ ሰው ሲመሽ ይህንኑ (አዝካር) ካለ፣ ይህንኑ መሰል ምንዳ ያገኛል፡፡» (ኢማሙ አህመድ በሙስነዳቸው ሀሰን በሆነ የዘገባ ሰንሰለት - ሰነድ ዘግበውታል)፡፡

14. አቢ ሁረይራ (ረ. ዐ) ዳግም እንዳስተላለፉት፣ የአላህ መልእክተኛ እንዲህ ብለዋል፡- «ሲያመሽ ሶስት ጊዜ፣ አዑዙ ቢከሊማቲላሂትታማት ሚን ሸርሪ ማኸለቅ ያለ ሰው፣ በዚሁ ሌሊት ተናዳፊ ነፍሳት አይጎዱትም፡፡»

«ሙሉ በሆኑት የአላህ ንግግሮች ከፈጠረው ነገር ሁሉ ተንኮል እጠበቃለሁ፡፡» (ኢማሙ አህመድ በሙስነዳቸው ሀሰን በሆነ የዘገባ ሰንሰለት ዘግበውታል)፡፡

15. ሙስሊም በትክክለኛ ዘገባው ኸውለት ቢንት ሀኪም (ረ. ዐ) እንዳስተላለፈችው፣ የአላህ መልእክተኛ እንዲህ ብለዋል፡- «የሆነ ቤትን የገባና፣ አዑዙ ቢከሊማቲላሂትታማት ሚን ሸርሪ ማ ኸለቅ ያለ ሰው፣ ከገባበት ቤት እስኪወጣ ድረስ ምንም ነገር አይጎዳውም፡፡»

16. ዐብደላህ ኢብኑ ዐብዱረህማን ኢብኑ አብዛ አባቱን ጠቅሶ እንዳስተላለፈው፣ የአላህ መልእክተኛ እንዲህ ይላሉ፡- «ሲያነጉ፣ አስበህና ዐላ ፊጥረቲል ኢስላም፤ ወዐላ ከሊመቲል ኢኽላስ፤ ወዐላ ዲኒ ነቢይዪና ሙሀመዲን (ሶ. ዐ. ወ)፤ ወዐላ ሚለቲ አቢይና ኢብራሂመ ሀኒፈን ሙስሊመን፤ ወማ ካነ ሚነል ሙሽሪኪን፡፡»

«በኢስላም ተፈጥሮ ላይ፣ ጥርት ባለው ንግግር፣ በነቢያችን

በሙሀመድ ሃይማኖት ላይ እንዲሁም በአባታችን በኢብራሂም ጎዳና ላይ ሆነን አንግተናል፡፡» (ኢማሙ አህመድ በሙስነዳቸው ትክክለኛ በሆነ የዘገባ ሰንሰለት -ሰነድ ዘግቦታል)፡፡

17. ዐብደላህ ኢብኑ ዐብዱረህማን ኢብኑ አቢ በክረተ ለአባቱ እንዲህ አለው፡- «አባቴ ሆይ! እኔ ሁል ጊዜ ማለዳ ማለዳ የምትለው የሆነ ነገር ላሰማህን? (እንዲህ በል፡-) አላሁምመ ዓፊኒ ፊ በደኒ፣ አላሁምመ ዓፊኒ ፊ ሰምዒ፤ አላሁምመ ዓፊኒ ፊ በሶሪይ፤ ላኢላሃ ኢልላ አንት»

«አላህ ሆይ! ለአካሌ ጤንነት ስጠው፤ አላህ ሆይ! ዓይኔን ጤነኛ አድርግልኝ፤ ከአንተ በስተቀር አምልኮት የሚገባው አምላክ የለም» ይህን ዚክር ሲነጋ ሶስት ጊዜ፣ ሲመሽ ሶስት ጊዜ ትደጋግመዋለህ፡፡ እንዲህም ትላለህ፡- አላሁምመ ኢንኒ አዑዙ ቢከ ሚነል ኩፍሪ ወልፈቅሪ፤ አላሁምመ ኢንኒ አዑዙ ቢከ ሚን ዐዛቢል ቀብሪ ላኢላሃ ኢልላ አንተ (ይህን ዱዓ) ሲነጋ ሶስት ጊዜ፣ ሲመሽ ሶስት ጊዜ ትደጋግመዋለህ፡፡

«አላህ ሆይ! ከክህደትና ከድህነት እንዲሁም ከቀብር ውስጥ ቅጣት በአንተ እጠበቃለሁ፤ ከአንተ ውጪ ሌላ አምላክ የለም፡፡» «አዎ ልክ ነህ» አለ፡፡ «ልጄ ሆይ! የአላህ መልእክተኛ በእነዚህ ዱዓዎች ዱዓ ሲያደርጉ ሰምቻለሁ፡፡ እኔ በሱናቸው (በፈለጋቸው) መጉዋዝ እወዳለሁ»፡፡ እሱም፣ የአላህ መልእክተኛ እንዲህ አሉ አለ፡- «የጭንቅ ጊዜ ዱዓዎች፡ - አላሁምመ ረህመተከ አርጁ፤ ፈላ ተኪልኒ ኢላ ነፍሲ ጦርፈተ ዓይን፤ ወአስሊህሊ ሸእኒ ኩለሁ፤ ላኢላሃ ኢልላ አንተ»፡፡«አላህ ሆይ! እዝነትህን እከጅላለሁ፤ ህያውና ራሱን ቻይ የሆንከው አምላክ ሆይ! በእዝነትህ እታገዛለሁ፤ ጉዳዬን ሁሉ አስተካክልልኝ፤ ለቅጽበት ያህል እንኳዋ ለራሴ አትተወኝ፡፡» እኔም በሱናቸው (በፈለጋቸው) መጉዋዝ

እወዳለሁ፡፡» (ኢማሙ አህመድና ቡኻሪ በሀዲስ ጥራዛቸው በአደበል ሙፍረድ ምዕራፍ ስር፣ እንዲሁም አቡ ዳውድና ነሳኢይ ሀሰን በሆነ የዘገባ ሰንሰለት ዘግበውታል)፡፡

ማንኛውም ሙስሊም በነጋ ቁጥር ላኢላሃ ኢለላህ፤ ወህደሁ ላሸሪከ ለሁ፤ ለሁል ሙልኩ ወለሁል ሀምዱ፤ ወሁወ ዓላ ኩሊ ሸይኢን ቀዲር የሚለውን ዚክር መቶ ጊዜ ማለቱ፣ እስኪመሽ ድረስ ዉሎውን ከሰይጣን ጥብቅ ይሆናል፡፡ ቀደም ብሎ እንደተወሳው፣ በትክክለኛ የቡኻሪና የሙስሊም ዘገባ አቢ ሁረይራ (ረ. ዐ) እንዳስተላለፉት፣ የአላህ መልእክተኛ እንዲህ ብለዋል፡- «ላኢላሃ ኢልለላህ፤ ወህደሁ ላሸሪከ ለሁ፤ ለሁል ሙልኩ ወለሁል ሀምዱ ወሁወ ዐላ ኩሊ ሸይኢን ቀዲር የሚለውን በቀን መቶ ጊዜ ያለ ሰው፣ አስር ባሪያዎችን ነጻ እንዳደረገ ቁጥር ነው፡፡ መቶ ምንዳዎችም ይጻፉለታል፤ መቶ ወንጀሎችም ይታበሱለታል፡፡ ይህን ማለቱ እስኪመሽ ድርስ ከሰይጣን መጠበቂያ ይሆነዋል፡፡ ይህን ዚክር ካለ ሰው የበለጠ ያለ ሰው ካልሆነ በስተቀር፣ ከዚህ ሰው የበለጠ ስራ የሰራ የለም፡፡ በቀን ውስጥ መቶ ጊዜ ሱብሃነላሂ ወቢሀምዲሂ ያለ ሰው፣ ወንጀሉ የባህር አረፋ ያህል እንኳዋ ቢሆን፣ ወንጀሉ ይረግፍለታል፡፡»